
224

ቀሪ በይ አገሬ

11ዋ152
ቁ.ሠ 224



ጸሐፊ አለን ፑዮን
ተርጓሚ አማረ ማሞ

274

መቅድም ።

« እሪ ፡ በይ ፡ አገሬ ፡ » በአጻጻፉ ፡ ከአርዕስቱ ፡ ጀምሮ ፡ ከምዕራፍ ፡ ምዕራፍ ፡ እየተቀባበለ ፡ የሮሮ ፡ የሥቃይ ፡ የፍርሃትና ፡ የጭንቀት ፡ ድምፅ ፡ የሚያሰማ ፡ ገድል ፡ ነው ። «እሪ ፡ በይ ፡ አገሬ ፤ ኡ ፡ ኡ ፡ በይ ፤ የፍትሕ ፡ ያለህ ፡ በይ ፤ የእርዳታ ፡ ያለህ ፡ በይ ፡ » የሚል ፡ የጣር ፡ ድምፅ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ባለታሪኮች ፡ ይሰማል ። ኡኡታው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከአጥናፍ ፡ እስከ ፡ አጥናፍ ፡ ለሚኖር ፡ ሰብአዊ ፡ ለሆነ ፡ ፍጡር ፡ ሁሉ ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ እንዲደርሰው ፡ የማንም ፡ ጎብረቱ ፡ ሰብ ፡ እንዲያዳምጠው ፡ በዚያም ፡ መንግሥት ፡ መክሮ ፡ እንዲያስበው ፡ የተሰነዘረ ፡ መልእክት ፡ ሲሆን ፡ መልእክተኛውም ፡ ስለ ፡ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ የሥቃይ ፡ ድምፅ ፡ ከአሰሙት ፡ የብዕር ፡ ጀግኖች ፡ አንዱ ፡ አለን ፡ ፔተን ፡ ነው ።

አለን ፡ ፔተን ፡ ስለ ፡ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ « እሪ ፡ በይ ፡ አገሬ ፡ » (Cry, the Beloved Country) በሚለው ፡ መጽሐፉ ፡ ለዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ያሰማው ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ጮሆና ፡ አስተጋብቶ ፡ ጸጥ ፡ እልም ፤ እልም ፡ ጭጭ ፤ የሚል ፡ ድምፅ ፡ አልሆነም ። እያደር ፡ ድምፁ ፡ እያየለ ፡ ከአገር ፡ አገር ፡ እየተቀባበለና ፡ እያስተጋባ ፡ ሲሄድ ፡ የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ እንዲያተኩር ፡ የሚያሳስበው ፡ መሆኑን ፡ መጽሐፉን ፡ ያነበበ ፡ ሁሉ ፡ ይገነዘበዋል ።

በዚህ ፡ በአለንበት ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ስለሚካሄደው ፡ የዘርና ፡ የቀለም ፡ አድልዎ ፤ የሥነ

መንግሥት ፣ ሕገ ፣ ወጥነት ፣ ብዙ ፣ አገሮች ፣ የውግዘት ፣ ድምፅ ፣ አሰምተዋል ። ብዙዎቹም ፣ ለጊዜው ፣ ተሰምቶ ፣ ወዲያው ፣ ምውት ፣ በሚሆን ፣ የውግዘት ፣ ቃል ፣ ብቻ ፣ ሳይወሰኑ ፣ በፍርድ ፣ ሸንጐ ፣ ተቋቁመው ፣ ትክክለኛ ውን ፣ ፍትሕ ፣ ለማግኘት ፣ ያደረጉት ፣ ተጋድሎ ፣ አይዘ ነጋም ። ከአፍሪቃ ፣ አሀጉር ፣ ኢትዮጵያና ፣ ላይቤሪያ ፣ በዓ ለም ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ያደረጉት ፣ ትግል ፣ አንድ ፣ ታላቅ ፣ የታሪክ ፣ ምዕራፍ ፣ የያዘ ፣ ጀብዱ ፣ ነው ።

አለን ፣ ፒተንም ፣ በበኩሉ ፣ አቤቱታውን ፣ ለዓለም ፣ ሕዝብ ፣ በዚህ ፣ መጽሐፍ ፣ አሰምቶአል ። አለን ፣ ፒተን ፣ አንዱን ፣ ወገን ፣ ወንጅሎ ፣ አንዱን ፣ ወገን ፣ አልሾነገለም። አድልዎ ፣ በሌለበት ፣ ሁኔታ ፣ በደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ ውስጥ ፣ ያለውን ፣ የዘር ፣ ልዩነት ፣ በቀላል ፣ አገላለጥ ፣ በጠለቀ ፣ አስተያየት ፣ ጉልህ ፣ አድርጎ ፣ ያብራራል ። የመጽሐፉ ፣ ታሪክ ፣ የተተለመው ፣ በአንድ ፣ ተራ ፣ የዙሱ ፣ ቁስ ፣ ቤተ ፣ ሰብ ፣ አካባቢ ፣ ሲሆን ፣ አንባቢ ፣ የመልእክቱን ፣ ምሳሌ ፣ ለማግኘት ፣ ሩቅ ፣ አይሆንበትም ። ታሪኩ ፣ በእ ውነት ፣ ላይ ፣ የተመሠረተ ፣ ልብ ፣ ወለድ ፣ ታሪክ ፣ ነው ። በደራሲው ፣ ማስታወሻ ፣ መሠረት ፣ በመጽሐፉ ፣ የተጠ ቀሱት ፣ ሰዎች ፣ ልብ ፣ ወለድ ፣ ቢሆኑም ፣ በእውነት ፣ ላይ፣ የተመሠረቱ ፣ ናቸው ። በመጽሐፉ ፣ የተገለጡት ፣ ድርጊ ቶች ፣ በከፊል ፣ እርግጠኛነት ፣ ይኖራቸዋል ። ለምሳሌ ፣ አውቶቡስ ፣ ላለመሳፈር ፣ የተደረገው ፣ አድማ ፣ አሰስ ፣ ገሰሱ ፣ የሞላበት ፣ ከተማ ፣ መመሥረቱ ፣ በአዴንዳልስ ረስት ፣ የወርቅ ፣ ማዕድን ፣ መገኘት ፣ የማዕድን ፣ ሠራተ ኞች ፣ የሥራ ፣ ማቆም ፣ አድማ ፣ ሁሉ ፣ ከእውነት ፣ የተፈ ተለ ፣ ታሪክ ፣ ነው ።

ሆድና ፣ ጀርባ ፣ የሆኑ ፣ ጎብረተ ፣ ሰቦች ፣ የሚኖሩባት ፣ አገር ፣ ይህች ፣ ደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ አሥራ ፣ ሰባት ፣ ሚሊ ዮን ፣ ሕዝብ ፣ ይኖርባታል ። ከእነዚህ ፣ ውስጥ ፣ ሦስት ፣ ሚሊዮን ፣ ተኩል ፣ የሚሆኑት ፣ ነጮች ፣ ናቸው ። የተቀሩት ፣ ሁለት ፣ ሚሊዮን ፣ ከሚሆኑት ፣ ክልሶችና ፣ እስያውያን ፣ በስተቀር ፣ ሌሎቹ ፣ ጥቁር ፣ አፍሪቃውያን ፣ ናቸው ። እነ ኝህ ፣ ጎብረተ ፣ ሰቦች ፣ የደም ፣ ጥርስ ፣ ተናከሰው ፣ በፍ ርሃት ፣ ተውጠውና ፣ ተደፋፍጠው ፣ ይኖራሉ ። አገሪቱ ፣ ግን ፣ በመካከል ፣ ትጮሃለች ።

የሮሮ ፣ አገር ፣ የሆነችው ፣ ደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ አሪ ፣ የምትልበት ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ አለ ። አዙሮ ፣ ላየው ፣ ሁሉ ፣ ወርቃዊ ፣ ጊዜን ፣ ዓላማ ፣ ቢስ ፣ በመሆንና ፣ በመደናገር ፣ ማባከን ፣ ያስጮሃል ። ለምለሙን ፣ የገጠር ፣ መሬት ፣ የአ ሁኑ ፣ ትውልድ ፣ ሲከዳውና ፣ ሁሉም ፣ ወደ ፣ ከተማ ፣ ሲኮ በልል ፣ የገጠር ፣ መሬት ፣ ሌጣ ፣ ሲቀር ፣ የምድር ፣ የተፈ ጥሮ ፣ የላይ ፣ አከናፍ ፣ የሆኑት ፣ ዛፎች ፣ እያደር ፣ ተገፈው፣ ሲያልቁና ፣ ሲጠፉ ፣ ሳሮች ፣ ሲደርቁ ፣ እርቃኑ ፣ የተጋለ ጠው ፣ ገጠር ፣ ገላው ፣ ተልጦ ፣ የውስጥ ፣ አብራኩ ፣ ሳይ ቀር ፣ በነፋስና ፣ በውኃ ፣ ተሸርሽሮ ፣ ሲያልቅ ፣ ሁለንተ ናው ፣ ቀፎ ፣ ሲሆን ፣ የሚያስጮህ ፣ ነው ። በእርእያ ፣ ሥላሴ ፣ የተፈጠረውን ፣ እካል ፣ ያለ ፣ አግባቡ ፣ መያዝ ፣ ያስጮሃል ። ደጉ ፣ እያለ ፣ ከፉን ፣ ነገር ፣ መምረጥ ፣ ያስ ጮሃል ። አለን ፣ ፒተን ፣ እነዚህን ፣ የመሳሰሉ ፣ የሚያስ ጮሁ ፣ ነገሮች ፣ በዚህ ፣ ጥልቅ ፣ በሆነ ፣ መጽሐፉ ፣ የዳሰ ሳቸው ፣ በአንባቢ ፣ ልቦና ፣ ተተክለው ፣ የሚቀሩ ፣ እልቆ ፣ መሣፍርት ፣ የሌላቸው ፣ ነገሮች ፣ ሞልተዋል ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሁኔታ ፡ ራሱን ፡ ለቻለ ፡ ጎብረተ ፡ ሰብ ፡ ራሱን ፡ በቻለ ፡ ብሔራዊ ፡ ቋንቋው ፡ ተተርጉሞ ፡ ሲቀ ርብ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ። « እሪ ፡ በይ ፡ አገሬን ፡ » አቶ ፡ አማረ ፡ ማሞ ፡ የተረጐሙት ፡ የመጽሐፉ ፡ ደራሲ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ የደቡብ ፡ አፍሪቃን ፡ ሕዝብ ፡ ባህ ልና ፡ ጠባይ ፡ ሲገልጡ ፡ በተረቡበት ፡ የአጻጻፍ ፡ ስልት ፡ መንገድ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አተረጓጐም ፡ የደራሲ ውን ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ ስለማያናጋውና ፡ በተለይም ፡ እንደ ፡ ተቀባበለ ፡ መልእክት ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ ሳይጨመር ፡ ወይም ፡ ሳይቀነስ ፡ ወይም ፡ ጠባዩን ፡ ሳይለውጥ ፡ እንዳለ ፡ ለአንባቢ ፡ ስለሚደርስ ፡ ማንንም ፡ ሊያረካ ፡ ይችላል ።

ግርማ ፡ ዳመኑ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ. ም ።

ክፍል ፡ አንድ ።

—1—

ከኢኮፖ ፡ ወደ ፡ ኮረብቶቹ ፡ የሚያደርስ ፡ አንድ ፡ ወጣ ፡ የሆነ ፡ መንገድ ፡ አለ ። ኮረብቶቹ ፡ ለምለም ፡ ሳር ፡ የለበሱ ፡ ውበታቸው ፡ ዓይን ፡ እስኪታክት ፡ ቢታይ ፡ የማ ይጠገብ ፡ ነው ። ወደ ፡ ካሪስብሩክ ፡ የሚወስደው ፡ መን ገድ ፡ አሥር ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡ ኮረብቶቹን ፡ እቅ ርጦ ፡ ያልፋል ። ከዚያም ፡ አካባቢውን ፡ ጭጋግ ፡ ካልጋ ረደው ፡ በቀር ፡ በውበቱ ፡ ወደር ፡ የሌለውን ፡ ከአፍሪቃ ፡ ሸለቆዎች ፡ አንዱን ፡ አሽቄልቊሎ ፡ ማየት ፡ ይቻላል ። የአካ ባቢው ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ በሳርና ፡ በቁጥቋጦ ፡ ተሸልሞአል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ የብቸኝነት ፡ ስሜት ፡ ያላት ፡ ቲቲሆያ ፡ የተባለችው ፡ ወፍ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማል ። ከበታቹ ፡ የኡም ዚምኩሉ ፡ ሸለቆ ፡ ጕሠውን ፡ ከድራከንስበርግ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ያመራል ። ከወንዙ ፡ ማዶ ፡ ብዙ ፡ ኮረብቶች ፡ ተሰልፈዋል ። ከኮረብቶቹ ፡ ባሻገር ፡ የኢንጌሌና ፡ የምሥ ራቅ ፡ ግሪኳላንድ ፡ ተራሮች ፡ ይታያሉ ።

ሳሩ ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ ያደገ ፡ በመሆኑ ፡ የበቀለበትን ፡ መሬት ፡ ሸፍኖታል ። በያለበት ፡ እንደ ፡ ሹሩባ ፡ የተጐነ ጐነው ፡ ሳር ፡ የዝናቡን ፡ ጠብታ ፡ እየተቀበለ ፡ የጭጋ ጉን ፡ ርጥበት ፡ እየሳበ ፡ መሬቱን ፡ ያርሰዋል ። ከመሬቱ ፡ የተረፈው ፡ ፈላሽ ፡ ከወንዞቹና ፡ ከጅረቶቹ ፡ ጋር ፡ ይቀላ

ቀላል ። ሳሩን ፡ ከብቶች ፡ ያለ ፡ እግባብ ፡ ግጠውት ፡ ወይም ፡ ሰደድ ፡ እሳት ፡ በልቶት ፡ መሬቱ ፡ አልተራቈተም ። አካባቢው ፡ ፈጣሪ ፡ ሽልሞ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ በመሆኑ ፡ ያደረጉትን ፡ ጫማ ፡ አውልቆ ፡ የሚቆምበት ፡ ቅዱስ ፡ ምድር ፡ ይመስላል ። መሬትዋ ፡ የጠበቃትንና ፡ የተከባከባትን ፡ ትጠብቃለች ፤ ትከባከባለችም ። ቸል ፡ ብሎ ፡ የሚተዋትን ፡ ግን ፡ ለረሃብና ፡ ለእርዛት ፡ አሳልፋ ፡ ትሰጠዋለች ።

መሬቱ ፡ ሳር ፡ እንደልቡ ፡ የበቀለበትና ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ እንደ ፡ ሹራብ ፡ የተጐነጐነበት ፡ በመሆኑ ፡ አፈሩ ፡ አይታይም ። በለመለመ ፡ ሳር ፡ ያጌጡት ፡ ኮረብቶች ፡ አሸቈልቍለው ፡ ወደ ፡ ሸለቆው ፡ ሲደርሱ ፡ መልካቸውን ፡ ይለውጣሉ ። ለዓይን ፡ ዕረፍት ፡ በሚሰጥ ፡ ለምለምነት ፡ ፈንታ ፡ መልካቸው ፡ እየቀላና ፡ እየገረጣ ፡ ይሄዳል ። መሬቱ ፡ የሚወርደውን ፡ ዝናብና ፡ ጤዛ ፡ አይዝም ። የወንዞቹና ፡ የጅረቶቹ ፡ መውረጃዎች ፡ አንድ ፡ ጠብታ ፡ ውኃ ፡ አይታይባቸውም ። ሳሩን ፡ ብዙ ፡ ከብቶች ፡ ግጠውታል ፤ ሰደድ ፡ እሳትም ፡ ተነሥቶ ፡ አቃጥሎታል ። ጫማ ፡ አድርገው ፡ ካልቆሙበት ፡ የፀሐይዋ ፡ ግለት ፡ የደንጊያው ፡ ስለት ፡ እግርን ፡ ይጐዳል ። መሬትዋን ፡ ያሰበላት ፡ የተጠነቀቀላት ፡ የጠበቃት ፡ የለም ፤ እርስዋም ፡ ለሰዎች ፡ አትበገርም ፤ አትጠቅማቸውምም ። ቲቲሆያ ፡ የተባለችው ፡ ወፍ ፡ ድምፅ ፡ እንኳ ፡ በአካባቢው ፡ አይሰማም ።

መልካቸው ፡ ፍም ፡ የሚመስለው ፡ ታላላቅ ፡ ኮረብቶች ፡ ተራቊተው ፡ ቆመዋል ። አፈሩም ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ተበጭቆ ፡ ተነሥቶአል ። በኮረብቶቹ ፡ ላይ ፡ ነጐድጓድ ፡ ያጐረመርምባቸዋል ፤ ደመናውም ፡ ዶፉን ፡ ያወርድባቸዋል ። ጕርፉም ፡ አፈሩን ፡ እያግበሰበሰ ፡ ጥርግ ፡ ይላል ።

ቍልቍል ፡ በሚታየው ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ሴቶች ፡ መሬቱን ፡ ይጭራሉ ። የሚዘሩት ፡ በቆሎ ፡ የሰው ፡ ቁመት ፡ አይደርስም ። በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩት ፡ ባልቴቶችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ እናቶችና ፡ ሕፃናት ፡ ናቸው ። ወንዶቹ ፡ ኮረዶቹና ፡ ጕረምሶቹ ፡ አገር ፡ ለቀው ፡ ሄደዋል ። ምን ፡ ይደረግ ፡ መሬትዋ ፡ ልታስተዳድራቸው ፡ አልቻለችም ።

—2—

አንዲት ፡ ትንሽ ፡ ልጅ ፡ ከእንጨትና ፡ ከቆርቆሮ ፡ ወደ ፡ ተሠራው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እየሮጠች ፡ ሄደች ። በእጅዋ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ ይዛለች ። ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ቤት ፡ በር ፡ በጥንቃቄ ፡ አንኳኳች ። ቄስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ኩማሎ ፡ ከጽሕፈት ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ « ይግቡ ፡ » አለ ።

ትንሽዋ ፡ ልጅ ፡ በሩን ፡ ስትፈራ ፡ ስትቸር ፡ ከፍታ ፡ ገባች ።

— ደብዳቤ ፡ ይዤ ፡ መጥቻለሁ ፡ ኡምፋንዲሲ ። (1)

— ከየት ፡ አገኘሽው ፡ የእኔ ፡ ልጅ ?

— ከሱቅ ፡ ነው ፡ ኡምፋንዲሲ ። በሱቅ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ፈረንጅ ፡ ለእርስዎ ፡ እንዳደርስ ፡ ላከኝ ።

— ወዲህ ፡ በዪው ፡ የእኔ ፡ ልጅ ። በዪ ፡ ደህና ፡ ሁኚ ።

ትንሽዋ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ አልሄደችም ። እግርዋን ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ እያሻሸች ፡ ጣቶችዋን ፡ እያፍተለተለች ፡ ቁማ ፡ ቀረች ።

(1) መምህር ፡ አባ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

— እርቦሻል ፣ እንዴ ፣ የእኔ ፣ ልጅ ?
— በጣም ፣ አልራበኝም ፣ ኡምሩንዲሲ ።
— ትንሽ ፣ ትንሽ ፣ ራብ ፣ አድርጎሻል ?
— አዎን ፣ ኡምሩንዲሲ ፣ ትንሽ ፣ እርቦኛል ።
— እስቲ ፣ እማማ ፣ ዘንድ ፣ ሂጂ ። እርስዋ ፣ የሚበላ ፣ ነገር ፣ አታጣም ።

ትንሽዋ ፣ ልጅ ፣ ጠረጴዞችና ፣ ወንበሮች ፣ የተደረደሩበትን ፣ የግድግዳ ፣ ሰዓት ፣ አበቦች ፣ የበቀሉባቸው ፣ ማሰሮዎች ፣ ብዙ ፣ መጻሕፍት ፣ የሚገኙበትን ፣ ቤት ፣ እግሮችዋ ፣ እንዳይደፍሩት ፣ በማለት ፣ በዝግታ ፣ ተራመደች ።

ኩማሎ ፣ ደብዳቤውን ፣ በእጁ ፣ ይዞ ፣ ያገላብጥ ፣ ጀመር ። ደብዳቤው ፣ በብዙ ፣ ሰው ፣ እጅ ፣ የገባ ፣ መሆኑ ፣ በመቁሸሹ ፣ ይታወቃል ። የተላከው ፣ ከጆሐንስበርግ ፣ ነበር ።

ኩማሎ ፣ በጆንስበርግ ፣ ብዙ ፣ የሥጋ ፣ ዘመዶች ፣ ነበሩት ። እናጢው ፣ ወንድሙ ፣ ዮሐንስ ፣ በሶፊያታውን ፣ ጆሐንስበርግ ፣ የንግድ ፣ ሥራ ፣ አቋቁሞአል ። ታናሽ ፣ እኅቱ ፣ ጌርትሩድ ፣ በማዕድን ፣ ሥራ ፣ ውስጥ ፣ ለመቀጠር ፣ ሄዶ ፣ የቀረውን ፣ ባልዋን ፣ ፍለጋ ፣ ከታናሽ ፣ ልጅዋ ፣ ጋር ፣ እንደ ፣ ሄደች ፣ አልተመለሰችም ። አክስቱን ፣ ፍለጋ ፣ የሄደው ፣ የኩማሎ ፣ አንዱ ፣ ልጁ ፣ አቤሴሎም ፣ ወደ ፣ ዚያው ፣ ሂዶ ፣ ቀርቶአል ። ከተጠቀሱት ፣ የቀረቡም ፣ ባይሆኑ ፣ ኩማሎ ፣ በጆሐንስበርግ ፣ ብዙ ፣ ዘመዶች ፣ ነበሩት ። ብዙዎቹ ፣ ዘመዶቹ ፣ ደብዳቤ ፣ ከጻፉለት ፣ ብዙ ጊዜ ፣ በመሆኑና ፣ የእጅ ፣ ጽሕፈታቸውንም ፣ እንኳ ፣ በመ

ርሳቱ ፣ የደረሰው ፣ ደብዳቤ ፣ ከማን ፣ እንደ ፣ ተላከለት ፣ ማረጋገጥ ፣ አታተው ።

ወዲህ ፣ ወዲያ ፣ ቢያገላብጠውም ፣ ከማን ፣ እንደ ፣ ተላከ ፣ የሚያመለክት ፣ ምልክት ፣ አጣበት ። እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ደብዳቤ ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ከተከፈተ ፣ የማይመለስ ፣ በመሆኑ ፣ መክፈቱ ፣ ጭንቅ ፣ ሆነበት ።

ባለቤቱን ፣ ጠርቶ ፣—ልጅቱ ፣ ሂዶች ? ብሎ ፣ ጠየቃት ።
— እየበላች ፣ ናት ።
— መልካም ፣ ነው ፤ ትብላ ። አንድ ፣ ደብዳቤ ፣ አምጥታ ፣ ነበር ። ስለ ፣ ደብዳቤው ፣ የምታውቂው ፣ ነገር ፣ አለ ?
— እንዴት ፣ አድርጌ ፣ ነው ፣ የማውቀው ፣ እስጢፋኖስ?
— ምናልባት ፣ ብዬ ፣ ነው ። እስቲ ፣ ተመልከቺው ።

ደብዳቤውን ፣ ተቀብላ ፣ በእጅዋ ፣ ደባበሰችው ። የዳበላው ፣ ስሜት ፣ ደብዳቤው ፣ የመጣበትን ፣ ሊያረጋግጥላት ፣ አልቻለም ። አድራሻውን ፣ በቀስታና ፣ በጥንቃቄ ፣ ማንበብ ፣ ጀመረች ።

ቄስ ፣ እስጢፋኖስ ፣ ኩማሎ ፣
ቅዱስ ፣ ማርቆስ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣
እንዶትሼኒ ፣
ናታል ።

እንደምንም ፣ ተበራታ ፣— ከልጃችን ፣ አይደለም ፣ አለች ።

— አይደለም ፣ ከልጃችን ፣ አይመስለኝም ፣ ብሎ ፣ የሥጋት ፣ ትንፋሽ ፣ ተነፈሰ ።

— ምናልባት ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ ይሆን ? አለች ።

— አዎን ፤ ምናልባት ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ የተጻፈ ፡ ይሆናል ።
— ከጌርትሩድ ፡ የተላከ ፡ አይመስለኝም ፡ አለች ።
— ምናልባት ፡ ከወንድሜ ፡ ከዮሐንስ ፡ ይሆናል ።
— ከዮሐንስ ፡ የተላከ ፡ አይመስለኝም ፡ አለች ። ሁለቱም ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ አሉ ።

— ደብዳቤ ፡ ማግኘት ፡ እንመኛለን ፤ ሲመጣልን ፡ ግን ፡ መክፈቱን ፡ እንፈራለን ፡ አለች ።

— ደግሞ ፡ የምን ፡ መፍራት ፡ ነው ! ክፈችው ! አላት ።

ብዙ ፡ ደብዳቤዎችን ፡ ከፍታ ፡ ስለማታውቅ ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ በጥንቃቄ ፡ አንቦልኩን ፡ ገለጠችው ። በዝግታም ፡ ለራስዋ ፡ ብቻ ፡ ማንበብ ፡ ጀመረች ።

—እንደሚሰማ ፡ አድርገሽ ፡ አንብቢው ፡ — አላት ። ድምፅዋን ፡ ከፍ ፡ አድርጋ ፡ የዙሉ ፡ ተወላጅ ፡ እንግሊዝኛን ፡ እንደሚያነብ ፡ ፊደሎቹን ፡ እየቁጠረች ፡ ደብዳቤውን ፡ ማንበብ ፡ ጀመረች ።

የሚስዮን ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡
ሶፊያታውን ፡
ጆሐንስበርግ ፡
መስከረም ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም.

«በክርስቶስ ፡ ውድ ፡ ወንድሜ ፤

«ስሚ ፡ ጌርትሩድ ፡ ኩማሎ ፡ የሚባል ፡ ልጅግር ፡ ቤት ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ጆሐንስበርግ ፡ አግኝቼአት ፡ በኢንዶ

ትሼኒ ፡ የሚገኘው ፡ የቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህን ፡ የቄስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ኩማሎ ፡ እኅት ፡ መሆንዋን ፡ ጠይቄ ፡ ለመረዳት ፡ ችያለሁ ። ልጅቱ ፡ በጠና ፡ ሕመም ፡ ላይ ፡ ስለምትገኝ ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ ጆሐንስበርግ ፡ እንድትመጣ ፡ አሳስብሃለሁ ። በሶፊያታውን ፡ ወደሚገኘው ፡ የሚስዮን ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ ስትደርስ ፡ ቄስ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ምሲማንጉ ፡ ብለህ ፡ ጠይቅ ። ከዚያም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ምክር ፡ እሰጥሃለሁ ። ስለማረፊያ ፡ ስፍራ ፡ አታስብ ። ዋጋው ፡ መጠነኛ ፡ የሆነ ፡ የማረፊያ ፡ ቦታ ፡ አዘጋጅቼ ፡ እቆይሃለሁ ።»

በክርስቶስ ፡ ወንድምህ ፡
ቴዎፍሎስ ፡ ምሲማንጉ ።

ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ በሐሳብ ፡ ተውጠው ፡ ቀሩ ። በመጨረሻው ፡ እርስዋ ፡ ተነፈሰች ።

— ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ?
—ምኑን ?
— ይህን ፡ ደብዳቤ ። ጉዳዩን ፡ ሰምተኸዋል ።
— አዎን ፡ ሰምቼዋለሁ ። ነገሩ ፡ ቀላል ፡ አይደለም ።
— እርግጥ ፡ ነው ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። ምን ፡ ለማድረግ ፡ አስበሃል ?
— ልጅቱ ፡ በልታ ፡ ጨረሰች ?
ባለቤቱ ፡ ወደ ፡ ማዕድ ፡ ቤት ፡ ሂዳ ፡ ልጅትዋን ፡ ይዛ ፡ ተመለሰች ።
— በላሽ ፡ የእኔ ፡ ልጅ ?
— አዎን ፡ ኡምፉንዲሲ ።

— ደብዳቤውን ፡ ስላመጣሽልኝ ፡ አመሰግናለሁ ። ለፈረንጁ ፡ ምስጋናዬን ፡ አቅርቢልኝ ።

— እሺ ፡ ኡምፉንዲሲ ።

— በይ ፡ ደህና ፡ ዋዪ ።

— ደህና ፡ ይሁኑ ፡ ኡምፉንዲሲ ።

— ደህና ፡ ይሁኑ ፡ እማማ ።

— ደህና ፡ ሁኚ ፡ የእኔ ፡ ልጅ ።

ልጅቱ ፡ በቀስታ ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ አመራች ። በጥንቃቄ ፡ እንደ ፡ ከፈተችው ፡ በጥንቃቄ ፡ ዘግታው ፡ ወጣች ።

ልጅቱ ፡ እንደወጣች ፡ —ታዲያ ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ አስበሃል ? አለችው ።

— ምኑን ?

በለዘበ ፡ እንደበት ፡— የደብዳቤውን ፡ ነገር ፡— አለችው ።

ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከተከዘ ፡ በኋላ ፡—የቅዱስ ፡ ቻድን ፡ ገንዘብ ፡ አምጭልኝ ፡— አላት ። ወጣ ፡ ብላ ፡ አንድ ፡ የእህል ፡ መስፈሪያ ፡ የመሰለ ፡ ጣሳ ፡ ይዛ ፡ ተመለሰች ። ጣሳውን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ የችግሩን ፡ መፍትሔ ፡ የሚነግረው ፡ ይመስል ፡ ትዙር ፡ ብሎ ፡ ይመለከተው ፡ ጀመር ።

በመጨረሻውም ፡— ምንም ፡ ብታመነታ ፡ አልቀረለትም ፡— አለችው ።

— ይህን ፡ ገንዘብ ፡ ለማጥፋት ፡ ምን ፡ መብት ፡ አለኝ ? አላት ። — ይህ ፡ ገንዘብ ፡ የተጠራቀመው ፡ አቤሴሎም ፡ ቅዱስ ፡ ቻድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲገባበት ፡ ነበር ።

— የአቤሴሎም ፡ ቅዱስ ፡ ቻድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ ዘበት ፡ ነው ።

ቁጣ ፡ ባለ ፡ መንፈስ ፡ — እንዴት ፡ እንዲህ ፡ ትያለሽ ? እንዲህ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ከአንደበትሽ ፡ ይወጣል ፡—አላት ።

ተስፋ ፡ በቁረጠ ፡ አነጋገር ፡ — እርሱ ፡ ያለው ፡ ጆሐንስበርግ ፡ ነው ። ጆሐንስበርግ ፡ የሄደ ፡ መመለሻ ፡ የለውም ፡—አለችው ።

— አሁንማ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተናግረሻል ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከአንደበትሽ ፡ ወጥቶአል ። ገንዘቡም ፡ ላሰብነው ፡ ጉዳይ ፡ ሊውል ፡ አልቻለም ። መንገዱን ፡ አንቺው ፡ ከፍ ተሽዋል ። በከፈትሽው ፡ ጐዳና ፡ መጓዝ ፡ አለብን ። መጨረሻውን ፡ አምላክ ፡ ያብጀው ፡ ብቻ ።

ምርር ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ — መንገዱን ፡ የከፈትኩት ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ። እንተ ፡ ባይገባህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከተከፈተ ፡ ቆይቶአል ፡— አለችው ።

እርሱም ፡ በበኩሉ ፡ በመመረር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— — አንድ ፡ ልጅ ፡ ነበረን ። ዙሉዎች ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ይወልዳሉ ። እኛ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ነበረን ። እርሱም ፡ ይባስ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ጆሐንስበርግ ፡ ሄደ ። አንቺ ፡ እንዳልሽው ፤ ጆሐንስበርግ ፡ የሄደ ፡ መመለሻ ፡ የለውም ። ጆሐንስበርግ ፡ የሄደ ፡ ለዘመዶቹ ፡ ደብዳቤ ፡ እንኳን ፡ አይጽፍም ። ጆሐንስበርግ ፡ የሄደ ፡ ቅዱስ ፡ ቻድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ለጥቁሮች ፡ ኑሮ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ትምህርት ፡ ለመማር ፡ አይፈቅድም ። ጆሐንስበርግ ፡ የገባ ፡ ወሬው ፡ አይሰማም ፤ ዱካው ፡ አይያዝም ። ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ደግሞ ፡ . . .

የጀመረውን ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ እንዲጨርስ ፡ ልትረዳው ፡ ባለመቻልዋ ፡—

— ይኸው ፡ በእጄ ፡ ይገርዋለሁ ፡— አለ ። አሁንም ፡ ዝም ፡ ስላለችው ። —ይኸው ፡ በእጄ ፡ ይገርዋለሁ ፡ እኮ ፡— አለ ።

— ራስህን ፡ አትጉዳ ፡— አለችው ።

— ራስህን ፡ አትጉዳ ? ራስህን ፡ አትጉዳ ? እኔ ፡ ራሴን ፡ አልጐዳም ። የሚጐዱኝስ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ። የገዛ ፡ ልጄ ፡ የገዛ ፡ እኅቴ ፡ የገዛ ፡ ወንድሜ ፤ ከሄዱ ፡ የማይመለሱ ፡ ዘመድ ፡ ይሠጋል ፡ የማይሱ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ፤ እንዲያው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እነርሱ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ምን ፡ ግድ ፡ አላቸው !

ድምፁ ፡ ወደ ፡ ቊጣ ፡ ተለወጠ ።

— ወደ ፡ ፈረንጁ ፡ ሂጂና ፡ ሌሎች ፡ ደብዳቤዎች ፡ እንዳሉ ፡ ጠይቂው ፡— አላት ። ምናልባት ፡ ከጠረጴዛው ፡ ሥር ፡ ወድቀው ፡ ዕቃ ፡ ተጭኖአቸው ፡ ይሆናል ። ዛፎቹ ፡ ላይ ፡ ተመልከች ። ምናልባት ፡ ንፋሱ ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ አውጥቶ ፡ ጥሎአቸው ፡ ይሆናል ።

— ኧረ ፡ እኔንም ፡ አሠቃየኸኝ ፡ ብላ ፡ ጮኸችበት ። ወዲያው ፡ ወደ ፡ አእምሮው ፡ ተመልሶ ፡ በትሕትና ፡—አንቺንስ ፡ ማሠቃየት ፡ የለብኝም ፡— አላት ።

እጁን ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ ዘርግቶ ፡—

— ይኸውልሽ ፡ ውሰጂና ፡ ከፈችው ፡— አላት ። እጅ

ችዋ ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ቆርቆሮውን ፡ ተቀብላ ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ዘረገፈችው ።

ጥቂቶች ፡ ያረጁ ፡ ብሮችና ፡ በብዛት ፡ የሚቈጠሩ ፡ ከብርና ፡ ከመዳብ ፡ የተሠሩ ፡ ፍራንኮች ፡ ጠረጴዛውን ፡ ሞሉት ።

— ቊጠሪው ፡ አላት ።

እርስዋም ፡ የብሮቹንና ፡ የፍራንኮቹን ፡ ዋጋ ፡ ለማረጋገጥ ፡ እያገላበጠች ፡ ከተመለከተች ፡ በኋላ ፡ በጥንቃቄ ፡ ቈጠረች ።

— ሰማንያ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ከሰባ ፡ አምስት ፡ ሳንቲም ፡— አለችው ።

— ሃምሳ ፡ ስድስት ፡ ብር ፡ ከሰባ ፡ አምስት ፡ ሳንቲም ፡ እወስዳለሁ ፡— አላት ።

— ሁሉንም ፡ ውሰደው ፡ እስጢፋኖስ ፡— አለችው ።

— ለሐኪም ፡ ቤት ፡ ለመድኃኒት ፡ ለሌላም ፡ ችግር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያስፈልግህ ፡ ይሆናልና ፡ ሁሉንም ፡ ይዘህ ፡ ሂድ ። ባንክ ፡ ቤት ፡ ያለውም ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ፡ ሰባ ፡ ብር ፡ ደርሶአል ።

— እርሱንማ ፡ ያጠራቀምሁት ፡ ምድጃ ፡ እንድትገዥበት ፡ ነበር ፡— አላት ።

— ግድ ፡ የለም ፡ ምድጃው ፡ ይቆይ ፡— አለችው ።

— ምንም ፡ እንኳን ፡ ያንን ፡ ገንዘብ ፡ ያጠራቀምነው ፡ አቤሴሎም ፡ ቅዱስ ፡ ቻድ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲገባ ፡ ቢሆንም ፡ የእኔ ፡ ሐሳብ ፡ በገንዘቡ ፡ ጥቁር ፡ ሙሉ ፡ ልብስ

ጥቁር ፣ ባርኔጣ ፣ ነጭ ፣ የቄስ ፣ ኮሌታ ፣ እንድትገዛበት ፣ ነበር ።

— ግድ ፣ የለም ፣ ስለ ፣ እርሱ ፣ አታስቢ ። እስቲ ፣ ልሂድ ፣ እኮ ፣ . . .

— ነገ ፣ ከካሪስብሩክ ፣ ትነሣለህ ፣— አለችው ።

— ለጳጳሱ ፣ ደብዳቤ ፣ ልጻፍና ፣ ከሄድኩ ፣ የምቆይበትን ፣ ጊዜ ፣ እንደግላውቅ ፣ ላስረዳቸው ።

እንደ ፣ ምንም ፣ ብሎ ፣ ከተቀመጠበት ፣ ተነሣና ፣ እፊትዋ ፣ ቆመ ።—ስላላዘንኩሽ ፣ ይቅር ፣ በይኝ ። ወደ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ሄጂ ፣ ጸሎት ፣ ላድርስ ፣— አላት ።

ከቤት ፣ ወጥቶ ፣ ወደ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ሲያዘግም ፣ በመስኮት ፣ አሾልካ ፣ ተመለከተችው ። በመጨረሻውም ፣ ወንበሩ ፣ ላይ ፣ ተቀመጠች ። ራስዋን ፣ ጠረጴዛው ፣ ላይ ፣ ድፍት ፣ አድርጋ ፣ ጥቁር ፣ ሴት ፣ ወይም ፣ ማንኛውም ፣ ድዳ ፣ እንስሳ ፣ መከራውን ፣ ብቻውን ፣ እንደሚሸከም ፣ ውስጥ ፣ ውስጡን ፣ የሚያንብናትን ፣ ሥቃይ ፣ በትዕግሥትና ፣ በጸጥታ ፣ ትቀበለው ፣ ጀመር ።

* * *

መንገዶች ፣ ሁሉ ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ይወስዳሉ ። ሴሲቱን ፣ በሙሉ ፣ ባቡሮች ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ይጓዛሉ ። ግራ ፣ ቀኙን ፣ የሚቃኘው ፣ የባቡር ፣ መብራት ፣ በሐዲዱ ፣ መሥመር ፣ ላይ ፣ በሳሩና ፣ በደንጊያዎቹ ፣ ላይ ፣ በግረፍ ፣ የተኛውን ፣ አገር ፣ ይቀሰቅሳል ። በባቡር ፣ ውስጥ ፣ ሽልብ ፣ የሚያደርጋቸው ፣ ዓይናች ፣ የታደሉ ፣ ናቸው ።

ካሪስብሩክ ፣ ሆኖ ፣ ባቡሩ ፣ ከታሳቁ ፣ ሽለቆ ፣ ወደ ፣ ኮረብቶቹ ፣ እያዘገመ ፣ ሲመጣ ፣ ማየት ፣ ያስደስታል ። የአገሩ ፣ ሰዎች ፣ የባቡሩን ፣ ፉጨት ፣ በመስማት ፣ ብቻ ፣ እንዲህ ፣ ካለ ፣ መንገድ ፣ እንዲህ ፣ ካለ ፣ እርሻ ፣ እንዲህ ፣ ካለው ፣ ወንዝ ፣ አጠገብ ፣ ደረሰ ፣ ይላሉ ። እስጢፋኖስ ፣ ኩማሎ ፣ ባቡር ፣ ጣቢያ ፣ የደረሰው ፣ ከመነሻው ፣ ጊዜ ፣ አንድ ፣ ሰዓት ፣ ቀደም ፣ ብሎ ፣ ቢሆንም ፣ ለእርሱ ፣ የባቡሩ ፣ ድምፅም ፣ ሆነ ፣ የሰው ፣ ውካታ ፣ አልተሰማውም ፣ ነበር ። የሚያሰላስለው ፣ የመንገዱን ፣ ርቀት ፣ ያሰበበት ፣ ስፍራ ፣ ደርሶ ፣ የሚያወጣውን ፣ ገንዘብ ፣ ነበር ። የእጎቱ ፣ ሕመም ፣ ምን ፣ ዓይነት ፣ እንደሆነ ፣ ለሕክምናስ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ገንዘብ ፣ እንደሚያስፈልግ ፣ ማን ፣ ያውቃል ? ይዞአት ፣ እንዲመለስ ፣ የተገደደ ፣ እንደሆን ፣ ወጪው ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ይሆን ? ከሁሉም ፣ በላይ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ብዙ ፣ መንገዶች ፣ ያሉት ፣ ትልቅ ፣ ከተማ ፣ ነው ። ያዩት ፣ ሰዎች ፣ እንደሚሉት ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ ባንዱ ፣ ጐዳና ፣ ወደ ፣ ታች ፣ በመውረድ ፣ ባንደኛው ፣ ወደ ፣ ላይ ፣ በመውጣት ፣ እንዴ ፣ የረገጠውን ፣ መንገድ ፣ ሁለተኛ ፣ ሳይደግም ፣ ቀኑን ፣ በሙሉ ፣ ሊያሳልፍ ፣ ይችላል ። ሰው ፣ አውቶቡስ ፣ ካልተሳፈረ ፣ የፈለገበት ፣ አይደርስም ፣ ይላሉ ። አውቶቡሱ ፣ እንደ ፣ ራሱ ፣ አገር ፣ የፈለጉበት ፣ የሚያደርስ ፣ አይደለም ። የአውቶቡሱ ፣ ብዛት ፣ ስፍር ፣ ቁጥር ፣ የለውም ፤ ምናልባት ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ የሚፈልገው ፣ አውቶቡስ ፣ ከአሥር ፣ አውቶቡሶች ፣ ወይም ፣ ከሃያ ፣ አውቶቡሶች ፣ መካከል ፣ አንዱ ፣ ይሆናል ። አንድ ፣ መነሻውና ፣ መድረሻው ፣ ያልታወቀ ፣ አውቶቡስ ፣ የተሳፈሩ ፣ እንደሆን ፣ ያልታሰበ ፣ ስፍራ ፣

ወስዶ ፡ ይጥላል ። በጆሐንስበርግ ፡ መንገድ ፡ ማቋረጥ ፡ አደገኛ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ሰው ፡ መንገድ ፡ ሳያቋርጥ ፡ እን ዴት ፡ ሊዘዋወር ፡ ይችላል ? እንዲት ፡ የእንዶትሼኒ ፡ ተወ ላጅ ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ ባልዋ ፡ በጠና ፡ ታሞአል ፡ ብለዋት ፡ ለመጠየቅ ፡ ሄዳ ፡ ሳለ ፡ የአሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ዋን ፡ ዓይንዋ ፡ እያየ ፡ የጭነት ፡ መኪና ፡ ገጭቶ ፡ አልገደ ለባትም ?

እስጢፋኖስ ፡ ኩማሎን ፡ በቃላት ፡ ሊገለጥ ፡ የማይ ቻል ፡ ታላቅ ፡ ሥጋት ፡ ይዞ ፡ ያንገላታው ፡ ጀመር ። ልጃ ችን ፡ ያለው ፡ የት ፡ ነው ? እስከ ፡ አሁንስ ፡ ለምን ፡ አንድ ፡ ብጣሽ ፡ ወረቀት ፡ አልጻፈም ?

ባቡሩ ፡ ፉጨቱን ፡ እያሰማ ፡ መጣ ። በደቡብ ፡ አፍ ሪቃ ፡ እንደሚገኙት ፡ የገጠር ፡ ባቡሮች ፡ ሁሉ ፡ ይህም ፡ በጥቁር ፡ መገደኞች ፡ የተሞላ ፡ ነበር ። በተለይ ፡ በዚህ ፡ ባቡር ፡ ውስጥ ፡ ከጥቁር ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ቀለም ፡ አይታ ይም ። በአካባቢው ፡ የሚኖሩት ፡ ነጮች ፡ በባቡር ፡ መጓ ዙን ፡ ከተውት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖአቸዋል ።

ኩማሎ ፡ የገዛ ፡ ወገኖቹ ፡ ተፋፍገው ፡ ወደሚገኙበት ፡ ለጥቁሮቹ ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ተወሰነው ፡ ክፍል ፡ ገባ ። ጥቂቶቹ ፡ ጥቁሮች ፡ የአገር ፡ የማይሉት ፡ ወይም ፡ የፈረንጅ ፡ የማይሉት ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል ። ጥቂቶቹ ፡ ደግሞ ፡ በፈረንጅ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ የብርድ ፡ ልብስ ፡ ደርበውበታል ። ሴቶቹ ፡ ግማሽ ፡ እርቃናቸውን ፡ በሚገልጸው ፡ የሀገር ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ብርድ ፡ ልብስ ፡ አጣፍተዋል ። ወንዶቹ ፡ የሀገር ፡ ልብሳቸውን ፡ እርግፍ ፡ አድርገው ፡ የተውት ፡ ይመስላል ።

ቀኑ ፡ ሞቃት ፡ ነበር ። በባቡሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሽታ ፡ አፍንጫ ፡ ይተነፍጋል ። ኩማሎ ፡ ትሑት ፡ ሰው ፡ በመ

ሆኑ ፡ የቦታው ፡ አለመስማማት ፡ የሰዎቹ ፡ አጉል ፡ ጠረን ፡ እምብዛም ፡ አላስቸገረውም ።

ባቡሩ ፡ ፉጨቱን ፡ አሰምቶ ፡ ንቅናቄ ፡ ጀመረ ። ኩማሎ ፡ እቆመበት ፡ እንዳለ ፡ ተንገዳገደ ። ወድቂ ፡ መሳቂያ ፡ እንዳልሆን ፡ በማለት ፡ በቶሎ ፡ ቦታውን ፡ ያዘ ። ረጅሙ ፡ ጉዞውም ፡ ተጀመረ ። ሥጋትና ፡ ፍርሃት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያዙት ። እዚያ ፡ ስደርስ ፡ ምን ፡ ይገጥመኝ ፡ ይሆን ? የሚ ለው ፡ ፍርሃት ፡ ልጆች ፡ መንገድ ፡ ሲያቋርጡ ፡ የሚሞቱ በት ፡ የታላቁ ፡ ከተማ ፡ ፍርሃት ፡ የእጎቱ ፡ የጌርትሩድ ፡ ሕመም ፡ ፍርሃት ፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ መሞቱና ፡ መኖሩ ፡ ያልታወቀው ፡ የልጁ ፡ የአቤሴሎም ፡ ፍርሃት ፡ ይዞ ፡ ያንገ ላታው ፡ ጀመር ።

ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ የውኃ ፡ ሽታ ፡ እየሆነ ፡ በመ ሄድ ፡ ላይ ፡ ከሚገኘው ፡ ከራሱ ፡ ዓለም ፡ ወጥቶ ፡ ለእርሱ ፡ ባልተፈጠረ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ የመገኘቱ ፡ ፍርሃት ፡ ሰላም ፡ ነሣው ።

ከኪሱም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱሱን ፡ አውጥቶ ፡ ማንበብ ፡ ጀመረ ። ለኩማሎ ፡ ተጨባጭነትና ፡ ውንነት ፡ ያለው ፡ የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

—4—

ባቡሩ ፡ ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ሲጓዝ ፡ አደረ ። ኩማ ሎም ፡ ሰማይና ፡ ምድሩ ፡ ሊላቀቅ ፡ ሲል ፡ ከእንቅልፉ ፡ ብንን ፡ አለ ። በአካባቢው ፡ የሚታየው ፡ አገር ፡ ውበቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አይባልም ። ለጥ ፡ ያለው ፡ ሜዳ ፡ ስፋቱ ፡ ዓይን ፡

እስኪታክት ፣ ቢታይ ፣ አይዘለቅም ። ለኩማሎ ፣ ማን ኛውም ፣ ነገር ፣ እንግዳ ፣ እየሆነበት ፣ ሄደ ። እንግሊዝኛ ፣ ብቻ ፣ የተማረ ፣ የዙሉ ፣ ተወላጅ ፣ ሊያስተውላቸው ፣ የማ ይችሉ ፣ አዳዲስ ፣ ስሞች ፣ ይገጥሙት ፣ ጀመር ። በጽሑ ፍም ፣ ሆነ ፣ በቃል ፣ የሚነገሩት ፣ አዳዲስ ፣ የሆኑት ፣ የቦታ ፣ ስሞች ፣ ከዚህ ፣ ቀደም ፣ ሰምቶ ፣ በማያውቀው ፣ አፍሪካ ንስ ፣ በተባለው ፣ ቋንቋ ፣ ነበር ።

ከመንገደኞቹ ፣ አብዛኞቹ ፡—

— የማዕድኑ ፣ ስፍራ ፣ ያውላችሁ ፣ እያሉ ፣ ሲያወኩ ፣ ይሰማሉ ። ብዙዎቹ ፣ የሚጓዙት ፣ በማዕድኑ ፣ ውስጥ ፣ ለመሥራት ፣ መሆኑ ፣ ግልጽ ፣ ነው ።

— ማዕድን ፣ የሚባለው ፣ ያ ፣ በሩቅ ፣ የሚታየው ፣ ጠፍጣፋው ፣ ኮረብታ ፣ ነው ? ሲል ፣ ኩማሎ ፣ ጠየቀ ።

— ያ ፣ የሚታየው ፣ ከማዕድኑ ፣ የወጣው ፣ ኮረትና ፣ አሸዋ ፣ ነው ፣ ኡምፉንዲሲ ። ወርቁ ፣ ተወስዶለታል ።

— ይህ ፣ ሁሉ ፣ ኮረትና ፣ አሸዋ ፣ እንዴት ፣ አድርጎ ፣ ሊወጣ ፣ ቻለ ?

— እኛ ፣ ጉድጓድ ፣ ውስጥ ፣ ገብተን ፣ ቆፍረን ፣ እና ወጣለን ፣ ኡምፉንዲሲ ። መቆፈር ፣ ሲያቅተን ፣ ፈረንጆቹ ፣ መጥተው ፣ አለቱን ፣ በዲናሚት ፣ ይፈነቃቅሉታል ። እኛም ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ወደ ፣ ጉድጓዱ ፣ ውስጥ ፣ ገብተን ፣ የፈረ ሰውን ፣ ድንጋይ ፣ በመሬት ፣ ውስጥ ፣ ለውስጥ ፣ በሚሄድ ፣ መንኰራኵር ፣ እየጫንን ፣ ወደ ፣ ላይ ፣ እናወጣዋለን ።

— መንኰራኵሩ ፣ እንዴት ፣ አድርጎ ፣ ወደ ፣ ላይ ፣ ሊወጣ ፣ ይችላል ?

— መንኰራኵሩ ፣ የታሰረበትን ፣ ሽቦ ፣ እየጠቀለለ ፣ ወደላይ ፣ የሚስብ ፣ አንድ ፣ ትልቅ ፣ መዘውር ፣ አለ ። ይቆዩ ፣ ብቻ ፣ አሳይዎታለሁ ።

ኩማሎ ፣ ለጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ምንም ፣ ላይናገር ፣ ተቀ መጠ ። ከፍርሃትና ፣ ከሥጋት ፣ የተነሣ ፣ የልቡ ፣ ትርታ ፣ እየጨመረ ፣ ሄደ ።

— ያውና ፣ መዘውሩ ፣ ኡምፉንዲሲ ፤ ያውልዎት ።

አንድ ፣ ትልቅ ፣ ከብረት ፣ የተሠራ ፣ ሕንፃ ፣ በሩቁ ፣ ይታያል ። ከበላዩ ፣ አንድ ፣ ትልቅ ፣ ክብ ፣ ነገር ፣ ለዓይን ፣ በሚያሳስት ፣ ፍጥነት ፣ ይሽከረከራል ። በአካባቢው ፣ ታላ ላቅ ፣ ሕንፃዎች ፣ ይታያሉ ። ከጢስ ፣ መውጫው ፣ እንፋ ሎት ፣ ቱማ ፣ እያለ ፣ ይወጣል ። ሰዎች ፣ ወዲህ ፣ ወዲያ ፣ ይሯ ሯጣሉ ። በአንድ ፣ ታላቅ ፣ ነጭ ፣ ኮረብታ ፣ ላይ ፣ የጭነት ፣ ካሚዮኖች ፣ ይርመሰመሳሉ ። አውቶሞቢሎች ፣ ካሚዮ ኖችና ፣ አውቶቡሶች ፣ አካባቢውን ፣ አጣበውታል ።

— ጆሐንስበርግ ፣ ማለት ፣ ያ ፣ ነው ? ብሎ ፣ ጠየቀ ።

አብዛኞቹ ፣ ቦታውን ፣ ደህና ፣ አድርገው ፣ ስለሚያው ቁት ፣ እርስ ፣ በርሳቸው ፣ እየተያዩ ፣ ተሳሳቁ ።

ከመንገደኞቹ ፣ አንዱ ፡—

— ያ ፣ ምንም ፣ አይደለም ፣—አለ ።—በጆሐንስበርግ ፣ የሚታዩት ፣ ቤቶች ፣ ቁመታቸው ፣ ምን ፣ ልበልዎት ፤ በምን ፣ መለኪያ ፣ ላስረዳዎት ፣ እንዲያው ፣ ዝም ፣ ማለት ፣ ይሻላል ።

የባቡር ፣ ሐዲድ — አሁንም ፣ የባቡር ፣ ሐዲድ — ተአምር ፣ ነው ! በግራም ፣ በቀኝም ፣ የሚታየው ፣ የባቡር ፣ ሐዲድ ፣ ብቻ ፣ ነው ። ሜዳው ፣ በሙሉ ፣ በባቡር ፣ ሐዲድ ፣

ተሸፍኖአል ። አንድ ፡ ባቡር ፡ በተቀመጠበት ፡ በኩል ፡ ውልብ ፡ ብሎ ፡ ሲያልፍ ፡ ኩማሎ ፡ ከድንጋጤው ፡ የተ ነሣ ፡ ከመቀመጫው ፡ ብድግ ፡ አለ ። የባቡሩ ፡ መቆሚያ ፡ ጣቢያ ፡ ጉልቄ ፡ መሳፍርት ፡ የለውም ። በብዙ ፡ መቶ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ በየጣቢያው ፡ ቆመዋል ። ባቡሩ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ብሎአቸው ፡ እብስ ፡ ይላል ።

የቤቶቹ ፡ ቁመት ፡ እያደገ ፡ የመንገዶቹ ፡ ብዛት ፡ ለቊጥር ፡ አላሳች ፡ እየሆነ ፡ ሄደ ። በዚህ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መውጫ ፡ መግቢያውን ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ለማግኘት ፡ ይቻላል ? ለዓይን ፡ ያዝ ፡ በማድ ረጉ ፡ የመንገድ ፡ ዳር ፡ መብራቶች ፡ ብርሃናቸውን ፡ መስ ጠት ፡ ጀምረዋል ።

ከመንገደኞቹ ፡ አንዱ ፡ በጣቱ ፡ እያመለከተ ፡—

— ኡምፉንዲሲ ፡ ጆሐንስበርግ ፡ ያውልዎት ፡— አለ ።

ታላላቅ ፡ ሕንፃዎች ፡ ታዩት ። በሕንፃዎቹ ፡ ላይ ፡ የተተከሉት ፡ ቀይና ፡ አረንጓዴ ፡ መብራቶች ፡ ሕንፃዎቹን ፡ ሲያሀሉ ፡ ምንም ፡ አይቀራቸውም ። መብራቶቹ ፡ አንዴ ፡ ይበራሉ ፡ አንዴ ፡ ይጠፉሉ ። በጠርሙስ ፡ ውስጥ ፡ ውኃ ፡ እየተንቈረቈረ ፡ ወርዶ ፡ ብርጭቆውን ፡ ሲሞላው ፡ መብ ራቱ ፡ ይጠፋል ። እንደ ፡ ገና ፡ ሲበራ ፡ ጠርሙሱ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ይቆምና ፡ ብርጭቆው ፡ ባዶ ፡ ይሆናል ። እንደገና ፡ መብራቱ ፡ ጠፍቶ ፡ ሲበራ ፡ ጠርሙሱ ፡ ተዘቅዝቆ ፡ ውኃ ፡ ብርጭቆው ፡ ውስጥ ፡ ሲንቈረቈር ፡ ይታያል ። ጥቁርና ፡ ነጭ ፡ (ብላክ ፡ ኤንድ ፡ ኋይት ፡) የሚል ፡ አረንጓዴ ፡ ጽሑፍ ፡ ይነበባል ። የሚታየው ፡ ቀለም ፡ ግን ፡ ቀይና ፡ አረንጓዴ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ምሥጢር ፡ ማን ፡ ሊያስተውለው ፡ ይችላል ?

ኩማሎ ፡ አንዳች ፡ ቃል ፡ አይተነፍስም ። ከፍርሃቱ ፡ የተነሣ ፡ ራስ ፡ ምታት ፡ ከፉኛ ፡ ይዞታል ። ባቡሩ ፡ ወደ ፡ ጣቢያው ፡ ይገሠግሣል ። በመጨረሻው ፡ ከአንድ ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ ሥር ፡ ቆመ ። በሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ይርመሰመሳሉ ። ብዙዎቹ ፡ እንደ ፡ አሸን ፡ ከም ድር ፡ ውስጥ ፡ እየፈሉ ፡ ይወጣሉ ። ግማሾቹ ፡ ወደ ፡ ፎቅ ፡ ይወጣሉ ። ግማሾቹም ፡ አሽቈልቊለው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ውስጥ ፡ ሲገቡ ፡ ይታያሉ ። ጥቁሮች — ነጮች — ይወ ጣሉ — ይገባሉ ።

ከባቡሩ ፡ ወርዶ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚገርፈውን ፡ ሕዝብ ፡ ተከትሎ ፡ ወጣ ። በውጭ ፡ የሚሰማው ፡ ጩኸት ፡ ጆሮ ፡ ያደነቁራል ። የአውቶሞቢሉ ፡ የአውቶቡሱ ፡ ብዛት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እይ ባልም ። አብረውት ፡ ከጣቢያው ፡ የወጡት ፡ ሰዎች ፡ መን ገዱን ፡ አቋርጠው ፡ አለፉ ። እርሱ ፡ ግን ፡ ለማቋረጥ ፡ ፈራ ። የትራፊኩ ፡ መብራት ፡ ከአረንጓዴ ፡ ወደ ፡ ብጫ ፡ ከብጫ ፡ ወደ ፡ ቀይ ፡ ከቀይ ፡ ወደ ፡ አረንጓዴ ፡ ይፈራ ረቃል ። አረንጓዴው ፡ መብራት ፡ ሲበራ ፡ ማቋረጥ ፡ መቻ ሉን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያውቃል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለማቋረጥ ፡ ሲቃጣ ፡ ከዚህ ፡ መጣ ፡ የማይባል ፡ ትልቅ ፡ መኪና ፡ በአጠገቡ ፡ ውልብ ፡ ብሎ ፡ ያልፋል ። ይህስ ፡ የጉድ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ያፈገፍጋል ። ቢቸግረው ፡ ሰው ፡ የሚጠብቅ ፡ መስሎ ፡ የእንድ ፡ ሕንፃ ፡ ግድግዳ ፡ ተጠግቶ ፡ ቆመ ። ልቡ ፡ ከፉኛ ፡ ተሸበረ ። የሚያረጋጋው ፡ ነገርም ፡ አጣ ። እምላኬ ፡ ጠብቀኝ ፤ አምላኬ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ጠብቀኝ ፡ እያለ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ለማጽናናት ፡ ሞከረ ።

አንድ ፣ ወጣት ፣ ልጅ ፣ ኩማሎ ፣ ወደ ፣ ቆመበት ፣ ቀረብ ፣ ብሎ ፣—

— ወዴት ፣ ለመሄድ ፣ ይፈልጋሉ ፣ ኡምፋንዲሲ ? ሲል ፣ ጠየቀው ።

— ወደ ፣ ሶፊያታውን ፣ ነው ፣ ወዳጄ ።

— አብረን ፣ እንሂድና ፣ እረዳዎታለሁ ።

የሚረዳው ፣ በማግኘቱ ፣ በአንድ ፣ በኩል ፣ ሲደሰት ፣ በአንድ ፣ በኩል ፣ ደግሞ ፣ ዋርጣሬ ፣ ገባው ።

ታላላቅ ፣ በሆኑ ፣ ሕንፃዎች ፣ በኩል ፣ ለረጅም ፣ ጊዜ ፣ ከሄዱ ፣ በኋላ ፣ ኩማሎ ፣ ሻንጣውን ፣ የያዘበት ፣ እጁ ፣ መዛል ፣ ጀመረ ። በመጨረሻው ፣ ብዙ ፣ አውቶቡሶች ፣ ከቆሙበት ፣ ደረሱ ።

— ሰዎች ፣ ተራቸውን ፣ የሚጠብቁበት ፣ ቦታ ፣ ያው ልዎት ። እርስዎም ፣ እዚያ ፣ ሄደው ፣ ይቁሙ ። ለመሆኑ ፣ ለቲኬት ፣ መግዣ ፣ የሚሆን ፣ ገንዘብ ፣ አለዎት ?

ወጣቱ ፣ ልጅ ፣ ላደረገለት ፣ ዕርዳታ ፣ የተሰማውን ፣ ደስታ ፣ ለመግለጽ ፣ በማለት ፣ ቶሎ ፣ ሻንጣውን ፣ መሬት ፣ አስቀምጦና ፣ ቦርሳውን ፣ ከኪሱ ፣ አውጥቶ ፣ የቲኬቱን ፣ ዋጋ ፣ እንኳን ፣ ሳይጠይቅ ፣ አሥር ፣ ብር ፣ መዘ ፣ ሰጠው ።

—እኔ ፣ ቲኬቱን ፣ ገዝቼልዎት ፣ እስክመጣ ፣ እርስዎ ፣ ተራዎን ፣ ይያዙ ።

— መልካም ፣ ነው ።

ልጁ ፣ አሥር ፣ ብሩን ፣ ተቀብሎ ፣ ሄደ ። ኩማሎም ፣ ልጁ ፣ ከሄደ ፣ በኋላ ፣ ፍርሃት ፣ ፍርሃት ፣ ይለው ፣ ጀመር ።

ሻንጣውን ፣ እንቅ ፣ አድርጎ ፣ ይዞ ፣ ጠጋ ፣ ጠጋ ፣ እያለ ፣ ወደ ፣ አውቶቡሱ ፣ ተቃረበ ። ልጁ ፣ ከአሁን ፣ አሁን ፣ ትኬቱን ፣ ይዞልኝ ፣ ይመጣል ፣ ብሎ ፣ ቢጠባበቅ ፣ ምንም ፣ ብቅ ፣ ሳይል ፣ ቀረ ። አንድ ፣ ነገር ፣ ያሳሰበው ፣ ይመስል ፣ የቆመበትን ፣ መስመር ፣ ለቅቆ ፣ ልጁ ፣ እጥፍ ፣ ወዳለበት ፣ ማዕዘን ፣ ሄደ ። እዚያም ፣ ቆሞ ፣ ቢመለከት ፣ ምንም ፣ አጣ ። እንደ ፣ ምንም ፣ ተበራትቶ ፣ ወደ ፣ አንድ ፣ ሽምገል ፣ ያለ ፣ ሰውዬ ፣ ተጠግቶ ፣ —

— እባክዎን ፣ የትኬት ፣ መሸጫው ፣ ቢሮ ፣ የት ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ያሳዩኝ ? ሲል ፣ ጠየቀ ።

— የትኛውን ፣ የቲኬት ፣ ቢሮ ፣ ኡምፋንዲሲ ?

— የአውቶቡስ ፣ ቲኬት ፣ የሚገዛበት ።

— ቲኬት ፣ የሚሸጠው ፣ በአውቶቡስ ፣ ላይ ፣ ነው ። እዚህ ፣ ምንም ፣ የቲኬት ፣ መሸጫ ፣ ቢሮ ፣ የለም ።

የሰውዬው ፣ ሁኔታ ፣ ጨዋነቱን ፣ ይገልጻል ። ኩማሎም ፣ ያነጋገረው ፣ በትሕትና ፣ ነበር ።

— አንድ ፣ ልጅ ፣ ከቢሮ ፣ ቲኬት ፣ እገዛልሃለሁ ፣ ቢለኝ ፣ አሥር ፣ ብር ፣ አንሥቼ ፣ ሰጥቼው ፣ ነበር ፣— አለ ።

—አታልሎዎታል ፣ ኡምፋንዲሲ ። ከዚያ ፣ ወዲህ ፣ ልጁን ፣ አይተውታል ? እስከ ፣ መቼውም ፣ ሊያዩት ፣ አይችሉም ። እኔን ፣ ይከተሉኝ ። ወደ ፣ ሶፊያታውን ፣ ነው ፣ የሚሄዱት?

— አዎን ፣ ወደ ፣ ሶፊያታውን ፣ ነው ። ወደ ፣ ሚስዮኑ ፣ ማረፊያ ፣ ቤት ።

— መልካም ። እኔም ፣ የምሄደው ፣ ወደዚያው ፣ ነው ። አንድ ፣ የምጠብቀው ፣ ሰው ፣ ነበር ። እስካሁን ፣ ጠብቄው ፣

አልመጣም ። አብረን ፣ እንሄዳለን ። ቄስ ፣ ምሲማንጉን ፣ ያውቃሉ ?

— አዎን ። ከእርሱ ፣ የተላከ ፣ አንድ ፣ ደብዳቤ ፣ ይዤ አለሁ ።

ሁለቱም ፣ አብረው፣ ተራቸውን ፣ መጠበቅ ፣ ጀመሩ ። በመጨረሻውም ፣ አውቶቡስ ፣ ውስጥ ፣ ገብተው ፣ ጉዞ አቸውን ፣ ቀጠሉ ። አውቶቡሱ ፣ ጉዞውን ፣ ፈጽሞ ፣ አንድ ፣ ትንሽ ፣ መንገድ ፣ ዳር ፣ ደርሶ ፣ ቆመ ። ኩማሎና ፣ ጓደኛው ፣ ከአውቶቡሱ ፣ ወርደው ፣ ራቅ ፣ ያለ ፣ መንገድ ፣ በእግራቸው ፣ ሄዱ ። በመጨረሻውም ፣ መብራት ፣ ወደ ሚበራበት ፣ ወደ ፣ አንድ ፣ ቤት ፣ ደርሰው ፣ በሩን ፣ አን ኳኩ ።

አንድ ፣ የቄስ ፣ ልብስ ፣ የለበሰ ፣ ዘለግ ፣ ያለ ፣ ልጅ ግር ፣ ሰው ፣ በሩን ፣ ከፍቶ ፣ ወጣ ።

— ቄስ ፣ ምሲማንጉ ፣ ከእንዶትሼኒ ፣ የመጡትን ፣ ወዳጅዎን ፣ ቄስ ፣ ኩማሎን ፣ ይገርልዎት ፣ መጥቻለሁ ።

— ግቡ ፣ ግቡ ፣ ወዳጆቼ ። እንኳን ፣ ደህና ፣ መጣህ ፣ ቄስ ፣ ኩማሎ ። መቼም ፣ እህልና ፣ ውኃ ፣ ሳያምራችሁ ፣ አልቀረም ። ሚስተር ፣ ማፎሎ ፣ ትንሽ ፣ ቆየት ፣ ብለህ ፣ አብረን ፣ እንጋበዝ ።

ሚስተር ፣ ማፎሎ ፣ ሊቆይ ፣ ባለመቻሉ ፣ ትቶአቸው ፣ ሄደ ። ኩማሎም ፣ አንድ ፣ ትልቅ ፣ ሶፋ ፣ ላይ ፣ ዘፍ ፣ ብሎ ፣ ተቀመጠ ። መኖሪያ ፣ ቤቱ ፣ ደስ ፣ የሚያሰኝ ፣ ነበር ። አረፍ ፣ ብሎ ፣ ያንን ፣ ትርምስምስና ፣ ዝብርቅርቅ ፣ የሞላበ ትን ፣ ከተማ ፣ መርሳት ፣ ፈለገ ። የጆሐንስበርግ ፣ ጉዞው ፣ በመፈጸሙና ፣ ያረፈው ፣ ከደህና ፣ ሰው ፣ ቤት ፣ በመሆኑ ፣

አምላኩን ፣ በልቡ ፣ ውስጥ ፣ አመሰገነ ። ጊዜው ፣ ሲደ ስር ፣ ስለ ፣ መጣበት ፣ ጉዳይ ፣ መወያየታቸው ፣ ባይቀርም ፣ ለጊዜው ፣ ካሰበበት ፣ በደህና ፣ መድረሱ ፣ ለልቡ ፣ ሰላ ምና ፣ እርጋታ ፣ሰጠው ።

—5—

— በአንድ ፣ የቤተክርስቲያናችን ፣ ታማኝ ፣ አባል ፣ በሆነች ፣ ሴት ፣ ቤት ፣ ደህና ፣ ማረፊያ ፣ ተገኝቶአል ። የሴ ትዮዋ ፣ ስም ፣ ወይዘሮ ፣ ሊቴቤ ፣ ይባላል ። ለማረፊያው ፣ በሳምንት ፣ የሚከፈለው ፣ አንድ ፣ ብር ፣ ከሃምሳ ፣ ሳንቲም ፣ ብቻ ፣ ነው ። ምግብም ፣ በሚስዮኑ ፣ ጣቢያ ፣ አብረን ፣ እንመገባለን ፣— አለ ፣ ምሲማንጉ ።

ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ ማዕድ ፣ ወደ ፣ ተሰናዳበት ፣ ክፍል ፣ አብረው ፣ ገቡ ። ኩማሎ ፣ ከብዙ ፣ ጥቁሮችና ፣ ነጮች ፣ ቀሳውስት ፣ ጋር ፣ ተዋወቀ ። የማዕድ ፣ ጸሎት ፣ ካደረሱ ፣ በኋላ ፣ መመገብ ፣ ጀመሩ ።

ከኩማሎ ፣ አጠገብ ፣ የተቀመጡት ፣ ቄስ ፣ እንግሊ ዛዊ ፣ ነበሩ ። እርሳቸውም ፣ ከየት ፣ እንደ ፣ መጣና ፣ የአገሩ ፣ ሁኔታ ፣ እንዴት ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ኩማሎን ፣ ይጠይቁት ፣ ጀመር ። በአቅራቢያው ፣ ተቀምጦ ፣ የሚነጋገሩትን ፣ ይሰማ ፣ የነበረ ፣ አንድ ፣ ጥቁር ፣ ቄስ ፣ ከፍ ፣ ባለ ፣ ድምፅ ፣ —እኔም ፣ የኢኮፖ ፣ ተወላጅ ፣ ነኝ ። አባትና ፣ እናቴ ፣ የሚኖሩት ፣ እዚያው ፣ ነው ። ለመሆኑ ፣ አገር ፣ ደህና ፣ ነው ? ብሎ ፣ ጠየቀ ።

ኩማሎም ፣ ስለ ፣ አገሩ ፣ ርቀት ፣ ስለ ፣ ተራሮቹና ፣ ስለ ፣ ሸለቆዎቹ ፣ ያጫውታቸው ፣ ጀመር ። ስለ ፣ ትውልድ ፣

አገሩ ፣ ያለውን ፣ ፍቅር ፣ በአነጋገሩ ፣ ስለ ፣ ተገነዘቡት ፣ ሁሉም ፣ ጸጥ ፣ ብለው ፣ ይሰሙት ፣ ነበር ። እርሱም ፣ ስለ ፣ መሬቱ ፣ ጠፍነት ፣ መሬቱ ፣ እየተራቈተ ፣ ሳር ፣ አላበቅል ፣ ስለ ፣ ማለቱ ፣ ስለ ፣ ወንዞቹ ፣ መድረቅ ፣ በአገሩ ፣ የሚኖሩት ፣ ሽማግሌዎች ፣ ባልቴቶች ፣ እናቶችና ፣ ሕፃናት ፣ ብቻ ፣ ስለ ፣ መሆናቸው ፣ አንድ ፣ ባንድ ፣ አዋያቸው ።

የሚዘራው ፣ ቦቆሎ ፣ ከሰው ፣ ቁመት ፣ እንደማይበልጥ ፣ ነገራቸው ። በአገሩ ፣ የሚኖሩት ፣ ጎሳዎች ፣ ጎብረት ፣ እንዴት ፣ እንደ ፣ ተፋለሰ ፣ ብዙ ፣ ትዳር ፣ እንዴት ፣ እንደ ፣ ፈረሰ ፣ የሰዎች ፣ ግብረ ፣ ገብነት ፣ እንዴት ፣ እንደ ፣ ተበላሸ ፣ ቤታቸውን ፣ ትተው ፣ የሄዱት ፣ መመለስ ፣ ቀርቶ ፣ ብጣሽ ፣ ወረቀት ፣ እንኳን ፣ ለዘመድ ፣ አዝማድ ፣ እንደማይጽፉ ፣ እንዲህ ፣ ያለው ፣ ጉድ ፣ የተፈጠረው ፣ በእንዶትሼኒ ፣ ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ በአካባቢው ፣ በሙሉ ፣ መሆኑን ፣ ዘርዝሮ ፣ ገለጸላቸው ። የጌርትሩድንና ፣ የአቤሴሎምን ፣ ስም ፣ ግን ፣ አላነሣም ።

ሰዎቹም ፣ ስለ ፣ አገሩ ፣ ጠፍ ፣ መሆን ፣ ስለ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ጎሳዎች ፣ ተናቃላ ፣ ሆኖ ፣ መቅረት ፣ ስለ ፣ ትዳር ፣ መፍረስ ፣ ተወልደው ፣ ካደጉበት ፣ አገር ፣ እየኮበለሉ ፣ በመሄድ ፣ ወጋቸውንና ፣ ባህላቸውን ፣ እርግፍ ፣ አድርገው ፣ ትተው ፣ ስድ ፣ ኑሮ ፣ ስለሚኖሩ ፣ ጐረምሶችና ፣ ኮረዶች ፣ ይወያዩ ፣ ጀመር ። የወንጀልን ፣ ሥራ ፣ እየቀሰሙ ፣ ስለሚያድጉ ፣ ሕፃናት ፣ ወንጀልን ፣ ሥራዬ ፣ ብለው ፣ ስለ ፣ ያዙት ፣ ወሮበሎች ፣ በጥቂሮች ፣ ወንጀለኝነት ፣ ምክንያት ፣ በጆሐንስበርግ ፣ ነጮች ፣ ዘንድ ፣ ስለ ፣ ተፈጠረው ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ፍርሃት ፣ ሐሳብ ፣ ለሐሳብ ፣ ሲለዋወጡ ፣ ከመካከላቸው ፣ አንዱ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ሜይል ፣ የተባለውን ፣ ጋዜጣ ፣

ይዞ ፣ መጣ ። በጋዜጣውም ፣ ላይ ፣ ጠበዕድሜ ፣ የገፉ ፣ ባልና ፣ ሚስት ፣ ብቸኛ ፣ በሆነች ፣ ቤታቸው ፣ ውስጥ ፣ እንዳሉ ፣ ተደብድበው ፣ ሀብታቸውን ፣ ተዘረፉ ፤ አራት ፣ ጥቁሮች ፣ በጥርጣሬ ፣ ተይዘዋል ፣» የሚሉ ፣ ቃላት ፣ በጉልህ ፣ ይታይበት ፣ ነበር ።

ጋዜጣውን ፣ ይዞ ፣ የመጣው ፣ ሰውዬ ፣ — ይሀን ፣ የመሰለው ፣ ወንጀል ፣ በየዕለቱ ፣ ይፈጸማል ፣— አለ ። —ይህ ፣ ሁኔታ ፣ የሚያስፈራው ፣ ነጮችን ፣ ብቻ ፣ አይደለም ። በሶፊያታውን ፣ የምንኖረው ፣ እንኳን ፣ በጣም ፣ እንፈራለን ። ሰሞኑን ፣ እነዚሁ ፣ ወሮበሎች ፣ አንዲት ፣ የእኛው ፣ የሆነችውን ፣ አፍሪቃዊት ፣ ልጃገረድ ፣ ይዘው ፣ ከደበደብዋት ፣ በኋላ ፣ የገንዘብ ፣ ቦርሳዋን ፣ ነጠቋት ። ከአቅራቢያው ፣ ሰዎች ፣ መድረሳቸው ፣ በጀ ፣ እንጂ ፣ ጠልፈው ፣ ወስደው ፣ ሕግዋን ፣ ለመግሠስ ፣ አስበው ፣ ነበር ።

ኩማሎ ፣ አጠገብ ፣ ተቀምጠው ፣ የነበሩት ፣ እንግሊዛዊ ፣ ቄስ ፣ ቀበል ፣ አድርገው ፣ እንዲህ ፣ አሉ ። — ስለዚህ ፣ ጉዳይ ፣ እያደር ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ ትሰማለህ ፣ ብዙ ፣ ጥፋት ፣ የሚፈጸመው ፣ በአንተ ፣ አገር ፣ ብቻ ፣ አይደለም ። እስቲ ፣ ለሁሉም ፣ በሰፊው ፣ እንጨዋወታለን ።

ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ ምሲማንጉ ፣ ኩማሎን ፣ ወደ ፣ መኖሪያ ፣ ቤቱ ፣ ይዞት ፣ ሄደ ።

ወደ ፣ እንግዳ ፣ ማረፊያ ፣ ክፍል ፣ ገብተው ፣ እረፍ ፣ ካሉ ፣ በኋላ ፣ ኩማሎ ፣ — ችኩልህ ፣ አትበለኝ ፣ እንጂ ፣ የእጎቴን ፣ ወሬ ፣ ለመስማት ፣ ጓጉቻለሁ ፣ — አለ ።

ምሲማንጉም ፣ — እርግጥ ፣ ነው ፣ ሥጋት ፣ እንዳለብህ ፣ ይገባኛል ። እስካሁንም ፣ ዝም ፣ በማለቴ ፣ ምን ፣ ያለው ፣

ግድ ፣ የለሽ ፣ ነው ፣ ሳትለኝ ፣ አልቀረህም ። ፈቃድህ ፣ ቢሆን ፣ መጀመሪያ ፣ እንድ ፣ ጥያቄ ፣ ላቀርብልህ ፣ እወ ዳለሁ ። ለመሆኑ ፣ እኅትህ ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ የመጣ ችው ፣ ለምን ፣ ነበር ?

ጥያቄው ፣ ጥቂት ፣ ግራ ፣ የሚያጋባ ፣ ቢሆንም ፣ እን ኳን ፣ የእኅቱ ፣ ባል ፣ በግዕድን ፣ ውስጥ ፣ እንዲሠራ ፣ ተመ ልምሎ ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ እንደ ፣ ሄደ ፣ የሥራ ፣ ጊዜው ፣ ከተፈጸመ ፣ በኋላ ፣ ባለመመለሱና ፣ የመኖሩ ፣ ወይም ፣ የመሞቱ ፣ ወሬ ፣ ጨርሶ ፣ በመጥፋቱ ፣ እኅቱ ፣ ጌርትሩድ ፣ ባልዋን ፣ ፍለጋ ፣ ልጅዋን ፣ ይዛ ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ እንደ ፣ ሄደች ፣ አንድ ፣ ባንድ ፣ አስረዳው ። ምሲማንጉም ፣ የተነገረውን ፣ ሰምቶ ፣ ዝም ፣ በማለቱ ፣—

— በጣም ፣ ታመልች ፣ እንዴ ? በማለት ፣ ሥጋት ፣ የተ ቀላቀለበት ፣ ጥያቄውን ፣ አቀረበ ።

— አዎን ፣ አለ ፣ ምሲማንጉ ፣ ምርር ፣ ብሎ ፣—እኅትህ ፣ በጠና ፣ ታመልች ። ሕመምዋ ፣ ግን ፣ አንተ ፣ የምታስበው ፣ ሕመም ፣ አይደለም ። የያዛት ፣ አደገኛ ፣ የሆነ ፣ ሕመም ፣ ነው ። አንተ ፣ ወደዚህ ፣ እንድትመጣ ፣ የፈለግሁት ፣ መጀ መሪያ ፣ ልጅቱ ፣ ብቸኝነት ፣ ያጠቃት ፣ መሆኑን ፣ ስለ ፣ ተረ ዳሁ ፣ ሁለተኛ ፣ የቂስ ፣ ወንድም ፣ እንዳላት ፣ ስለ ፣ ሰማሁ ፣ ነው ። እዚህ ፣ ከመጣች ፣ ወዲህ ፣ ባልዋን ፣ ያገኘችው ፣ አይመስለኝም ። ለጊዜው ፣ ደግሞ ፣ የምትኖረው ፣ ከባል ፣ ጋር ፣ አይደለም ። ወይስ ፣ ከብዙ ፣ ባሎች ፣ ጋር ፣ ትኖራለች ፣ ልበል ?

—አምላኬ ፣ እንዴት ፣ ታደርገኛለህ ፣— አለ ፣ ኩማሎ ።

— ለጊዜው ፣ የምትኖረው ፣ በዚሁ ፣ አቅራቢያ ፣ በሚገኝ ፣ ክላርሞንት ፣ በተባለ ፣ ስፍራ ፣ ነው ። ስፍራው ፣

በጆሐንስበርግ ፣ ውስጥ ፣ መጥር ፣ ከተባሉት ፣ አንዱ ፣ ነው ። ቦታውን ፣ ፖሊሶች ፣ አዘውትረው ፣ ይጐበኙታል ። ከእነርሱ ፣ ጕብኝት ፣ በኋላ ፣ መንገዱ ፣ በአልኮል ፣ ይታጠ ባል ። በደረሱበት ፣ ሁሉ ፣ ከአልኮል ፣ በስተቀር ፣ ሌላ ፣ ነገር ፣ አይሸትም ።

—በዛሬ ፣ ጊዜ ፣ የሚጠመቀው ፣ መጠጥ ፣ ሰዎችን ፣ በቀ ላሉ ፣ እንዲያሰክር ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ሥራ ፣ ሥሮች ፣ ይቀላቀ ልበታል ። ከዚህም ፣ የተነሣ ፣ የዛሬው ፣ መጠጥ ፣ በሕዝ ባችን ፣ ዘንድ ፣ ከተለመደው ፣ ፈጽሞ ፣ የተለየና ፣ ጉዳትን ፣ የሚያስከትል ፣ ነው ። የእኅትህም ፣ ሥራ ፣ ይህንን ፣ የመ ሰለውን ፣ መጠጥ ፣ እየጠመቀች ፣ መሸጥ ፣ ነው ። ነገሩ ፣ በጣም ፣ የሚያሳዝን ፣ ነው ። ዳሩ ፣ ግን ፣ አንዳችም ፣ ነገር ፣ ልደብቅህ ፣ አልሻም ። የእኅትህ ፣ ሥራ ፣ መጠጥ ፣ መሸጥ ፣ ብቻ ፣ አይደለም ። ካላፊ ፣ ካግዳሚው ፣ ገንዘብ ፣ እየተቀ በለች ፣ የሽርሙጥና ፣ ተግባር ፣ ትፈጽማለች ። በቅርቡ ፣ መጠጥ ፣ ቤትዋ ፣ ውስጥ ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ ተገድሎአል ። ወደ ፣ እርስዋ ፣ መጠጥ ፣ ቤት ፣ የሚሄዱት ፣ ሰዎች ፣ ዋና ፣ ተግባር ፣ መጠጣት ፣ ቁማር ፣ መጫወት ፣ በዱላ ፣ መፈና ከትና ፣ በጩቤ ፣ መሸካሸክ ፣ ነው ። እርስዋም ፣ ከዚሁ ፣ የተነሣ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ወኅኒ ፣ ቤት ፣ ገብታለች ።

ምሲማንጉ ፣ በወንበሩ ፣ ላይ ፣ ተደላድሎ ፣ በመቀ መጥ ፣ በጠረጴዛው ፣ ላይ ፣ የነበረውን ፣ መጽሐፍ ፣ ወዲህ ፣ ወዲያ ፣ እያገላበጠ ፣—

— መቼም ፣ ይህ ፣ አሁን ፣ የነገርኩህ ፣ የሚያሳዝን ፣ ዜና ፣ መሆኑ ፣ ይሰማኛል ፣— አለ ። ኩማሎም ፣ በቃል ፣ ሳይሆን ፣ ራሱን ፣ በማነቃነቅ ፣ የጉዳዩን ፣ እውነትኝነት ፣ አረጋገጠ ።

ሁለቱም ፣ ለጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ዝም ፣ አሉ ። በመጨረሻም ፣ ኩማሎ ፣ — ልጁስ ፣ አብሮአት ፣ ይሆን ? ሲል ፣ ጠየቀ ።

—አዎን ፣ አብሮአት ፣ ነው ፤ እንደ ፣ ነገርኩህ ፣ ቦታው ፣ ለልጅ ፣ ቀርቶ ፣ ለአዋቂ ፣ የሚስማማ ፣ አይደለም ። እንተንም ፣ እስከዚህ ፣ ድረስ ፣ ካስጠራሁባቸው ፣ ምክን ያቶች ፣ አንዱ ፣ የልጁ ፣ ጉዳይ ፣ ነው ። በእናትየው ፣ በኩል ፣ ያለው ፣ ተስፋ ፣ ብዙም ፣ ባይሆን ፣ ልጁን ፣ ከዚህ ፣ አጉል ፣ ኑሮ ፣ ማዳን ፣ ሳይቻል ፣ አይቀርም ።

—የምትኖርበት ፣ ስፍራ ፣ የት ፣ ነው ፣ አልኸኝ ?

— ካለንበት ፣ ቦታ ፣ ብዙም ፣ አይርቅም ። ነገ ፣ እኔው ፣ ራሴ ፣ እስከዚያው ፣ ድረስ ፣ እወስድሃለሁ ።

— የእኔ ፣ ጉድ ፣ ይኸው ፣ ብቻ ፣ አይደለም ። ሌላ ፣ ከባድ ፣ ጎዘን ፣ ደግሞ ፣ አለብኝ ።

— መቼም ፣ የምታዋየው ፣ ሌላ ፣ ዘመድ ፣ የለህም ፤ ለእኔው ፣ ንገረኝ ።

— እርግጥ ፣ ነው ፣ ለአገሩ ፣ እንግዳ ፣ ለሰው ፣ ባዳ ፣ ነኝ ።

የሆዱን ፣ አውጥቶ ፣ ሊነግረው ፣ ሲል ፣ አንደበቱ ፣ ታሰረ ። ከራሱ ፣ ጋር ፣ ሲታገል ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ አሳለፈ ። ምሲማንጉም ፣ — ምንም ፣ አይደል ፣ ቀስ ፣ ብለህ ፣ ትነ ግረኛለህ ፣— አለው ።

— ጉዳዩ ፣ ቀላል ፣ አይደለም ። ታላቅ ፣ ጎዘን ፣ ነው ፣ የደረሰብን ።

— በወንድ ፣ ወይም ፣ በሴት ፣ ልጅ ፣ ምክንያት ፣ ይሆን ?

—ካልክስ ፣ በወንድ ፣ ልጃችን ፣ ምክንያት ፣ ነው ።

— እንግዲያውስ ፣ ጉዳዩን ፣ ዘርዝረህ ፣ ንገረኝ ።

— ልጃችን ፣ አቤሴሎም ፣ ይባላል ። እርሱም ፣ አክስቱን ፣ ፍለጋ ፣ ወደዚሁ ፣ መጥቶ ፣ የውኃ ፣ ሽታ ፣ ሆኖ ፣ ቀርቶአል ። እናቱም ፣ እኔም ፣ የጻፍንለት ፣ ደብዳቤ ፣ ሁሉ ፣ «አድራሻቸው ፣ ያልታወቀ ፣» እየተባለ ፣ ይመለስልናል ። እዚህ ፣ ከመጣሁ ፣ ወዲህ ፣ የሰማሁት ፣ ሁሉ ፣ የበለጠ ፣ ሥጋት ፣ ላይ ፣ ጥሎኛል ።

— አትሥጋ ፣ እርሱንም ፣ እንፈልገዋለን ። ምናልባት ፣ እጎትህ ፣ አድራሻውን ፣ ታውቅ ፣ ይሆናል ። አሁን ፣ ለጊዜው ፣ ከሩቅ ፣ መንገድ ፣ መጥተህ ፣ ስለ ፣ ደከምህ ፣ ወደ ፣ ማረፊያ ፣ ክፍልህ ፣ እወስድሃሁ ።

— አዎን ፣ የሚሻል ፣ ይመስለኛል ።

ሁለቱም ፣ ከተቀመጡበት ፣ ብድግ ፣ አሉ ።

—ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ውስጥ ፣ ጸሎት ፣ የማድረስ ፣ ልማድ ፣ አለኝ ። ምናልባት ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያኑ ፣ ባቅራቢያችን ፣ እንደሆን ፣ ልታሳየኝ ፣ ትችላለህ ? አለ ፣ ኩማሎ ።

— አዎን ፣ በዚያው ፣ በኩል ፣ ነው ፣ የምናልፈው ።

ኩማሎም ፣ በትሕትና ፣ ቃል ፣— አንተም ፣ በጸሎትህ ፣ አትርሳኝ ፣— አለ ።

— ሥራ ፣ ቢበዛብኝም ፣ እዚህ ፣ እስካለህ ፣ ድረስ ፣ በተቻለኝ ፣ ሁሉ ፣ እረዳሃለሁ ።

— ያሰንብትልኝ ።

የኩማሎ ፣ የአንጋገሩ ፣ ትሕትና ፣ የምሲማንጉን ፣ ልብ ፣ ስለ ፣ ነካው ፣— እኔን ፣ ደህና ፣ ሰው ፣ ነው ፣ ብለህ ፣ አታስብ ። እኔ ፣ ራሱን ፣ ወዳድና ፣ ኃጢአተኛ ፣ ሰው ፣ ነኝ ። እስከዚህም ፣ ለመድረስ ፣ የበቃሁት ፣ እግዚአብሔር ፣ የምሕረት ፣ እጁን ፣ ስለ ፣ ሜነብኝ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ አለ ።

ምሲማንጉ ፡ የኩማሎን ፡ ሻንጣ ፡ ብድግ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ራመድ ፡ ሲል ፡ ኩማሎ ፡ አንድ ፡ የምነግርህ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡— አለ ።

— መልካም ፡ ነው ፡ ንገረኝ ።

— በጆሐንስበርግ ፡ አንድ ፡ ወንድም ፡ አለኝ ። ወሬውን ፡ ከሰማሁ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖኛል ። ስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ ኩማሎ ፡ ይባላል ። ሥራው ፡ አናጢነት ፡ ነው ።

ምሲማንጉም ፡ ሳቅ ፡ እያለ ፡— እርሱንማ ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ አውቀዋለሁ ። ለዘመዶቹ ፡ ደብዳቤ ፡ መጻፊያ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ አይደለም ። እርሱ ፡ ታላቅ ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ ወጥቶታል ፡— አለ ።

— የፖለቲካ ፡ ሰው ? የእኔ ፡ ወንድም ?

— አዎን ፡ ወንድምህ ፡ በፖለቲካ ፡ ሽንጎ ፡ ታላቅ ፡ ከሚባሉት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ነው ።

ምሲማንጉ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ አለ ።

— በጎዘን ፡ ላይ ፡ ጎዘን ፡ ጨመረብኝ ፡ አትበለኝ ፡ እንጂ ፡ ወንድምህ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈጽሞ ፡ ተለይቶ አል ። የሚሰብከው ፡ ፍልስፍናም ፡ ለደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ደኅንነት ፡ እግዚአብሔር ፡ መሥራት ፡ ያቃተውን ፡ ሰው ፡ መሥራት ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ነው ።

— ምን ፡ እግር ፡ ጣለኝ ።

— ልትማረር ፡ ይብቃ ።

— አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ክፉኛ ፡ ሥጋት ፡ ይይዘኛል ። ለመሆኑ ፡ ጳጳሱ ፡ ይህን ፡ ጉዴን ፡ ቢሰሙ ፡ ምን ፡ ይሉ ፡ ይሆን ?

— ምን ፡ ሊሉ ፡ ይችላሉ? ይህ ፡ አሁን ፡ ሲፈጸም ፡ የምናየውን ፡ ለወጥ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ያለ ፡ ጳጳስ ፡ እንኳን ፡

ሊያግደው ፡ አይችልም ። ቀድሞ ፡ ማን ፡ ሆነና ፡ የሚያግደው ? መፈጸም ፡ አለበት ።

— እንዴት ፡ እንዲህ ፡ ትላለህ? ኧረ ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፡ ትላለህ?

— አዎን ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፡— አለ ፡ ምሲማንጉ ፡ በጥሞና ፡ አንደበት ። — ዓለም ፡ የተተለመለትን ፡ አቅጣጫ ፡ ተከትሎ ፡ እንዳይራመድ ፡ የሚያግደው ፡ ነገር ፡ የለም ። ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እንደምታወቀው ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ። በበኩሌ ፡ ነጮችን ፡ የመጥላት ፡ ፍላጎት ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ የለም ። አባቴን ፡ ከጨለማ ፡ ያወጡት ፡ ነጮች ፡ ናቸው ። ቀደም ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩልህ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ከአንተ ፡ መሠወር ፡ አልፈልግም ። የልቤን ፡ ነው ፡ የማዋይህ ። የሚያሳዝነው ፡ የብዙ ፡ ነገሮች ፡ መፍረስ ፡ አይደለም ። የሚያሳዝነው ፡ የፈረሰው ፡ ሳይጠገን ፡ መቅረቱ ፡ ነው ። ፈረንጆች ፡ ወገኖቻችንን ፡ ባይተዋርና ፡ ተናቃላ ፡ አድርገዋቸዋል ። ይቅርታ ፡ አድርግልኝ ፡ እንጂ ፡ ሁናቴው ፡ ፈጽሞ ፡ የሚጠገን ፡ አይደለም ። የትዳር ፡ መፍረስ ፡ ሲበረክት ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ መቅኖ ፡ ማጣቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ሕፃናት ፡ በወሮ ፡ በልነት ፡ የሚያድጉት ፡ የሸመገሉ ፡ ነጮች ፡ የሚደበደቡትና ፡ የሚዘረፉት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ግንባሩን ፡ በእጁ ፡ ዳበስ ፡ እያደረገ ፡ ንግግሩን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ቀጠለ ፡—

— ፈረንጆች ፡ ለጥቅማቸው ፡ ሲሉ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ጎሳዎቻችንን ፡ የኑሮ ፡ አቅዋም ፡ አፈረሱ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በፈረሰው ፡ ላይ ፡ በምትኩ ፡ የሠሩት ፡ ነገር ፡ የለም ። ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እያወጣሁ ፡ እያወረድሁ ፡ አስቤበታ

ለሁ ። የምናገረው ፣ ሁሉ ፣ የለበጣ ፣ አይደለም ። እውነት ፣ መሆኑንም ፣ ፍጹም ፣ ልቤ ፣ ያምንበታል ። ይህንንም ፣ ስል ፣ ፈረንጆች ፣ ሁሉ ፣ ከአንድ ፣ ባሕር ፣ የተቀዱ፣ ናቸው፣ ማለቱ ፣ አይደለም ። የፈረስውን ፣ መልሰው ፣ ለመገንባት ፣ ሕይወታቸውን ፣ የሚሠው ፣ አልፎ ፣ አልፎ ፣ አይታጡም ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ እንዲህ ፣ ያሉት ፣ ብዙዎች ፣ አይደሉም ። ከእነርሱም ፣ መካከል ፣ ብዙዎቹ ፣ ይፈራሉ ። እንደ ፣ እውነቱ ፣ ከሆነስ ፣ ይህች ፣ አገር ፣ የምትተዳደረው ፣ በፍርሃት ፣ ነው ፣ ለማለት ፣ ይቻላል ።

ጥቂት ፣ ሳቅ ፣ ብሎ ፣ ኩማሎን ፣ እየተመለከተ ፣ ንግግሩን ፣ ቀጠለ ፣ — ይህ ፣ ጉዳይ ፣ እንዲህ ፣ በቁመና ፣ ተወ ያይተውት ፣ የሚያልቅ ፣ አይደለም ። ጸጥ ፣ ያለ ፣ አእምሮና ፣ ምቹ ፣ ጊዜ ፣ ያስፈልገዋል ። እንደ ፣ እኔ ፣ ቢሆን ፣ ከአባ ፣ ቪንሴንት ፣ ጋር ፣ ተገናኝተህ ፣ ስለዚህ ፣ ጉዳይ ፣ ሐሳብ ፣ ለሐሳብ ፣ ብትለዋወጥ ፣ መልካም ፣ ይመስለኛል ። እርሳቸው ፣ ፈረንጅ ፣ ስለ ፣ ሆኑ ፣ እቅጭዋን ፣ ሊነግሩህ ፣ ይችላሉ ። አባ ፣ ቪንሴንት ፣ እኒያ ፣ ቅድም ፣ ስለ ፣ አገርህ ፣ ሌላ ፣ ጊዜ ፣ እንጨዋወታለን ፣ ያሉህ ፣ ቁስ ፣ ናቸው ።

— እምን ፣ እስታውሳለሁ ።

* * *

— ወይዘሮ ፣ ሊቴቤ ፣ እንግዳ ፣ ይገርልዎት ፣ መጥቻለሁ ። ቁስ ፣ እስጢፋኖስ ፣ ኩማሎ ፣ ይባላሉ ።

— እንኳን ፣ ደህና ፣ መጡ ፣ ኡምፉንዲሲ ። ለማረፊያ ፣ ያዘጋጀሁልዎት ፣ ክፍል ፣ ትንሽ ፣ ናት ። ነገር ፣ ግን ፣ በንጹሕ ፣ የተዘጋጀች ፣ ስለ ፣ ሆነች ፣ እንደምትስማማዎት ፣ ተስፋ ፣ አደርጋለሁ ።

— በጣም ፣ ደስ ፣ ይለኛል ።

— በል ፣ በደህና ፣ እደር ፣ ነገ ፣ ጠዋት ፣ በአንድ ፣ ሰዓት ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ እንገናኝ ።

— ደህና ፣ እደር ፣ በሰላም ፣ ያገናኘን ።

— በደህና ፣ ይደሩ ፣ ኡምፉንዲሲ ።

ወይዘሮ ፣ ሊቴቤ ፣ ኩማሉን ፣ በንጹሕ ፣ ወደ ፣ ተዘጋጀችው ፣ ትንሽ ፣ ክፍል ፣ ወሰዳ ፣ ሻማ ፣ አበራችለት ።

— የሚያስፈልግዎት ፣ ሌላ ፣ ነገር ፣ ቢኖር ፣ ይንገሩኝ ፣ ኡምፉንዲሲ ።

— አመሰግናለሁ ።

— በደህና ፣ ይደሩ ፣ ኡምፉንዲሲ ።

— በደህና ፣ ይደሩ ፣ ወይዘሮ ፣ ሊቴቤ ።

ለጥቂት ፣ ጊዜ ፣ መኝታ ፣ ቤቱ ፣ ውስጥ ፣ ቆሞ ፣ የሰማውን ፣ ሁሉ ፣ በልቡ ፣ ውስጥ ፣ ያሰላስል ፣ ጀመር ። ከአርባ ፣ ስምንት ፣ ሰዓት ፣ በፊት ፣ ከእንዶትሼኒ ፣ ለመነሣት ፣ ከባለቤቱ ፣ ጋር ፣ ዕቃውን ፣ ያሰናዳ ፣ ነበር ። ከሃያ ፣ አራት ፣ ሰዓት ፣ በፊት ፣ በባቡር ፣ ተሳፍሮ ፣ በጨለማ ፣ የተሸፈነውን ፣ አገር ፣ ለማቋረጥ ፣ ይጓዝ ፣ ነበር ። አሁን ፣ ግን ፣ አሰበበት ፣ ደርሶ ፣ የሰዎች ፣ ውካታና ፣ ጫጫታ ፣ በየሰዎቹም ፣ እማካይነት ፣ የአንድ ፣ ታላቅ ፣ ከተማ ፣ ትርምስ ፣ ይሰማዋል ። ጆሐንስበርግ — ጆሐንስበርግ ። ያየውና ፣ የሰማው ፣ ሁሉ ፣ እውነት ፣ አልመስል ፣ አለው ።

—6—

ክላረሞንት ፣ ከጆሐንስበርግ ፣ ሩቅ ፣ አይደለችም ። ማንኛውም ፣ ሰው ፣ መሬት ፣ ገዝቶ ፣ መኖሪያ ፣ ጎጆውን ፣ ሊሠራ ፣ የሚችልባት ፣ ሶፊያታውን ፣ በጆሐንስበርግ ፣

ማዘጋጀ ፡ ቤት ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ዌስተርን ፡ ኔቲቭ ፡ ታወንሺፕና ፡ የጆሐንስበርግ ፡ ጥራጊ ፡ ማከማቻ ፡ የሆነችው ፡ ክላረሞንት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አይራራቁም ። እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ መንደሮች ፡ በምዕራብ ፡ ኒውላንድስ ፡ በምሥራቅ ፡ ዌስትዴኔ ፡ በተባሉት ፡ የነጮች ፡ መኖሪያ ፡ ሰፈሮች ፡ ይዋሰናሉ ።

ምሲማንጉና ፡ ኩማሎ ፡ ጉዞአቸውን ፡ ቀጥለው ፡ ክላረሞንት ፡ ደረሱ ። ኩማሎ ፡ በመንደሩ ፡ ንጽሕና ፡ ማጣት ፡ በቤቶቹ ፡ እፍግፍግ ፡ ብሎ ፡ መሠራት ፡ በየመንገዶቹ ፡ ጻር ፡ በተቆለለው ፡ ቆሻሻ ፡ ብዛት ፡ ጎዘን ፡ ተሰማው ።

— ያች ፡ ሴትዮ ፡ ትታይሃለች ?

— አዎን ፡ ትታየኛለች ።

— ከመንደሩ ፡ መጠጥ ፡ ሻጮች ፡ አንድዋ ፡ ናት ። ጆሐንስበርግ ፡ ከሚኖሩት ፡ ሴቶች ፡ መካከል ፡ በሀብት ፡ የሚስተካከላት ፡ የለም ፡ ይባላል ።

— እነዚህ ፡ ልጆችስ? ለምን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አይሄዱም ?

— አብዛኛዎቹ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ አይፈልጉም ፤ ጥቂቶቹንም ፡ ወላጆቻቸው ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አይሰዱአቸውም ፤ ሌሎቹም ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ስፍራ ፡ በማጣት ፡ የቀሩ ፡ ናቸው ።

— ቤቱ ፡ ያውና ። ቁጥር ፡ አሥራ ፡ አንድ ። ብቻህን ፡ ብትገባ ፡ አይሻልም ?

— የሚሻል ፡ ይመስለኛል ።

— ጉዳይህን ፡ ከጨረስህ ፡ በኋላ ፡ ቁጥር ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ውስጥ ፡ ፈልገኝ ። በዚያም ፡ አንዲት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ አባል ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ ትኖራለች ። እርስዋና ፡ ባልዋ ፡ ልጆቻቸውን ፡ በሚገባ ፡ ለማሳደግ ፡ የሚጥሩ ፡ ጨዋ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ናቸው ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ አለባቸው ።

እቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሳቅና ፡ ውካታ ፡ ይሰማል ። ምናልባት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ሥጋት ፡ ስላደረበት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሳቁ ፡ ራሱ ፡ አጉል ፡ በመሆኑ ፡ አይታወቅም ፡ ልቡ ፡ ይፈራና ፡ ይሸበር ፡ ጀመር ። የሴት ፡ ድምፅ ፡ የወንዶች ፡ ድምፅ ፡ ይሰማል ። በሩን ፡ አንኳኳ ፤ ተከፈተለት ።

— እኔ ፡ ነኝ ፡ የእናቴ ፡ ልጅ ። እርስዋ ፡ ግን ፡ ድንግጥ ፡ ብላ ፡ ፊቱ ፡ ቆመች ። ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሸሸት ፡ እንደማለት ፡ ቃጣት ። ዞር ፡ ብላ ፡ እንድ ፡ ነገር ፡ ተናገረች ። ለእርሱ ፡ ግን ፡ የተናገረችው ፡ አልተሰማውም ። ወንበሮች ፡ ይነሣሉ ። የሌላም ፡ ነገር ፡ ድምፅ ፡ ይሰማል ። ወደ ፡ እርሱ ፡ ዞር ፡ ብላ ፡—

— ቤቱ ፡ እስኪዘጋጅ ፡ ነው ፡ ወንድሜ ፡—አለችው ።

እርሱ ፡ ሠግቶአል ። እርስዋም ፡ ፈርታለች ። ሁለቱም ፡ ተፋጠው ፡ ቆመዋል ። ወደ ፡ ኋላ ፡ ዞር ፡ ብላ ፡ ቤቱ ፡ ተሰናድቶ ፡ እንደሆን ፡ አየች ። አንድ ፡ በር ፡ ሲዘጋ ፡ ተሰማ ።

እንደምንም ፡ ብላ ፡— ግባ ፡ ወንድሜ ፡—አለችው ። እጅዋንም ፡ ዘርግታ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠችው ። እጅዋ ፡ ረጥቦአል ፤ ቀዝቅዞአል ፤ ሕይወት ፡ ያለበት ፡ አይመስልም ።

— ወደ ፡ አንቺ ፡ ነው ፡ የመጣሁት ፡— አላት ።

— መልካም ፡ ነው ።

— ምንም ፡ ደብዳቤ ፡ አልጻፍሽልንም ።

— አዎን ፡ አልጻፍሁም ።

— ባልሽ ፡ የት ፡ ነው?

— አላገኘሁትም ።

— ስለ ፣ እርሱም ፣ አልጻፍሽልንም ።
— አዎን ፣ አልጻፍሁም ።
— ይህን ፣ ሁሉ ፣ ጊዜ ፣ በሥጋት ፣ እንደምንኖር ፣ አልተሰማሽም ?
— ደብዳቤ ፣ መላኪያ ፣ ገንዘብ ፣ አጥቼ ፣ ነው ።
— ያሥራ ፣ አምስት ፣ ሣንቲም ፣ ቴምብር ፣ አጣሽ ፣

አንዳችም ፣ ቃል ፣ አትመልስም ። ቀናም ፣ ብላ ፣ አታየውም ።
— ሀብታም ፣ ሆነሻል ፣ ማለትን ፣ ሰምቻለሁ ።
— ምንም ፣ ሀብት ፣ የለኝም ።
— እስር ፣ ቤት ፣ ገብተሽ ፣ ነበር ፣ ማለትን ፣ ሰምቻለሁ ።
— አዎን ፣ ገብቼ ፣ ነበር ።
— በመሸታ ፣ ምክንያት ፣ ነው ?

ነገሩን ፣ ሁሉ ፣ በዝምታ ፣ ማሳለፍ ፣ የማይቻል ፣ መሆኑ ፣ ተሰማት ። በራስዋ ፣ ጥፋት ፣ ሳይሆን ፣ በሌላ ፣ ሴት ፣ ምክንያት ፣ መሆኑን ፣ ገለጠችለት ።

— ከሴትዮዋ ፣ ጋር ፣ ትኖሪ ፣ ነበር ፣ ማለት ፣ ነዋ ?
— አዎን ።
— ይህችን ፣ ከመሰለች ፣ አጉል ፣ ሴት ፣ ጋር ፣ ምን ፣ አጋጠመሽ ?
— ሌላ ፣ መጠጊያ ፣ አልነበረኝም ።
— አሻሻጭዋ ፣ ነበርሽ ፣ ማለት ፣ ነዋ ?
— ምን፣አድርጊ፣ትለኛለህ፣ለልጁ፣ገንዘብ፣አስፈለገኝ !
— ልጁ ፣ የት ፣ ነው ?

እንዲያው ፣ ለይምሰል ፣ ግራ ፣ ቀኙን ፣ ከተመለከተች ፣ በኋላ ፣ ወጣ ፣ ብላ ፣ ልጁን ፣ ትጣራ ፣ ጀመር ። ያ ፣ ለዛ ፣

የነበረው ፣ ድምፅዋ ፣ ለጆሮ ፣ የሚቀፍ ፣ ሆኖአል ። ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በፊት ፣ የሰማው ፣ ሳቅና ፣ ውካታ ፣ ትዝ ፣ አለው ። ሁኔታዋ ፣ ሁሉ ፣ የኑሮዋን ፣ አሳዛኝነት ፣ ይተር ክለት ፣ ጀመር ።

— ልጁ ፣ አሁኑ ፣ ይመጣል ፣— አለችው ።
— ለመሆኑ ፣ የት ፣ ነው ፣ ያለው?
— የሚያመጣው ፣ ሰው ፣ ልኬአለሁ ።

የሥጋትና ፣ የተስፋ ፣ መቀላቀጥ ፣ ስሜት ፣ በገጽዋ ፣ ይታያል ። በቆመችበት ፣ አጠገብ ፣ ያለውን ፣ ግድግዳ ፣ በጣቶችዋ ፣ ትደባብሰዋለች ። ሳያስበው ፣ ግልፍ ፣ አለው ።

— ለመሆኑ ፣ የት ፣ ነው ፣ የማርፈው? ብሎ ፣ ጠየቃት ።

ፍርሃትዋ ፣ በግልጽ ፣ ይታይ ፣ ጀመር ። ጉድዋን ፣ መደበቅ ፣ አልተቻላትም ። ቀላጣው ፣ ስላሸነፈው ፣ ለጥያቄው ፣ መልስ ፣ እስኪሰጠው ፣ አልጠበቀም ።

የገዛ ፣ ጉዱን ፣ ሌላ ፣ ሰው ፣ እንዳይሰማው ፣ በማለት ፣ ለዘብ ፣ ባለ ፣ ድምፅ ፣—

— ስማችንን ፣ አጠፋሽው ፤ መሸታ ፣ ሻጭ ፣ ሴትኛ ፣ አዳሪ ፣ አንድ ፣ ልጅሽን ፣ መሰብሰብ ፣ የተሳነሽ ፣ የቁስ ፣ እጎት ፣ እንዴት ፣ እንዲህ ፣ አድርገሽ ፣ ታዋርጅን ?

ሥቃይ ፣ እንደ ፣ በዛበት ፣ ድዳ ፣ እንሰሳ ፣ ትክ ፣ ብላ ፣ በጎዘን ፣ ተመለከተችው ።

— ይገርሽ ፣ ልሄድ ፣ ነው ፣ የመጣሁት ፣ አላት ። ወለሉ ፣ ላይ ፣ ድፍት ፣ ብላ ፣ ታለቅስ ፣ ጀመር ። ጎፍረትዋና ፣ ጭንቀትዋ ፣ በልቅሶ ፣ እንዲወጣላት ፣ የቈረጠች ፣ ይመስል ፣ ድምፅዋን ፣ ከፍ ፣ አድርጋ ፣ ልቅሶዋን ፣ ለቀቀችው ።

— እረ ፡ ሰው ፡ ይሰማናል ፡— አላት ።

ልቅሶዋን ፡ መግታት ፡ አቃታት ።

— አብረሽኝ ፡ ለመሄድ ፡ ትፈቅጃለሽ ?

ፈቃደኛ ፡ መሆንዋን ፡ ራስዋን ፡ በማነቃነቅ ፡ እየገለጠች ፡—

— ጆሐንስበርግ ፡ መኖር ፡ መርሮኛል ፡ ሰልችቶኛል ፡ ፈጽሞ ፡ አንገፍግፎኛል ። ሕፃኑም ፡ ሰልችቶታል ፡— አለችው ።

— እውነት ፡ ከልብሽ ፡ አብረሽኝ ፡ መሄድ ፡ ትፈቅጃለሽ?

አሁንም ፡ ራስዋን ፡ አወዛወዘች ። እንባ ፡ ይተናነቃት ፡ ጀመር ። — ጆሐንስበርግ ፡ አስጠልቶኛል ፡— እያለች ። በሥቃይ ፡ በደከሙ ፡ ዓይኖችዋ ፡ ተመለከተችው ። ከተስፋው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ የኩማሎ ፡ የልቡ ፡ ትርታ ፡ እየጨመረ ፡ ሄደ ።— እኔ ፡ አጕል ፡ ሴት ፡ ነኝ ፡ ወንድምዬ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጉድ ፡ ተሸክሜ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገሬ ፡ መግባት ፡ የምችል ፡ አይመስለኝም ።

ዓይኖቹ ፡ እንባ ፡ አዘሉ ። የርኅራኄ ፡ መንፈስ ፡ ቀሣጣውንና ፡ ብስጭቱን ፡ ድል ፡ አደረገው ። ከተደፋችበት ፡ አንሥቶ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ አስቀመጣት ። ፊትዋን ፡ በእጁ ፡ ደባበሰላት ። ልቡ ፡ በኀዘንና ፡ በርኅራኄ ፡ ተሞላ ።

— አምላክ ፡ ሆይ ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ አለ ። — እኔ ፡ ግን ፡ ነኝ ፡ ይቅርታን ፡ የምነፍግ ። ጸሎት ፡ እናድርስ ።

ሁለቱም ፡ ለጸሎት ፡ ተንበረከኩ ። ጕሪቤት ፡ እንዳይሰማ ፡ በማለት ፡ ጸጥ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ይጸልይ ፡ ጀመር ። ጸሎቱ ፡ እንዳበቃ ፡ ሁለቱም ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተያይዘው ፡ ተቀመጡ ።

— እንድ ፡ ነገር ፡ እንድትረጅኝ ፡ እለምንሻለሁ ፡— ስለ ፡ ልጃችን ፡ የምታውቂው ፡ ነገር ፡ አለ ?

— ጆሐንስበርግ ፡ በሚገኝ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሩብሪካ ፡ እየሠራ ፡ ሶፊያታውን ፡ ይኖራል ፡ ማለትን ፡ ሰምቼ ፡ ነበር ። የተለየ ፡ አድራሻው ፡ የት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ አላውቅም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የወንድማችን ፡ የዮሐንስ ፡ ልጅ ፡ ያለበትን ፡ ሳያውቅ ፡ አይቀርም ፤ ሁለቱ ፡ የማይለያዩ ፡ ጓደኞች ፡ መሆናቸውን ፡ አውቃለሁ ።

— መልካም ፡ ወደዚያው ፡ ሄጄ ፡ እፈልገዋለሁ ። አስቀድሚ ፡ ወይዘሮ ፡ ሊቱቤ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ያገኙልሽ ፡ እንደሆን ፡ መጠየቅ ፡ አለብኝ ። ለመሆኑ ፡ ብዙ ፡ ዕቃ ፡ አለሽ ?

— ብዙ ፡ ዕቃስ ፡ የለኝም ። ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ እነዚያ ፡ ወንበሮች ፡ አንድ ፡ አልጋ ፡ ጥቂት ፡ ድስቶችና ፡ ሳህኖች ፤ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

— ዕቃዎቹን ፡ የሚያደርስ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ይገር ፡ እመለሳለሁ ። እስከዚያው ፡ ተሰናጂ ።

— ልጁ ፡ ይኸውልህ ።

ሕፃኑ ፡ እቤት ፡ ገባ ። ልብሶቹ ፡ ቁሽሽዋል ። አፍንጫው ፡ ንፍጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ጣቱን ፡ አፉ ፡ ውስጥ ፡ አስገብቶ ፡ እየጠባ ፡ ዓይኖቹን ፡ በማቁለጭለጭ ፡ አጎቱን ፡ በፍርሃት ፡ መንፈስ ፡ ይመለከተው ፡ ጀመር ።

ኩማሎ ፡ ሕፃኑን ፡ ብድግ ፡ አድርጎ ፡ ታቀፈው ። እፍንጫውን ፡ ጠራርጎ ፡ ከሳመው ፡ በኋላ ፡ እየደባበሰ ፡ ያጫዋውተው ፡ ጀመር ።

— ከዚህ ፡ መሄድ ፡ ለሕፃኑ ፡ በጣም ፡ ይበጀዋል ።

ነፋስ ፣ እንደ ፣ ልብ ፣ በሚነፍስበት ፣ ትምህርት ፣ ቤት ፣ በሚ
ገኝበት ፣ አገር ፣ መኖር ፣ ይሻለዋል ።
— አዎን ፣ ይሻለዋል ፣— አለች ።
— በይ ፣ እንግዲህ ፣ ልሂድ ። ብዙ ፣ የምፈጽመው ፣
ሥራ ፣ አለብኝ ።

ከቤት ፣ ሲወጣ ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ እንደ ፣ ጉድ ፣ ይመ
ለከቱት ፣ ነበር ። ቁስን ፣ ደግሞ ፣ እዚህ ፣ ምን ፣ አመጣው ፣
የሚል ፣ ስሜት ፣ ሳያድርባቸው ፣ አልቀረም ። ምሲማን
ጉን ፣ ወዲያው ፣ አግኝቶ ፣ ያጋጠመውን ፣ ሁሉ ፣ አዋየው ።
ቀጥሎም ፣ እጎቱን ፣ ልጅዋንና ፣ ዕቃዋን ፣ የሚያጓጉዝለት ፣
ሰው ፣ እንዲያፋልገው ፣ ጠየቀው ።

— እሺ ፣ እንሂድ ፣— አለ ፣ ምሲማንጉ ። — ስለ ፣
አንተ ፣ እኔ ፣ ደስ ፣ ብሎኛል ።
— ትልቅ ፣ ሸክም ፣ ነው ፣ ከጫንቃዬ ፣ የወረደልኝ ።
የእግዚአብሔር ፣ ፈቃድ ፣ ሆኖ ፣ ሌላው ፣ ጉዳዬም ፣ እን
ደዚሁ ፣ ቢከናወንልኝ ፣ በጣም ፣ ዕድለኛ ፣ ነኝ ።

የዚያኑ ፣ ዕለት ፣ ማታ ፣ የጭነት ፣ መኪና ፣ ተከራይቶ ፣
ሊያመጣት ፣ ሄደ ። መኪናው ፣ ከስፍራው ፣ እንደ ፣ ደረሰ ፣
በብዛት ፣ የሚቈጠሩ ፣ ወሬ ፣ ሸማች ፣ ጐረቤቶች ፣ ተሰብ
ስበው ፣ ስለ ፣ ሁኔታው ፣ በግልጽ ፣ ይወያዩ ፣ ጀመር ።
ጥቂቶቹ ፣ — ደግ ፣ አደረገ ፣ ሲሉ ፣ ጥቂቶቹ ፣ ደግሞ ፣
የተለመደ ፣ የአራዳ ፣ ሳቃቸውን ፣ እያሰሙ ፣ ያፌዙ ፣ ነበር ።
ዕቃው ፣ ተጭኖ ፣ መኪናው ፣ መንቀሳቀስ ፣ ሲጀምር ፣
የኩማሎ ፣ ልብ ፣ ረጋ ፣ አለ ።

ወይዘሮ ፣ ሊቴቤ ፣ ክፍላቸውን ፣ አሳየቻቸው ። ለሕ
ፃኑና ፣ ለእናቱ ፣ ምግብ ፣ ቀረበላቸው ፣ ከመኝታ ፣ በፊት ፣

በምግብ ፣ ቤቱ ፣ ውስጥ ፣ ኩማሎ ፣ ወይዘሮ ፣ ሊቴቤና ፣
ጌርትሩድ ፣ አብረው ፣ ጸሎት ፣ አደረሱ ።

ከጸሎቱ ፣ በኋላ ፣ ለብዙ ፣ ዓመት ፣ ያህል ፣ ያልተሰ
ማው ፣ የመንፈስ ፣ ዕረፍት ፣ አረካው ። ጆሐንስበርግ ፣
ባሳለፈው ፣ በአንድ ፣ ቀን ፣ ውስጥ ፣ ተናቃላ ፣ የሆነው ፣
ነገዱ ፣ ወደ ፣ ቀድሞ ፣ መሠረቱ ፣ የተመለሰ ፣ የፈረሰው ፣
ትዳር ፣ እንደ ፣ ገና ፣ የታደሰ ፣ ጠፍታ ፣ የነበረችው ፣ ነፍስ ፣
የዳነች ፣ መሰለው ።

—7—

በሰዎች ፣ ዘንድ ፣ ሀብታም ፣ ነች ፣ እየተባለች ፣ ብት
ታማም ፣ እንኳ ፣ ጌርትሩድ ፣ የለበሰችው ፣ ልብስ ፣ ጭር
ንቁስ ፣ ራስዋ ፣ ላይ ፣ ያሰረችው ፣ ሻሽ ፣ የተጨማደደና ፣
የወረዛ ፣ በመሆኑ ፣ ወንድምዋን ፣ ጎፍረት ፣ ተሰማው ።
ከቋጠረው ፣ አነሥተኛ ፣ ገንዘብ ፣ ላይ ፣ አንሥቶ ፣ አንድ ፣
ቀለሙ ፣ ቀላ ፣ ያለ ፣ ቀሚስ ፣ ራስዋ ፣ ላይ ፣ የምታስረው ፣
ደህና ፣ ሻሽ ፣ ገዛላት ። ለሕፃኑ ፣ አንድ ፣ ሸሚዝ ፣ አንድ ፣
ቁምጣ ፣ ሱሪ ፣ አንድ ፣ ሹራብና ፣ ለመናፈጪያ ፣ የሚያ
ገለግሉ ፣ ሁለት ፣ ጠንካራ ፣ መሀረቦች ፣ ገዛለት ። በኪሱ ፣
ውስጥ ፣ እርሱና ፣ ባለቤቱ ፣ ለማድ ፣ ቤት ፣ ዕቃ ፣ መግዣ ፣
ያጠራቀሙት ፣ ሰባ ፣ ብር ፣ ያለበት ፣ የባንክ ፣ የገንዘብ ፣
ማጠራቀሚያ ፣ ደብተር ፣ ይገኛል ። ባለቤቱ ፣ እንደ ፣ ማን
ኛውም ፣ የቤት ፣ እመቤት ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ምድጃ ፣ ተግ
ዝቶላት ፣ እፎይ ፣ ለማለት ፣ በመመኘት ፣ ለረጅም ፣ ጊዜ ፣
ተስፋ ፣ ታደርግ ፣ ነበር ። ከስድሳ ፣ ብር ፣ ደመወዝ ፣ ውስጥ ፣
ሰባ ፣ ብር ፣ ለማጠራቀም ፣ ብዙ ፣ ትዕግሥትና ፣ ጥንቃቄ ፣

ማስፈለጉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ኩማሎ
ቂስ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ በየዕለቱ ፡ ጠቅር ፡ ያለ
ንጹሕ ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ ነበረበት ። ሰሞኑን ፡ ግን
የቅስና ፡ ኩሌታው ፡ እያደፈና ፡ እየተጨማደደ ፡ መሄድ
ጀምሮአል ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል? ከተጠ
ቀመው ፡ ሰባ ፡ ብር ፡ ውስጥ ፡ ማጕደል ፡ ላይቀርለት ፡ ነው
ባቡሩ ፡ በነፃ ፡ እያሳፍርም ። ለእኅቱ ፡ ዕቃ ፡ ማጓጓዣ
አሥር ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ መጠየቃቸው ፡ አይቀርም
ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይታፈስበታል ፡ ከሚባለው ፡ እጕል
ኑሮዋ ፡ እንዳች ፡ ቅርስ ፡ እንኳን ፡ ለመያዝ ፡ አለመቻልዋ
በጣም ፡ ገረመው ።

ጌርትሩድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጉድ ፡ ጉድ ፡ እያለች
ወይዘሮ ፡ ሊቴቤን ፡ ትረዳ ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ
ዋን ፡ እየሠራች ፡ ስታንጐራጕር ፡ ይሰማል ። ሕፃኑ ፡ አና
ጢዎች ፡ የጣሉትን ፡ ጡብና ፡ የእንጨት ፡ ጕማጅ ፡ እየሰ
በስበ ፡ ይጫወታል ። ፀሐይዋ ፡ ደምቃለች።በዚህ ፡ ትልቅ
ከተማ ፡ ውስጥ ፡ እንኳን ፡ ድንቢጦች ፡ ውር ፡ ውር ፡ እያሉ
ድምፃቸውን ፡ ያሰማሉ ። ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ምሲ
ማንጉ ፡ ሲመጣ ፡ አየ ። ለባለቤቱ ፡ ለመጻፍ ፡ የጀመረውን
ደብዳቤም ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አለው ።

— ተዘጋጅተሃል ?

— አዎን ፡ ተዘጋጅቻለሁ ። ለባለቤቴ ፡ ደብዳቤ
እጽፍ ፡ ነበር ።

— ባንተዋወቅም ፡ የከበረ ፡ ሰላምታዬን ፡ አቅርብልኝ ።

አንድ ፡ መንገድ ፡ ይዘው ፡ አቀበት ፡ ወጡ ። በሌላ
መንገድ ፡ ቀስ‌ልቀስ‌ል ፡ ወረዱ ። እንደ ፡ ገና ፡ በሌላ ፡ መንገድ
አሻቅበው ፡ ወጡ ። አንድ ፡ ሰው ፡ በጆሐንስበርግ ፡ መን

ጎዶች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ በመንሸራሸር ፡ አንድ
ጊዜ ፡ የረገጠውን ፡ መንገድ ፡ ሁለተኛ ፡ ሳይደግም ፡ ዕድ
ሜውን ፡ ሊፈጅ ፡ ይችላል ፡ የሚባለው ፡ እውነት ፡ መሆኑ ፡
ተሰማው ።

— የወንድምህ ፡ ሱቅ ፡ ያውና ፡ ይታይሃል?

— አዎን ፡ ይታየኛል ።

— አብረን ፡ ብንሄድ ፡ አይሻልም?

— አዎን ፡ አብረን ፡ ብንሆን ፡ የሚሻል ፡ ይመስለኛል ።

ወንድሙ ፡ ዮሐንስ ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጠ ፡
ከሁለት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ይነጋገራል ። እንደ ፡ አገራቸው ፡
ባላባት ፡ ሁለት ፡ እጆቹን ፡ ጕልበቱ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጎ
አል ። በበር ፡ በኩል ፡ የሚገባው ፡ ብርሃን ፡ ስለ ፡ ጋረደው ፡
ዮሐንስ ፡ ወንድሙ ፡ ኩማሎን ፡ ሊያውቀው ፡ አልቻለም ።

— ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ የእኔ ፡ ወንድም ።

— ጤና ፡ ይስጥልን ፡ ማን ፡ ልበል ?

— ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ ወንድሜ ፡ የእናቴ ፡ ልጅ ።

ዮሐንስ ፡ ከመቀመጫው ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ጕብኝውን ፡
በጥንቃቄ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ሳቅ ፡ ሳቅ ፡ ይለው ፡ ጀመር ፡—

— ኧረ ፡ ጕድ ፡ ፈላ ፡ ወንድሜ ፡ ነህ ፡ እንዴ? ጆሐን
ስበርግ ፡ ምን ፡ አመጣህ ?

ኩማሎ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ በዓይኑ ፡
ገረፍ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ — ለብርቱ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡
የመጣሁት ፡— አለው ።

ዮሐንስም ፡ ወደ ፡ እንግዶቹ ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ይቅርታ ፡
አድርጉልኝ ፡ እንደምታዩት ፡ ወንድሜ ፡ ድንገት ፡ መጥ
ቶብኛል ፡— አላቸው ።

ሁላቁ ፣ ለምች ፣ ከተቀመጡበት ፣ ተነሥተው ፣ ተሰና ብተው ፣ ወጡ ።

— ከቁስ ፣ ምሊማንጉ ፣ ጋር ፣ ትተዋወቃላችሁ ?

— እንዴታ ! ቁስ ፣ ምሊማንጉን ፣ የሚያውቅ ፣ ማን ፣ አለ ። እስቲ ፣ አረፍ ፣ በሉ ። ሻይ ፣ እንዲፈላልን ፣ ልዘዝ ። የጓደውን ፣ በር ፣ ከፍቶ ፣ ትእዛዝ ፣ አስተላለፈ ።

— ለመሆኑ ፣ ባለቤትህ ፣ አስቴር ፣ ደህና ፣ ናት ?

ዮሐንስም ፣ የተለመደ ፣ ፈገግታውን ፣ ካሳየ ፣ በኋላ ፣—

— አዬ ፣ ወንድሜ ፣ ባለቤቴ ፣ አስቴርማ ፣ ትታኝ ፣ ከጀደች ፣ አሥር ፣ ዓመት ፣ ሆኖአታል ።

— ሌላ ፣ አግብተሃል ?

— መቼም ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ያወቀችው ፣ ጋብቻ ፣ አይደለም ። የሆነ ፣ ሁኖ ፣ ሴትዮዋ ፣ ተስማምታኛለች ።

— ስለዚህ ፣ ሁሉ ፣ እንዳችም ፣ ነገር ፣ አልጸፍህልንም ።

— እርግጥ ፣ ምንም ፣ አልጸፍሁም ። ምንስ ፣ ብዬ ፣ እጽፋለሁ? የእንዶትሼኒ ፣ ሰዎች ፣ የጆሐንስበርግ ፣ ኑሮ ፣ አይ ገባችሁም ። አለመጻፉ ፣ ይሻላል ፣ ብዬ ፣ ነው ፣ ዝም ፣ ያልሁት ።

— አንድ ፣ የማይገባኝ ፣ ነገር ፣ አለ ። የጆሐንስበርግ ፣ ኑሮ ፣ ልዩ ፣ የሆነው ፣ በምን ፣ ምክንያት ፣ ነው ?

— ነገሩስ ፣ ቀላል ፣ አይደለም ። ይቅርታ ፣ አድርጉልኝና ፣ በእንግሊዝኛ ፣ ልናገር ። አንዳንድ ፣ ጉዳዮችን ፣ በሰፊው ፣ ለማብራራት ፣ በእንግሊዝኛ ፣ መናገር ፣ ይቀናኛል ።

— በል ፣ በእንግሊዝኛ ፣ ተናገር ፣ ወንድሜ ፣—አለ ፣ ኩማሎ ።

— በጆሐንስበርግ ፣ ውስጥ ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ አይቻለሁ ። ማንኛውም ፣ ነገር ፣ ከእንዶትሼኒ ፣ የተለየ ፣ ነው ። ሁኔ

ታውን ፣ ሁሉ ፣ አንድ ፣ በአንድ ፣ ለመረዳት ፣ እዚሁ ፣ መኖር ፣ ያስፈልጋል ። ዮሐንስም ፣ ወደ ፣ ወንድሙ ፣ እየተመለከተ ፣— በዚህ ፣ ከተማ ፣ ውስጥ ፣ እናንተ ፣ የማታውቁት ፣ አዲስ ፣ ነገር ፣ ተጠንስሶአል ፣— አለ ።

ንግግሩን ፣ እንደ ፣ ቆመ ፣ ቀጠለ ። ድምፁ ፣ ልዩ ፣ የሆነ ፣ ማስተጋባት ፣ ነበረው ። ወዲህ ፣ ወዲያ ፣ እየተንጐራደደ ፣ በመስኮት ፣ አሾልኮ ፣ ሲመለከት ፣ ጣራ ፣ ግድግዳውን ፣ ሲቃኝ ፣ አንድ ፣ የተደበቀ ፣ ነገር ፣ የሚፈልግ ፣ ይመስል ፣ ነበር ።

— በእንዶትሼኒ ፣ እኔ ፣ ማን ፣ ነበርሁ? አንተስ ፣ ማን ፣ ነህ? ሁለታችንም ፣ እዚህ ፣ ግቡ ፣ የማንባል ፣ ሰዎች ፣ አልነበርንም? ሰማይ ፣ ብልጭ ፣ ቢል ፣ በስመ ፣ አብ ፣ ለማይሉ ፣ ባላባቶችና ፣ ሹሞች ፣ እገሣ ፣ አልነበርም? በሚ ያልፉ ፣ በሚያገድሙ ፣ ጊዜ ፣ ሁሉ ፣ መስገድና ፣ እጅ ፣ መንሣት ፣ ነበረብኝ ። በጆሐንስበርግ ፣ ግን ፣ ክብር ፣ ያለ ኝና ፣ ተፈላጊ ፣ ሰው ፣ ነኝ ። የምተዳደርበት ፣ የራሴ ፣ ንግድ ፣ አለኝ ። ገበያ ፣ ደህና ፣ በሆነ ፣ ጊዜ ፣ በሣምንት ፣ ሰባ ፣ ሰማ ንያ ፣ ብር ፣ አተርፋለሁ ።

አሁንም ፣ መንገራደዱን ፣ ቀጠለ ። የሚናገረው ፣ በአጠገቡ ፣ ላልነበሩ ፣ ሰዎች ፣ ይመስል ፣ ነበር ።

— እርግጥ ፣ ነው ፣ እዚህ ፣ ሙሉ ፣ ነፃነት ፣ አለን ፣ ለማለት ፣ አልችልም ። ሰብአዊ ፣ መብታችን ፣ አለመጠበቁ ፣ የታወቀ ፣ ነው ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ከዚያ ፣ ከደደቡ ፣ ከዚያ ፣ ከደ ንቆሮው ፣ ከዚያ ፣ የነጮች ፣ ውሻ ፣ ከሆነው ፣ ባላባታችን ፣ ፈጽሞ ፣ ነፃ ፣ ነኝ ። እርሱ ፣ እንዳንላወስ ፣ እንዳንቀሳቀስ ፣ ነጮች ፣ ያጠመዱብን ፣ አጉል ፣ ወጥመድ ፣ ነው ።

ነገር ፣ የጀጠረ ፣ ፈገግታውን ፣ ካላየ ፣ በኋላ ፣ ፊቱን ፣ ወደ ፣ እንግዶቹ ፣ ዞር ፣ እደረገ ፣—

— እዚህ ፣ ምንም ፣ ወጽ መድ ፣ ሊይዘን ፣ አይችልም ። ሁሉም ፣ በያለበት ፣ እንክትክቱ ፣ ሲወጣ ፣ ይታያል ። ዛሬ ፣ በአንድ ፣ ስፍራ ፣ ረግቶ ፣ የሚገኝ ፣ ነገድና ፣ ጎሳ ፣ የትኛው ፣ ነው? አዲሱ ፣ ጎብረተ ፣ ሰብ ፣ ከዕለት ፣ ወደ ፣ ዕለት ፣ የሚ ፈጠረው ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ውስጥ ፣ ነው ። ወንድሜ ፣ አንድ ቀዋሚ ፣ ነገር ፣ በመፈጸም ፣ ላይ ፣ የሚገኘው ፣ ጆሐንስ በርግ ፣ ውስጥ ፣ ነው ።

ለጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ጋብ ፣ ካለ ፣ በኋላ ፣ ንግግሩን ፣ ቀጠለ ፣—

—ወንድሞቼ ፣ ሆይ ፣ እትቀየሙኝ ፣ እንጂ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያ ንም ፣ ብትሆን ፣ ቅድም ፣ ከጠቀስኩት ፣ ባላባት ፣ ምንም ፣ እትሻልም ። እንዲህ ፣ አድርጉ ፣ በዚህ ፣ ውጡ ፣ በዚያ ፣ ውረዱ ፣ ብቻ ፣ ትላለች ። አንድ ፣ ሰው ፣ በራሱ ፣ አስተያየት ፣ የመመራት ፣ መብት ፣ የለውም ። በየጊዜው ፣ የሚሰማው ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ ታማኝ ፣ ቅን ፣ አገልጋይ ፣ ሕግ ፣ አክባሪ ፣ መሆን ፣ እንዳለበት ፣ ነው ። ሕጉ ፣ ራሱ ፣ ሕጋዊ ፣ ቢሆንም ፣ ባይሆንም ፣ መከበር ፣ አለበት ፣ ይባልልኛል ። እርግጥ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ከቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ድምፅ ፣ እውነተኛ ፣ ነገር ፣ ይሰማል ፤ ጳጳሳትም ፣ በየጊዜው ፣ የሚወጡትን ፣ መብት ፣ ገፋፊ ፣ ሕጎች ፣ ይታወማሉ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ሃምሳ ፣ ዓመት ፣ ሙሉ ፣ ይህንኑ ፣ ድምፃቸውን ፣ ከማሰማት ፣ አላ ቋረጡም ። ሁኔታው ፣ እየባሰበት ፣ ሄደ ፣ እንጂ ፣ ምንም ፣ የተሻለ ፣ ነገር ፣ አልታየም ።

ድምፁ ፣ ጮክ ፣ እያለ ፣ ሄደ ። አሁንም ፣ በአጠገቡ ፣ የሌሉትን ፣ ሰዎች ፣ የሚያናግር ፣ ይመስል ፣ ነበር ።

— በጆሐንስበርግ ፣ የምታዩት ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ የተመ ሠረተው ፣ በማዕድን ፣ ላይ ፣ ነው ። እነዚያ ፣ ታላላቅ ፣ ሕንፃዎች ፣ ይህ ፣ ውብ ፣ የሆነ ፣ የከተማ ፣ አዳራሽ ፣ ግሩም ፣ በሆኑ ፣ መኖሪያ ፣ ቤቶች ፣ የተከበበው ፣ የሕዝብ ፣ መና ፈሻ ፣ ሁሉም ፣ ከማዕድኑ ፣ በወጣው ፣ ወርቅ ፣ የተሠራ ፣ ነው ። ያ ፣ የምታዩት ፣ የነጮች ፣ ሆስፒታል ፣ ከማዕድኑ ፣ በወጣው ፣ ወርቅ ፣ የተሠራ ፣ ነው ።

ድምፁ ፣ እየተለወጠ ፣ ሄደ ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ እንደ ፣ አንበሳ ፣ ለማግሳት ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ደግሞ ፣ እንደ ፣ በሬ ፣ ለመጮህ ፣ ይቃጣዋል ።

—እስቲ ፣ ለእኛ ፣ ወደ ፣ ተሠራው ፣ ሆስፒታል ፣ ሄዳ ችሁ ፣ በየወለሉ ፣ ላይ ፣ የተጋደሙትን ፣ ወገኖቻችንን ፣ ተመልከቱ ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ መረማመጃ ፣ እስኪጠፋ ፣ ድረስ ፣ ተጠጋግተው ፣ መተኛት ፣ ግድ ፣ ይሆንባቸዋል ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ወርቁን ፣ ቆፍረው ፣ የሚያወጡት ፣ እነርሱ ፣ ናቸው ። በቀን ፣ የሚከፈላቸው ፣ አንድ ፣ ብር ፣ ብቻ ፣ ነው ። ማዕድን ፣ ሠራተኞች ፣ ከደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ ግዛቶች ፣ ሁሉ ፣ እየጐረፉ ፣ ይመጣሉ ። ከእንዶትሼኒ ፣ ሳይቀር ፣ መጥተናል ። ትዳራችንን ፣ አፍርሰን ፣ ቤተ ፣ ሰቦቻችንን ፣ በያሉበት ፣ በትነን ፣ ስንመጣ ፣ እንደ ፣ ከብት ፣ በረት ፣ ውስጥ ፣ እን ታጐራለን ። በአንድ ፣ አዲስ ፣ የማዕድን ፣ ስፍራ ፣ ወርቅ ፣ ሲገኝ ፣ ላባችንን ፣ ከማንጠፍጠፍ ፣ በቀር ፣ የሚተርፈን ፣ ነገር ፣ የለም ። እያደገ ፣ የሚሄደው ፣ የነጮቹ ፣ ደመወዝና ፣ ድርሻ ፣ ነው ። ሲፈነጥዙ ፣ የሚታዩት ፣ እነርሱ ፣ ናቸው ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ አዲስ ፣ ነገር ፣ አይደለም ። በየጋዜጣው ፣ የምታነቡት ፣ ነው ። አዲስ ፣ ስፍራ ፣ ወርቅ ፣ ሲገኝ ፣ በብ ዛት ፣ እኛ ፣ እየመለመሉ ፣ የተለየ ፣ መንደር ፣ ሠርተው ፣

ያገሩናል ። በቀን ፣ ለአንድ ፣ ብር ፣ የምድር ፣ ማጎፀን ፣ ውስጥ ፣ ገብተን ፣ ስንቆፍር ፣ እንውላለን ። ገቢው ፣ እየበ ረከተ ፣ ሲሄድ ፣ የተሻለ ፣ የድካም ፣ ዋጋ ፣ እንከፈላቸው ፣ አይሉም ። ሐሳባቸው ፣ ሁሉ ፣ የተሻለ ፣ ቤት ፣ ለመሥራ ትና ፣ የተሻለ ፣ መኪና ፣ ለመግዛት ፣ ነው ። መላዋ ፣ ደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ የተመሠረተችው ፣ ከወርቅ ፣ በሚገኘው ፣ ሀብት ፣ ላይ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ የወርቅ ፣ ማዕድን ፣ ሥራ ፣ መስፋፋት ፣ አለበት ፣ ይላሉ ።

ድምፁ ፣ እየጐረነነ ፣ ሄዶ ፣ የሚያስተጋባ ፣ ነጐድ ጓድ ፣ መሰለ ።

— ይመስላቸዋል ፣ እንጂ ፣ ደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ የተመሠ ረተች ፣ ከወርቅ ፣ በሚገኘው ፣ ሀብት ፣ አይደለም ። ደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ የተመሠረተችውስ ፣ በእኛ ፣ ትከሻ ፣ በእኛ ፣ ድካም ፣ በእኛ ፣ ላብ ፣ ላይ ፣ ነው ። ፋብሪካው ፣ ቲያትሩ ፣ ሕንፃዎቹ ፣ እኛ ፣ የሠራናቸው ፣ ናቸው ። አንድ ፣ ባላባት ፣ ስለዚህ ፣ ሁሉ ፣ ምን ፣ ያውቃል ? በጆሐንስበርግ ፣ ግን ፣ ይህን ፣ የማያውቅ ፣ የለም ።

ንግግሩን ፣ አቋርጦ ፣ ዝም ፣ አለ ። እንግዶቹም ፣ ምንም ፣ አልተነፈሱ ። ንግግሩና ፣ ሁኔታው ፣ ሁሉ ፣ ዝም ፣ የሚያ ሰኝ ፣ ነበር ። እስጢፋኖስ ፣ ኩማሎም ፣ የገዛ ፣ ወንድሙ ፣ አዲስ ፣ ሰው ፣ ስለ ፣ ሆነበት ፣ ዝም ፣ ብሎ ፣ ተቀመጠ ።

ዮሐንስ ፣ ዞር ፣ ብሎ ፣ ወንድሙን ፣ ተመለከተው ።

— ጳጳሱ ፣ እንዲህ ፣ አትሁኑ ፣ እንዲህ ፣ አታድርጉ ፣ አይ ገባም ፣ አይፈቀድም ፣ እያለ ፣ ይሰብከናል ። ራሱ ፣ ግን ፣ አንዳች ፣ ነገር ፣ አይጐድልበትም ። የእርሱ ፣ ቄሶች ፣ እን

ኳን ፣ ከአንተ ፣ ደመወዝ ፣ አራት — አምስት — ስድስት ፣ እጥፍ ፣ ያገኛሉ ።

ወንበሩ ፣ ላይ ፣ አረፍ ፣ ብሎ ፣ የፊቱን ፣ ላብ ፣ ለመ ጥረግ ፣ አንድ ፣ ቀይ ፣ መሀረብ ፣ አወጣ ።

— ይህን ፣ ሁሉ ፣ ነገር ፣ ተመራምሬ ፣ ደርሼበታለሁ ። ወደ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያንም ፣ የማልሄደው ፣ ስለዚህ ፣ ነው ።

— ለእኛ ፣ ደብዳቤ ፣ መጻፍ ፣ ያቋረጥኸው ፣ ስለዚህ ፣ ነው ?

— ምናልባት ፣ ሊሆን ፣ ይችላል ።

— ባለቤትህን ፣ አስቴርን ፣ የፈታሃት ፣ ስለዚህ ፣ ነው ?

— አዎን ፣ ይህም ፣ ሊሆን ፣ ይችላል ። ማንኛውንም ፣ ነገር ፣ በደብዳቤ ፣ ማስረዳት ፣ ያዳግታል ። ኑሮአችንም ፣ ሆነ ፣ ባህላችን ፣ የተለያየ ፣ እየሆነ ፣ ሄዶአል ።

— ለመሆኑ ፣ በዚህ ፣ ከተማ ፣ ባህልና ፣ ወግ ፣ አለ? አለ ፣ ምሲማንጉ ።

ዮሐንስም ፣ ወደ ፣ እርሱ ፣ ዞር ፣ ብሎ ፣ — በዚህ ፣ ከተማ ፣ በየዕለቱ ፣ እያየለ ፣ የሚሄድ ፣ አንድ ፣ አዲስ ፣ ነገር ፣ — አለ ። እርሱም ፣ ለቤተ ፣ ክርስቲያንም ፣ ሆነ ፣ ለባላባት ፣ ኃይል ፣ የሚበገር ፣ አይደለም ። አንድ ፣ ቀን ፣ ታዩታላችሁ ።

— ባለቤትህስ ? ለምን ፣ ትታህ ፣ ሄደች ?

— እርስዋማ ፣ አዲሱ ፣ ስሜቴና ፣ እስተያየቴ ፣ አል ገባ ፣ ስላላት ፣ ይሆናል ፣ — አለ ፣ ዮሐንስ ፣ እየሳቀ ።

ምሲማንጉ ፣ ነገሩን ፣ ፍርጥ ፣ በማድረግ ፣ — እርስዋ ፣ በባልና ፣ በሚስት ፣ መካከል ፣ ያለው ፣ ታማኝነት ፣ እን ዲጠበቅ ፣ ስለ ፣ ፈለገች ፣ ነው ፣ ያልተስማማችሁት ፣ — አለ ።

ዮሐንስም ፣ በጥርጣሬ ፣ ዓይን ፣ ክፉኛ ፣ ተመለከተው ።

— ታማኝነት? አለ ፡ ዮሐንስ ፡ ነገሩ ፡ እንዳልገባው ፡ በማ
ስመሰል ። ሥሮቹም ፡ ከቅጣው ፡ የተነሣ ፡ ግትርትር ፡
አሉ ። ኩማሎም ፡ ወንድሙ ፡ ከፉ ፡ ቃል ፡ እንዳይናገር ፡
በመሥጋት ፡ — እረ ፡ ሻይው ፡ ከመጣ ፡ ቆይቶአል ፤ እን
ጋበዘው ፡ እንጂ ፡ — አለ ።

ሴትዮዋም ፡ ሻይውን ፡ እያዞረች ፡ ለእንግዶች ፡ አደ
ለች ። እገሊት ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ ከእንግዶቹ ፡ ጋር ፡ ያስተዋወ
ቃት ፡ አልነበረም ። ሥራዋን ፡ ጨርሳ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ገባ ፡
እንዳለች ፡ ኩማሎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

— ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ንግግርህን ፡ ሁሉ ፡ በጥሞና ፡
ሰምቼአለሁ ። በሰማሁት ፡ ሳላዝን ፡ አልቀረሁም ። በአንድ ፡
በኩል ፡ እንጋገርህ ፡ ራሱ ፡ አሳዝኖኛል ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡
ደግሞ ፡ የተናገርኸው ፡ አብዛኛው ፡ እውነት ፡ በመሆኑ ፡
ልቤ ፡ ተነከቶአል ። አሁን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ ።
ከሁሉ ፡ አስቀድሜ ፡ ግን ፡ ጌርትሩድ ፡ አብራኝ ፡ እንደ ፡
ሆነችና ፡ ወደ ፡ እንዶትሼኒ ፡ ለመመለስ ፡ እንደምትፈቅድ ፡
ልገልጽልህ ፡ እወዳለሁ ።

— እሱማ ፡ በግን ፡ ዕድል ። ጀሐንስበርግ ፡ ለብቸኛ ፡
ሴት ፡ የሚስማማ ፡ ስፍራ ፡ አይደለም ። እኔም ፡ አገር ፡
ቤት ፡ እንድትመለስ ፡ ለማድረግ ፡ ሞክሬ ፡ ነበር ። እርስዋ ፡
ስላልፈቀደች ፡ ሳይሆንልኝ ፡ ቀረ ። አሁንማ ፡ ከተገናኘን ፡
ዘመን ፡ የለውም ።

— አሁን ፡ የመጣሁበትን ፡ ልጠይቅህ ። ለመሆኑ ፡
ልጄ ፡ ያለበትን ፡ ታውቃለህ ?

የጭንቀትና ፡ የሥጋት ፡ ምልክት ፡ በዮሐንስ ፡ ፊት ፡
ላይ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። እንደ ፡ ገና ፡ መሀረቡን ፡ ከኪሱ ፡
ውስጥ ፡ አወጣ ።

— መቼም ፡ ከእኔ ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ የማይለያዩ ፡ ጓደ
ኞች ፡ መሆናቸውን ፡ ሳትሰማ ፡ አልቀረህም ።

— አዎን ፡ ሰምቻለሁ ።

— የዛሬ ፡ ወጣቶች ፡ እንዴት ፡ እንደሆኑ ፡ ታውቃ
ለህ ። በበኩሌ ፡ ምንም ፡ አልፈርድባቸውም ። በተለይ ፡
የእኔ ፡ ልጅ ፡ ከእንጀራ ፡ እናቱ ፡ ጋር ፡ ሲስማማ ፡ አልቻ
ለም ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመካከላችው ፡ ሰላምን ፡ ለመመሥረት ፡
ታግዬ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አልሆነልኝም ። በመጨ
ረሻው ፡ ልሂድ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ። ጥሩ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡
አትሂድ ፡ ብዬ ፡ አላስገደድሁትም ። ልጅህም ፡ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ መሄዱን ፡ አውቃለሁ ።

— ለመሆኑ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የሄዱት ?

— የሄዱበትን ፡ እርግጠኛውን ፡ ስፍራ ፡ አላውቅም ።
አለክሳንድራ ፡ እንደሚኖሩ ፡ የሰማሁ ፡ ይመስለኛል ።
እስቲ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ። ልክ ፡ ነው ፡ አስታውሳለሁ ፡ በዱ
ርንፎንታዬን ፡ ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ጀምረው ፡ ነበር ።
አድራሻውንም ፡ አውቀዋለሁ ።

ሁለቱም ፡ ዮሐንስ ፡ ኩማሎን ፡ ተሰናብተው ፡ ወጡ ።
ምሲማንጉም ፡ ኩማሎን ፡ እንዲህ ፡ አለው ።

— ወንድምህ ፡ ቀላል ፡ ሰው ፡ አይደለም ። ሹቁ ፡
ሁልጊዜ ፡ በሰዎች ፡ እንደ ፡ ተጫነቀ ፡ ነው ። ተሰብስበው ፡
የሚያወጉት ፡ ቅድም ፡ የሰማነውን ፡ ንግግር ፡ ዓይነት ፡
ነው ። ወንድምህንና ፡ ዱቡላን ፡ ማዳመጥ ፡ ስብሰባ ፡ በሚ
ደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ወንድምህ ፡ ሲናገር ፡
እንደ ፡ አንበሳ ፡ ያገሳል ፡ ይላሉ ። ሲፈልግ ፡ ሰዎችን ፡
ጨርቃቸውን ፡ ሊያስጥላቸው ፡ ይችላል ፡ ይላሉ ። ወጎኒ ፡

ቤት ፡ እንዳይከቱት ፡ በመፍራት ፡ ተከታዮቹ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ እንዲነሣሡ ፡ ሊያደርግም ፡ ይላሉ ።

— እንድ ፡ ነገር ፡ ልንገርህ ፡ አለ ፡ ምሲማንጉ ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፡— የወንድምህ ፡ ንግግር ፡ ብዙ ፡ እውነት ፡ አለበት ። ለጊዜው ፡ ሥልጣኑን ፡ የያዙት ፡ ነጮች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ ሥልጣን ፡ ለመጨበጥ ፡ እንታገላለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥቁሮችም ፡ ሆኑ ፡ ነጮች ፡ ለሥልጣንም ፡ ሆነ ፡ ለገንዘብ ፡ ያላቸውን ፡ ጉጉት ፡ እርግፍ ፡ አድርገው ፡ ትተው ፡ በጎብረት ፡ ለአገራቸው ፡ ደኅንነት ፡ ካልሠሩላት ፡ ለወደፊቱ ፡ ተስፋ ፡ ሊኖረን ፡ አይችልም ።

ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ፊቱን ፡ ቅጭም ፡ አድርጎ ፡ ካሰላሰለ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— በጣም ፡ የሚያስፈራኝ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። እርሱም ፡ ነጮች ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እናፍቅራችሁ ፡ ሲሉ ፡ ልባችን ፡ በጥላቻ ፡ ደንድኖ ፡ እንዳያገኙት ፡ ነው ። በዚህ ፡ አካሄዳችን ፡ ዱርንፎንታዬን ፡ ቶሎ ፡ አንደርስም ። እስቲ ፡ ፈጠን ፡ እንበል ፡— አለ ፡ ምሲማንጉ ።

* * *

የፋብሪካው ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ ቢያደርጉላቸውም ፡ እንኳ ፡ የዱርንፎንታዬን ፡ ጕዞአቸው ፡ ምንም ፡ ሳይቀናላቸው ፡ ቀረ ። የፋብሪካው ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ አቤሲሎም ፡ በኤንድ ፡ ስትሪት ፡ ቁጥር ፡ ፻፩ ፡ ሶፊያታውን ፡ ከምትኖር ፡ እመት ፡ እንዴላ ፡ ከተባለች ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ተዳብሎ ፡ የሚኖር ፡ መሆኑን ፡ አስረዳቸው ።

ወደ ፡ ሶፊያታውን ፡ ተመልሰው ፡ ኤንድ ፡ ስትሪት ፡ ቁጥር ፡ ፻፩ ፡ ቢጠይቁ ፡ እንደ ፡ ተባለውም ፡ ወይዘሮ ፡ እንዴላን ፡ አገኙ ።

እርስዋም ፡ እንግዶቹን ፡ በትሕትና ፡ ተቀበለች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አቤሴሎም ፡ እዚያም ፡ አልተገኘም ። ወይዘሮ ፡ እንዴላ ፡ ከጥቂት ፡ ወራት ፡ በፊት ፡ ትቶት ፡ ስለ ፡ ሄደው ፡ ዕቃ ፡ አቤሴሎም ፡ የጻፈላትን ፡ ደብዳቤ ፡ በማስታወስ ፡ እንግዶቹን ፡ አስቀምጣ ፡ ደብዳቤውን ፡ ፍለጋ ፡ ገባች ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ አነሥተኛ ፡ ሳጥን ፡ አምጥታ ፡ ያለበትን ፡ ሰባራ ፡ ስንጥር ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ዘርግፋ ፡ ፍለጋዋን ፡ ቀጠለች ። ምሲማንጉም ፡ ድካም ፡ ያጠቃውን ፡ የዋሕ ፡ ገጽዋን ፡ እየተመለከተ ፡ የምትሠራውን ፡ ሲከታተል ፡ ፍለጋዋን ፡ ተወት ፡ አድርጋ ፡ በኀዘንና ፡ በመገረም ፡ ኩማሎን ፡ ትክ ፡ ብላ ፡ ተመለከተችው ። በመጨረሻም ፡ ደብዳቤውን ፡ አግኝታ ፡ አድራሻውን ፡ አሳየቻቸው ። አድራሻውም ፡ በወይዘሮ ፡ እምኬዚ ፡ በኩል ፡ ፫፱ ፡ ትዌንቲ ፡ ሰርድ ፡ አቬኒው ፡ አለክሳንድራ ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጡ ።

በኋላም ፡ ሻይ ፡ ካልጠጣችሁ ፡ አትሄዱም ፡ ተባሉ ። ሻይውን ፡ ጠጥተው ፡ ተሰናብተው ፡ ሲወጡ ፡ ቀኑ ፡ ለዓይን ፡ ይዞ ፡ አገኙት ። የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ሊሸኛቸው ፡ ከቤት ፡ ወጣ ፡ አለ ። ምሲማንጉ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረት ፡ ብሎ ፡ ሴትዮዋን ፡—

— ጓደኛዬን ፡ ቅድም ፡ እንደዚያ ፡ በኀዘን ፡ ዓይን ፡ ለምን ፡ ተመለከትሽው? ብሎ ፡ ጠየቃት ። ወደ ፡ መሬት ፡ አቀርቅራ ፡ እየተመለከተች ፡—

— ኡምፉንዲሲ ፡ አይደለም ? አለች ።

— ነው ፡ አላት ።

— የልጁን ፡ ጓደኞች ፡ እኔና ፡ ባለቤቴ ፡ አልወደድናቸውም ። ከእኛም ፡ የተለየው ፡ ስለዚሁ ፡ ነው ።

— ይገባኛል ። ሌላ ፣ የምታውቂው ፣ የባስ ፣ ነገር ፣ አለ ?

— በበኩሌ ፣ ምንም ፣ የተለየ ፣ ነገር ፣ አላየሁበትም ። ጓደኞቹን ፣ ብቻ ፣ አልወደድኋቸውም ።

ጥቂት ፣ ራቅ ፣ ብለው ፣ ከሄዱ ፣ በኋላ ፣ ከቤቱ ፣ ባለ ቤት ፣ ተሰነባብተው ፣ ጉዞአቸውን ፣ ወደ ፣ ሚስዮኑ ፣ ማረፊያ ፣ አመሩ ።

— ነገ ፣ ወደ ፣ አለክሳንድራ ፣ እንሄዳለን ፣— አለ ፣ ምሲማንጉ ።

ኩማሎ ፣ እጁን ፣ ወዳጁ ፣ ክንድ ፣ ላይ ፣ ጫን ፣ አድርጎ ፣ — መቼም ፣ ጆሐንስበርግ ፣ የመጣሁት ፣ ለደህና ፣ ነገር ፣ አይደለም ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ በአንተ ፣ ብርታት ፣ ብዙ ፣ ደስታና ፣ መጽናናትን ፣ አግኝቻለሁ ፣— አለ ።

— እባክህን ፣ እሱን ፣ ተወው ፣—አለ ፣ ምሲማንጉ ። — ቶሎ ፣ ቶሎ ፣ ካልሄድን ፣ ጠማችንን ፣ ማደራችን ፣ ነው ።

—8—

በማግሥቱ ፣ ምሲማንጉና ፣ ኩማሎ ፣ በአውቶቡስ ፣ ተሳፍረው ፣ ከተጓዙ ፣ በኋላ ፣ አለክሳንድራ ፣ የሚሄዱ ፣ አውቶቡሶች ፣ መቆሚያ ፣ ስፍራ ፣ ደረሱ ። እዚያም ፣ አንድ ያላሰቡት ፣ መሰናክል ፣ አጋጠማቸው ። አንድ ፣ ወጣት ፣ ወደ ፣ ምሲማንጉ ፣ ቀረብ ፣ ብሎ ፣—

— ወደ ፣ አለክሳንድራ ፣ ነው ፣ የሚሄዱት ፣ ኡምፉንዲሲ ? አለው ።

— አዎን ፣ ወዳጄ ።

— ኡምፉንዲሲ ፣ እኛ ፣ እዚህ ፣ የቆምነው ፣ በዚህ ፣

አውቶቡስ ፣ እንዳይጠቀሙ ፣ ልናግድዎት ፣ ነው ። ልናግድዎት ፣ የምንሞክረውም ፣ በኃይል ፣ ሳይሆን ፣ በመግባባት ፣ መንፈስ ፣ ነው ። በዚህ ፣ አውቶቡስ ፣ ተሳፍረው ፣ ቢሄዱ ፣ የጥቁሮችን ፣ ትግል ፣ እንዳደከሙ ፣ ይቁጠሯል ። እኛ ፣ በበኩላችን ፣ የመሳፈሪያው ፣ ዋጋ ፣ ወደ ፣ አሥር ፣ ሳንቲም ፣ እስኪመለስ ፣ ድረስ ፣ በአውቶቡስ ፣ ላንሳፈር ፣ አድመናል ።

— እርግጥ ፣ እርግጥ ! ስለ ፣ አድማው ፣ ሰምቼአለሁ ፣— አለ ፣ ምሲማንጉ ፣ ወደ ፣ ኩማሎ ፣ መለስ ፣ ብሎ ።— እኔ ፣ ነኝ ፣ ጥፋተኛው ፣ ወዳጄ ። አውቶቡስ ፣ አለመኖሩን ፣ ረስቼዋለሁ ፤ በአውቶቡስ ፣ ላይ ፣ አድማ ፣ መደረጉን ፣ እንዴት ፣ ዘነጋሁት ?

— ጉዳያችን ፣ ለነገ ፣ የሚባል ፣ አይደለም ፣— አለ ፣ ኩማሎ ፣ በትሕትና ።

— የእኛም ፣ ትግል ፣ ጊዜ ፣ የሚሰጥ ፣ አይደለም ፣— አለ ፣ ሰውዬው ፣ በጥሞና ፣ ቃል ።

— ለአንድ ፣ ጊዜ ፣ መሄጃ ፣ ብቻ ፣ ሃያ ፣ ሳንቲም ፣ ካልከፈላችሁ ፣ ይሉናል ። በቀን ፣ አርባ ፣ ሳንቲም ፣ መሆኑ ፣ ነው ። የአንዳንዶቻችን ፣ የሳምንት ፣ ገቢ ፣ ከአሥራ ፣ ሁለት ፣ እስከ ፣ አሥራ ፣ አምስት ፣ ብር ፣ ብቻ ፣ ነው ።

— በእግር ፣ ለመሄድ ፣ ይርቃል? አለ ፣ ምሲማንጉ ።

— አዎን ፣ ይርቃል ፣ ኡምፉንዲሲ ። አሥራ ፣ ሰባት ፣ ኪሎ ፣ ሜትር ፣ ነው ።

— አዬ ፣ እንደ ፣ እኔ ፣ ያለው ፣ ደካማ ፣ ሽማግሌ ፣ አይዘልቀውም ፣ በለኛ ።

— እንደ ፣ እርስዎ ፣ ያሉ ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ በየዕለቱ ፣ የሚመላለሱት ፣ በእግር ፣ ነው ። ሴቶች ፣ በሽተኞች ፣ ሕፃናት ፣ ሳይቀሩ ፣ በእግራቸው ፣ ነው ፣ የሚሄዱት ። መንገድ ፣ የሚጀምሩት ፣ ከሌሊቱ ፣ በአሥር ፣ ሰዓት ፣ ላይ ፣ ነው ።

ቀን ፡ ሲለፉ ፡ ውለው ፡ ቤታቸው ፡ የሚገቡት ፡ ከምሽቱ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ ነው ። ያገኘዋትን ፡ ቀማምሰው ፡ ጋደም ፡ ብለው ፡ እንቅልፍ ፡ ሸለብ ፡ ሲያደርጋቸው ፡ ሰዓቱ ፡ ይደርስና ፡ መነሣት ፡ ግድ ፡ ይሆንባቸዋል ። ከች ግር ፡ የተነሣ ፡ ጥቁር ፡ ውኃ ፡ ብቻ ፡ ቀምሰው ፡ ወደ ፡ ሥራ ቸው ፡ የሚመለሱ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። በዚህ ፡ በአውቶ ቡስ ፡ እንዳትሳፈሩ ፡ ለማስገደድ ፡ አንችልም ፡ ኡምፉንዲሲ ። ይህ ፡ የጀመርነው ፡ ትግል ፡ ግን ፡ የሁላችንንም ፡ ጎብረት ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው ። እኛ ፡ ከተሸነፍን ፡ በሶፊያታውን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሌሎችም ፡ ከተሞች ፡ ተጨማሪ ፡ የአው ቶቡስ ፡ ኪራይ ፡ መክፈል ፡ ይኖርብናል ።

— ጉዳዩን ፡ ተረድቼዋለሁ ። መልካም ፡ ነው ፡ በአ ውቶቡስ ፡ አንሳፈርም ።

ሰውዬው ፡ ስላሳዩት ፡ ጎብረት ፡ ካመሰገናቸው ፡ በኋላ ፡ ተግባሩን ፡ ለመቀጠል ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አመራ ።

— እንዴት ፡ ያለ ፡ አንደበት ፡ አለው ፡ እባክህን ? አለ ፡ ኩማሎ ።

— ይኸውልህ ፡ ዝነኛው ፡ ዱቡላ ፡ ማለት ፡ እርሱ ፡ ነው ፡— አለ ፡ ምሲማንጉ ፡ በሹክሹክታ ።

— የወንድምህ ፡ ጓደኛ ፡ ነው ። ሰዎች ፡ ወንድምህ ፡ ርቱእ ፡ አንደበት ፡ አለው ፡ ይላሉ ። ይህ ፡ ሰውዬ ፡ ግን ፡ ድፍረት ፡ አለው ፡ ይላሉ ። ፍርሃት ፡ የማይበግረው ፡ በመ ሆኑ ፡ መንግሥትም ፡ ይፈራዋል ። ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ አን ዳችም ፡ አያስብም ። አሁንም ፡ ሰዎች ፡ በአውቶቡስ ፡ እን ዳይሳፈሩ ፡ ለማድረግ ፡ ሥራውን ፡ ትቶአል ፡ ይባላል ። ሚስቱም ፡ ይህንኑ ፡ የመሰለውን ፡ ተግባር ፡ በአለክሳን ድራ ፡ ታከናውናለች ፡ ይባላል ።

— በጣም ፡ የሚያኮራ ፡ ተግባር ፡ ነው ። መቼም ፡ ጆሐንስበርግ ፡ ብዙ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ የሚታይበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ።

— እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ አባል ፡ ነበሩ ። አሁን ፡ ግን ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ እርግፍ ፡ አድርገው ፡ ትተውታል ። ሁሉም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ድምፅ ፡ እንጂ ፡ አድራጎት ፡ የላትም ፡ ይላሉ ። ወደ ፡ ጉዳያችን ፡ እንመለ ስና ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ የሚሻለን ፡ ይመስልሃል ?

— እኔ ፡ በበኩሌ ፡ በእግር ፡ ለመሄድ ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ።

— ሲሄዱ ፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡ ሲመለሱ ፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ቅርብ ፡ እንዳይመስልህ ።

— እኔ ፡ እንደሆንሁ ፡ ግድ ፡ የለኝም ። እንደምታው ቀው ፡ ያለሁት ፡ በሥጋት ፡ ላይ ፡ ነው ። ጆሐንስበርግ ፡ ብቸኛ ፡ የሆነ ፡ ወጣት ፡ የሚኖርበት ፡ ከተማ ፡ አይደለም ።

— መልካም ፡ እንሂድ ፡ ካልህ ፡ እንሂድ ።

ከዚያም ፡ ተነሥተው ፡ ጉዞአቸውን ፡ ቀጠሉ ። ብዙ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ መኪና ፡ አጠገ ባቸው ፡ ቆመ ። ሹፌሩ ፡ ነጭ ፡ ነበር ።

— ወዴት ፡ ነው ፡ የምትሄዱት ? ሲል ፡ ጠየቃቸው ። ምሲማንጉም ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ባርኔጣውን ፡ እያወረደ ፡—

— ወደ ፡ አለክሳንድራ ፡ ነው ፡— አለ ።

— እኔም ፡ ጠርጥሬአለሁ ፤ በሉ ፡ ግቡ ።

ወደ ፡ አለክሳንድራ ፡ መግቢያ ፡ መንገድ ፡ ሲደርሱ ፡ ስለ ፡ ተደረገላቸው ፡ ታላቅ ፡ እርዳታ ፡ ሰውዬውን ፡ ከልብ ፡ አመሰገኑት ።

— መንገዱ ፡ እንዲህ ፡ የሚዘለቅ ፡ አይደለም ። ደግሞም ፡ አውቶቡስ ፡ የላችሁም ፡— አለ ፡ ነጩ ፡ ሹፌር ።

መንገዱን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይቀጥል ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ ቁመው ፡ ይመለከቱት ፡ ጀመር ። እርሱ ፡ ግን ፡ መኪናውን ፡ አዙሮ ፡ ወደ ፡ መጣበት ፡ ወደ ፡ ጆሐንስበርግ ፡ ተመለሰ ።

— የሚገርም ፡ ነገር ፡ ነው ፡— አለ ፡ ምሲማንጉ ።

ወደ ፡ ትዌንቲ ፡ ሰርድ ፡ አቬኒው ፡ ለመድረስ ፡ በእግር ፡ ብዙ ፡ መሄድ ፡ ነበረባቸው ። በጉዞአቸው ፡ አያሌ ፡ ጐዳናዎችን ፡ እያቋረጡ ፡ በሚያልፉበት ፡ ጊዜ ፡ አለከሳንድራ ፡ ከጆሐንስበርግ ፡ ከተማ ፡ ከልል ፡ ውጭ ፡ መሆንዋንና ፡ ጥቁሮች ፡ በከተማይቱ ፡ ውስጥ ፡ መሬት ፡ ገዝተው ፡ የገዛ ፡ መኖሪያቸውን ፡ ለመሥራት ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ምሲማንጉ ፡ ለኩማሎ ፡ አስረዳው ። የአለከሳንድራ ፡ ጐዳናዎች ፡ በሚገባ ፡ የተጠበቁ ፡ እይደሉም ። በመንገዶቹ ፡ ዳር ፡ ዳር ፡ መብራት ፡ አልተተከለም ። በከተማይቱ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመኖሪያ ፡ ቤት ፡ ችግር ፡ ስላለ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ግቢው ፡ ውስጥ ፡ ዛኒጋባዎችን ፡ እየቀለሰ ፡ ያከራያል ። ዛኒጋባዎቹም ፡ የወሮበሎችና ፡ የወንበዴዎች ፡ መከማቻ ፡ ነበሩ ። በየስፍራው ፡ መሸታ ፡ ቤቶችና ፡ ሴትኛ ፡ አዳሪዎች ፡ በብዛት ፡ ይታያሉ ።

በመጨረሻም ፡ የሚፈልጉትን ፡ ቤት ፡ አገኙ ። አንዲት ፡ ሴት ፡ በሩን ፡ ከፈተችላቸው ። የመጡበትን ፡ ጉዳይ ፡ ገለጡላት ። የግድዋን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንዲገቡ ፡ አደረገች ።

— ልጁ ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ አይኖርም ፡ ማለት ፡ ነዋ ፡ ወይዘሮ ፡ እምኬዚ ።

— ከእኔ ፡ ቤት ፡ ከወጣ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖታል ። የሚኖርበትንም ፡ አላውቅም ።

— ከቤትሽ ፡ ከወጣ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይሆነዋል?

— ብዙ ፡ ወራቶች ፡ አልፈዋል ። አንድ ፡ ዓመት ፡ ላይሆነው ፡ አይቀርም ።

— ጓደኛ ፡ ነበረው?

— የአጎቴ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ኩማሎ ፡ ነበር ።

— የሄዱበትን ፡ ስፍራ ፡ ምንም ፡ አታውቂም?

— እዚህም ፡ እዚያም ፡ እንሄዳለን ፡ ሲያሉ ፡ ያወሩ ፡ ነበር ። የዛሬ ፡ ልጆች ፡ ወሬ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ታውቃላችሁ ።

— ለመሆኑ ፡ የአቤሴሎም ፡ ጠባይ ፡ እንዴት ፡ ነበር? ሲል ፡ ኩማሎ ፡ ጠየቃት ።

በዓይንዋ ፡ ላይ ፡ የሥጋት ፡ ምልክት ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። ኩማሎንም ፡ ሥጋት ፡ ያዘው ። በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሥጋትና ፡ ፍርሃት ፡ ሰፈነበት ።

— ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላየሁበትም ፡ — አለች ።

— ለምን ፡ ፍርሃት ፡ ፍርሃት ፡ ይልሻል ፡ ታዲያ?

— አልፈራሁም ፡— አለች ።

— ታዲያ ፡ ምን ፡ ያንቀጠቅጥሻል? አለ ፡ ምሲማንጉ ።

— በርዶኝ ፡ ነው ፡— አለች ።

በፍርሃትና ፡ በጥርጣሬ ፡ ተመለከተቻቸው ።

— እናመሰግንሻለን ፡ ደህና ፡ ሁኚ ፡—አለ ፡ ምሲማንጉ ።

— ደህና ፡ ሁኑ ፡— አለች ።

ወጣ ፡ እንዳሉ ፡ ኩማሎ ፡— አንድ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነገር ፡ መኖር ፡ አለበት ፡— አለ ።

— እኔንም ፣ አሥግቶኛል ፣— አለ ፣ ምሊማንጉ ።

— ሁለት ፣ ሆነን ፣ መሄዳችን ፣ ጥርጣሬ ፣ ሳያሳድ
ርባት ፣ አልቀረም ። ከአውራ ፣ ጐዳናው ፣ እንደ ፣ ደረስህ ፣
ወደ ፣ ግራ ፣ ታጥፈህ ፣ አቀበቱን ፣ ወጣ ፣ እንዳልህ ፣ አንድ ፣
ቡና ፣ ቤት ፣ ታገኛለህ ። እዚያ ፣ ግባና ፣ ጠብቀኝ ።

አሁንም ፣ እንደ ፣ ከፋት ፣ በሩን ፣ ከፈተችለት ።

— ከፖሊስ ፣ ዘንድ ፣ የመጣሁ ፣ እንዳይመስልሽ ፣—
አላት ፣ ምሊማንጉ ። — ከፖሊስ ፣ ጋር ፣ ምንም ፣ ጉዳይ ፣
የለኝም ። ጉዳይ ፣ እንዲኖረኝም ፣ የምሻ ፣ ሰው ፣ አይደ
ለሁም ። እኔን ፣ የሚያላስበኝ ፣ ልጁ ፣ የጠፋበት ፣ የአንድ ፣
ሽማግሌ ፣ አባት ፣ ጭንቀት ፣ ነው ።

ይሉኝታ ፣ የያዛት ፣ ይመስል ፣—ያሳዝናል ፣—አለች ።

— እርግጥ ፣ ነገሩ ፣ ያሳዝናል ። ዳሩ ፣ ግን ፣ የደበቅሽ
ውን ፣ ምሥጢር ፣ ሳታወጪ ፣ የምለቅሽ ፣ እንዳይመስ
ልሽ ፣ — አላት ።

— ምንም ፣ የማወጣው ፣ ምሥጢር ፣ የለኝም ፣— አለ
ችው ።

— አውቄብሻለሁ ፣ ፈርተሽ ፣ ነው ፣ የምትንቀጠ
ቀጪውም ፣ ስለ ፣ በረደሽ ፣ አይደለም ።

— ምን ፣ እንቀጠቀጠኝ? አለችው ።

— እኔ ፣ ምን ፣ አውቃለሁ ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ እንዲህ ፣
በፍርሃት ፣ የምትንቀጠቀጭበትን ፣ ምክንያት ፣ ሳላውቅ ፣
አለቅሽም ። ቢያስፈልግም ፣ ፖሊስ ፣ ጣቢያ ፣ እንደርሳ
ለን ። መቼም ፣ ሌላ ፣ መሄጃ ፣ የለም ።

— ብቸኛ ፣ ለሆነች ፣ ሴት ፣ ቀላል ፣ ነገር ፣ አይደለም ፣—
አለችው ።

— ልጁ ፣ ለጠፋበት ፣ ሽማግሌ ፣ አባት ፣ ቀላል ፣
ነገር ፣ አይደለም ፣— አላት ።

— ፍርሃት ፣ ፍርሃት ፣ ብሎኛል ፣— አለችው ።

— እርሱም ፣ እንዳንቺው ፣ ፈርቶአል ። የፈራ ፣ መሆኑ ፣
አይታይሽም?

— አዎን ፣ ታይቶኛል ፣— አለችው ።

— እንግዲያውስ ፣ እነዚያ ፣ ሁለት ፣ ወጣቶች ፣ ከአ
ንቺ ፣ ጋር ፣ በነበሩበት ፣ ጊዜ ፣ ምን ፣ ዓይነት ፣ ኑሮ ፣ ይኖሩ ፣
እንደ ፣ ነበር ፣ ንገሪኝ ።

እርስዋ ፣ ግን ፣ በፈሩና ፣ እንባ ፣ ባቀረሩ ፣ ዓይኖችዋ ፣
ከመመልከት ፣ በስተቀር ፣ አንዳች ፣ ቃል ፣ አልተነፍስ ፣
አለች ። በቀላሉ ፣ የማትበገር ፣ መሆንዋን ፣ ተገነዘበ ።

— ቂስ ፣ ነኝ ። አታምኚኝም? አላት ። እርስዋ ፣ ግን ፣
ጭጭ ፣ አለች ።

— ወንጌል ፣ አለሽ? ካላመንሽኝ ፣ ወንጌል ፣ ጨብጬ ፣
ልማልልሽ ፣— አላት ።

ለሁለተኛ ፣ ጊዜ ፣— ወንጌል ፣ ጨብጬ ፣ ልማልልሽ ፣
ነው ፣ የምልሽ ፣ እስኪላት ፣ ድረስ ፣ ዝም ፣ ብላ ፣ ተቀመ
ጠች ። እየጨቀጨቀ ፣ ስላስቸገራት ፣ የግድዋን ፣ ተነሥታ ፣
ወደ ፣ አንድ ፣ ሌላ ፣ ክፍል ፣ ገባች ። ጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ቆይታ ፣
መጽሐፍ ፣ ቅዱስ ፣ ይዛ ፣ ወጣች ።

— እንደ ፣ ነገርኩሽ ፣ የቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ካህን ፣
ነኝ ። እስከ ፣ ዛሬ ፣ ድረስ ፣ ንግግሬ ፣ አዎን — አዎን —
አይደለም — አይደለም — ብቻ ፣ ነው ። በእኛ ፣ ምክን
ያት ፣ አንዳችም ፣ ክፉ ፣ ነገር ፣ እንደማይደርስብሽ ፣ እጁን ፣
በዚህ ፣ ወንጌል ፣ ላይ ፣ ጭኜ ፣ እምልልሻለሁ ።

— ለመሆኑ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ኑሮ ፣ ይኖሩ ፣ ነበር?
አላት ።

— በእኩለ ፣ ሌሊት ፣ በዶሮ ፣ ጩኸት ፣ ላይ ፣ ብዙ ፣
ነገሮችን ፣ ይዘው ፣ ይመጡ ፣ ነበር ፣ ኡምፉንዲሲ ። ልብሱ ፣

ለዓቱ ፣ ገንዘቡ ፣ በቆርቆሮ ፣ የታሸገው ፣ ምግብ ፣ መጠን ፣ አልነበረውም ።

— ደም ፣ አይተሽባቸው ፣ ታውቂያለሽ ?

— ደምስ ፣ አይቼባቸው ፣ አላውቅም ፣ ኡምፉንዲሲ ።

— ይህም ፣ አንድ ፣ ተስፋ ፣ ነው ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ ከዚህ ፣ ለምን ፣ ለቀቁ?

— ለምን ፣ እንደ ፣ ለቀቁ ፣ አልገባኝም ። እኔ ፣ እንደ ምገምተው ፣ ከሆነ ፣ የፖሊስ ፣ መከታተል ፣ ስለ ፣ በዛባቸው ፣ ሳይሆን ፣ አይቀርም ።

— የአንቺን ፣ ቤት ፣ ከአንድ ፣ ዓመት ፣ በፊት ፣ መልቀቃቸውን ፣ ነግረሽኛል ። የሄዱበትን ፣ ቦታ ፣ አላውቅም ፣ ብለሽ ፣ በዚህ ፣ መጽሐፍ ፣ ትምያለሽ ? አላት ።

መሐላዋን ፣ ለመደርደር ፣ እጅዋን ፣ ወደ ፣ መጽሐፉ ፣ ልትዘረጋ ፣ ስትል ፣— ግድ ፣ የለም ፣ ተይው ፣— አላት ። ተስፋቢቶአት ፣ ኩማሎ ፣ ወዳለበት ፣ ለመሄድ ፣ ወጣ ፣ እንዳለ ፣ ከኋላው ፣ እየተጣራች ፣—

— ሕላቤኒ ፣ የተባለ ፣ ታክሲ ፣ ነጂ ፣ ጓደኛቸው ፣ ነበር ። አውቶቡስ ፣ መቆሚያው ፣ አጠገብ ፣ ይኖራል ፤ እዚያ ፣ ብትጠይቁ ፣ ማንም ፣ ሰው ፣ ያሳያችኋል ፣— አለችው ።

— አመሰግናለሁ ፣ ወይዘሮ ፣ እምኬዚ ፣ ደህና ፣ ሁኚ ።

ከቡና ፣ ቤቱም ፣ እንደ ፣ ደረሰ ፣ ኩማሎን ፣ አገኘው ። ወደ ፣ ታክሲ ፣ መቆሚያ ፣ ስፍራ ፣ አብረው ፣ ሄዱ ። ምሲ ማንጉ ፣ ከሰዎች ፣ በተረዳው ፣ ምልክት ፣ መሠረት ፣ ወደ ፣ ታክሲ ፣ መቆሚያው ፣ ስፍራ ፣ ሄዶ ፣ ሕላቤኒን ፣ አገኘው ።

— እንደምን ፣ ዋሉ ፣ ኡምፉንዲሲ ።

— ታክሲ ፣ ልከራይ ፣ እፈልጋለሁ ። እኔንና ፣ ጓደኛዬን ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ድረስ ፣ በምን ፣ ያህል ፣ ታደርሰናለህ?

— ለእርስዎ ፣ ስል ፣ በአምስት ፣ ብር ፣ አደርሳችኋለሁ ፣ ኡምፉንዲሲ ።

— በጣም ፣ ውድ ፣ ነው ።

— ሌላ ፣ ታክሲ ፣ ቢጠይቁ ፣ ከሰባትና ፣ ከስምንት ፣ ብር ፣ በታች ፣ አይወስዱም ።

ታክሲ ፣ ነጂውም ፣ ሞዱሩን ፣ ሊያስነሣ ፣ ሲል ፣ ምሲ ማንጉ ፣ አቋረጠውና ፣ አቤሴሎም ፣ ኩማሎ ፣ የተባለ ፣ ወጣት ፣ የሚገኝበትን ፣ ስፍራ ፣ ልትነግረኝ ፣ ትችላለህ? ብሎ ፣ ጠየቀው ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ሰውዬው ፣ ክው ፣ አለ ። ምሲ ማንጉም ፣ ወዲያውኑ ፣ መለስ ፣ አድርጎ ፣—

— ለክፉ ፣ ነገር ፣ የመጣሁ ፣ እንዳይመስልህ ። ይህ ፣ ጓደኛዬ ፣ የአቤሴሎም ፣ አባት ፣ ነው ። ከናታል ፣ ድረስ ፣ ልጁን ፣ ለመፈለግ ፣ መጥቶ ፣ በያለበት ፣ ይንከራተታል ።

— እርግጥ ፣ ነው ፣ አቤሴሎምን ፣ አውቀዋለሁ ።

— አሁን ፣ የት ፣ የሚገኝ ፣ ይመስልሃል ?

— በሻንቲታውን ፣ የሚኖር ፣ መሆኑን ፣ ሰምቻለሁ ።

— ይህንንም ፣ ማወቅ ፣ ትልቅ ፣ ነገር ፣ ነው ። በል ፣ እንግዲህ ፣ በአንተ ፣ ታክሲ ፣ ነው ፣ የምንሄደው ።

ሁለቱም ፣ በታክሲ ፣ ተሳፍረው ፣ ከአለክሳንድራ ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ በሚወስደው ፣ አውራ ፣ ጐዳና ፣ ጉዞ አቸውን ፣ ቀጠሉ ።

— የብስክሌቶችን ፣ ብዛት ፣ ታያለህ? እነዚህ ፣ ሁሉ ፣ ከሥራ ፣ የሚመለሱ ፣ የአለክሳንድራ ፣ ነዋሪዎች ፣ ናቸው ። በአውቶቡስ ፣ ላይ ፣ በተደረገው ፣ አድማ ፣ ምክንያት ፣ ከዚህ ፣ እልፍ ፣ ስንል ፣ በሺህ ፣ የሚቈጠሩ ፣ እግረኞች ፣ እናያለን ።

እውነትም ፣ ጥቂት ፣ አልፍ ፣ እንዳሉ ፣ ሰዎች ፣ የእግ
ረኛውን ፣ መንገድ ፣ አጫንቀው ፣ ሲጓዙ ፣ አዩ ። ብዙዎች ፣
ነጮች ፣ በመኪናቸው ፣ ጥቁሮችን ፣ እያሳፈሩ ፣ ወደ ፣ አለ
ክሳንድራ ፣ ይወስድዋቸው ፣ ነበር ። በአንድ ፣ መስቀልኛ ፣
መንገድ ፣ ላይ ፣ ቆም ፣ እንዳሉ ፣ አንድ ፣ የትራፊክ ፣
ፖሊስ ፣ ነጮቹን ፣ ባለመኪናዎች ፣ አቁሞ ፣ ጥቁሮችን ፣
ለማሳፈር ፣ የተሰጣቸው ፣ ፈቃድ ፣ እንዳለ ፣ እንዲያሳዩት ፣
ሲወተውታቸው ፣ ነው ።

— ገንዘብ ፣ አልተቀበልንም ፣— አለ ፣ ከነጮቹ ፣ ባለ ፣
ተሽከርካሪዎች ፣ አንዱ ።

— ገንዘብ ፣ ባትቀበልም ፣ በአውቶቡስ ፣ መስመር ፣
ተሳፋሪዎች ፣ ጭነህ ፣ መሄድ ፣ አልተፈቀደልህም ፣— አለ ፣
ፖሊሱ ። — እንግዲያው ፣ ክሰሰኝ ፣— አለው ፣ ነጩ ።
የክርክሩን ፣ ፍጻሜ ፣ ሳይሰሙ ፣ መንገዳቸውን ፣ ቀጠሉ ።

* * *

ቀኑ ፣ ለዓይን ፣ እየያዘ ፣ ሄደ ። ወደ ፣ አለክሳንድራ ፣
የሚጐርፈው ፣ ሕዝብ ፣ ግን ፣ አሁንም ፣ መንገዱን ፣ እንዳ
ጣበበው ፣ ነው ። መኪናዎችም ፣ እየቆሙ ፣ ደካሞችን ፣
ሴቶችንና ፣ አካለ ፣ ስንኩሎችን ፣ ማሳፈራቸውን ፣ አላቋረ
ጡም ። በኩማሎ ፣ ገጽ ፣ ላይ ፣ ልዩ ፣ የሆነ ፣ የደስታ ፣ ፈገግታ ፣
ይታያል ። ይህም ፣ ሊሆን ፣ የቻለው ፣ ነጮች ፣ ጥቁሮችን ፣
በደስታ ፣ ሲረዱአቸው ፣ በማየቱ ፣ ነው ። እውነት ፣ አለው ፣
እንዲህ ፣ ያለው ፣ አደራረግ ፣ አዘውትሮ ፣ የሚገጥም ፣ ነገር ፣
አይደለም ። ኩማሎም ፣ ያየውን ፣ ሁሉ ፣ በልቡ ፣ ውስጥ ፣
እያሰላሰለ ፣ ሲጓዝ ፣ ሳያስበው ፣ ድንገት ፣—

— ልብ ፣ የሚነካ ፣ ነው ፣ ልብ ፣ የሚነካ ፣ ነው ፣— አለ ።

— ምኑ ፣ ነው ፣ ልብ ፣ የሚነካው ? የነጮቹ ፣ ደግነት ፣
ነው ?

— አይደለም ፣ አይደለም ፣ እንደ ፣ እውነቱ ፣ ከሆነ ፣
ስለ ፣ እርሱ ፣ አልነበረም ፣ የማስበው ።

ከተቀመጠበት ፣ ቀና ፣ ብሎ ፣ ዶረቱን ፣ በኃይል ፣ ይመታ ፣
ጀመር ።

— እንግዲያውስ ፣ ክሰሰኝ ፣ ማለቱ ።

— አዎን ፣ እንግዲያውስ ፣ ክሰሰኝ ፣ ማለቱ ፣ እኔንም ፣
ልቤን ፣ ነክቶታል ፣— አለ ፣ ምሲማንጉም ።

—9—

መንገዶች ፣ ሁሉ ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ይወስዳሉ ።
ጥቁር ፣ ነጭ ፣ ሳይለዩ ፣ ሁሉንም ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ያደር
ሳሉ ። አዝመራ ፣ ቢስት ፣ በጆሐንስበርግ ፣ ሥራ ፣ ይገኛል ።
ለመንግሥት ፣ ግብር ፣ የሚከፈል ፣ ገንዘብ ፣ ሲታጣ ፣ ጆሐ
ንስበርግ ፣ ወዲህ ፣ ወዲያ ፣ ተሯሩጦ ፣ ከዕዳ ፣ መገላገል ፣
ይቻላል ። የአባት ፣ እርስት ፣ ሲጠብ ፣ ተነሥቶ ፣ ወደ ፣
ጆሐንስበርግ ፣ አብስ ፣ ማለት ፣ ይቻላል ። ድንገት ፣ ዲቃላ ፣
ያረገዘች ፣ ሴት ፣ ዓይንሽ ፣ ላፈር ፣ ወደማትባልበት ፣ ወደ ፣
ጆሐንስበርግ ፣ ኮብልላ ፣ መገላገል ፣ ትችላለች ።

ጥቁሮቹ ፣ ወደ ፣ አለክሳንድራ ፣ ወይም ፣ ወደ ፣ ሶፊ
ያታውን ፣ ወይም ፣ ደግሞ ፣ አርላንዶ ፣ እየሄዱ ፣ ክፍል ፣
ተከራይተው ፣ ሲቸግራቸውም ፣ አንድ ፣ ቤት ፣ ለብዙ ፣
ተጋርተው ፣ ይኖራሉ ።

— ቤቶች ፣ የሚከራይ ፣ ክፍል ፣ አለ ?

— ኧረ ፣ የለንም ።

— እዚህ ፡ ቤት ፡ የሚከራይ ፡ ክፍል ፡ አላችሁ ?
— አከራይተነዋል ።
— እዚህስ ? የሚከራይ ፡ ክፍል ፡ የላችሁም ?
— መኖርስ ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ላከራየው ፡ አልፈ
ልግም ። ያለኝ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ነው ። የምንኖሪ
ውም ፡ ስድስት ፡ ሆነን ፡ ነው ። ልጆቹም ፡ እያደጉ ፡ ነው፡
የሚሄዱት ። የልጆቹ ፡ መማሪያ ፡ መጻሕፍት ፡ ደግሞ ፡
ያለ ፡ ገንዘብ ፡ አይመጣም ። የባለቤቴም ፡ ጤና ፡ እንደ ፡
ነገሩ ፡ ነው ። ለመሆኑ ፡ ባከራይህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ትከ
ፍላለህ ?
— በሳምንት ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ከአሥራ ፡ አምስት ፡
ሳንቲም ፡ እከፍላለሁ ።
— ይቅር ፡ አላከራይም ።
— እሺ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ከሃምሳ ፡ ልከፈል ።
— አንድ ፡ ብር ፡ ከሃምሳ ። ቤትን ፡ ታቅፈው ፡ ቢቀ
መጡት ፡ ሆድ ፡ አይሞላ ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ልጆች ፡
እያደጉ ፡ ሲሄዱ ፡ በሚገባ ፡ ተደላድሎ ፡ መኖር ፡ ያስፈል
ጋቸዋል ። እንዲያው ፡ ተደላድለው ፡ ቢቀመጡ ፡ ምን ፡
ያደርጋል ። ሆድ ፡ እንደሆን ፡ ጊዜ ፡ አይሰጥም ። መቼም ፡
ምን ፡ ይደረግ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ተኩል ፡ ከከፈልህ ፡ ክፍሉን ፡
መከራየት ፡ ትችላለህ ።

ቤቱ ፡ ምንም ፡ አይልም ። ነገር ፡ ግን ፡ መተናፈሻ ፡
የለውም ። ያለችው ፡ ክፍል ፡ ሁለት ፡ ናት ። የቤቱ ፡ ሰዎች ፡
የሚገቡ ፡ የሚወጡት ፡ በአንድ ፡ በር ፡ ነው ። አንዱ ፡
ሲተኛ ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ ተራምዶ ፡ ያልፋል ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ ልጆቹ ፡ ትንሽ ፡ ጠገብ ፡ ብለው ፡ የሚበሉበት ፡
ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ተገኝቶአል ። የቤቱ ፡ ባለቤቶች ፡

ምናልባት ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወደሲኒማ ፡ ለመሄድ ፡
ይችሉ ፡ ይሆናል ።
— ይህችን ፡ ሴትዮ ፡ አልወዳትም ፤ ባሌን ፡ እንዴት ፡
አድርጋ ፡ ነው ፡ የምትመለከተው ። ይህን ፡ ጐረምሳ ፡
አልወደድኩትም ፤ ልጄን ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ነው ፡
የሚመለከተታት ። ይህ ፡ ሰውዬ ፡ አስፈርቶኛል ፤ እን
ዴት ፡ ነው ፡ የሚገላምጠኝ ፤ ልጄን ፡ ምን ፡ ሊያደርጋት ፡
አስቦአል ።
— አዝናለሁ ፡ ቤቴን ፡ መልቀቅ ፡ አለባችሁ ።
— ምን ፡ መሄጃ ፡ አለንና ።
— ቤቱ ፡ መተናፈሻ ፡ አጥቶአል ፤ ምንም ፡ ማድ
ረግ ፡ አልችልም ።
— ቤት ፡ እንዲሰጠን ፡ ስማችንን ፡ አስመዝግበናል።
እስከናገኝ ፡ ታገሡን ።
— አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ የጠበቁት ፡ ሳያገኙ ፡
እናንተ ፡ ትናንት ፡ መጥታችሁ ፡ እናገኛለን ፡ ብላችሁ ፡
ነው ፡ ተስፋ ፡ የምታደርጉት ?
— አንድ ፡ ዘመዳችን ፡ በአንድ ፡ ወሩ ፡ አግኝቶአል።
— በጉቦ ፡ ይሆናል ።
— እኛ ፡ እንደሆን ፡ ለጉቦ ፡ የምናወጣው ፡ ገንዘብ ፡
የለንም ።
— አዝናለሁ ፡ እንዲህ ፡ ተጨናንቀን ፡ አብረን ፡ ልን
ኖር ፡ አንችልም ።

በአርላንዶ ፡ ብቻ ፡ በየቤቱ ፡ በደባልነት ፡ የሚኖሩ ፡
አሥር ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ ይባላል ።
— ዱቡላ ፡ ያለውን ፡ ሰምተሃል ? በአርላንዶ ፡ የገዛ፡
ቤታችሁን ፡ መሥራት ፡ አለባችሁ ፡ ይላል ።

— በማን ፣ ቦታ ፣ ላይ ፣ ነው ፣ ቤታችንን ፣ የምንሠራው ?

— የባቡሩ ፣ ሐዲድ ፣ በተዘረጋበት ፣ ገላጣ ፣ ቦታ ፣ አቅራቢያ ፣ ይላል ፣ ዱቡላ ።

— በምናችን ፣ ነው ፣ ቤቱን ፣ የምንሠራው ?

— አጠና ፣ ከጫካ ፣ ቆርጠህ ፣ ሳር ፣ ከሜዳ ፣ አጭደህ ፣ አሮጌ ፣ ጆንያ ፣ ቀጣጥለህ ፣ መሥራት ፣ ነው ።

— ክረምቱ ፣ ሲገባስ ።

— ክረምት ፣ ሲገባ ፣ የግድ ፣ ቤት ፣ ይሠሩልናል ።

— እሱን ፣ ተወው ። ለመሆኑ ፣ ክረምት ፣ ሲገባ ፣ ምን ፣ ይውጠናል ።

ቤት ፣ ለማግኘት ፣ ስድስት ፣ ዓመት ፣ የጠበቁ ፣ አሉ ። ያሉትም ፣ ቤቶች ፣ ከዕለት ፣ ወደ ፣ ዕለት ፣ እየተጣበቡ ፣ ይሄዳሉ ። ሰዎችም ፣ ከያለበት ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ መጉረፋቸውን ፣ አያቋርጡም ። በአውሮፓና ፣ በሰሜን ፣ አፍሪቃ ፣ ጦርነት ፣ ተነሥቶአል ፣ ስለ ፣ ተባለ ፣ የቤቱን ፣ ሥራ ፣ ዞር ፣ ብሎ ፣ ያየው ፣ የለም ።

* * *

የአርላንዶ ፣ ነዋሪዎች ፣ ሌሊቱን ፣ በሙሉ ፣ ይሯሯጣሉ ። የሁሉም ፣ ቤት ፣ መብራት ፣ እንደ ፣ በራ ፣ ነው ።

— እኔ ፣ ብረታ ፣ ብረቱን ፣ እይዛለሁ ፣ አንቺ ፣ ደግሞ ፣ ሕፃኑን ፣ ታቀፊ ። ልጂ ፣ አንተ ፣ ደግሞ ፣ አጠናዎቹን ፣ ተሸከም ፣ አንተ ፣ ደግሞ ፣ ጆንያዎቹን ፣ የባቡሩ ፣ ሐዲድ ፣ የተዘረጋበት ፣ አገጠብ ፣ ወደሚገኘው ፣ ገላጣ ፣ ስፍራ ፣ አግዝ ።

ሰዎች ፣ ሁሉ ፣ ወደዚያው ፣ ይገሰግሱ ። ግማሹ ፣ ሲቆፍር ፣ ግማሹ ፣ ሲቀጠቅጥ ፣ ይሰማል ። ደግነቱ ፣ ሌሊቱ ፣ አይበርድም ። ዝናብም ፣ የለም ።

— ይህንን ፣ ምቹ ፣ ስፍራ ፣ ስለ ፣ መራችሁን ፤ እናመሰግናለን ፣ ሚስተር ፣ ዱቡላ ። ለኮሚቴው ፣ የምንከፍለው ፣ ድርሻችን ፣ ሠላሳ ፣ አምስት ፣ ሳንቲም ፣ ይኸውና ፣ ሚስተር ፣ ዱቡላ ። ያሰንብትልን ፣ ሚስተር ፣ ዱቡላ ።

ሻንቲ ፣ ታውን ፣ ሌሊቱን ፣ ተቄርቊራ ፣ አደረች ። በነጋታው ፣ ጠዋት ፣ ላያት ፣ ሁሉ ፣ የምታስደንቅ ፣ ትርኢት ፣ ነበረች ።

ሻንቲ ፣ ታውን ፣ ሌሊቱን ፣ ተሠርታ ፣ አደረች ። ጋዜጦቹም ፣ ስለ ፣ እርስዋው ፣ ብቻ ፣ ያወራሉ ። የጋዜጦቹ ፣ አርእስቶችና ፣ ፎቶግራፎች ፣ ከሩቁ ፣ ይማርካሉ ። ደግነቱ ፣ ኪራይ ፣ አይከፈልበትም ፤ ለኮሚቴው ፣ የሚፈልገው ፣ ሠላሳ ፣ አምስት ፣ ሳንቲም ፣ እምብዛም ፣ የሚጎዳ ፣ አይደለም ።

ሻንቲ ፣ ታውን ፣ በአንድ ፣ ሌሊት ፣ ዕድሜ ፣ ተሠርርታ ፣ ያደረች ፣ ከተማ ፣ ናት ።

— ሕፃንዋ ፣ ያስላታል ። ግንባርዋም ፣ ክፉኛ ፣ ያተኩሳል ። የግድ ፣ ሆኖብን ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እዚያው ፣ የነበርንበት ፣ ይሻላት ፣ ነበር ። ብርዱ ፣ ደግሞ ፣ በያለበት ፣ ነው ፣ የሚገባው ።

— ክረምት ፣ ገብቶ ፣ ዝናም ፣ መጣል ፣ ሲጀምር ፣ ምን ፣ ይውጠን ፣ ይሆን ? አይዞሽ ፣ ልጂ ፣ እናትሽ ፣ አለችልሽ ። በጣም ፣ አትሳዪ ፣ ልጂ ፣ እናትሽ ፣ አለችልሽ ።

የልጅቱ ፣ ሳል ፣ እየጠና ፣ ሄደ ። ግንባርዋም ፣ እንደ ፣ እሳት ፣ ያቃጥላል ።

— እሽሩሩ ፣ ልጄ ፣ ለእናትሽ ፣ ይሁን ። ውጭ ፣ ሰዎች ፣ ይስቃሉ ፣ ይቀልዳሉ ፣ ይቆፍራሉ ፣ ይቀጠቅጣሉ ፣ በማላውቀው ፣ ቋንቋ ፣ የሚናገሩም ፣ ብዙዎች ፣ ናቸው ። አይዞሽ ፣ የእኔ ፣ ልጅ ፣ የተወለድሽበት ፣ ሸለቆ ፣ ውበቱ ፣ እንዲህ ፣ አይደለም ። ውኃው ፣ ከድንጋይ ፣ ጋር ፣ ይጫ ወታል ፤ የነፋሱ ፣ ሽውታ ፣ ያቀዘቅዝሻል ። ላሞቹም ፣ ውኃ ፣ ለመጠጣት ፣ ወደ ፣ ወንዝ ፣ ወርደው ፣ ዛፎቹ ፣ ሥር ፣ ይቆማሉ ። እሽሩሩ ፣ ልጄ ፣ አምላኬ ፣ ሆይ ፣ ፊትህን ፣ መልስልን ፤ ክርስቶስ ፣ ሆይ ፣ ፊትህን ፣ መልስልን ፤ ፈረንጅ ፣ ሆይ ፣ ፊትህን ፣ መልስልን ።

— ዝናብ ፣ ሲጥል ፣ ክረምት ፣ ሲገባ ፣ ምን ፣ እንሆ ናለን ? እዚያ ፣ ማዶ ፣ ኮረብታ ፣ ላይ ፣ የሚሠሩትን ፣ ቤቶች ፣ ተመልከቱ ። ጣሪያው ፣ ተከድኖ ፣ ለማለቅ ፣ ተቃርቦአል ። አንድ ፣ ቀን ፣ ሌሊት ፣ ወደዚያው ፣ ተዛውረን ፣ ከክረምቱ ፣ ዶፍ ፣ እናርፋለን ።

—10—

— ወዳጄ ፣ ሆይ ፣ ሻንቲ ፣ ታውን ፣ ማለት ፣ ይኸ ፣ ነው ። በዚህ ፣ አላዛኝ ፣ በሆነ ፣ ስፍራ ፣ በሚገኙት ፣ ጠባብ ፣ መንገዶች ውስጥ ፣ ውር ፣ ውር ፣ የሚሉት ፣ ሕፃናት ፣ እንኳን ፣ ሳቅና ፣ ጫዋታ ፣ ያሰማሉ ። አንድ ፣ ቆርቆሮ ፣ ጥቂት ፣ አጠናዎች ፣ የጀንያ ፣ ቅዳጅ ፣ አንድ ፣ ሽክም ፣ ሳር ፣ ከወደቀ ፣ ወይም ፣ ካረጀ ፣ ቤት ፣ የተወሰደ ፣ መዝገያ ፤ የመኖሪያ ፣ ቤቱ ፣ አሠራር ፣ እስከዚህ ፣ ድረስ ፣ ብቻ ፣ ነው ። በብልሃት ፣ ከተወተፈው ፣ ቀዳዳ ፣ ጢስ ፣ ቱማ ፣ እያለ ፣ ይወጣል ፤ የምግቡ ፣ ሽታ ፣ እውድ ፣ ያደርጋል ። ከያለበት ፣ የሰዎች ፣ ድምፅ ፣ ይሰማል ። ፀሐይ

ዋም ፣ ዙል ፣ ከመሰለው ፣ ሰማይ ፣ ሙቀትዋን ፣ ትቸራለች ። ክረምት ፣ ሲገባ ፣ ዝናብ ፣ መጣል ፣ ሲጀምር ፣ ምን ፣ ይሻላቸው ፣ ይሆን ?

— ያችን ፣ ነርስ ፣ ተመልከታት ። በቀይና ፣ በነጭ ፣ ቀለም ፣ ያጌጠውን ፣ የማዕርግ ፣ ልብስዋን ፣ ለብሳ ፣ ስትሄድ ፣ አታስደስትም ? ነጮቹ ፣ ብዙዎቹን ፣ በዚህ ፣ ሙያ ፣ በማሠልጠን ፣ ላይ ፣ ይገኛሉ ። አንድ ፣ ነገር ፣ በጣም ፣ ይደንቅኛል ። በአንዳንድ ፣ ሙያ ፣ ወደ ፣ ፊት ፣ ስንገፋ ፣ በሌላው ፣ ደግሞ ፣ አንዲት ፣ ስንዝር ፣ እንኳን ፣ እንራመድም ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ብዙዎቹ ፣ ሴቶች ፣ ወጣቶቻችን ፣ በአስተማሚነትና ፣ በሕክምና ፣ ሙያ ፣ እንዲሠለጥኑ ፣ የሚረዱን ፣ ብዙ ፣ ነጮች ፣ ወዳጆች ፣ አሉን ።

— ጤና ፣ ይስጥልኝ ፣ ነርስ ።

— ጤና ፣ ይስጥልኝ ፣ ኡምፉንዲሲ ።

— አቤሴሎም ፣ ኩማሎ ፣ የተባለ ፣ ወጣት ፣ ታውቂያለሽ ?

— አዎን ፣ እውቃለሁ ። ከዚህ ፣ ከሄደ ፣ ቆይቶአል ። የሚኖረውም ፣ እዚያ ፣ የሚታየው ፣ ቤት ፣ ውስጥ ፣ ነበር ።

— ጤና ፣ ይስጥልኝ ፣ እዚህ ፣ ቤት ።

— ጤና ፣ ይስጥልኝ ፣ ኡምፉንዲሲ ፣ — አለች ፣ የቤቱ ፣ ባለቤት ፣ እንግዶቹን ፣ በፈገግታ ፣ እየተቀበለች ።

— አቤሴሎም ፣ ኩማሎ ፣ የተባለ ፣ ልጅ ፣ ፍለጋ ፣ ነው ፣ የመጣነው ።

— አዎን ፣ አቤሴሎም ፣ ኩማሎ ፣ ከእኔ ፣ ጋር ፣ ይኖር ፣ ነበር ። የሚኖርበት ፣ ስፍራ ፣ በማጣቱ ፣ ስላሳዘነኝ ፣ እስጠግቹው ፣ ነበር ። በኋላ ፣ ግን ፣ ፖሊሶች ፣ መጥተው ፣ ከዚህ ፣ ወሰዱት ፣ በቅርቡ ፣ እንደ ፣ ሰማሁት ፣ ጠባይ ፣ ማረሚያ ፣ አስገብተውታል ፣ ይባላል ።

— ጠባይ ፡ ማረሚያ ?
— አዎን ፡ ያ ፡ ከሆስፒታሉ ፡ በስተጀርባ ፡ የሚገ
ኘው ፡ ትልቁ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።
— አመሰግንሻለሁ ፡ ደህና ፡ ሁኚ ።
— በል ፡ እንሂድ ፡ ወዳጄ ።

ሁለቱም ፡ አንዳች ፡ ቃል ፡ ሳይተነፍሱ ፡ መንገዳቸ
ውን ፡ ቀጠሉ ። ኩማሎ ፡ ለጥ ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ እያደ
ናቀፈው ፡ ሊወድቅ ፡ ይቃጣው ፡ ጀመር ። ምሲማንጉም፡
በእጁ ፡ ደግፎ ፡ እየመራው ፡—

— በርታ ፡ ወዳጄ ፡—አለው ።
— እንዳንዴ ፡ ብርታቴ ፡ ሁሉ ፡ ጥሎኝ ፡ እብስ ፡
ይላል ። መቼም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንደማይቀር ፡ ልቤ ፡ ነግ
ሮኛል ።
— እኔም ፡ ሠግቼ ፡ ነበር ።
— እንተን ፡ ሥጋት ፡ የጀመረህ ፡ በአለከሳንድራ ፡
እንደ፡ሆነ ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ። እኔን ፡ ቀደም ፡ አድርገህ ፡ አስ
ወጥተህ ፡ ከሴትዮዋ ፡ ጋር ፡ ለመነጋገር ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ቀረት፡
ባልህ ፡ ጊዜ ፡ . . . ለመሆኑ ፡ ሴትዮዋ ፡ ምን ፡ ነገረችህ ?
— እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ወጣቶች ፡ አጉል ፡ ነገር ፡ ሰም
ደዋል ፡ አለችኝ ። በርከት ፡ ያሉ ፡ የተሰረቁ ፡ ዕቃዎች ፡
ይዘው ፡ ይመጡ ፡ እንደ ፡ ነበርም ፡ ነገረችኝ ።
— ይህ ፡ የጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ የሚሉት ፡ እውነት ፡
አሁን ፡ ጠባይ ፡ ያርም ፡ ይሆን ?
— ስፍራውን ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ አላውቀውም ።
ሰዎች ፡ ስለ ፡ ስፍራው ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ የተለያየ፡
ነው ።እንያ ፡ እንግሊዛዊው ፡ ወዳጅህ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ጠባይ፡
ማረሚያው ፡ ያላቸው ፡ ግምት ፡ መልካም ፡ ነው ።

እንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ ጠባይ ፡
ማረሚያው ፡ ግቢ ፡ ደረሱ ። የራሳቸው ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡
አንድ ፡ ትሕትና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ቀረብ ፡
ብሎ ፡ ምን ፡ እንደሚፈልጉ ፡ ጠየቃቸው ። እነርሱም ፡
አቤሴሎም ፡ ኩማሎን ፡ ፍለጋ ፡ የመጡ ፡ መሆናቸውን ፡
ገለጡለት ። ሰውዬውም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ቢሮ ፡ ወሰዳ
ቸው ። በቢሮው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ልጅግር ፡ ነጭ ፡ ተቀ
በላቸው ። የመጡበትንም ፡ ጉዳይ ፡ በአፍሪካንስ ፡ ቋንቋ ፡
ጠየቃቸው ።

— የጓደኛዬን ፡ ልጅ ፡ አቤሴሎም ፡ ኩማሎን ፡
ፍለጋ ፡ ነው ፡ የመጣነው ፡—አለ ፡ ምሲማንጉ ፡ በአፍሪካ
ንስ ፡ ቋንቋ ።
— አቤሴሎም ፡ ኩማሎ ? እርሱንማ ፡ ደህና ፡ አድ
ርጌ ፡ አውቀዋለሁ ። ምነው ፡ ዘመድ ፡ የለኝም ፡ ብሎኝ ?
ምሲማንጉም ፡ ወደ ፡ ኩማሎ ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ በዙሉ ፡
ቋንቋ ፡—
— ልጅህ ፡ ዘመድ ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ የተመዘ
ገበው ፡ አለው ።
— አፍሮ ፡ ነው ፡— አለ ፡ ኩማሎ ። ቀጥሎም ፡
አፍሪካንስ ፡ ቋንቋ ፡ ለመነጋገር ፡ ባለመቻሌ ፡ አዝና
ለሁ ፡ በልና ፡ ንግርልኝ ፡—አለው ። ይህንንም ፡ ያለበት ፡
ምክንያት ፡ ነጮች ፡ አፍሪካንስ ፡ የማይነጋገሩትን ፡ ጥቁ
ሮች ፡ አይወዱዋቸውም ፡ ማለትን ፡ ስለ ፡ ሰማ ፡ ነበር ።
— በምትፈልገው ፡ ቋንቋ ፡ መናገር ፡ ትችላለህ ፡—
አለ ፡ ነጩ ። ልጅህ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ መል
ካም ፡ ጠባይ ፡ አሳይቶአል ። የወደፊት ፡ ኑሮው ፡ እንደሚ
ቃናለት ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።

— ከዚህ ፡ ለቅቆአል ፡ ማለትዎ ፡ ነው ?

— አዎን ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ የተሰናበተው ። በአንድ ፡ በኩል ፡ ጠባዩን ፡ በማሻሻሉ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ዕድሜውን ፡ በመገመት ፡ ከሁሉም ፡ በላይ ፡ አንድ ፡ ያረገዘችለት፡ልጅ ፡ ስለ ፡ ነበረች ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ልናደርግለት ፡ ቻልን ። ልጅቱ ፡ ልትጠይቀው ፡ ስትመጣ ፡ የፍቅር ፡ ስሜቱን ፡ ይገልጽላትና፡ ስለሚወለደውም ፡ ሕፃን ፡ ደኅንነት ፡ ይጨነቅ ፡ ነበር ። ልጅቱም ፡ ትወደው ፡ ነበር ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ በማመዛዘን ፡ ልጅቱንና ፡ የሚወለደውን ፡ ሕፃን ፡ ለማስተዳደር ፡ ተግቼ ፡ እሠራለሁ ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ተስፋ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ከዚህ ፡ እንዲወጣ ፡ አደረግን ።

— ሚስት ፡ አግብቶአል ፡ ማለት ፡ ነዋ ?

— ጋብቻው ፡ ገና ፡ አልተፈጸመም ፡ ኡምፉንዲሲ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለጋብቻው ፡ የሚያስፈልገው ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ተዘጋጅቶአል ። ልጅቱም ፡ ዘመድ ፡ የላትም ፤ አቤሴሎምም ፡ ዘመድ ፡ የለኝም ፡ በማለቱ ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ በማዘጋጀት ፡ ላይ ፡ ነኝ ።

— ያስንብትልኝ ፡ ጌታዬ ። በእነርሱ ፡ ስም ፡ ሆኜ፡ ከልብ ፡ አመሰግንዎታለሁ ።

— ምንም ፡ አይደለም ፤ ሥራችን ፡ ነው ። አንተ ፡ ግን ፡ በሥርዓት ፡ ለምን ፡ አላገባም ፡ ብለህ ፡ አትጨነቅ ። ዋናው ፡ ነገር ፡ ጠባዩን ፡ አሳምሮ ፡ ልጅቱንና ፡ ሕፃኑን ፡ ለማስተዳደር ፡ መቻሉ ፡ ነው ።

— ይህንን ፡ የጀመርሁትን ፡ ሥራ ፡ እስክጨርስ ፡ ወጣ ፡ ብላችሁ ፡ ብትጠብቁኝ ፡ አቤሴሎምና ፡ ልጅቱ ፡ ወደሚኖሩበት ፡ ወደ ፡ ፒምቪል ፡ አደርሳችኋለሁ ። ለጊ

ዜው ፡ እርሱ ፡ የሚገኘው ፡ በዘመድ ፡ ብርታት ፡ ባገኘሁት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ነው ። ስለ ፡ ጠባዩም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ትጋቱ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ደርሰውኛል ። ገንዘብ ፡ እንዲያጠራቅም ፡ በሰጠሁት ፡ ምክር ፡ መሠረት ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ ያህል ፡ ባንክ ፡ አስቀምጦአል ።

— ምስጋናዬ ፡ ወሰን ፡ የለውም ፡ ጌታዬ ።

— ምንም ፡ አይደል ፤ ሥራችን ፡ ነው ።

ከነጩ ፡ የጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ኃላፊ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ፒምቪል ፡ ተጉዘው ፡ ከአንዲት ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ በር ፡ ሲደርሱ ፡ መኪናው ፡ ቆመ ። አንዲት ፡ ገና ፡ ልጅነትዋን ፡ ያልጨረሰች ፡ ልጅ ፡ ተቀበለቻቸው ።

— አቤሴሎምን ፡ ፍለጋ ፡ ነው ፡ የመጣነው ፡— አለ፡ ነጩ ። አብሮኝ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ኡምፉንዲሲ ፡ አባቱ ፡ ነው ።

— ባለፈው ፡ ቅዳሜ ፡ እስፕሪንግስ ፡ ሄዶ ፡ አልተመለሰም ፡— አለች ።

ነጩ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ አለ ። ፊቱ ፡ ላይ ፡ ጭንቀት ፡ የተቀላቀለበት ፡ የቊጣ ፡ ምልክት ፡ ይታይበት ፡ ጀመር ።

— ዛሬ ፡ ማክሰኞ ፡ ነው ፡ እኮ ! እስከ ፡ አሁን ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ የሰማኸው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ?

— ምንም ፡ አልሰማሁም ።

— መቼ ፡ እመለሳለሁ ፡ ብሎኻል ?

— አልነገረኝም ።

በግድ ፡ የለሽነትና ፡ በለበጣ ፡ መንፈስ ፡—

— ተመልሶ ፡ ይመጣል ፡ ብላችሁ ፡ ነው ? ሲል ፡ ጠየቀ ።

እርስዋም ፣ በግድ ፣ የለሽነትና ፣ በለበጣ ፣ መንፈስ ፣—
—እኔ ፣ ምን ፣ አውቃለሁ ፣— አለች ። የአነጋገርዋ ፣
ስሜት ፣ ማጣትና ፣ ተስፋ ፣ መቁረጥ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ መጠበ
ቅንና ፣ መከዳትን ፣ የለመደችው ፣ መሆንዋን ፣ ይገልጻል ።
የኩማሎም ፣ ልብ ፣ በጎዘን ፣ ተነካ ።
— እንግዲህ ፣ ምን ፣ ይሻልሻል ? አላት ።
— አላውቅም ፣— አለችው ።

ኩማሎ ፣ ልጅቱን ፣ ሊያነጋግራት ፣ ሲል ፣ ምሲማ
ንጉ ፣ ከልጅትዋ ፣ ገለል ፣ አድርጎ ፣—

— እንግዲህ ፣ ይብቃን ። እዚህ ፣ ምንም ፣ ማድረግ ፣
አይቻልም ። ብንሄድ ፣ ይሻላል ። እርስዋን ፣ የመሰሉ ፣
በሺህ ፣ የሚቁጠሩ ፣ ወጣት ፣ ሴቶች ፣ በጆሐንስበርግ ፣
ይገኛሉ ፣— አለው ።
— አንተ ፣ ነገሩ ፣ አልገባህም ፣— አለ ፣ ኩማሎ ።
ሕፃኑ ፣ የልጅ ፣ ልጇ ፣ መሆኑ ፣ ነው ፣ እኮ !
— የልጅ ፣ ልጅህ ፣ ለመሆኑ ፣ ምን ፣ ማረጋገጫ ፣ አለህ ?
አለ ፣ ምሲማንጉ ፣ በቁጣ ፣ ቃል ። — ለምሳሌ ፣ ይህ ፣
ገና ፣ የሚወለደው ፣ ሕፃን ፣ የልጅ ፣ ልጅህ ፣ ነው ፣ እንበል ።
እርሱን ፣ የመሰለ ፣ ስንት ፣ የልጅ ፣ ልጆች ፣ እንዳሉህ ፣
ታውቃለህ ? ጠዋትም ፣ ማታም ፣ እነርሱኑ ፣ እንፈልግ ፣
ነው ፣ የምትለው ? እንዲህ ፣ ያለው ፣ ነገር ፣ ከተፈለገ ፣
ማለቂያ ፣ የሚኖረው ፣ ይመስልሃል ?

ኩማሎም ፣ በመንገድ ፣ የሚተላለፉት ፣ ተሽከርካሪ
ዎች ፣ ባነሡት ፣ አቧራ ፣ ተሸፍኖ ፣ ከጓደኛው ፣ አንደ
በት ፣ በሰማው ፣ ኃይለ ፣ ቃል ፣ በመደንገጥ ፣ እቆመበት ፣
ከው ፣ ብሎ ፣ ቀረ ። በመጨረሻውም ፣ አንዳች ፣ ቃል ፣

ሳይተነፍስ ፣ መኪናው ፣ ውስጥ ፣ ገብቶ ፣ ሰፍራውን ፣
ያዘ ።

ከጥቁሮቹ ፣ መንደር ፣ መውጫ ፣ ላይ ፣ ሲደርሱ ፣
መኪናው ፣ ቆመ ። ነጩም ፣ ወደ ፣ አንድ ፣ ቢሮ ፣ ገባ ።
ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ ፊቱን ፣ ቅጭም ፣ አድርጎ ፣ ተመ
ለሰ ።

— ሥራ ፣ ወደጀመረበት ፣ ፋብሪካ ፣ ስልክ ፣ ደውዬ ፣
ነበር ፣— አለ ፣ ነጩ ።— ነገር ፣ ግን ፣ በዚህ ፣ ሳምንት ፣
ሥራ ፣ አልገባም ፣ አሉኝ ።

ኦርላንዶ ፣ እንደ ፣ ደረሱ ፣ መኪናው ፣ ቆመ ።

— ምናልባት ፣ እዚህ ፣ መውረድ ፣ ይሻላችኋል ፣—
አለ ፣ ነጩ ።
— ከመኪናው ፣ እንደ ፣ ወረዱ ፣ ነጩ ፣ ወደ ፣ ኩማሎ ፣
ዞር ፣ ብሎ ፣—
— ያሰብነው ፣ ባለመሳካቱ ፣ አዝናለሁ ፣— አለ ።
— አዎን ፣ በጣም ፣ ያሳዝናል ። ድካምዎ ፣ ሁሉ ፣
ከንቱ ፣ መሆኑ ፣ በጣም ፣ ያሳዝናል ፣— አለ ፣ ኩማሎ ።
— እኔስ ፣ ሥራዬ ፣ ነው ፣ የአንተ ፣ ልፋት ፣ ነው ፣
የሚያሳዝነው ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ ተስፋ ፣ መቁረጥ ፣ የለብ
ንም ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ አንድ ፣ ወጣት ፣ ሳያስበው ፣
ይታሰራል ፣ ወይም ፣ ደግሞ ፣ አደጋ ፣ ደርሶበት ፣ ሆስፒታል ፣
ይገባል ። አንድ ፣ ሰው ፣ ከቤት ፣ ከወጣ ፣ በኋላ ፣ ብዙ ፣
ነገር ፣ ሊደርስበት ፣ ይችላል ። ተስፋ ፣ መቁረጥ ፣ የለብ
ህም ፣ ኡምፉንዲሲ ። እኔም ፣ በበኩሌ ፣ ያለበትን ፣
አጠያይቃለሁ ።

ነጩ ፣ መኪናውን ፣ አስነሥቶ ፣ ሲሄድ ፣ ቁመው ፣ ተመለከቱት ።

— እንዴት ፣ ያለው ፣ ጥሩ ፣ ሰው ፣ ነው ። እንግዲህ፣ እናዝግም ፣ አለ ፣ ኩማሎ ። ምሲማንጉ ፣ ግን ፣ ያለበት ፣ ቆሞ ፣ ቀረ ።

— ከአንተ ፣ ጋር ፣ ለመሄድ፣ ጎፍረት፣ ይሰማኛል ፡— አለ ፣ ምሲማንጉ ፣ ፊቱን ፣ በጎዘንና ፣ በጸጸት ፣ አኩማ ትሮ ።

ኩማሎ ፣ በመገረም ፣ ይመለከተው ፣ ጀመር ።

— ለተናገርሁት ፣ የማይገባ ፣ ቃል ፣ ይቅርታ ፣ አድርግልኝ ፡— አለ ።

— የልጅ ፣ ልጆችህን ፣ እንፈልጋቸው ፣ ወይ ፣ ያል ከውን ፣ ነው ? አታስብ ፣ ይቅር ፣ ብዬሃለሁ ። . . . አንድ፣ ነገር ፣ ብቻ ፣ ልንግረህ ።

ምሲማንጉም ፣ ዓይን ፣ ዓይኑን ፣ እየተመለከተ ፡—

— ባትነግረኝም ፣ ገብቶኛል ።

— ምንድር ፣ ነው ፣ የገባህ ?

— ልጅቱ ፣ ዘንድ ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ይገርህ ፣ እንድሄድ፣ መፈለግህ ።

የፀሐዩ ፣ ሐሩር ፣ ገና ፣ ያልበረደለትን ፣ የአርላንዶን ፣ መንገድ ፣ ይዘው ፣ ይነኩት ፣ ጀመር ። በሁለቱም ፣ ላይ፣ ዝምታ ፣ ነግሦአል ። በየፊናቸው ፣ ከሐሳባቸው ፣ ጋር ፣ ይታገሉ ፣ እንደ ፣ ነበር ፣ በግልጽ ፣ ይታያል ።

—11—

በሚስዮኑ ፣ ግቢ ፣ ያሳለፉት ፣ ምሽት ፣ ደስ ፣ የሚ ያሰኝ ፣ ነበር ። ሁልጊዜ ፣ ጉንጫቸው ፣ ፍም ፣ የሚመስ ለው ፣ አባ ፣ ቪንሴንትም ፣ እዚያው ፣ ነበሩ ። አሁንም ፣ ስለ ፣ ኩማሎ ፣ አገር ፣ አንሥተው ፣ ይጨዋወቱ ፣ ነበር ። አባ ፣ ቪንሴንት ፣ አንዳንዴ ፣ አገራቸው ፣ ትዝ ፣ ሲላቸው ፣ ስለ ፣ እርሻው ፣ ስለ ፣ ማሳው ፣ ስለ ፣ ዌስትሚኒስቴር ፣ አቤ ፣ በየስፍራው ፣ ስለሚገኙት ፣ ታላላቅ ፣ ካቴድራሎች፣ ያወሩ ፣ ነበር ። በእንደዚህ ፣ ያለ ፣ አኳኋን ፣ እያወጉ ፣ ተቀ ምጠው ፣ ሳሉ ፣ ከቄሶቹ ፣ አንዱ ፣ አንድ ፣ የምሽት ፣ ጋዜጣ ፣ እምጥቶ ፣ በመጀመሪያው ፣ ገጽ ፣ ላይ ፣ በጉልህ ፣ የተጻፈውን ፣ አርእስት ፣ አሳያቸው ።

አርእስቱ ፣ «የታወቀው ፣ የፖርክዎልድ ፣ መሐንዲስ፣ አርሰር ፣ ጃርቪስ ፣ ተገደለ ። በወንጀሉ ፣ ጥቁሮች ፣ ተጠር ጥረዋል ፡» ይላል ።

— የእርሱ ፣ ሞት ፣ ለደቡብ ፣ አፍሪቃ ፡— ትልቅ ፣ ጉዳት ፣ ነው ፡— አሉ ፣ ነጩ ፣ ቄስ ።

— አርሰር ፣ ጃርቪስ ፣ ደፋርና ፣ ታላቅ ፣ የእውነት ፣ ተከራካሪ ፣ ነበር ። የእርሱ ፣ ሞት ፣ ለቤተ ፣ ክርስቲያናች ንም ፣ ትልቅ ፣ ጉዳት ፣ ነው ።

— ሚቹ ፣ ጃርቪስ ፣ ነው ? አለ ፣ ምሲማንጉ ፣ በድንጋጤ ። —እንዴት ፣ ያሳዝናል ። እርሱማ ፣ በግላዲዮሉስ ፣ ጉዳና ፣ የሚገኘው ፣ የከላሬሞንት ፣ አፍሪቃውያን ፣ ወጣቶች ፣ ክበብ ፣ ፕሬዚደንት ፣ አልነበረም ።

አባ ፣ ቪንሴንት ፣ ወደ ፣ ኩማሎ ፣ ዞር ፣ ብለው ፣—

— አንተም ፣ ላታውቀው ፣ እትቀርም ፣ እኮ ፤ በሃይ ፕሉስ ፣ ካሪስብሩክ ፣ የሚኖረው ፣ የሚስተር ፣ ጀምስ ፣ ጃርቪስ ፣ ልጅ ፣ ነው ፡— አሉ ።

— አባቱን ፣ አውቃለሁ ፣ — አለ ፣ ኩማሎ ፣ እያ ዘነ ። —የዓይን ፣ እውቂያ ፣ ማለቱ ፣ ነው ። ከእንዶትሼኒ፣ ከፍ ፣ ብሎ ፣ አንድ ፣ እርሻ ፣ አላቸው ። አንዳንዱም ፣ በቤተ ፣ ክርስቲያናችን ፣ በኩል ፣ በፈረስ ፣ ተቀምጠው ፣ ያልፋሉ ። ሚቹ ፣ ልጁን ፣ ግን ፣ የማውቀው ፣ አይመስለ ኝም ።

ጥቂት ፣ ደቂቃዎች ፣ ሁሉም ፣ ዝም ፣ አሉ ።

ከዚያም ፣ — አዎን ፣ ትዝ ፣ ይለኛል ፣ አንድ ፣ ቁመ ናው ፣ የሚያምር ፣ ትንሽ ፣ ልጅ ፣ በፈረስ ፣ ላይ ፣ ተቀምጦ ፣ ከእንጨት ፣ የተሠራ ፣ ጠመንጃ ፣ አንግቶ ፣ በቤተ ፣ ክርስቲ ያናችን ፣ በኩል ፣ ያልፍ ፣ ነበር ። አንድ ፣ ቁመናው ፣ የሚ ያምር ፣ ወጣት ፣ ልጅ — አዎን — ትንሽ ፣ ትንሽ ፣ ትዝ ፣ ይለኛል ።

እንደ ፣ ገና ፣ ዝም ፣ አለ ። አንድ ፣ ቁመናው ፣ የሚ ያምር ፣ ወጣት ፣ ድንገት ፣ ሲቀጭ ፣ በጎዘን ፣ ኃይል ፣ ተይዞ ፣ ዝም ፣ የማይል ፣ ማን ፣ አለ ?

— በጋዜጣው ፣ ላይ ፣ የተጻፈውን ፣ ላንባብብላችሁ፣ አሉ ፣ አባ ፣ ቪንሴንት ።

« በዛሬው ፣ ዕለት ፣ ከቀኑ ፣ በሰባት ፣ ሰዓት ፣ ተኩል፣ ላይ ፣ ተቀማጭነቱ ፣ ፕላንቴሽን ፣ መንገድ ፣ ፖርከዎልድ፣ የሆነው ፣ ሚስተር ፣ አርሰር ፣ ጃርቪስ ፣ በአንድ ወሮበላ ፣ እጅ ፣ በሽጉጥ ፣ ተገደለ ። ገዳዩ ፣ ጥቁር ፣ ነው ፣ ይባላል ። ወንጀሉ ፣ በተፈጸመበት ፣ ሰዓት ፣ የሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣

ባለቤት ፣ ከሁለት ፣ ልጆችዋ ፣ ጋር ፣ ለጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ዕለ ፍት ፣ ከሄደችበት ፣ አልተመለሰችም ፣ ነበር ። የዚያኑ ፣ ዕለት ፣ ጠዋት ፣ ሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ በጉንፋን ፣ ምክን ያት ፣ እቤት ፣ ውሎ ፣ ነበር ።

« አንድ ፣ ወሮበላ ፣ ከሁለት ፣ የግብር፣ አበሮቹ፣ ጋር፣ በቤቱ ፣ ውስጥ ፣ ሰው ፣ የለም ፣ በማለት ፣ በማድ፣ ቤቱ ፣ በኩል ፣ ገብተው ፣ በመጀመሪያ ፣ የሚስተር ፣ ጃርቪስን ፣ አሽከር ፣ ሕሊናውን ፣ እስኪስት ፣ ድረስ ፣ ይደበድቡታል ። ሚስተር ጃርቪስ ፣ በቤቱ ፣ ውስጥ ፣ የተኛሣውን ፣ ትር ምስ ፣ ለማጣራት ፣ ወደ ፣ ማድ ፣ ቤቱ ፣ ብቅ ፣ እንዳለ ፣ ወንበዴው ፣ ሽጉጡን ፣ አውጥቶ ፣ ተኩሶ ፣ ይገድለዋል ።

« ይህ ፣ አሳዛኝ፣ ሁኔታ ፣ ከመፈጸሙ ፣ ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በፊት ፤ ሦስት ፣ ጥቁሮች ፣ ጎረምሶች ፣ በፕላንቴሽን ፣ መን ገድ ፣ ላይ ፣ ታይተዋል ። የሚቹ ፣ ጥቁር ፣ አሽከር ፣ ጥቁ ሮች ፣ ሆስፒታል ፣ ገብቶአል ። ነፍስ ፣ ዘርቶ ፣ ንግግር ፣ ሲጀምር ፣ ወንጀለኛውን ፣ ለመከታተል ፣ የሚረዱ ፣ መረ ጃዎችን ፣ ለፖሊስ ፣ እንደሚሰጥ ፣ ይጠበቃል ። ለጊዜው ፣ ሁኔታው ፣ አስጊ ፣ ነው ፣ ይባላል ።

« ሚርተር ፣ ጃርቪስ ፣ ከዚህ ፣ ዓለም ፣ በሞት ፣ የተለ የው ፣ ሚስቱን ፣ የዘጠኝ ፣ ዓመት ፣ ወንድ ፣ ልጁንና ፣ የአ ምስት ፣ ዓመት ፣ ሴት ፣ ልጁን ፣ ትቶ ፣ ነው ።

« ሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ ለማኅበራዊ ፣ ኑሮ ፣ ፕሮብሌ ሞች ፣ መፍትሔ ፣ ለማግኘትና ፣ የጥቁሮቹን ፣ የኑሮ ፣ ደረጃ ፣ ለማሻሻል ፣ ያደርገው ፣ በነበረው ፣ ጥረትና ፣ አገ ልግሎት ፣ የታወቀ ፣ ሰው ፣ ነበር ። »

ከመካከላቸው ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ የሚተነፍስ ፡ አል
ነበረም ። ያቺ ፡ ቅጽበት ፡ ስለ ፡ እርሻ ፡ ስለ ፡ ማሳ ፡ ስለ ፡
አገር ፡ ውበት ፡ የሚነጋገሩባት ፡ አልነበረችም ። እነዚህ ፡
የጥፋት ፡ ዜና ፡ የማይለያቸው ፡ ጋዜጦች ፡ በተገለጡ ፡
ቍጥር ፡ የሰው ፡ ልብ ፡ በጎዘን ፡ በፍርሃትና ፡ በጥላቻ ፡
እየደነደነ ፡ ይሄዳል ። ተናቃላ ፡ ሆነው ፡ ለቀሩት ፡ ጎሳ
ዎች ፡ ተረስቶ ፡ ለቀረው ፡ የአባቶች ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡
አፍ ፡ አውጥቶ ፡ ማልቀስ ፡ ይገባል ። ለሞተው ፡ ሰው ፡
ባልዋን ፡ ላጣችው ፡ ሴት ፡ አባታቸውን ፡ ለተነጠቁት ፡
ሕፃናት ፡ እሪ ፡ ብሎ ፡ ማልቀስ ፡ ይገባል ። እሪ ፡ በይ ፡
ውድ ፡ አገሬ ፤ ገና ፡ ምኑን ፡ አይተሽ ። ሰዎች ፡ በማይዝና
ኑባት ፡ በዚች ፡ ውብ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ፀሐይዋ ፡ ብርሃንዋን ፡
አንጣልላዋለች ። ሁሉም ፡ የሚታገለው ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡
ካለው ፡ ፍርሃት ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ኩማሎ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ተነሥቶ ፡—

— ደክሞኛል ፡ ለመተኛት ፡ ወደ ፡ ክፍሌ ፡ እሄዳ
ለሁ ፤ ሁላችሁም ፡ ደህና ፡ እደሩ ፡— አለ ።
— እኔ ፡ እሸኝሃለሁ ፡— አለ ፡ ምሲማንጉ ።

ኩማሎና ፡ ምሲማንጉ ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ ወይዘሮ ፡
ሊቴቤ ፡ ቤት ፡ አመሩ ። ኩማሎም ፡ ጭንቀት ፡ ያጠቃ
ውን ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ምሲማንጉ ፡ መልሶ ፡—

— እንጃ ፡ ይኸ ፡ ነገር ፡ እንጃልኝ ፤ ልቤን ፡ የሚያ
ሸብረው ፡ ፍርሃት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡— ፍርሃት — ፍርሃት—
ፍርሃት — አለ ።
— እርግጥ ፡ ነው ፡ ስሚትህ ፡ ይገባኛል ። በብዙ ፡
ሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ በሚኖሩበት ፡ በጆሐንስበርግ ፡

ከተማ ፡ ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ነገር ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል ። አዳ
ንዴ ፡ ሳስበው ፡ ግን ፡ በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ መፍራት ፡
ሞኝነት ፡ ነው ፡— አለ ፡ ምሲማንጉ ።
— ይኸ ፡ አስተዋይ ፡ ወይም ፡ ሞኝ ፡ የሚያሰኝ ፡
ነገር ፡ አይደለም ። እንዲያው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ፍርሃት ፡ ነው ።
— አብረን ፡ ጸሎት ፡ እናድርስ ?
— ሁለመናዬ ፡ ባዶ ፡ ሆኖአል ። በውስጤ ፡ ለጸ
ሎት ፡ የሚሆኑ ፡ ቃላት ፡ የሉም ።
— እንግዲያው ፡ ደህና ፡ እደር ።
— ደህና ፡ እደር ።

አንዳንዴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህችን ፡ ዓለም ፡ እር
ግፍ ፡ አድርጎ ፡ የሚተውበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ ይቻል ፡
ይሆን ?

—12—

ፍርሃት ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ መንገሡ ፡ የማይታበል ፡
እውነት ፡ ነው ። ሕገ ፡ ወጦች ፡ እየበዙ ፡ ሲሄዱ ፡ ሰዎች ፡
ምን ፡ አቅም ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላል ? የእያንዳንዱ ፡
ሰው ፡ ልብ ፡ በፍርሃት ፡ በሚጨነቅበት ፡ ጊዜ ፡ በአገሪቱ ፡
ውበት ፡ መርካት ፡ በዚያች ፡ ተቈጥባ ፡ በተሰጠችው ፡
የሰባ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ መደሰት ፡ በምድሩ ፡ ላይ ፡ የሚ
ንጣለለውን ፡ ፀሐይ ፡ እፎይ ፡ ብሎ ፡ መሞቅ ፡ ማን ፡ ይች
ላል ? ውበታቸው ፡ ወደ ፡ አስጊነት ፡ በተለወጠው ፡
ዛፎች ፡ ውስጥ ፡ በመዝናናት ፡ መንሸራሸርን ፡ ማን ፡
ይደፍራል ? በማይታወቅ ፡ ምሥጢር ፡ በተሸፈነው ፡
ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ማን ፡ እፎይ ፡ ብሎ ፡ መተኛት ፡ ይች

ላል ? ሁል ፡ ከመሰለው ፡ ለማይ ፡ ሥር ፡ ተጋድመው ፡ የከዋከብትን ፡ ውበት ፡ እየተመለከቱ ፡ ስለ ፡ ወደ ፡ ፊት፡ ኑሮአቸው ፡ የፍቅር ፡ ሕልም ፡ የሚያልሙት ፡ ፍቅረኞች ፡ ሁሉ ፡ የት ፡ አሉ ?

በመቶና ፡ በሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ድምፆች ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ የታያቸውን ፡ መፍትሔ ፡ ከማሰማት ፡ ቦዝነው ፡ አያውቁም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በጉዳዩ ፡ የተጨነቀ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከእነዚህ ፡ ድምፆች ፡ አንዳችም ፡ የተጨበጠ ፡ ምክር ፡ ለማግኘት ፡ አይችልም ። ምክንያቱም ፡ አንዱን ፡ ሲጠይቁት ፡ እንዲህ ፡ ካልሆነ ፡ ሲል ፤ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ያወራል ፤ ሦስተኛው ፡ ዘንድ ፡ ሲኬድ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያልታለመ ፡ መፍትሔ ፡ አምጥቶ ፡ ይሽውላችሁ ፡ ይላል ።

— በሰፈራችን ፡ የፖሊሶች ፡ ቊጥር ፡ አነስተኛ ፡ መሆኑ ፡ በጣም ፡ የሚያሳፍር ፡ ነው ። ጸጥታችን ፡ በሚገባ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተውን ፡ ባለሥልጣን ፡ በጥብቅ ፡ መጠየቅ ፡ ያስፈልጋል ።

— የዚህ ፡ አገር ፡ ጥቊሮች ፡ ጥረታቸውን ፡ በሙሉ ፡ የሚሠሙለት ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ የኑሮ ፡ ዓላማ ፡ በፊታቸው ፡ እንዲደቀን ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ከሚፈጽሙት ፡ ወንጀል ፡ ፍርሃት ፡ ልንገላገል ፡ እንችላለን ፡ ማለት ፡ ዘበት ፡ ነው ። ጥቊሮቹ ፡ መጠጥን ፡ ሽርሙጥናንና ፡ ወንጀልን ፡ የሚያዘወትሩት ፡ ሕይወታቸው ፡ ትርጉምና ፡ ዓላማ ፡ እንደሌለው ፡ ሲረዱ ፡ መሆኑ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። የፖሊስ ፡ ኃይል ፡ እንዲጠነክር ፡ መጠየቅ ፡ ለጊዜው ፡ ይረዳ ፡ እንደሆን ፡ እንጂ ፡ ዘላቂ ፡ የሆነ ፡ መፍትሔ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ።

— የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ መበርከት ፡ የጥቊሮች ፡ ወጣቶችን ፡ ወንጀል ፡ ሳይቀንሰው ፡ አይቀርም ።

— የትምህርት ፡ ቤት ፡ መበርከት ፡ ጮሌ ፡ የሆኑ ፡ ወንጀለኞችን ፡ በማበርከት ፡ ሁኔታውን ፡ የሚያብሰው ፡ አይመስልህም ?

— ለጥቊሮች ፡ የሚሆኑ ፡ የመዝናኛ ፡ ስፍራዎች ፡ ከነጮች ፡ ሰፈር ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ለምን ፡ አይሠራም ?

— መልካም ፤ ከሚኖሩበት ፡ ስፍራ ፡ መሃል ፡ አራዳ፡ ለመድረስ ፡ ከዚያም ፡ ተመልሰው ፡ ቤታቸው ፡ ለመግባት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ይወስድባቸዋል ? አንተስ ፡ ብትሆን ፡ ለአሽከርህና ፡ ለገረድህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የሰን በት ፡ ዕረፍት ፡ ትሰጣቸዋለህ ?

— እንዲህ ፡ ተከራክረን ፡ የምንዘልቀው ፡ አይመስለኝም ። በሉ ፡ ተውት ።

አዎን ፡ ከዚህም ፡ ከዚያም ፡ በመቶና ፡ በሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ድምፆች ፡ ይሰማሉ ። እንዱ ፡ ተነሥቶ ፡ እንዲህ ፡ ቢደረግ ፡ ይበጃል ፡ ሲል ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ ቢደረግ ፡ ነው ፡ የሚበጀው ፡ ይላል ። እንግዲህ ፡ የየትኛውን፡ ቃል ፡ አምኖ ፡ መቀበል ፡ ይቻላል ? ከነጮች ፡ ይልቅ ፡ የጥቊሮች ፡ ብዛት ፡ ከፍ ፡ ያለበትን ፡ የዚህችን ፡ አገር ፡ ሁኔታ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ መምራት ፡ ይቻላል ?

ውድ ፡ አገሬ ፡ ሆይ ፡ የፍርሃታችን ፡ ወራሽ ፡ ለሆኑት ፡ ገና ፡ ላልተወለዱት ፡ ሕፃናት ፡ አልቅሽላቸው ። ስለ ፡ ውበትሽ ፡ ስለ ፡ ልምላሜሽ ፡ በማሰብ ፡ በልባቸው ፡ ጥልቅ ፡ ፍቅር ፡ እንዳያድርባቸው ። ምንጮችሽና ፡ ጅረቶችሽ ፡ በጣቶቻቸው ፡ ሥር ፡ ኮለል ፡ እያሉ ፡ ሲወርዱ፡

እያዩ ፣ ከት ፣ ብለው ፣ እንዳይስቁ ። ፀሐይ ፣ ስትጠልቅ ፣ የተራራውንና ፣ የኮረብታውን ፣ የሸለቆውንና ፣ የሸንተረሩን ፣ በብርሃን ፣ መጥለቅለቅ ፣ እየተመለከቱ ፣ እንዳይተክዙ ። የአእዋፋትን ፣ ጥዑም ፣ ዜማ ፣ እየሰሙ ፣ መንፈሳቸው ፣ እንዳይረካ ። በተራሮችና ፣ በሸለቆዎች ፣ ውበት ፣ ልባቸው ፣ እንዳይማረክ ። ይህን ፣ ሁሉ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ፍርሃት ፣ ይነጥቃቸዋልና ። . . . እሪ ፣ በይ ፣ አገሬ ።

* * *

— ሚስተር ፣ ምሲማንጉ ?

— እንደምን ፣ ሰነበቱ ፣ ወይዘሮ ፣ እንድሌላ ?

— ሚስተር ፣ ሚስማንጉ ፣ ፖሊሶች ፣ ቤቴ ፣ ድረስ ፣ መጥተው ፣ የጓደኞዎን ፣ የኡምፉንዲሲውን ፣ ልጅ ፣ ሲፈልጉት ፣ ነበር ።

— ለምን ፣ ነበር ፣ የፈለጉት ?

— ለምን ፣ እንደሚፈልጉት ፣ አልገለጹልኝም ።

— ለከፉ ፣ ነገር ፣ ይሆን ፣ የፈለጉት ?

— ለደህና ፣ ነገር ፣ የፈለጉት ፣ አልመሰለኝም ፣ ኡምፉንዲሲ ። እኔም ፣ ፈርቼ ፣ አድራሻውን ፣ ሰጠኋቸው ። ወይዘሮ ፣ እምኬዚ ፣ ፪፯ ፣ ትዌንቲ — ሰርድ ፣ አቬኒው ፣ አለከሳንድራ ። ከፖሊሶቹ ፣ አንዱ ፣ ወይዘሮ ፣ እምኬዚማ ፣ የታወቀች ፣ የሌቦች ፣ ዋሻ ፣ የቀማኞች ፣ መሸሻ ፣ ናት ፣ ሲል ፣ ሰማሁት ።

— አድራሻውን ፣ ሰጠሻቸው ?

— አጠፋሁ ፣ እንዴ ፣ ኡምፉንዲሲ ? ፈርቼ ፣ ነው ፣ እኮ ።

— አላጠፋሽም ፣ ሕጉ ፣ የሚያዝዘው ፣ ነው ። ሕጉን ፣ ማክበር ፣ አለብን ።

ምሲማንጉ ፣ ሴትዮዋን ፣ አመስግኖ ፣ አሰናበታት ። ለጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ቆም ፣ ካለ ፣ በኋላ ፣ ዞር ፣ ብሎ ፣ ወደ ፣ ክፍሉ ፣ ገባ ። ለመሄድ ፣ በሩን ፣ ከፍቶ ፣ ወጣ ፣ ሲል ፣ ኩማሎ ፣ ወደ ፣ እርሱ ፣ ሲመጣ ፣ አገኘው ።

— መሄድህ ፣ ነው ፣ እንዴ ?

ምሲማንጉ ፣ ዝም ፣ አለ ። ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላም ፣—

— አዎን ፣ ልሄድ ፣ አስቤ ፣ ነበር ።

ለሁሉም ፣ ነገር ፣ እስቲ ፣ ገባ ፣ በል ፣—አለ ፣ ምሲማንጉ ።—ያቺ ፣ በቅርብ ፣ ቀን ፣ ቤትዋ ፣ ድረስ ፣ ሄደን ፣ የነበረው ፣ በኤንድ ፣ ስትራት ፣ የምትኖረዋ ፣ ወይዘሮ ፣ እንድሌላ ፣ አሁን ፣ በቅርቡ ፣ እኔ ፣ ዘንድ ፣ መጥታ ፣ ሄደች ። ፖሊሶች ፣ ልጁን ፣ ፍለጋ ፣ እቤትዋ ፣ ድረስ ፣ መምጣታቸውንና ፣ እርስዋም ፣ የወይዘሮ ፣ እምኬዚን ፣ አድራሻ ፣ የሰጠቻቸው ፣ መሆኑን ፣ ገልጻልኛለች ፣— አለው ።

ኩማሎም ፣ በሹክሹክታ ፣ ቃል ፣—

— ለምን ፣ ይሆን ፣ የሚፈልጉት ? አለ ።

— ለምን ፣ እንደሚፈልጉት ፣ አልታወቀም ። ድንገት ፣ ደረስህብኝ ፣ እንጂ ፣ ጉዳዩን ፣ ለማጣራት ፣ ወደዚያው ፣ ሹልክ ፣ ብዬ ፣ መሄዴ ፣ ነበር ።

— ለመሆኑ ፣ ብቻህን ፣ ልትሄድ ፣ ኖሮአል ?

— አዎን ፣ ብቻዬን ፣ ለመሄድ ፣ አስቤ ፣ ነበር ። አሁን ፣ ግን ፣ ጉዳዩን ፣ ከሰማኸው ፣ አብረን ፣ እንሄዳለን ። መቼም ፣ አውቶቡስ ፣ የለም ፤ በታክሲ ፣ እንሄዳለን ።

— የታክሲውን ፣ ኪራይ ፣ እኔ ፣ ኝ ፣ የምከፍለው ።

— ኧረ ፣ አትችለውም ፣ ብዙ ፣ ገንዘብ ፣ ነው ፣ የሚ
ያስፈልገው ።

ኩማሎም ፣ ከኮቱ ፣ ኪስ ፣ ውስጥ ፣ ቦርሳውን ፣ አው
ጥቶ ፣—

— ይኸው ፣ በቂ ፣ ገንዘብ ፣ አለኝ ፣—አለ ።

— ገንዘብ ፣ ካለህስ ፣ መልካም ። በል ፣ እንግዲያው፣
ታክሲ ፣ እንፈልግ ።

* * *

— ጤና ፣ ይስጥልኝ ፣ ወይዘሮ ፣ እምኬዚ ፣
ወይዘሮ ፣ እምኬዚ ፣ ገና ፣ ስታያቸው ፣ ቁጣ ፣ ብላ ፣
ወደ ፣ ኋላ ፣ ማፈግፈግ ፣ ጀመረች ።

— ፖሊሶች ፣ እንቺ ፣ ዘንድ ፣ መጥተው ፣ ነበር ?
ለመሆኑ ፣ ምን ፣ እንፈልጋለን ፣ አሉ ?

— ልጁን ፣ ነዋ !

— አሁንስ ፣ ወዴት ፣ ነው ፣ የሄዱት ?

— ወደ ፣ ሻንቲ ፣ ታውን ።

ነገሩ ፣ ደስ ፣ ያላላት ፣ ይመስል ፣ አሁንም ፣ ወደ ፣
ኋላዋ ፣ አፈገፈገች ።

— ከዚህ ፣ ቀደም ፣ አላውቅም ፣ ወዳልሽው ፣ አድራሻ፣
ነው ፣ የሄዱት ? አላት ፣ ምሲማንጉ ፣ በማፌዝ ።

— ታዲያ ፣ ምን ፣ አድርጊ ፣ ትሉኛላችሁ ፤ ፖሊ
ሶች ፣ ናቸው ። አድራሻውን ፣ አሁንም ፣ አላውቀውም ፤
እንዲያው ፣ ዝም ፣ ብዬ ፣ ብቻ ፣ ሻንቲ ፣ ታውን ፣ ነው ፣ ያል
ኳቸው ።

ሻንቲ ፣ ታውን ፣ እንደ ፣ ደረሱም ፣ ከዚህ ፣ ቀደም ፣ ጐብ
ኝተውት ፣ ወደ ፣ ነበረው ፣ አንድ ፣ ቤት ፣ ጎራ ፣ አሉ ።

— ፖሊሶች ፣ እዚህ ፣ መጥተው ፣ ነበር ?

— አዎን ፣ መጥተው ፣ ነበር ፣ ኡምፋንዲሲ ።

— ማንን ፣ እንፈልጋለን ፣ አሉ ?

— ልጁን ።

— ለምን ፣ ነበር ፣ የፈለጉት ?

— ለምን ፣ እንደ ፣ ፈለጉት ፣ አልነገሩኝም ፣ ኡምፋንዲሲ ።

— ወዴት ፣ የሄዱ ፣ ይመስልሻል ?

— ወደ ፣ ጠባይ ፣ ማረሚያው ።

ጠባይ ፣ ማረሚያው ፣ እንደ ፣ ደረሱ ፣ ከነጩ ፣ አስተ
ዳዳሪ ፣ ረዳት ፣ ጋር ፣ ተገናኙ ።

— ፖሊሶች ፣ እዚህ ፣ መጥተው ፣ ነበር ?

— ገና ፣ አሁን ፣ ነው ፣ የሄዱት ።

— ምን ፣ ነበር ፣ የፈለጉት ?

— ልጁን ፤ አቤሲሎም ፣ ኩማሎን ።

— ለምን ፣ ፈልገውት ፣ ነበር ?

— ለምን ፣ እንደ ፣ ፈለጉት ፣ አላውቅም ።

— ጉዳዩ ፣ የሚያሠጋ ፣ መሆን ፣ አለመሆኑን ፣ አታ
ውቅም ?

— በእውነቱ ፣ አላውቅም ፣ ኡምፋንዲሲ ።

— በኋላስ ፣ ወዴት ፣ ሄዱ ?

— ወደ ፣ ፒምቪል ፣ ወደ ፣ ልጅቱ ፣ መኖሪያ ።

— አሁን ፣ ነው ፣ የሄዱት ፣ አልከኝ ?

— አዎን ፣ ገና ፣ አሁን ፣ ነው ፣ የሄዱት ።

* * *

— ጤና ፣ ይስጥልኝ ፣ የእኔ ፣ ልጅ ።

— ጤና ፣ ይስጥልኝ ፣ ኡምፋንዲሲ ።

— ፖሊሶች ፡ መጥተው ፡ ነበር ?
— አዎን ፡ ለጥቂት ፡ ነው ፡ የሄዱት ።
— ምን ፡ እንፈልጋለን አሉ ?
— አቤሴሎምን ፤ እኔም ፡ ከቅዳሜ ፡ ወዲህ ፡ አላየ ሁትም ፡ ብዬ ፡ ነገርኳቸው ።
— ለምን ፡ ነበር ፡ የፈለጉት ? በማለት ፡ ኩማሎ ፡ የጭንቀት ፡ ድምፁን ፡ ጣራው ፡ እስኪናወጥ ፡ ድረስ ፡ አሰማ ።

ልጅቱም ፡ በፍርሃት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እያፈገፈገች ፡—

— እኔ ፡ አላውቅም ፡— አለች ።
ምሲማንጉ ፡ ወደ ፡ ልጅቱ ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡— ለመ ሆኑ ፡ የሚያሠጋ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ይመስልሻል ? አላት ።
— ኧረ ፡ ሳያሠጋ ፡ አይቀርም ፡ ኡምፉንዲሲ ። ለመ ሆኑ ፡ ነገሩ ፡ ምንድር ፡ ነው? አለችው ።
— ምኑን ፡ አውቀነው ፡— አላት ።
— የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጣጣ ፡ አያልቅም ፡— አለች ።
—የመጣ ፡ እንደሆን ፡ አስታውቂን ፡ ብለውኛል ። ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻለኛል ? አለች ።
— ማስታወቅ ፡ ነዋ ፡—አላት ፡ ምሲማንጉ ። —እንደ ፡ መጣ ፡ ለእኛም ፡ አስታውቂን ።

★ ★ ★

— ስንት ፡ ነው ፡ ሂሳቡ ? አለ ፡ ምሲማንጉ ።
— አሥራ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ኡምፉንዲሲ ። ኩማሎ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ቦርሳውን ፡ አወጣ ።
— ወጭውን ፡ ብንጋራ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡— አለ ፡ ምሲማንጉ ።

— ስለ ፡ መልካም ፡ ሐሳብህ ፡ አመሰግንሃለሁ ። ሂሳቡን ፡ ግን ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ መክፈል ፡ አለብኝ ፡ እያለ ፡ ከዚያች ፡ ከተገባደደችው ፡ ገንዘቡ ፡ አሥራ ፡ አምስቱን ፡ ብር ፡ አውጥቶ ፡ ለታክሲ ፡ ነጅው ፡ ሰጠው ።
— ምነው ፡ ትንቀጠቀጣለህ ?
— ብርድ ፡ ብርድ ፡ ብሎኛል ።

ምሲማንጉ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ፀሐይዋ ፡ ኩል ፡ ከመስለው ፡ የአፍሪቃ ፡ ሰማይ ፡ ብርሃንዋንና ፡ ሙቀት ዋን ፡ ታወርዶዋለች ።

— ወደ ፡ እኔ ፡ ክፍል ፡ እንሂድ ። እሳት ፡ አንድደን ፡ እንሞቃለን ። ያኔ ፡ ይሻልሃል ፡— አለው ።

—13—

የዚያን ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ ኩማሎ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ብቻውን ፡ ተቀምጦ ፡ የደረሰበትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያሰላ ሰል ፡ ጀመር ።

— ለካስ ፡ ምሲማንጉ ፡ ያለው ፡ እውነት ፡ ነው ። በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ በሚኖሩበት ፡ ትልቅ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ እንዲህ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀ ርም ፡ ብሎ ፡ መሥጋትና ፡ መጨነቅ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ? እርግጥ ፡ ነው ፡ ልጄ ፡ ታላቁ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የውኃ ፡ ሽታ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቶአል ። የደረሱበት ፡ ሳይታወቅ ፡ የሚቀሩስ ፡ ሞልተው ፡ የለም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ልጄ ፡ ደፍሮ ፡ ሰው ፡ ሊገድል ፡— ኑጭ ፡ ሊገድል — አይይረግም — ፈጽሞ ፡ አይይረግም ! ኧረ ፡ በምን ፡ ታስቦ ፡ አቤሴሎም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ተግባር ፡ አይፈጽምም !

ሐሳቡ ፡ ወደ ፡ ልጅትዋና ፡ ገና ፡ ወዳልተወለደው ፡ የልጁ ፡ ልጅ ፡ አመራ ። አቤሴሎም ፡ ተገኝቶ ፡ ሁለቱ ፡ በሥርዓት ፡ ቢጋቡ ፡ የፈረሰውን ፡ ቤት ፡ ማቃናት ፡ ይቻላል ። ምናልባት ፡ አቤሴሎም ፡ ልጅቱን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እንዶትሼኒ ፡ ይመለስና ፡ የሚወለደው ፡ ሕፃን ፡ በአያቶቹ ፡ እጅ ፡ ከአቤሴሎም ፡ የተሻለ ፡ መከባከብ ፡ እየተደረገለት ፡ ያድግ ፡ ይሆናል ።

እዎን ፡ ምሲማንጉ ፡ እውነት ፡ አለው ። በብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ በሚኖሩበት ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ልጄ ፡ ምን ፡ ደርሶበት ፡ ይሆን ? ብሎ ፡ በሐሳብ ፡ መባከን ፡ ከጥርጣሬና ፡ ካለማወቅ ፡ የሚመነጭ ፡ ጭንቀት ፡ ነው ።

—14—

ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ኩማሎ ፡ ከጌርትሩድ ፡ ልጅ፡ ጋር ፡ ሊጫወት ፡ ሲል ፡ ምሲማንጉና ፡ የጠባይ ፡ ማረሚያው ፡ አስተዳዳሪ ፡ ፈረንጅ ፡ አብረው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሲመጡ ፡ አየ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድንጋጤ ፡ የሠራ ፡ አካላቱን ፡ በድን ፡ አደረገው ። እንደ፡ ምንም ፡ ተበራቶ ፡ ሊቀበላቸው ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ወጣ ። በሥጋት ፡ የተሸነፈውን ፡ ፊታቸውን ፡ በማየት ፡ ሹክሹክታቸውንም ፡ በመስማት ፡ የበለጠውን ፡ ሰውነቱ ፡ ራደ ።

— እንደ፡ ምን ፡ ዋልክ ፡ ኡምፉንዲሲ ። እዚህ ፡ ግድም፡ የምንነጋገርበት ፡ ስፍራ ፡ ይገኝ ፡ ይሆን ? አለ ፡ ፈረንጁ ።

ኩማሎም ፡ እየተርበደበደ ፡— ወደ ፡ ማረፊያ ፡ ክፍል ፡ እንግባ ፡— አለ ።

ሰዎቹን ፡ አስገብቶ ፡ በሩን ፡ መለስ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ተክሎ ፡ ቆመ ።

— የፈራኸው ፡ አልቀረም ፡—አለ ፡ ፈረንጁ ።

ኩማሎም ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ እንዳቀረቀረ ፡ ወንበሩ ፡ ላይ ፡ ዘፍ ፡ ብሎ ፡ ወለሉን ፡ አተኵሮ ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

— መቼም ፡ ጠባዩን ፡ በሚገባ ፡ ሳያርም ፡ አወጣችሁት ፡ እንደሚሉን ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡—አለ ፡ ፈረንጁ ።— አንድ ፡ ነገር ፡ ሊረዳን ፡ ይችል ፡ ይሆናል ። አብረውት ፡ የነበሩት ፡ ሁለቱ ፡ ጓደኞቹ ፡ ጠባይ ፡ ማረሚያችን ፡ የገቡ፡ አይደሉም ። ጥይቱን ፡ የተኮሰው ፡ ግን ፡ አቤሴሎም ፡ ነው ።

ምሲማንጉም ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ስሜቱን ፡ ገታ ፡ አድርጎ ፡— አብረውት ፡ ከነበሩት ፡ ሁለት ፡ የግብር ፡ አበሮቹ ፡ አንዱ ፡ የወንድምህ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡— አለ ።

ኩማሎ ፡ ከመቀመጫው ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ እየተገላመጠ ፡ ክፍሉን ፡ ከቃኘ ፡ በኋላ ፡ ኩቱን ፡ ከተሰቀለበት ፡ አውርዶ ፡ አጠለቀ ። ባርኔጣውንም ፡ አንሥቶ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ አደረገ ፤ ከዘራውንም ፡ ፊልጎ ፡ ያዘ ። ወደ ፡ ምሲማንጉና ፡ ወደ ፡ ፈረንጁ ፡ ፊቱን ፡ አቅንቶ ፡ እጅ ፡ የሚነሣ ፡ ይመስል ፡ ጐንበስ ፡ አለ ። ምን ፡ እንዳላቸው ፡ ግን ፡ አልሰሙትም ።

— የት ፡ ለመሄድ ፡ አስበሃል ? አለ ፡ ምሲማንጉ ።

ፈረንጁም ፡ ቀበል ፡ አድርጎ ፡—

— ወደ ፡ ወጎኒ ፡ ቤቱ ፡ መሄድ ፡ ከፈለገ ፡ ቀደም ፡ አድርጌ ፡ ከሸሙ ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ተነጋገርሁላችሁ ፡ ለመ ግባት ፡ ፍቃድ ፡ ማግኘት ፡ ይችላል ፡—አለ ።

ኩማሎም ፣ በነገሩ ፣ የተስማማ ፣ ይመስል ፣ ራሱን ፣ አነቃነቀ ። እንደ ፣ ገናም ፣ ክፍሉን ፣ ገልመጥ ፣ እያለ ፣ ከተ መለከተ ፣ በኋላ ፣ ኮቱን ፣ መልበሱንና ፣ ባርኔጣም ፣ ማድ ረጉን ፣ ተገነዘበ ። ሁኔታው ፣ ግር ፣ ስላለው ፣ ኮቱንና ፣ ባርኔጣውን ፣ በእጁ ፣ ደባበስ ፤ ዞር ፣ ብሎም ፣ የያዘውን ፣ ከዘራ ፣ ተመለከተ ።

— መጀመሪያ ፣ ወደ ፣ ወንድሜ ፣ ዘንድ ፣ መድረስ ፣ እፈልጋለሁ ፣—አለ ።

— በደስታ ፣ እከተልሃለሁ ።

— እኔም ፣ ሚስዮን ፣ ማረፊያ ፣ ቤት ፣ እጠብቃችኋ ለሁ ፣—አለ ፣ ፈረንጁ ።

ኩማሎ ፣ ተንሥቶ ፣ ወደ ፣ ወንድሙ ፣ ሰረር ፣ ገሠ ገሠ ።

ምሲማንጉም ፣ ኮረብታው ፣ ጫፍ ፣ ላይ ፣ ደረሰበት ። በእጁ ፣ ደገፍ ፣ አድርጎ ፣ አብረው ፣ ሲጓዙ ፣ ከሕፃን ፣ ወይም ፣ ከገመምተኛ ፣ ጋር ፣ የሚሄድ ፣ ይመስል ፣ ነበር ። በመጨረሻም ፣ ከሱቁ ፣ ደረሱ ። ወደ ፣ በሩ ፣ እንደ ፣ ተቃ ረቡ ፣ ኩማሎ ፣ ቆም ፣ አለ ። ዓይኖቹ ፣ ተከድነው ፣ ከንፈ ሮቹ ፣ ይንቀጠቀጡ ፣ ነበር ። ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ ዓይ ኖቹን ፣ ገለጥ ፣ አድርጎ ፣ ወደ ፣ ምሲማንጉ ፣ ዞር ፣ አለ ፣—

— ግድ ፣ የለህም ፣ አትከተለኝ ። እኔው ፣ ራሴ ፣ እወ ጣዋለሁ ፣—አለ ።

ኩማሎ ፣ ወንድሙ ፣ ሱቁ ፣ ውስጥ ፣ ዘው ፣ ብሎ ፣ ገባ ። ወንድሙ ፣ ዮሐንስ ፣ የተቻለው ፣ ጌታ ፣ ይመ ስል ፣ ወንበሩ ፣ ላይ ፣ ተኮፍሶ ፣ ከሁለት ፣ ሰዎች ፣ ጋር ፣ ይነጋገር ፣ ነበር ።

— እንደምን ፣ አመሸህ ፣ ወንድሜ ?

— እንደምን ፣ አመሹ ፣ ግን ፣ ልበል ?

— እንደምን ፣ አመሸህ ፣ ወንድሜ ፣ የእናቴ ፣ ልጅ?

— አንተ ፣ ነህ ፣ እንዴ ? እንኳን ፣ ደህና ፣ መጣህ ። አረፍ ፣ በል ።

— ኩማሎ ፣ መለስ ፣ ቀለስ ፣ ብሎ ፣ እንግዶቹን ፣ ተመለከተ ።

— ጭውውታችሁን ፣ በማቋረጤ ፣ አዝናለሁ ። ብርቱ ፣ ጉዳይ ፣ ስለ ፣ ያዘኝ ፣ ነው ፣ የመጣሁት ።

— እንግዲያውስ ፣ ወዳጆቼ ፣ ይቅርታ ፣ አድርጉ ልኝ ።

እንግዶቹም ፣ ተሰናብተው ፣ ወጡ ።

— ለመሆኑ ፣ የመጣህበት ፣ ጉዳይ ፣ ተሳካልህ ? የጠ ፋውስ ፣ ልጅ ፣ ተመርምሮአል ? በሕፃንነቴ ፣ ያጠናሁ ትን ፣ የመጽሐፍ ፣ ቅዱስ ፣ ትምህርት ፣ የዘነጋሁ ፣ እንዳይ መስልህ ። አልፎ ፣ አልፎ ፣ እጠቀምበታለሁ ፣—አለ ፣ ዮሐ ንስ ፣ በገዛ ፣ ንግግሩ ፣ ከት ፣ ብሎ ፣ እየሳቀ ።

— አዎን ፣ መገኘትስ ፣ ተገኝቶአል ። ዳሩ ፣ ግን ፣ በመ ጽሐፍ ፣ ቅዱስ ፣ ውስጥ ፣ እንደ ፣ ተነገረለት ፣ አባካኝ ፣ ልጅ ፣ የተገኘ ፣ እንዳይመስልህ ። ነፍስ ፣ አጥፍተሃል ፣ ፈረንጅ ፣ ገድለሃል ፣ ተብሎ ፣ ወኅኒ ፣ ቤት ፣ ገብቶልሃል ።

— ሰው ፣ ገድሎ ? ቀልዱና ፣ ሳቁ ፣ ጥሎት ፣ ሄደ ። ነፍስ ፣ ማለት ፣ የሚያስቅ ፣ ነገር ፣ አይደለም ። የነጭ ፣ ሞት ፣ ደግሞ ፣ ቀላል ፣ ነገር ፣ አይደለም ።

— አዎን ፣ በነፍስ ፣ ግዳይ ፣ ተይዞአል ። ፖርክዎ ልድ ፣ በሚሉት ፣ ስፍራ ፣ የሰው ፣ ቤት ፣ ሰብሮ ፣ ገብቶ ፣ ሊዘርፍ ፣ ሲል ፣ የደረሰበትን ፣ አንድ ፣ ነጭ ፣ ገድሎአል ።

— ከአንድ ፣ ሁለት ፣ ቀን ፣ በፊት ፣ ተፈጸመ ፣ የተ

ባለው ፡ ወንጀል ፡ ነው ? አስታውሳለሁ ፤ ማክሰኞ ፡ ዕለት ፡ ነበር ።

— እዎን ፡ እሱው ፡ ነው ።

— አስታውሳለሁ ።

እዎን ፡ ሁናቴው ፡ ደህና ፡ ሁኖ ፡ ይታወሰው ፡ ጀመር። የራሱ ፡ ልጅና ፡ የወንድሙ ፡ ልጅ ፡ የማይለያዩ ፡ ጓደኛ ሞች ፡ መሆናቸው ፡ ይታወሰው ፡ ጀመር ። የግንባሩ ፡ ሥሮች ፡ እየተገታተሩ ፡ ሄዱ ፤ ፊቱን ፡ ላብ ፡ አሰመጠው ። መሃረቡን ፡ አውጥቶ ፡ ፊቱን ፡ ያባብስ ፡ ጀመር ።

— እዎን ፡ የተሠራው ፡ ወንጀል ፡ መዘዙ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

— የእኔም ፡ ጉድ ፡ አለበት ?

— እዎን ፡ እርሱም ፡ አለበት ።

ዮሐንስም ፡ እየደጋገመ ፡ አምላኬ ፡ አምላኬ ፡ አለ ። ኩማሎም ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ እጁን ፡ ወንድሙ ፡ ትከሻ ፡ ላይ ፡ አሳርፎ ፡—

— ሆዴ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አዝሎአል ። ለጊዜው ፡ ላወጣው ፡ አልሻም ። ብዙ ፡ ሥቃይ ፡ እንዳለብህ ፡ ግን ፡ ይሰማኛል ። አንድ ፡ ፈረንጅ ፡ ወደ ፡ ወጎኒው ፡ ቤት ፡ ሲወስደኝ ፡ ከሚስዮን ፡ ማረፊያው ፡ ቤት ፡ ይጠብቀኛል ። አንተም ፡ አብረኸን ፡ ብትሄድ ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ። ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ ሚስዮን ፡ ማረፊያው ፡ አመሩ ። ኩማሎ ፡ ፍርሃቱና ፡ ጭንቀቱ ፡ የበረደለት ፡ ይመስል ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ይራመድ ፡ ነበር ። ወንድሙ ፡ ግን ፡ ሰውነቱ ፡ ጐብጦ ፡ ፊቱ ፡ በጎዘንና ፡ በፍርሃት ፡ ተቆራምዶ ፡ ነበር ።

ሚስዮኑ ፡ ግቢ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ እንግሊዛዊው ፡ ቄስ ፡ አባ ፡ ቪንሴንት ፡ ኩማሉን ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ ጨብጠው ፡—

— በእኔ ፡ በኩል ፡ ግድ ፡ የለህም ፤ የተቻለኝን ፡ ያህል ፡ ልረዳህ ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ፡—አሉት ።

* * *

በግርማው ፡ አስፈሪ ፡ የሆነው ፡ የወጎኒ ፡ ቤቱ ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ በር ፡ ተከፈተላቸውና ፡ ገቡ ። ዮሐንስን ፡ አንድ ፡ የወጎኒ ፡ ቤት ፡ ዘበኛ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ እየመራ ፡ ወሰደው ። ፈረንጁና ፡ ኩማሎ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ አመሩ ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ልጁን ፡ ይዘውት ፡ መጡ ።

ኩማሎ ፡ የልጁን ፡ እጅ ፡ በሁለት ፡ እጆቹ ፡ ግጥም ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ቆመ ። እንባውም ፡ ከዓይኖቹ ፡ ዱብ ፡ ዱብ ፡ እያለ ፡ በመውረድ ፡ አቤሴሎም ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ያርፍ ፡ ጀመር ። ልጁ ፡ ደስታና ፡ ፈገግታ ፡ ፈጽሞ ፡ ርቆታል ። የወጎኒ ፡ ቤት ፡ እጅ ፡ ጠባቡ ፡ አንቆ ፡ የያዘው ፡ ይመስል ፡ ራሱን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ያወራጫል ።

— ልጄ ፡ አንጀቴ ።

— አቤት ፡ አባቴ ።

— እንደምንም ፡ ብዬ ፡ አገኘሁህ ።

— አዎን ፡ አባቴ ።

— ምን ፡ ይደረጋል ፡ ብቻ ፤ በጊዜ ፡ አልደረስኩልህም ።

ለዚህ ፡ ቃል ፡ ልጁ ፡ አይመልስም ። በዝምታው ፡ መጽናናት ፡ ያገኝበት ፡ ይመስል ፡— የፈሰሰ ፡ ውኃ ፡

ይታፈላል ? በግለት ፡ ልጁን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይጠይቀዋል ።
ልጁ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አይሰጠውም ። አሁንም ፡
እየደጋገመ ፡ የፈሰስ ፡ ውኃ ፡ ተመልሶ ፡ ይታፈላል ፡
ይለዋል ። ልጁም ፡ ጭንቅ ፡ ስላለው ፡ ራሱን ፡ ወዲህና ፣
ወዲያ ፡ ሲያቅለሰልስ ፡ ዓይኑ ፡ ከፈረንጁ ፡ ዓይን ፡ ጋር ፡ ግጥም ፡
አለ ። ወዲያው ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ መለስ ፡ አድርጎ ፡—

— አዎን ፡ አባባ ፡ የፈሰሰ ፡ ውኃ ፡ አይታፈስም ፡—
አለ ።

— አንተን ፡ ፍለጋ ፡ ያልደረስሁበት ፡ ስፍራ ፡ የለም ።

ልጁ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አይሰጠውም ። ኩማሎ ፡
ጨብጦ ፡ የያዘውን ፡ የልጁን ፡ እጅ ፡ ለቀቀ ። ልጁም ፡
በድን ፡ ይመስል ፡ እጁን ፡ ዝልፍልፍ ፡ እያደረገ ፡ ወደ ፡
ጐኑ ፡ አወረደው ። አባትና ፡ ልጅን ፡ የሚያራርቅ ፡ የሐ
ሳብ ፡ ግድግዳ ፡ በመካከላቸው ፡ መኖሩ ፡ በግልጽ ፡ ይታይ ፡
ነበር ።

— ልጄ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ አሰቃቂ ፡ ተግባር ፡ ለምን ፡
ፈጸምህ ?

— ለምን ፡ እንዳደረግሁት ፡ አላውቅም ።

— ሽጉጥ ፡ ታጥቀህ ፡ ወደዚያ ፡ ምን ፡ ወሰደህ ?

— ሽጉጥ ፡ የታጠቅሁት ፡ ራሴን ፡ ለመጠበቂያ ፡
ነበር ። ጆሐንስበርግ ፡ አደገኛ ፡ ስፍራ ፡ ነው ። አንድ ፡
ሰው ፡ ተጠንቅቆ ፡ ካልተቀመጠ ፡ ማንኛውም ፡ ጊዜ ፡
አደጋ ፡ ሊደርስበት ፡ ይችላል ።

— ሽጉጥ ፡ ታጥቀህ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ምን ፡ ወሰደህ?

ልጁ ፡ ግን ፡ ጥያቄውን ፡ በዝምታ ፡ አለፈው ።

— ለመሆኑ ፡ ሽጉጡ ፡ ተይዞአል ?

— አዎን ።

— አንተ ፡ መሆንህ ፡ ተረጋግጦአል ?

— አዎን ፡ ራሴ ፡ አምኜአለሁ ።

— ምን ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ ያመንኸው ?

— ፈረንጁ ፡ ድንገት ፡ ቢደርስብኝ ፡ ፊርቼ ፡ ተኩ
ስሁበት ፤ ልገድለው ፡ ግን ፡ አላሰብሁም ፡ ብዬ ፡ አሰረድ
ቻቸዋለሁ ።

— የአጎትህ ፡ ልጅስ ? አብሮህ ፡ የነበረው ፡ ሦስተ
ኛውስ ?

— ስለ ፡ እነርሱም ፡ ነግሬአቸዋለሁ ። እነርሱ ፡
ለጊዜው ፡ አብረውኝ ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ በፈረንጁ ፡ ላይ ፡
የተኮሰሁበት ፡ እኔው ፡ ነኝ ።

— ለመስረቅ ፡ ነበር ፡ የሄዳችሁት ?

ይህንንም ፡ ጥያቄ ፡ በዝምታ ፡ አለፈው ።

— ጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ ገብተህ ፡ አልነበረም ?

አቤሴሎም ፡ ያደረገውን ፡ ቦት ፡ ጫማ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡
እያሻሸ ፡—

— አዎን ፡ ገብቼ ፡ ነበር ፡—አለ ።

— ደህና ፡ አድርገው ፡ ይዘውህ ፡ ነበር ?

— አዎን ፡ በሚገባ ፡ ይዘውኝ ፡ ነበር ፡— አለ ።

— ታዲያ ፡ ውለታቸው ፡ ይኸው ፡ ነው ?

ልጁ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አይመልስም ። ፈረንጁም ፡
ነገሩ ፡ ምንም ፡ ውጤት ፡ እንደሌለው ፡ በመገንዘብ ፡ አባ
ትና ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ቆሙበት ፡ ጠጋ ፡ አለ ። በእንደዚህ ፡
ያለ ፡ አኳኋን ፡ አእምሮአቸውን ፡ ሲያሠቃዩ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡
ማየት ፡ የሚገባ ፡ መስሎ ፡ አልታየውም ።

— ሰማህ ፣ አቤሴሎም ?

— አቤት ።

— ያስያዝኩህን ፣ ሥራ ፣ ለምን ፣ ትተህ ፣ ሄድህ? ፈረንጁም ፣ ለጥያቄው ፣ መልስ ፣ ሊያገኝ ፣ አልቻለም ። ይህን ፣ ለመሰሉት ፣ ጥያቄዎች ፣ ምን ፣ መልስ ፣ ይገኝላ ቸዋል ?

— እንደዚያ ፣ ታስብላትና ፣ ትጨነቅላት ፣ የነበረ ችውን ፣ ልጅስ? ከጠባይ ፣ ማረሚያው ፣ እንድትወጣ ፣ ያደረግነው ፣ በእርስዋ ፣ ምክንያት ፣ አልነበረም ?

የአቤሴሎም ፣ ዓይኖች ፣ ዕንባ ፣ ቋጠሩ ። ሊያለቅስ ፣ ያሰበው ፣ ከድቶአት ፣ ለሄደው ፣ ልጅ ፣ ይሆን ? ወይስ ፣ ለራሱ ፣ ያለቅስ ፣ ይሆን ?

— አንድ ፣ ነገር ፣ ብቻ ፣ ልጠይቅህ ፣ ልጄ ፣—አለ ፣ ኩማሎ ። እስከ ፣ ዛሬ ፣ ድረስ ፣ በዚህ ፣ አገር ፣ ስትኖር ፣ አንድ ፣ ጊዜም ፣ ደብዳቤ ፣ ጽፈህልን ፣ ወይም ፣ በሰው ፣ በኩል ፣ ሰላምታ ፣ ልከህልን ፣ አታውቅም ። ከአጕል ፣ ጓደኞች ፣ ጋር ፣ የገጠምኸው ፣ ሥራህም ፣ ስርቆትና ፣ ዝር ፊያ ፣ የሆነው ፣ ለመሆኑ ፣ ለምንድር ፣ ነው ?

ልጁም ፣ አባቱ ፣ የተናገረውን ፣ ጫፍ ፣ በመያዝ ፣—

— ከአጕል ፣ ጓደኞች ፣ ጋር ፣ ገጥሜ ፣ ነው ፣—አለ ።

— ይህ ፣ በቂ ፣ መልስ ፣ አይደለም ፣—አለ ፣ ኩማሎ ። ነገሩ ፣ እንደማያዛልቀው ፣ በመገንዘብ ፣ — ከአጕል ፣ ጓደኞች ፣ ጋር ፣ መግጠምህ ፣ ይገባኛል ። አንተ ፣ ራስህ ፣ ይህን ፣ ተግባር ፣ ለመፈጸም ፣ እንዴት ፣ ቻልህ ?

— ሰይጣን ፣ ነው ፣ ያሳተኝ ፣— አለ ።

ሽማግሌው ፣ ኩማሎ ፣ ተዳክሞአል ። ልጁም ፣ ድካም ፣ ድካም ፣ ብሎታል ። ፈረንጁም ፣ ወደ ፣ እነርሱ ፣ ቀረብ ፣ ብሎ ፣—

— አሁንም ፣ ልጅቱን ፣ ልታገባ ፣ ትፈቅዳለህ ? ሲል ፣ አቤሴሎምን ፣ ጠየቀው ።

— አዎን ፣ ጌታዬ ።

— እስቲ ፣ ምን ፣ ማድረግ ፣ እንደሚቻል ፣ አስብበ ታለሁ ። አሁን ፣ ግን ፣ ጊዜው ፣ ስለ ፣ ደረሰ ፣ መሄድ ፣ አለ ብን ፣—አለ ።

— ሌላ ፣ ጊዜ ፣ ተመልሰን ፣ መምጣት ፣ እንችላለን ?

— አዎን ፣ ትችላለህ ። የጕብኝቱን ፣ ሰዓት ፣ ስንወጣ ፣ እንጠይቃለን ።

— ደህና ፣ ሁን ፣ ልጄ ።

— ደህና ፣ ሁን ፣ አባቴ ።

ኩማሎና ፣ ፈረንጁ ፣ ከወጎኒ ፣ ቤቱ ፣ ቅጥር ፣ ግቢ ፣ ወጡ ። ወጣ ፣ እንዳሉ ፣ ዮሐንስን ፣ አገኙት ። የቀድሞ ፣ ፍርሃቱና ፣ ድንጋጤው ፣ ገለል ፣ ያለለት ፣ ይመስላል ። ቁና ፣ ቁና ፣ እየተነፈሰ ፣—

— በፍጥነት ፣ ጠበቃ ፣ መፈለግ ፣ አለብን ፣— አለ ።

— ጠበቃ? የምን ፣ ጠበቃ ፣ ነው? የምን ፣ ገንዘብ ፣ በከንቱ ፣ ማባከን ፣ ነው ። ጉዳዩ ፣ እንደሆን ፣ ግልጽ ፣ ነው ። ምንም ፣ ዓይነት ፣ ጠበቃ ፣ ቢመጣ ፣ የተሠራውን ፣ ወን ጀል ፣ ሊያስተባብል ፣ አይችልም ።

— የትኛው ፣ ጉዳይ ? አለ ፣ ዮሐንስ ።

— ገና ፣ አልገባህም? እነዚህ ፣ ሦስት ፣ ልጆች ፣ ሰው ፣ የሌለበት ፣ መስሎአቸው ፣ አንድ ፣ ቤት ፣ ገቡ ። ማድ ፣

ቤት ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ አሽከር ፡ ደብድበው ፡ በሞ
ትና ፡ በሕይወት ፡ መካከል ፡ ተውት ። የቤቱ ፡ ጌታ ፡
ድምፅ ፡ ሰምቶ ፡ ወጣ ፡ ሲል ፡ — የእኔ ፡ ልጅ...የእንት ፡
አይደለም ፡ ... የእኔ ፡ ... የራሴ ፡ ልጅ ፡ ተኮሰበት ። ለኒ
ዚው ፡ የሰጠው ፡ ምክንያት ፡ ፈርቼ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነው ።
ጉዳዩ ፡ ይሽው ፡ ነው ። አሁንም ፡ አልገባህም ?

— መልካም፡መልካም ፡—አለ ፡ ዮሐንስ ።—ይህ ፡ ሁሉ ፡
የሰው ፡ ወሬ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሰዎች ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡
ያወሩት ፡ ነው ። ለመሆኑ ፡ አቤሴሎም ፡ ታሪኩን ፡ ያወ
ራልህ ፡ ሰዎች ፡ ባሉበት ፡ ነው ?

— እውነት ፡ ከሆነ ፡ በማንስ ፡ ፊት ፡ ቢወራ ፡ ምን ፡
አለበት ?

በዮሐንስ ፡ ገጽ ፡ የመዝናናት ፡ መልክ ፡ ይታይበ
ታል ።

— ምናልባት ፡ አንተ ፡ ጠበቃ ፡ አያስፈልግህ ፡ ይሆ
ናል ። ፈረንጁን ፡ ተኩሼ ፡ ገደልሁት ፡ ካለ ፡ ምንም ፡ ማድ
ረግ ፡ አይቻል ፡ ይሆናል ።

— አንተስ ፡ ጠበቃ ፡ ያስፈልገኛል ፡ ነው ፡ የምትለው ?

ዮሐንስ ፡ በፈገግታ ፡ የፈካ ፡ ፊቱን ፡ ለወንድሙ ፡
እያሳየ ፡—

—ልጄን ፡ በምሥጢር ፡ የሚያነጋግረው ፡ ጠበቃ ፡
ሳያስፈልገኝ ፡ አይቀርም ፡—አለ ።

ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በጉዳዩ ፡ ካሰበበት ፡ በኋላ ፡—
ስማኝ ፡ ወንድሜ ፤ ጉዳዩ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ የእኔ ፡ ልጅም ፡
ሆነ ፡ ሦስተኛው ፡ ወጣት ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡
ስፍራ ፡ ለመገኘታቸው ፡ ምንም ፡ ማስረጃ ፡ የለም ።

— ማስረጃ ፡ የለውም ? ልጄስ ? ማስረጃ ፡ አይሆንም ?
ዮሐንስ ፡ የወንድሙን ፡ ንግግር ፡ በማቋረጥ ፡—
— የአንተ ፡ ልጅ ፡ አሥሩን ፡ ቢያወራ ፡ ማን ፡ይቀ
በለዋል ፡—አለ ።

አንጋገሩ ፡ የለበጣ ፡ አልነበረም ። ይህን ፡ ሐሳብ ፡
ያቀረበው ፡ ካንጀቱ ፡ ነበር ።

ኩማሎ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ወንድሙ ፡ መለስ ፡ አደረገ ።
ወንድሙ ፡ ግን ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ሳይመለከተው ፡ መንገዱን ፡
ይቀጥል ፡ ጀመር ። ኩማሎም ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ እያዘገመ ፡
ከትልቁ ፡ የወጎኒ ፡ ቤት ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ወደ ፡ ጐዳናው ፡
አመራ ። — አደራህን ፡ አምላኬ ፡ አደራህን ፡ አትተ
ወኝ ፡—አለ ። ወዲያውም ፡ በእኔ ፡ በኩል ፡ ግድ ፡ የለም ፤
በሚቻለኝ ፡ሁሉ ፡ ልረዳህ ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ፡ ብለው ፡ የተናገ
ሩት ፡ የአባ ፡ ቪንሴንት ፡ ቃል ፡ ትዝ ፡ አለው ። ወደ ፡
እርሳቸው ፡ ለመሄድ ፡ ቍርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አደረገ ።

—15—

ኩማሎ ፡ በጎዘንና ፡ በትካዜ ፡ ወደ ፡ ማረፊያው ፡
ወደ ፡ ወይዘሮ ፡ ሊቴቤ ፡ ቤት ፡ ተመለሰ ። እመት ፡ ሊቴ
ቤና ፡ እኅቱ ፡ በዝምታ ፡ ተቀበሉት ፤ እርሱም ፡ ሊያነጋ
ግራቸው ፡ አልፈቀደም ። ከሕፃኑም ፡ ጋር ፡ የመጫወት ፡
ፍላጎት ፡ አልነበረውም ። ወደ ፡ ሚስዮኑ ፡ ማረፊያ ፡ ለመ
ሄድ ፡ የሚያስችለው ፡ ኃይልና ፡ ብርታት ፡ እስኪያገኝ ፡
ድረስ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ። ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተቀ
ምጠ ፡ ዕረፍት ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ የጠባይ ፡ ማረሚ
ያው ፡ አስተዳዳሪ ፡ ፈረንጅ ፡ በሩን ፡ አንኳኩቶ ፡ ገባ ።

— ኡምፉንዲሲ ።

— አቤት ?

— ስለ ፣ ጠበቃው ፣ ጉዳይ ፣ እንድንነጋገር ፣ ነው ፣ የመጣሁት ። እንደሚመስለኝ ፣ ጠበቃ ፣ ሳያስፈልግ ፣አይ ቀርም ። ጠበቃ ፣ ያስፈልጋል ፣ የምለውም ፣ እውነቱን ፣ ሸፍኖ ፣ ለማስቀረት ፣ ሳይሆን ፣ የወንድምህ ፣ አያያዝ ፣ አላምር ፣ ስላለኝ ፣ ነው ። የእርሱ ፣ ፍላጎት ፣ የራሱም ፣ ልጅ ፣ ሆነ ፣ ሦስተኛው ፣ ግብረ ፣ አበር ፣ ከአቤሴሎም ፣ ጋር ፣ አልነበሩም ፣ ብሎ ፣ ለመካድ ፣ ነው ። እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ሁኔታ ፣ ጉዳዩን ፣ እንዴት ፣ ወዳለ ፣ አቅጣጫ ፣ እንደሚመራው ፣ እኔና ፣ አንተ ፣ እናውቅም ። አንድ ፣ የሕግ ፣ ጠበቃ ፣ ግን ፣ የነገሩን ፣ አዝማሚያ ፣ ሊያውቅ ፣ ይችላል ። አንድ ፣ ሴላ ፣ ነገር ፣ ደግሞ ፣ አለ ። አቤሴሎም ፣ ሽንጥ ፣ የተኮሰሁት ፣ ፈረንጁን ፣ ለመግደል ፣ ሳይሆን ፣ ከድንጋጤ ፣ የተነሣ ፣ ነው ፣ ብሎአል ። ይህ ፣ ነገር ፣ እውነት ፣ መሆኑን ፣ ለፍርድ ፣ ቤት ፣ በሚገባ ፣ ለማስረዳት ፣ ጠበቃ ፣ ያስፈልጋል ።

— አዎን ፣ እውነት ፣ ነው ።

— ለመሆኑ ፣ የምታውቀው ፣ ጠበቃ ፣ አለ? ለምሳሌ ፣ የቤተ ፣ ክርስቲያናችሁ ፣ አባል ፣ የሆነ?

— እኔ ፣ የማውቀው ፣ ጠበቃ ፣ የለም ። ነገር ፣ግን ፣ አባ ፣ ቪንሴንት ፣ የሚያውቁት ፣ ጠበቃ ፣ አይጠፉም ።

ሁለቱም ፣ ተያይዘው ፣ ወደ ፣ ሚስዮን ፣ ማረፊያው ፣ አመሩ ። ከአባ ፣ ቪንሴንት ፣ ጋር ፣ ተገናኝተው ፣ በጉዳዩ ፣ ላይ ፣ ተነጋገሩበት ።

— በዚህ ፣ ጉዳይ ፣ ጥብቅና ፣ መቆም ፣ የሚችል ፣ አንድ ፣ ደህና ፣ ሰው ፣ አውቃለሁ ፣— አሉ ፣ አባ ፣ ቪንሴንት ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ከእውነት ፣ ውጭ ፣ ምንም ፣ ለማድረግ ፣ መሞ

ከር ፣ የለብንም ። ለመከላከያ ፣ የምናቀርበውም ፣ ልጁ ፣ ሽጉጡን ፣ የተኮሰው ፣ ፈረንጁን ፣ ለመግደል ፣ ሳይሆን ፣ ድንገት ፣ ስለ ፣ ደረሰበት ፣ ድንጋጤ ፣ ይዞት ፣ ነው ፣ የሚለውን ፣ ሐሳብ ፣ ነው ።

— የጋብቻውስ ፣ ነገር? አለ ፣ የጠባይ ፣ ማረሚያው ፣ አስተዳዳሪ ።

— ስለ ፣ ጋብቻውም ፣ ቢሆን ፣ ጠበቃውን ፣ እጠ ይቀዋለሁ ። በአሁኑ ፣ ሁኔታ ፣ የጋብቻውን ፣ ሥነ ፣ ሥር ዓት ፣ መፈጸም ፣ ይቻል ፣ እንደሆን ፣ አላውቅም ። ከተ ቻለ ፣ በደስታ ፣ አጋባቸዋለሁ ።

አባ ፣ ቪንሴንት ፣ እጃቸውን ፣ ኩማሎ ፣ ክንድ ፣ ላይ ፣ አረፍ ፣ አድርገው ፣— አይዞህ ፣ በርታ ፣ አሉት ፣ — መ ቸም ፣ ልጅህ ፣ በፈጸመው ፣ ወንጀል ፣ ከባድ ፣ ቅጣት ፣ እንደሚደርስበት ፣ የታወቀ ፣ ነው ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ጠበቃው ፣ ደህና ፣ አድርጎ ፣ ከተሟገተለት ፣ በሕይወቱ ፣ ላይ ፣አደጋ ፣ እንደማይደርስበት ፣ ተስፋ ፣ አለኝ ።

ፈረንጁ ፣ ወጣ ፣ እንዳለ ፣ ኩማሎና ፣ አባ ፣ ቪንሴንት ፣ ተቀምጠው ፣ ውይይታቸውን ፣ ቀጠሉ ።

— ይኸውልዎት ፣ ልፋቴና ፣ ድካሜ ፣ ሁሉ ፣ እን ዲህ ፣ መና ፣ ሆኖ ፣ ቀረ ፣— አለ ፣ ኩማሎ ።

— አዎን ፣ በጣም ፣ ያሳዝናል ።

— መጀመሪያ ፣ እንዲያው ፣ ዝም ፣ ብዬ ፣ በፍለጋ ፣ ብቻ ፣ ጊዜዬን ፣ አሳለፍሁ ። እያደር ፣ እያደር ፣ ሥጋት ፣ እየያዘኝ ፣ ሄደ ። የፍለጋው ፣ ጊዜ ፣ እየተራዘመ ፣ በሄደ በት ፣ መጠን ፣ ሥጋቱ ፣ ወደ ፣ ፍርሃት ፣ መለወጥ ፣ ጀመረ ። በመጨረሻውም ፣ ፍርሃቱ ፣ በልቤ ፣ ውስጥ ፣ ሥር ፣ ሰዶ ፣ ያሠቃየኝ ፣ ጀመር ። ልቤ ፣ ክፉኛ ፣ መሸበር ፣ የጀ

መረው ፡ አለክሳንድራ ፡ እያለሁ ፡ ነው ። ስውነቴ ፡ የተ
ርበደበደውና ፡ መቆም ፡ መቀመጥ ፡ የተሳነኝ ፡ ግን ፡ እር
ስዎ ፡ ቤት ፡ ሁነን ፡ እንድ ፡ ፈረንጅ ፡ በጥቁሮች ፡ እጅ ፡
የመገደሉን ፡ ወሬ ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ሽማግሌው ፡ ኩማሎ ፡ የክፍሉን ፡ ወለል ፡ ትክ ፡
ብሎ ፡ እየተመለከተ ፡ የሆዱን ፡ በሆዱ ፡ በማውጣትና ፡ በግ
ውረድ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አሳለፈ ። በመጨረሻውም ፡ ከራሱ ፡
ጋር ፡ የሚነጋገር ፡ ይመስል ፡— ምሲማንጉ ፡ በብዙ ፡ ሺህ ፡
የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ በሚኖሩበት ፡ ከተማ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡
ሥጋትና ፡ ፍርሃት ፡ እያስፈልግም ፡ ባለኝ ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡
ተጽናንቼ ፡ ነበር ፡— አለ ።

— በእንድ ፡ በኩል ፡ ተጽናንቼ ፡ ነበር ፤ በሌላ ፡
በኩል ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ አልተጽናናሁም ፡—አለ ፡ ኩማሎ ፡
ንግግሩን ፡ በመቀጠል ። — አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ከሺህ ፡
ሰዎች ፡ መካከል ፡ በእንዱ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ፡ የሚባለው ፡
አደጋ ፡ ደርሶብኛል ፡ ብዬ ፡ ማመን ፡ ያዳግተኛል ። እንዳ
ንዴ ፡ ነገሩን ፡ ቆም ፡ ብዬ ፡ ሳስበው ፡ እንዲያው ፡ ሕልም ፡
ነው ፡ ቅዠት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእውነት ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡
አይደለም ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ለቅጽበት ፡
ያህል ፡ ይፈጠራል ።

— እኔና ፡ ባለቤቴ ፡ በእንዶትሼኒ ፡ ስንኖር ፡ እንዲህ ፡
ያለው ፡ ነገር ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ሳይደርስብን ፡ አይቀርም ፡
የሚል ፡ ሥጋት ፡ ፈጽሞ ፡ አልነበረብንም ። የልጃችን ፡
ሁኔታ ፡ እንደዚህ ፡ እየከፋ ፡ መሄዱን ፡ ምነው ፡ ቀደም ፡
ብለን ፡ ሰምተነው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ !

— ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አንዳችም ፡ የነገረን ፡ የለም ።
በእንዶትሼኒ ፡ ሳለን ፡ አገር ፡ አማን ፡ ነው ፡ በሚል ፡ እም

ነት ፡ እንኖር ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡
በግልጽ ፡ ለመረዳት ፡ ችለናል ። ሁኔታውን ፡ ከመነሾው ፡
የተረዱ ፡ ነበሩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ጉዳዩ ፡ የሚያገባቸው ፡
መስሎ ፡ ስላልታያቸው ፡ የልጃችን ፡ የሕይወቱ ፡ እርምጃ ፡
ወደ ፡ ጥፋት ፡ ሲያመራ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በማየት ፡ እዩ ፡
ጀሐንስበርግ ፡ ይኸም ፡ ልጅ ፡ እኮ ፡ እንደ ፡ ቀሩት ፡ ልጆች ፡
መበላሸቱ ፡ ነው ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

— የድርቆሽ ፡ ክምር ፡ ሳር ፡ ላይ ፡ የተኛ ፡ እንድ ፡
ሰው ፡ አለ ። በአቅራቢያው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ታይቶ ፡
የማይታወቅ ፡ ታላቅ ፡ አውሎ ፡ ነፋስ ፡ ተነሥቶአል ። ከዚ
ያም ፡ መጨረሻው ፡ ጥፋትና ፡ አልቂት ፡ የሆነ ፡ መብረ
ቅና ፡ ነጐድጓድ ፡ ይከተላል ። ሰዎችም ፡ ወደየቤታቸው ፡
ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከአደጋ ፡ ወደሚጠለሉበት ፡ ስፍራ ፡
እግሬ ፡ አውጭኝ ፡ እያሉ ፡ በአጠገቡ ፡ ያልፋሉ ። በሳሩ ፡
ላይ ፡ መተኛቱን ፡ እያዩ ፡ ወይም ፡ ሳያዩ ፡ ቀርተው ፡ እን
ደሆን ፡ አይታወቅም — አይቀሰቅሱትም — እንዲ
ያው ፡ ዝም ፡ ብለውት ፡ ያልፋሉ ።

አባ ፡ ቪንሴንት ፡ ደጋግመው ፡ ወዳጂ ፡— አሉት ።

— አቤት ፡ አባቴ ?

— ጎዘን ፡ ከፍርሃት ፡ ይሻላል ፡— አሉ ፡ አባ ፡ ቪን
ሴንት ፡ ደጋግመው ። —ፍርሃት ፡ አድካሚና ፡ አሥጊ ፡ በሆነ ፡
ጉዞ ፡ ይመስላል ። ጎዘን ፡ ግን ፡ ወዳሰቡበት ፡ መድረስን ፡
ያመለክታል ።

— የት ፡ ነው ፡ የደረስሁት ? ሲል ፡ ጠየቀ ፡ ኩማሎ ።

— አውሎ ፡ ነፋስ ፡ ሲነሣ ፡ ሰዎች ፡ ለቤታቸው ፡
ይሠጋሉ ፡— አሉ ፡ አባ ፡ ቪንሴንት ፡ የዙሉዎችን ፡
ምሳሌ ፡ በመጥቀስ ። — ቤት ፡ ሲፈርስ ፡ አንድ ፡ መላ ፡
ይፈለግለታል ። ሰዎች ፡ የአውሎ ፡ ነፋስን ፡ ወይም ፡ የማ

ዕበልን ፣ ኃይል ፣ መቋቋሚያ ፣ ጕልበት ፣ ግን ፣ የላቸውም ። የፈረሰውን ፣ ቤት ፣ ግን ፣ መልሰው ፣ መሥራት ፣ ይች ላሉ ።

— በዚህ ፣ ዕድሜዬ ? አለ ፣ ኩማሎ ። — ጕልማሳና ፣ ጕበዝ ፣ በነበርሁበት ፣ ጊዜ ፣ በሠራሁት ፣ ቤት ፣ ላይ ፣ የደረሰውን ፣ እደጋ ፣ አይተውታል ። ወደ ፣ ፊት ፣ ደግሞ ፣ እንዴት ፣ ያለ ፣ ቤት ፣ ልሠራ ፣ ነው ?

— የእግዚአብሔርን ፣ ጥበብ ፣ ማስተዋል ፣ የሚችል ፣ የለም ፣ — አሉ ፣ አባ ፣ ቪንሴንት ፣ ተስፋ ፣ በቈረጠ ፣ አነጋገር ።

ኩማሎም ፣ ብስጭትና ፣ መመረር ፣ በሌለበት ፣ አኳኋን ፣ እየተመለከታቸው ፣ —

— እግዚአብሔር ፣ ፊቱን ፣ ያዞረብኝ ፣ ይመስለኛል ፣ — አለ ።

— እምን ፣ ለአንተ ፣ ይመስልህ ፣ ይሆናል ። ዳሩ ፣ ግን ፣ የማይደረግ — ፈጽሞ ፣ የማይታሰብ ፣ ነገር ፣ ነው ።

— ስለ ፣ ተናገሩት ፣ ቃል ፣ አመሰግነዎታለሁ ፣ — አለ ፣ ኩማሎ ፣ በትሕትና ፣ ቃል ። — ዳሩ ፣ ግን ፣ የገዛ ፣ ልጄ ፣ ፈጽሞ ፣ እንግዳ ፣ ሆናብኛል ። ልጠጋው ፣ እንኳን ፣ አልችልም ። ስለ ፣ በደላቸው ፣ ሰዎች ፣ ሲያዝን ፣ አይታይም ። በፈጸመው ፣ ክፉ ፣ ተግባር ፣ ጎፍረት ፣ አይሰማውም ። ከዓይኖቹ ፣ እንባ ፣ ይፈላል ፤ ዳሩ ፣ ግን ፣ የሚያለቅሰው ፣ ስለ ፣ ሠራው ፣ ወንጀል ፣ ሳይሆን ፣ ስለ ፣ ራሱና ፣ ስለሚደርስበት ፣ እደጋ ፣ ብቻ ፣ ነው ።

አባ ፣ ቪንሴንት ፣ ይህንን ፣ ሲሰሙ ፣ — አሁንስ ፣ በቃህ ! ብለው ፣ ጮሁ ። — አእምሮህን ፣ ልትስት ፣ ምንም ፣ አልቀረህም ። ሂድና ፣ ጸሎት ፣ አድርስ ፤ ከዚያም ፣ ጥቂት ፣ አረፍ ፣ በል ። በልጅህም ፣ ላይ ፣ እንደዚህ ፣ ፈጥ

ነህ ፣ አትፍረድበት ። እርሱንም ፣ ዝም ፣ የሚያሰኘው ፣ ፍርሃት ፣ ይሆናል ። አምን ፣ ጸሎት ፣ አድርስ ፣ ዕረፍት ፣ አድርግ ፣ ብዬሃለሁ ፣ — አሉት ።

— ጸሎትህ ፣ ቃላትን ፣ ብቻ ፣ ማንበልበል ፣ ቢሆን ፣ ዕረፍትህም ፣ በአልጋ ፣ ላይ ፣ ተንጋሎ ፣ ማፍጠጥ ፣ ቢሆን ፣ እንኳ ፣ ግድ ፣ የለም ። ለራስህ ፣ አትጸልይ ፣ የእግዚአብሔርንም ፣ መንገድ ፣ ለመረዳት ፣ መጸለይ ፣ የለብህም ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ የተሠወረ ፣ ምሥጢር ፣ ነው ። ለመሆኑ ፣ የሕይወትን ፣ መውጪያ ፣ መግቢያ ፣ ማን ፣ ሊያስተውል ፣ ይችላል? ሕይወት ፣ ራሱ ፣ አንድ ፣ ምሥጢር ፣ አይደለም? ራስህ ፣ መጽናናትን ፣ ለማግኘት ፣ ሳትችል ፣ ለአንዲት ፣ ምስኪን ፣ ልጅ ፣ የምታዝነውና ፣ የምትራራው ፣ ለምን ድር ፣ ነው? ይህስ ፣ አንድ ፣ ምሥጢር ፣ አይደለም? ከዚህ ፣ ዓለም ፣ ጣጣ ፣ በሞት ፣ መገላገል ፣ መሻሉን ፣ ስታውቅ ፣ ከዛሬ ፣ ነገ ፣ ይሻለኛል ፣ በማለት ፣ መኖርን ፣ የምትመርጠው ፣ ለምንድር ፣ ነው? ይህም ፣ አንድ ፣ ምሥጢር ፣ ነው ፣ እኮ ። ለጊዜው ፣ ስለ ፣ እነዚህ ፣ ነገሮች ፣ አታስብ ፣ አትጨነቅ ። ወደፊት ፣ ትደርስበት ፣ ይሆናል ። አሁን ፣ ግን ፣ ለጌርትሩድና ፣ ለልጅዋ ፣ ወደ ፣ ፊት ፣ የእቤሴሎም ፣ ሚስት ፣ ስለምትሆነዋ ፣ ልጅና ፣ ስለሚወለደው ፣ ሕፃን ፣ ጸልይ ። ለባለቤትህ ፣ በእንዶትሼኒ ፣ ላሉት ፣ ዘመዶችህና ፣ ወዳጆችህ ፣ ጸልይ ። ባልዋን ፣ ሞት ፣ ስለ ፣ ነጠቃት ፣ ሴት ፣ ያለ ፣ አባት ፣ ስለቀሩት ፣ ሕፃናት ፣ ጸልይ ። ሳያስበው ፣ ስለተገደለው ፣ ሰውዬ ፣ ነፍስ ፣ ጸልይ ። በዚህ ፣ ሚስዮን ፣ ማረፊያ ፣ ለምንገኘው ፣ በጠቅላላው ፣ ክፋት ፣ ያፈረሰውን ፣ ጎብረት ፣ ስብ ፣ መልሰው ፣ ለመገንባት ፣ ለሚደክሙት ፣ ሁሉ ፣ ጸልይ ። ለራስህ ፣ ጽናትና ፣ ብርታት ፣ ጸልይ ። መልካም ፣ ነገር ፣ ለሚሠሩት ፣ ፈረንጆች ፣

ጸልይ ። በጎ ፣ ነገር ፣ ለመሥራት ፣ እያሰቡ ፣ ፍርሃት ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ ስለሚላቸው ፣ ፈረንጆች ፣ ጸልይ ። ለልጅህና ፣ ለወደፊት ፣ ሕይወቱ ፣ ከመጸለይ ፣ ቸል ፣ አትበል ።

— እየሰማሁዎት ፣ ነኝ ፦— አለ ፣ ኩማሎ ፣ በትሕትና ፣ ቃል ።

— አልፎ ፣ አልፎ ፣ ተመስገን ፣ ማለትን ፣ አትዘንጋ ። ተመስገን ፣ ማለትን ፣ የመሰለ ፣ ነገር ፣ የለም ። የልጅህን ፣ ጉዳይ ፣ ለእኔና ፣ ለምሲማንጉ ፣ ብትተውልን ፣ የተሻለ ፣ ይመስለኛል ። አንተ ፣ በጉዳዩ ፣ ተስፋ ፣ ስለ ፣ ቈረጥህ ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ፈቃድ ፣ በግልጽ ፣ ለመረዳት ፣ የተሳነህ ፣ ይመስለኛል ። እንግዲህ ፣ ልጄ ፣ ሂድና ፣ ጸልይ ፤ ሂድና ፣ ዕረፍት ፣ አድርግ ።

አባ ፣ ቪንሴንት ፣ ኩማሎን ፣ እስከ ፣ ሚስዮኑ ፣ ግቢ ፣ በር ፣ ድረስ ፣ ሸኝተው ፣ ሲሰናበቱት ፦—

— እኔ ፣ በበኩሌ ፣ ሌሊትና ፣ ቀን ፣ ሳልል ፣ እጸልይልሃለሁ ። እንድረዳህ ፣ የምትሻው ፣ ሌላ ፣ ነገር ፣ ቢኖር ፣ አይዞህ ፣ አለሁልህ ፦— አሉት ።

—16—

ኩማሎ ፣ በማግሥቱ ፣ ማንንም ፣ ሳያስከትል ፣ በባቡር ፣ ተሳፍሮ ፤ ያችን ፣ ከአቤሴሎም ፣ ያረገዘችውን ፣ ልጅ ፣ ለመጠየቅ ፣ ወደ ፣ ፒምቪል ፣ ሄደ ።

ከብዙ ፣ ጊዜ ፣ መውጣት ፣ መውረድ ፣ በኋላ ፣ ቤቱን ፣ አግኝቶ ፣ በሩን ፣ ለማንኳኳት ፣ በቃ ። ልጅቱም ፣ በሩን ፣ ከፍታ ፣ ፍርሃትና ፣ ሥጋት ፣ በተቀላቀለበት ፣ ፈገግታ ፣ ተቀበለችው ።

— እንደምን ፣ ሰነበትሽ ፣ ልጄ ?

— እግዚአብሔር ፣ ይመስገን ፣ ደህና ፣ ነኝ ፣ ኡምፉ ንዲሲ ።

ለወጉ ፣ ያህል ፣ በቤቱ ፣ ውስጥ ፣ በሚገኘው ፣ ወንበር ፣ ላይ ፣ በጥንቃቄ ፣ አረፍ ፣ ብሎ ፣ የፊቱን ፣ ወዝ ፣ ያብስ ፣ ጀመር ።

— ስለ ፣ ባልሽ ፣ የሰማሽው ፣ ነገር ፣ አለ ? አላት ።

ፊትዋን ፣ ቅጭም ፣ አድርጋ ፣ — ምንም ፣ አልሰማሁም ፦— አለችው ።

— አጉል ፣ ወሬ ፣ ይገርልሽ ፣ ነው ፣ የመጣሁት ። ወጎኒ ፣ ቤት ፣ ገብቶአል ፦— አላት ።

— ወጎኒ ፣ ቤት ?

— አዎን ፣ በጣም ፣ አሰቃቂ ፣ የሆነ ፣ ወንጀል ፣ ሠርቶ ፣ ወጎኒ ፣ ቤት ፣ ገብቶአል ።

ልጅቱ ፣ ግን ፣ ነገሩ ፣ አልገባትም ። ሁኔታውን ፣ ፍርጥ ፣ አድርጎ ፣ እንዲነግራት ፣ ዓይን ፣ ዓይኑን ፣ ትመለከተው ፣ ጀመር ። ገና ፣ ልጅነትዋን ፣ ያልጨረሰች ፣ በመሆንዋ ፣ ነገር ፣ በቀላሉ ፣ የሚገባት ፣ አልነበረችም ።

— ይኸውልሽ ፣ ፈረንጅ ፣ ገድሎ ፣ ታስሮልሻል ።

ይህንን ፣ ስትሰማ ፣ ልጅቱ ፣ ፊትዋን ፣ በእጆችዋ ፣ እፍን ፣ አድርጋ ፣ ይዛ ፣ እሪ ፣ ብላ ፣ ጮኸች ። ኩማሎም ፣ የጀመረውን ፣ ነገር ፣ መቀጠል ፣ ተሳነው ። ከአንደበቱ ፣ የወጣው ፣ ቃል ፣ ባመረቀዘ ፣ ቍስል ፣ ውስጥ ፣ እንደ ፣ ገባ ፣ እሾህ ፣ ተሰማው ። ልጅቱም ፣ አንድ ፣ አሮጌ ፣ ሳጥን ፣ ላይ ፣ ተቀምጣ ፣ ወለሉን ፣ አቀርቅራ ፣ ስትመለከት ፣ እንባዋ ፣ በጉንጮችዋ ፣ ላይ ፣ ኮለል ፣ እያለ ፣ ይወርድ ፣ ጀመር ።

— ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ልነግርሽ ፡ የምችል ፡ አይመ ስለኝም ። ልጄ ፡ የፈረንጆቹን ፡ ጋዜጣ ፡ ማንበብ ፡ ትችያ ለሽ ?

— አዎን ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ አነባለሁ ።

— እንግዲያው ፡ ጋዜጣውን ፡ እዚሁ ፡ እተውልሻ ለሁ ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ልነግርሽ ፡ ያሰብሁት ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ነው ። አመጣጤ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ላነጋግርሽ ፡ ነበር ። ለመሆኑ ፡ ከልጄ ፡ ጋር ፡ መጋባት ፡ ትፈልጊያለሽ ?

— እርስዎ ፡ እንዳሉ ፡ ኡምፉንዲሲ ።

— እውነት ፡ ከልብሽ ፡ ፈቅደሽ ፡ ታገቢዋለሽ?

— አዎን ፡ ከልቤ ፡ ላገባው ፡ እፈቅዳለሁ ፡ ኡም ፉንዲሲ ።

— ፈቃድሽ ፡ መሆኑን ፡ ሳላረጋግጥ ፡ ከቤተ ፡ ሰቤ ፡ ጋር ፡ እንድትቀላቀዪ ፡ ማድረግ ፡ አልፈቅድም ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልጅቱ ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ ደስታ ፡ ባፈካው ፡ ፊትዋ ፡ እየተመለከተችው ፡—

— ፈቃደኛ ፡ ነኝ ፡— አለችው ።

እርሱም ፡ — የምንኖርበት ፡ ስፍራ ፡ እሩቅ ፡ ነው ፡— አላት ። — የእኛ ፡ አገር ፡ የመኪና ፡ ጉዳናዎች ፡ የኤሌክ ትሪክ ፡ መብራትና ፡ አውቶቡሶች ፡ የሉትም ። እኔና ፡ ባለ ቤቴ ፡ የምንኖረው ፡ ብቻችንን ፡ ነው ። ሰፈራችንም ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ነው ። ለመሆኑ ፡ ትውልድሽ ፡ ዙሉ ፡ ነው ?

— አዎን ፡ ኡምፉንዲሲ ።

— ወላጆችሽ ፡ የት ፡ ይኖራሉ?

— አባቴና ፡ እናቴ ፡ ከተፋቱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜአቸው ፡ ነው ። አባትና ፡ እናቴ ፡ ሁልጊዜ ፡ ይጣሉ ፡ ነበር ። የጠ

ባቸው ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ የእናቴ ፡ በየጊዜው ፡ መስ ከር ፡ ነበር ።

— አባትሽ ፡ እንቺንም ፡ እናትሽንም ፡ ትቶአችሁ ፡ ሄደ ፡ ማለት ፡ ነዋ? ለመሆኑ ፡ አባትሽ ፡ ትቶአችሁ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ አደረግሽ ?

— ወደ ፡ ሶፊያታውን ፡ ሄድሁ ።

— በሶፊያታውን ፡ የምትኖሪ ፡ ብቻሽን ፡ ነበር ?

— ብቻዬን ፡ አልነበረም ።

— ከመጀመሪያው ፡ ባልሽ ፡ ጋር ፡ ትኖሪ ፡ ነበራ? አለ ፡ ኩማሎ ፡ በለበጣ ፡ አነጋገር ።

ልጅቱም ፡ ንግግሩ ፡ የለበጣ ፡ መሆኑን ፡ ባለመገንዘብ ፡—

— አዎን ፡ ከመጀመሪያ ፡ ባሌ ፡ ጋር ፡ እኖር ፡ ነበር ፡— አለች ።

— እስከ ፡ ዛሬ ፡ ያገባሻቸው ፡ ባሎች ፡ ስንት ፡ ናቸው?

ልጅቱም ፡ ከአንገት ፡ በላይ ፡ በመሳቅ ፡— ከተቀ መጠችበት ፡ ሳጥን ፡ የቀረፈችውን ፡ ስንጣሪ ፡ እንጨት ፡ የምታፍተለትልበትን ፡ እጅዋን ፡ እየተመለከተች ፡—

— ሦስት ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ፡— አለች ።

— የመጀመሪያው ፡ ባልሽ ፡ ምን ፡ ሆነ?

— ወንጀል ፡ ሠርተሃል ፡ ተብሎ ፡ ተያዘ ፡ ኡምፉ ንዲሲ ።

— ሁለተኛውስ?

— እርሱም ፡ እንደዚሁ ።

— ሦስተኛውም ፡ አልቀረለትማ ፡— አለ ፡ ኩማሎ ፡ በመረረ ፡ አነጋገር ።

ከተቀመጠበት ፡ ብድግ ፡ እንዳለ ፡ አንድ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ተናግሬ ፡ ላስቀይማት ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡

በልቡ ፡ ውስጥ ፡ አደረበት ። ነገሩ ፡ የማይገባ ፡ መሆኑን ፡ በግስረዳት ፡ ሕሊናው ፡ ቢወቅሰውም ፡ እንኳ ፡ ለስሜቱ ፡ መገንፈል ፡ መሸነፍ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ፡ —

— ምስተኛው ፡ ባልሽም ፡ ተይዘልሻል ። የአሁኑስ ፡ በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ነው ፡ የተያዘው ። የቀሩት ፡ ባሎችሽስ? እንደዚሁ ፡ ነፍስ ፡ ገዳዮች ፡ ነበሩ? አላት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኩማሎ ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የርኅራኄ ፡ ስሜት ፡ ተፈጠረ ።

— ለመሆኑ ፡ ዕድሜሽ ፡ ስንት ፡ ነው? አላት ።

— እንጃ ፤ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ሳይሆነኝ ፡ አይቀርም ፡— አለችው ።

በርኅራኄ ፡ መንፈስ ፡ እየተመለከታት ፡— ልጄን ፡ አገባለሁ ፡ ያልሽ ፡ በእውነት ፡ ከልብሽ ፡ ነው? አላት ። እርስዋም ፡ እጁን ፡ ሙጭጭ ፡ አድርጋ ፡ ይዛ ፡—

— አዎን ፡ ከልቤ ፡ ነው ፡— አለችው ።

— እዚያ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ሄደሽ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ መኖር ፡ ቅር ፡ አይልሽም?

— ምንም ፡ ቅር ፡ አይለኝም ፡ ኡምፉንዲሲ ።

— ለመሆኑ ፡ ለጋብቻ ፡ የሚሆን ፡ ደህና ፡ ልብስ ፡ አለሽ ?

— አዎን ፡ ጥቂት ፡ ልብሶች ፡ አሉኝ ፡ ኡምፉንዲሲ ።

— ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በዚህ ፡ አካባቢ ፡ መኖር ፡ የሚያስፈልግሽ ፡ መስሎ ፡ አይታየኝም ። እኔ ፡ በምኖርበት ፡ አቅራቢያ ፡ ማረፊያ ፡ እፈልግልሻለሁ ።

ኩማሎም ፡ ተሰናብቶአት ፡ ከቤት ፡ ወጣ ። ልጅቱም ፡ እስከ ፡ ምድራፉ ፡ ድረስ ፡ ተከተለችው ። ጥቂት ፡

እርምጃዎች ፡ ሄድ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ልጅቱ ፡ ፈገግታ ፡ በተሞላ ፡ ዓይኖችዋ ፡ ስትመለከተው ፡ አየ ። ከዚያም ፡ ሥጋቱና ፡ ጭንቀቱ ፡ ቀለል ፡ እንዳለለት ፡ ሰው ፡ በመራመድ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ። አባ ፡ ቪንሴንት ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ እጸልይልሃለሁ ፡ ብለው ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ ድንገት ፡ ትዝ ፡ አለው ። ጥቂት ፡ እልፍ ፡ እንዳለ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ ። ልጅቱ ፡ አሁንም ፡ እርሱ ፡ ወደሚገኝበት ፡ አቅጣጫ ፡ ትመለከት ፡ ነበር ።

* * *

— እመት ፡ ሊቴቤ ፡ ከአቤሴሎም ፡ ያረገዘችውን ፡ ልጅ ፡ ታሪክ ፡ ሰምተዋል ፡ አይደለም? ወጎኒ ፡ ቤት ፡ ቢገባም ፡ ልጅህ ፡ ባሌ ፡ እንዲሆን ፡ ፈቃደኛ ፡ ነኝ ፡ ትላለች ። ጋብቻው ፡ ቢፈጸምም ፡ ባይፈጸምም ፡ እንዶትሼኒ ፡ ይዣት ፡ ሄጄ ፡ ዘመድ ፡ መካከል ፡ እንድትገላገል ፡ አስቤአለሁ ።

— ከመሄዳችሁ ፡ በፊት ፡ ወደዚህ ፡ ቢያመጡአት ፡ አይሻልም ፡ ኡምፉንዲሲ?

— እርሱማ ፡ ትልቅ ፡ ዕርዳታ ፡ ነው ፡ እመት ፡ ሊቴቤ ። — ውለታዎ ፡ ብቻ ፡ በዛብኝ ።

— ለዚህ ፡ ጊዜ ፡ ካልሆንን ፡ የመኖራችን ፡ ትርጉሙ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ኡምፉንዲስ ?

ኩማሎ ፡ ልጁን ፡ ለመጠየቅ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለ ውን ፡ የወህኒ ፡ ቤት ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ በር ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ እን ግዳ ፡ ማረፊያው ፡ ገባ ። ልጁም ፡ ተጠርቶ ፡ ቀረበ ። ከሥጋ ትና ፡ ከተስፋ ፡ መቁረጥ ፡ የተነሣ ፡ የተዝለፈለፈውን ፡ የል ጁን ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ጨበጠ ፡ እንባ ፡ እንቅ ፡ አደረገው ።

— ልጄ ፡ ለጤናህ ፡ ደህና ፡ ነህ?

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ፊቱን ፡ ካባቱ ፡ ፊት ፡ በማሸሽ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ያሉትን ፡ መስኩቶች ፡ በማፈራረቅ ፡ እየተ መለከተ ፡—

— እዎን ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ አባቴ ፡ — አለ ።

— ላማክርህ ፡ የምሻው ፡ እንድ ፡ ጉዳይ ፡ አለኝ ። ከልጅቱ ፡ ጋር ፡ ለመጋባት ፡ ቍርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አድርገሃል?

— አዎን ፡ ብንጋባ ፡ ፈቃዴ ፡ ነው ።

— አባ ፡ ቪንሴንት ፡ የተባሉ ፡ እንድ ፡ ወዳጄ ፡ አሉኝ ። ጋብቻው ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችልበትን ፡ መንገድ ፡ እንዲያ ጣሩና ፡ ሳይዘገይ ፡ እንዲፈጸም ፡ እጠይቃቸዋለሁ ። ከዚ ህም ፡ በቀር ፡ እኒሁ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ደህና ፡ ጠበቃ ፡ ሊፈ ልጉልህ ፡ ተስፋ ፡ ስጥተውኛል ።

በአቤሴሎም ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ የተስፋ ፡ ጭላንጭል ፡ ይታይበት ፡ ጀመር ።

— ጠበቃ ፡ ትፈልግ ፡ የለም?

— አዎን ፡ ጠበቃ ፡ ሳይረዳ ፡ አይቀርም ፡ ይላሉ ።

— ሁለቱ ፡ ልጆች ፡ አብረውህ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ለፖ ሊስ ፡ አስታውቀህ ፡ የለም?

— አዎን ፡ አስታውቄአለሁ ። በቀደምም ፡ ጠያቂ ውኝ ፡ ነግሬአቸዋለሁ ።

— ከነገርካቸው ፡ በኋላስ?

— ልጆቹ ፡ ከታሰሩበት ፡ ተጠርተው ፡ መጡ ።

— በኋላስ?

— ለፖሊሶቹ ፡ የተናገርሁትን ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ በቍጣ ፡ ገንፍለው ፡ በፖሊሶቹ ፡ ፊት ፡ ያልሠራነውን ፡ ነው ፡ የሚላክክብን ፡ እያሉ ፡ ይሰድቡኝ ፡ ጀመር ።

— ቀጥሎስ?

— አንተ ፡ የምትለውን ፡ ለመፈጸማችን ፡ ምን ፡ ማስረጃ ፡ አለህ? ሲሉ ፡ ጥያቄ ፡ አቀረቡልኝ ። እኔም ፡ የነበረኝ ፡ ማስረጃ ፡ የተናገርኩት ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ መሆ ኑን ፡ ድጋግሜ ፡ ማስታወቅ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ሌላ ፡ ሰው ፡ ሳይሆን ፡ እነዚሁ ፡ ሁለት ፡ ጓደኞቼ ፡ በዚያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አብረውኝ ፡ ነበሩ ።

ይህን ፡ ሲናገር ፡ እንባ ፡ እንቅ ፡ ያደርገው ፡ ጀመር ። ንግግሩንም ፡ በመቀጠል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። — ዓይናቸ ውን ፡ ድርቅ ፡ አድርገው ፡ የሚበቃቸውን ፡ ያህል ፡ ከሰ ደቡኝ ፡ በኋላ ፡— እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ለምን ፡ ትዋሻለህ? እያሉ ፡ ተሳለቁብኝ ።

— ጓደኞቼ ፡ ትላቸው ፡ አልነበረም?

— አዎን ፡ ጓደኞቼ ፡ ነበሩ ።

— አሁን ፡ ግን ፡ አጋለጡህ?

— መሆኑ ፡ ነው ።

— እንግዲህ ፡ በርታ ፡ ልጄ ። እንደ ፡ ምንም ፡ ብለን ፡ የሚረዳህን ፡ ጠበቃ ፡ እንፈልጋለን ። ጠበቃውም ፡ ቢገኝ ፡ ከእውነት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንዳትነግረው ።

— እውነቱን ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ የምነግረው ። ሳይዘገይ ፣ ብቻ ፣ ይምጣልኝ ።

— አታስብ ። ቶሎ ፣ ይመጣል ። አባ ፣ ቪንሴንት ፣ ሊጐበኙህ ፣ ይመጣሉ ። ጋብቻውም ፣ በቶሎ ፣ እንዲፈጸም ፣ እናደርጋለን ። ልጅቱም ፣ ያለችው ፣ ከእኔው ፣ጋር ፣ ነው ። ከእኔው ፣ ጋር ፣ ወደ ፣ እንዶትሼኒ ፣ ሄዳ ፣ እዚያው ፣ እንድትገላገል ፣ ተስማምተናል ።

— መልካም ፣ ነው ፣ አባባ ።

— እንግዲህ ፣ ለእናትህ ፣ ጻፍላት ።

— እሺ ፣ እጽፍላታለሁ ።

— በል ፣ እንባህን ፣ ጥረግ ።

የወጎኒ ፣ ቤቱ ፣ ዘበኛ ፣ አባትና ፣ ልጅ ፣ ወደሚነጋገሩበት ፣ ጠጋ ፣ ብሎ ፣ —አቤሴሎም ፣ አንድ ፣ ጠበቃ ፣ ሊያነጋግርህ ፣ መጥቶአል ። እርስዎ ፣ ግን ፣ ይሂዱ ፣ —አለ ።

* * *

ኩማሎ ፣ ወደ ፣ ሚስዮን ፣ ማረፊያው ፣ ተመልሶ ፣ ከአባ ፣ ቪንሴንት ፣ ጋር ፣ ሻይ ፣ ተጋብዞ ፣ እንዳበቃ ፣ ጠበቃው ፣ ሊያነጋግረው ፣ መጣ ።

— ሚስተር ፣ ኩማሎ ፣ በልጅህ ፣ ጉዳይ ፣ ጥብቅና ፣ ልቆም ፣ ወስኜአለሁ ፣— አለ ፣ ጠበቃው ፣ ለሁለቱም ፣ ሰዎች ፣ ሰላምታ ፣ እየሰጠ ።

— በጉዳዩም ፣ ልነጋገርበት ፣ የወሰንኩት ፣ ለእግዚአብሔር ፣ ስል ፣ ነው ። እንደ ፣ ተረዳሁት ፣ ከሆነ ፣ ጉዳዩ ፣ ቀላል ፣ ነው ። ልጁ ፣ መሣሪያ ፣ የተኮሰኩት ፣ ልገድል ፣ አስቤ ፣ ሳይሆን ፣ ከድንጋጤ ፣ የተነሣ ፣ ነው ፣ ብሎአል ።

ከእንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ ያለው ፣ የእኔ ፣ ተግባር ፣ ልጅህ ፣ የነገረኝ ፣ ሁሉ ፣ እውነት ፣ መሆኑን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ እንዲቀበለው ፣ መጣር ፣ ነው ። በተቻለኝ ፣ መጠን ፣ ልጁ ፣ ሽጉጡን ፣ የተኮሰው ፣ ለመግደል ፣ አስቦ ፣ ሳይሆን ፣ ከድንጋጤ ፣ የተነሣ ፣ መሆኑን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ እንዲቀበለው ፣ ማድረግ ፣ አለብኝ ። በዚህም ፣ ምክንያት ፣ ልጁ ፣ የሚናገረው ፣ እውነት ፣ አይደለም ፣ ብለው ፣ ለሚከራከሩት ፣ ሁለቱ ፣ ልጆች ፣ ጥብቅና ፣ ልቆምላቸው ፣ አልችልም ። ሚስተር ፣ ኩማሎ ፣ ነገሩን ፣ በግልጽ ፣ ተረድተኸው ፣ የለም?

— አዎን ፣ ተረድቼአለሁ ።

— ሚስተር ፣ ኩማሎ ፣ አሁን ፣ ከአንተ ፣ የምፈልገው ፣ ስለ ፣ ልጅህ ፣ ማንኛውንም ፣ ነገር ፣ በግልጽ ፣ እንድትነግረኝ ፣ ነው ። መቼ ፣ እንደ ፣ ተወለደ ፣ የትውልድ ፣ አገሩን ፣ በሕፃንነቱ ፣ ምን ፣ ዓይነት ፣ ልጅ ፣ እንደ ፣ ነበረ ፣ በልጅነቱ ፣ ታዛዥና ፣ እውነት ፣ የሚናገር ፣ መሆን ፣ አለመሆኑን ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ የመጣበትን ፣ ጊዜና ፣ ምክንያት ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ከመጣ ፣ በኋላ ፣ ምን ፣ ይሠራ ፣ እንደ ፣ ነበር ፣ ዘርዝረህ ፣ እንድታስረዳኝ ፣ እፈልጋለሁ ።

— መልካም ፣ ነው ፤ ሁሉንም ፣ ዘርዝሬ ፣ እነግርዎታለሁ ።

— ይህንን ፣ ሰውዬ ፣ በማግኘታችን ፣ እግዚአብሔርን ፣ ማመስገን ፣ አለብን ፣—አሉ ፣ አባ ፣ ቪንሴንት ፣ ጠበቃው ፣ ወጣ ፣ እንዳለ ። በጣም ፣ ችሎታ ፣ ያለው ፣ የታወቀ ፣ ሰው ፣ ነው ። ከዚህም ፣ በቀር ፣ ጥቁሮቹን ፣ ለመርዳት ፣ ብዙ ፣ ይታገላል ።

— ጉዳዩ ፣ እንዲህ ፣ በፍጥነት ፣ ስለ ፣ ተሳካ ፣ ከእግዚአብሔር ፣ ጋር ፣ እርስዎን ፣ ማመስገን ፣ አለብኝ ። ይሁን ፣

እንጂ ፣ አንድ ፣ የሚያሳስበኝ ፣ ነገር ፣ አለ ። ይገርው ፣ የመ
ጣሁት ፣ ገንዘብ ፣ እንደሆን ፣ ወደግለቁ ፣ ነው ።

— በጉዳዩ ፣ ጥብቅና ፣ የምቆመው ፣ ለእግዚአብሔር ፣
ስል ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ሲናገር ፣ አልሰማህም ፣ እንዴ? እንዳ
ለው ፣ ከሆነ ፣ ምንም ፣ አትከፍልም ፤ ብትከፍልም ፣ብዙ ፣
አይሆንም ።

— ጥብቅና፣ የሚቆምልኝ፣ ለእግዚአብሔር፣ ሲል ፣ ነዋ?

— አንድ ፣ ጠበቃ ፣ በዚህ ፣ ጉዳይ ፣ ለእግዚአብሔር ፣
ስል ፣ እንጋገርበታለሁ ፣ ካለ ፣ ምንም ፣ ገንዘብ ፣ አይጠ
ይቅም ፣ ማለት ፣ ነው ።

ኩማሎም ፣ የሚናገረው ፣ መላ ፣ ቅጡ ፣ ጠፋው ።

—እንዲህ ፣ ያለ ፣ ደግነት ፣ አይቼም ፣ አላውቅ ፣—
አለ ። ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ወዲህ ፣ እንባ ፣ በቀላሉ ፣ ያሸንፈው ፣
ስለ ፣ ነበር ፣ ከአባ ፣ ቪንሴንት ፣ ፊቱን ፣ ዞር ፣ አደረገ ።
አባ ፣ ቪንሴንትም ፣ በፈገግታ ፣ እየተመለከቱት ፣—በል ፣
እንግዲህ ፣ ደህና ፣ ሁን ፣— ብለው ፣ አሰናበቱት ።

ክፍል ፡ ሁለት ።

—18—

ከኢኮፖ ፣ ወደ ፣ ኮረብቶቹ ፣ የሚያመራ ፣ አንድ ፣
ውብ ፣ የሆነ ፣ መንገድ ፣ አለ ። ኮረብቶቹ ፣ በለምለም ፣
ሳር ፣ የተሸፈኑና ፣ ውበታቸው ፣ ዓይን ፣ እስኪታክት ፣
ቢታይ ፣ የማይጠገብ ፣ ነው ። ወደ ፣ ካሪስብሩክ ፣ የሚወ
ስደው ፣ መንገድ ፣ አሥር ፣ ኪሎ ፣ ሜትር ፣ ያህል ፣ ኮረ
ብቶቹን ፣ አቋርጦ ፣ ያልፋል ። ከዚያም ፣ አካባቢውን ፣
ጭጋግ ፣ ካልጋረደው ፣ በስተቀር ፣ በውበቱ ፣ ወደር ፣ የማ
ይገኝለትን ፣ ከአፍሪቃ ፣ ሸለቆዎች ፣ አንዱን ፣ አሸቄልቍሎ ፣
ማየት ፣ ይቻላል ። ግራ ፣ ቀኙ ፣ ሳርና ፣ ቁጥቋጦ ፣ ለብሶ
አል ። አልፎ ፣ አልፎ ፣ የብቸኝነት ፣ ስሜት ፣ ያለው ፣ ቲቲ
ሆያ ፣ የተባለችው ፣ ወፍ ፣ ድምፅ ፣ ይሰማል ። ከበታቹ ፣
የኡምዚምኩሉ ፣ ሸለቆ ፣ ጉዞውን ፣ ከድራከንስበርግ ፣
ወደ ፣ ባሕሩ ፣ ያመራል ። ከወንዙ ፣ ማዶ ፣ ብዙ ፣ ኮረብ
ቶች ፣ ተሰልፈዋል ። ከኮረብቶቹ ፣ ባሻገር ፣ የኢንጌሊና ፣
የምሥራቅ ፣ ግሪኳላንድ ፣ ተራሮች ፣ ይታያሉ ።

ሳሩ ፣ እንደ ፣ ልቡ ፣ ያደገ ፣ በመሆኑ ፣ የበቀለበትን ፣
መሬት ፣ ሸፍኖታል ። እንደ ፣ ሹሩባ ፣ የተጐነጐነው ፣ ሳር ፣
የዝናቡን ፣ ጠብታ ፣ እየተቀበለ ፣ የጭጋጉን ፣ እርጥበት ፣
እየሳበ ፣ መሬቱን ፣ ያርሰዋል ። ከመሬቱ ፣ የተረፈውም ፣
ፈላሽ ፣ ከወንዞቹና ፣ ከጅረቶቹ ፣ ጋር ፣ ይቀላቀላል ።
ሳሩን ፣ ያለ ፣ አግባብ ፣ ከብቶች ፣ አልጋጡትም ፤ ወይም ፣
ደግሞ ፣ ሰደድ ፣ እሳት ፣ ተነሥቶ ፣ መሬቱ ፣ አልተራቆተም ።

በጋራው ፣ ጫፍ ፣ ላይ ፣ ሁለት ፣ ኮረብቶች ፣ የሚያ
ዋስኑት ፣ ውብ ፣ የሆነ ፣ ትንሽ ፣ ሸለቆ ፣ አለ ። በዚያም ፣
እንድ ፣ መኖሪያ ፣ ቤትና ፣ ለጥ ፣ ያሉ ፣ የእርሻ ፣ ማሳዎች ፣
ይገኛሉ ። ባለቤቶቹ ፣ ላለፈው ፣ ላገደመው ፣ ሁሉ ፣ እን
ዲህ ፣ ያለ ፣ እርሻ ፣ በእካባቢው ፣ አይገኝም ፣ እያሉ ፣ ማው
ራት ፣ አይታክታቸውም ።

እርሻው ፣ ሐይ ፣ ፕሌስ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራል ። ባለ
ቤቱ ፣ ጀምስ ፣ ጃርቪስ ፣ ይባላል ። እርሻው ፣ ከእንዶ
ትሼኒና ፣ ከሉምዚምኩሉ ፣ ሸለቆ ፣ ከፍ ፣ ብሎ ፣ ይታያል ።

* * *

ጃርቪስ ፣ ፊቱን ፣ ቅጭም ፣ አድርጎ ፣ የማሳውን ፣
አስተራረስ ፣ ይመለከታል ። ጊዜው ፣ ከቀትር ፣ በኋላ ፣
ነበር ። በሰማዩ ፣ ገጽ ፣ ላይ ፣ አንዳችም ፣ የደመና ፣ ፍን
ጣቂ ፣ አይታይም ። በአካባቢው ፣ ዝናብ ፣ ዝናብ ፣ የማ
ይል ፣ አልነበረም ። ነገር ፣ ግን ፣ ምድሩ ፣ የዝናብ ፣
ጠብታ ፣ ካገኘ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ አልፎታል ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣
ማረሻው ፣ ክው ፣ ብሎ ፣ የደረቀውን ፣ አፈር ፣ እየፈረካከ
ሰው ፣ ያልፋል ። አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ደግሞ ፣ እንደ ፣ ብረት ፣
በጠጠረው ፣ የማሳው ፣ ገጽ ፣ ላይ ፣ ይንሸራተታል ።

ጃርቪስ ፣ እንድ ፣ ሁለት ፣ የማይሰሙ ፣ ቃላት ፣ጣል ፣
አድርጎ ፣ ውሻውን ፣ ተጣራ ። ከዚያም ፣ የእግር ፣ መንገ
ድዋን ፣ ይዞ ፣ ወደ ፣ ጋራው ፣ ጫፍ ፣ አሻቅቦ ፣ ወጣ ። ድር
ቅቱ ፣ ጋራው ፣ ላይ ፣ ገና ፣ አልደረሰም ። ምክንያቱም ፣
ሳሩ ፣ ከጭጋጉ ፣ የሚያገኘውን ፣ ርጥበት ፣ ይስብ ፣ ነበር ።
የነፋሱ ፣ ሽውታ ፣ ቅዝቃዜ ፣ ነበረው ። አሽቄልቀሉ ፣ የሚ

ታየው ፣ መሬት ፣ ላይ ፣ የበቀለው ፣ ሳር ፣ ግን ፣ ከንዳዱ ፣
የተነሣ ፣ ክው ፣ ብሎአል ። የእንዶትሼኒ ፣ ኮረብቶች ፣
እፅዋትና ፣ በቀልት ፣ የሚባል ፣ ነገር ፣ አይታይባቸውም ።
ጋራው ፣ ላይ ፣ የሚኖሩት ፣ ገበሬዎችም ፣ ሸለቆውንና ፣
ኮረብቶቹን ፣ እያነደደ ፣ በመሄድ ፣ ላይ ፣ የሚገኘው ፣ ድር
ቀት ፣ ከጊዜ ፣ ብዛት ፣ ሳይደርስብን ፣ አይቀርም ፣ በማለት ፣
ሥጋት ፣ ያውካቸው ፣ ነበር ።

መሬቱ ፣ በጐርፍና ፣ በጅረት ፣ እየተቦረቦረ ፣ አል
ቆአል ። ሰብሉም ፣ ከመከር ፣ ወደ ፣ መከር ፣ እያነሰ ፣ ይሄ
ዳል ። የአገሩ ፣ ነዋሪዎች ፣ አፈሩ ፣ በውኃ ፣ እየታጠበ ፣
እንዳይሄድ ፣ የሚያግደውን ፣ መከላከያ ፣ ግድብ ፣ መሥ
ራት ፣ ቢያውቁ ፣ ወይም ፣ ደግሞ ፣ ኮረብቶቹን ፣ አግድ
ሞሽ ፣ ማረስ ፣ ቢችሉ ፣ ሁኔታው ፣ እንዲህ ፣ እየከፋ ፣ ባል
ሄደም ፣ ነበር ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ኮረብቶቹ ፣ አንዳንድ ፣
ስፍራ ፣ አዘቅትነት ፣ ይሰማቸዋል ። አንዳንዶቹም ፣ ለመ
ታረስ ፣ የተፈጠሩ ፣ አይመስሉም ። ከዚህም ፣ በቀር ፣
በሬዎቹ ፣ ሰውነታቸው ፣ ያለቀ ፣ በመሆኑ ፣ ማረሻውን ፣
ቍልቍል ፣ መሳብ ፣ ይቀናቸዋል ። ሰዎቹም ፣ ስለ ፣ እርሻ ፣
ዘዴ ፣ አንዳችም ፣ ነገር ፣ የማያውቁ ፣ መሐይሞች ፣ናቸው ።

ተቀምጠው ፣ ሲያስቡት ፣ ችግሩ ፣ መፍትሔ ፣ የሚገ
ኝለት ፣ አይመስልም ። በቂ ፣ ትምህርትና ፣ ሥልጣኔ ፣ችግ
ሩን ፣ ያስወግደዋል ፣ የሚሉ ፣ አሉ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ከተማ
ሩት ፣ ወጣቶች ፣ መካከል ፣ እጁን ፣ እያለሳለሰ ፣ በከተማ ፣
ከመኖር ፣ በስተቀር ፣ ወደ ፣ ባላገር ፣ ተመልሶ ፣ እርፍ ፣
የጨበጠ ፣ አፈር ፣ የረገጠ ፣ የለም ። አለ ፣ የሚባለውም ፣
የእርሻ ፣ ሥራ ፣ የሚካሄደው ፣ በሽማግሌዎችና ፣ በአሮ
ጊቶች ፣ ነው ። ወጣቶቹ ፣ የከተማውና ፣ የማዕድኑ ፣

ኑሮ ፣ በቅቶአቸው ፣ ወደ ፣ ባላገር ፣ ሲመለሱ ፣ ፀሐይ ፣ ላይ ፣ እየተንቃቁ ፣ መጠጥ ፣ ከመጋትና ፣ የማይበጠስ ፣ ወጋቸውን ፣ ከማውጋት ፣ በስተቀር ፣ የሚረባ ፣ ነገር ፣ ሲፈጽሙ ፣ አይታዩም ።

ጃርቪስ ፣ ወደ ፣ ጋራው ፣ ጫፍ ፣ ሲያሻቅብ ፣ ይህንን ፣ ሐሳብ ፣ በአእምሮው ፣ ውስጥ ፣ ያወጣ ፣ ያወርድ ፣ ነበር ። ጋራው ፣ ጫፍ ፣ ላይ ፣ እንደ ፣ ደረሰ ፣ አንድ ፣ ድንጋይ ፣ ላይ ፣ አረፍ ፣ አለ ። ባርኔጣውን ፣ ከራሱ ፣ አውርዶ ፣ የነፋሱን ፣ ሽውታ ፣ ይቀበል ፣ ጀመር ። በጋራው ፣ ጫፍ ፣ ላይ ፣ ሆኖ ፣ የሚታየው ፣ ታላቁ ፣ የኡምዚምኩሉ ፣ ሸለቆ ፣ ውበት ፣ ፍጹም ፣ አይጠገብም ።

ጃርቪስ ፣ ከተቀመጠበት ፣ አሽቄልቅሎ ፣ ቢመለከት ፣ አንድ ፣ መኪና ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ ሲያመራ ፣ አየ ። ወዲያው ፣ የኢኮፖ ፣ ፖሊስ ፣ መኪና ፣ መሆኑን ፣ አወቀ ። የተለመደ ፣ የዘብ ፣ ተግባራቸውን ፣ ለማከናወን ፣ የመጡ ፣ ፖሊሶች ፣ ናቸው ፣ ብሎ ፣ አሰበ ።

የጃርቪስ ፣ ባለቤት ፣ የመኪናውን ፣ ድምፅ ፣ ሰምታ ፣ ከቤት ፣ ብቅ ፣ አለች ። ወዲያው ፣ ሁለት ፣ ፖሊሶች ፣ ከመኪናው ፣ ወረዱ ። ባለቤቱ ፣ እርሱ ፣ ወደሚገኝበት ፣ ኮረብታ ፣ ጫፍ ፣ ስታመለክት ፣ በማየቱ ፣ እርሱን ፣ ፍለጋ ፣ የመጡ ፣ መሆናቸው ፣ ገባው ። ቍልቍለቱን ፣ መውረድ ፣ ከመጀመሩ ፣ በፊት ፣ ታላቁን ፣ ሸለቆ ፣ ዞር ፣ ዞር ፣ እያለ ፣ በዓይኑ ፣ ቃኘ ። ነገር ፣ ግን ፣ አንዳችም ፣ የዝናብ ፣ ምልክት ፣ አልታየውም ። ከዚያም ፣ ውሻውን ፣ አስከትሎ ፣ ቍልቍል ፣ ጉዞውን ፣ ጀመረ ። የመንገዱ ፣ አጋማሽ ፣ ላይ ፣ ሲደርስ ፣ ፖሊሶቹ ፣ መኪናቸውን ፣ እርሻው ፣ ዳር ፣ አቁመው ፣ እርሱን ፣ ፍለጋ ፣ ዳገቱን ፣ ሲወጡ ፣ አየ ። እጁን ፣ አርገብግቦ ፣ ያለበትን ፣ አቅጣጫ ፣ ካመለከታቸው ፣ በኋላ ፣ አንድ ፣ ደንጊያ ፣ ላይ ፣ አረፍ ፣ ብሎ ፣ ይጠብቃቸው ፣ ጀመር ። ሻምበሉም ፣ ብቻውን ፣ ጃርቪስ ፣ ወዳለበት ፣ አመራ ።

— ታዲያስ ፣ ሻምበል ፣ ዝናብ ፣ ይዘውልን ፣ ነው ፣ የመጡት ?

ሻምበሉ ፣ ሽለቆውንና ፣ ባሻገሩ ፣ የሚታዩትን ፣ ተራራዎች ፣ ለመመልከት ፣ ዞር ፣ አለ ።

— ኧረ ፣ ምንም ፣ የዝናብ ፣ ምልክት ፣ አይታየኝም ።

— እኔም ፣ ምንም ፣ አልታይ ፣ ብሎኝ ፣ ትቼዋለሁ ። ለመሆኑ ፣ ዛሬ ፣ ምን ፣ አመጣዎት ?

ሁለቱም ፣ እጅ ፣ ለእጅ ፣ ተጨባበጡ ። ሻምበሉ ፣ ጃርቪስን ፣ ትክ ፣ ብሎ ፣ ተመለከተው ።

— ሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ አጉል ፣ ወሬ ፣ ይዤልዎት ፣ ነው ፣ የመጣሁት ።

— አጉል ፣ ወሬ ?

ጃርቪስ ፣ ልቡ ፣ ክፉኛ ፣ ተሸበረ ። ድንጋዩ ፣ ላይ ፣ አረፍ ፣ ብሎ ፣ —

— ስለ ፣ ልጄ ፣ ይሆን ? ሲል ፣ ጠየቀ ።

— አዎን ፣ ስለ ፣ ልጅዎ ፣ ነው ።

— ሞተ ፣ እንዳይሉኝ ።

— አዎን ፣ ሚስተር ፣ ጃርቪስ ።

ሻምበሉ ፣ ለጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ዝም ፣ ካለ ፣ በኋላ ፣ —

— ዛሬ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ በሰባት ፣ ሰዓት ፣ ተኩል ፣ ላይ ፣ በጥይት ፣ ተመትቶ ፣ ሞተ ፣ — አለ ።

ጃርቪስ ፣ ከመቀመጫው ፣ ብድግ ፣ አለ ። ከንፈሮቹ፣ እየተንቀጠቀጡ ፡— በጥይት ፣ ተመትቶ ፣ ሞተ? ማን ፣ ገደለው? ሲል ፣ ጠየቀ ።

— ሊሰርቅ ፣ ቤቱ ፣ የገባ ፣ አንድ ፣ ጥቁር ፣ ነው ፣ ይባላል ።

— እግዚአ ፣ መሐረን ፣ ክርስቶስ !

— በጣም ፣ አዝናለሁ ፣ ሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ክፉ ፣ ወሬ ፣ ይገልዎት ፣ በመምጣቴ ፣ በጣም ፣አዝ ናለሁ ።

ሻምበሉ ፣ እጁን ፣ ለጃርቪስ ፣ ዘረጋለት ። እርሱ ፣ ግን ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ድንጋዩ ፣ ላይ ፣ ዘፍ ፣ ብሎ ፣ እየደጋ ገመ ፡— እግዚአ ፣ መሐረን ፣ ክርስቶስ ! ይል ፣ ጀመር ።

— ሻምበል ፣ ወሬውን ፣ ለባለቤቴ ፣ አልነገሯትም ፣ አይደለም ?

— የለም ፣ አልነገርኳቸውም ።

ጃርቪስም ፣ ግንባሩን ፣ ቅጭም ፣ አድርጎ ፣ የልጁን ፣ መርዶ ፣ ለባለቤቱ ፣ የሚነግርበትን ፣ ዘዴ ፣ ያሰላስል ፣ ጀመር ።

— እርስዋ ፣ እንደ ፣ ሆነች ፣ ጠንካራ ፣ አይደለችም ፣ እንዴት ፣ እንደምትሆን ፣ አላውቅም ፡— አለ ።

— ሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ አስፈላጊውን ፣ ዕርዳታ ፣ እንዳደርግልዎት ፣ ከበላይ ፣ ታዝዤአለሁ ። ዛሬ ፣ ማታ ፣ በሚነሣው ፣ አውሮፕላን ፣ ብትሄዱ ፣ እኩለ ፣ ሌሊት ፣ ላይ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ለመግባት ፣ ትችላላችሁ ።

— እሺ ፣ በአይሮፕላን ፣ ብንሄድ ፣ ይሻላል ። እግ ዚአ ፣ መሐረን ፣ ክርስቶስ ።

ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ ጃርቪስና ፣ ሻምበሉ ፣ ቤት ፣ ደረሱ ።

— ጃርቪስ ፣ ምንድር ፣ ነው ፣ ትርምሱ ? አለች ፣ ባለቤቱ ።

— እባክሽ ፣ አንድ ፣ አጉል ፣ ወሬ ፣ ሰምቼአለሁ ። እስቲ ፣ ወደ ፣ ቢሮ ፣ ገባ ፣ እንበል ። ሻምበል ፣ ቴሌፎን ፣ ይፈልጉ ፣ የለም ? ያለበትን ፣ ያውቁታል ?

— አዎን ፣ ሚስተር ፣ ጃርቪስ ።

ሻምበሉ ፣ ቴሌፎኑ ፣ ወደሚገኝበት ፣ ስፍራ ፣ አም ርቶ ፣ ከፖሊስ ፣ ጣቢያው ፣ ጋር ፣ ስለ ፣ አውሮፕላኑ ፣ይነ ጋገር ፣ ጀመር ።

ወዲያውም ፣ በአንድ ፣ ጆሮው ፣ የቴሌፎን ፣ ማዳመ ጫውን ፣ ደቅኖ ፣ ሁለተኛው ፣ ጆሮው ፣ በጃርቪስ ፣ ባለ ቤት ፣ ዋይታና ፣ ለቅሶ ፣ እንዳይደነቍር ፣ በእጁ ፣ ግጥም ፣ አድርጎ ፣ ዘጋው ።

—19—

ጃርቪስና ፣ ባለቤቱ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ አይሮፕላን ፣ ጣቢያ ፣ እንደ ፣ ደረሱ ፣ አንድ ፣ ልጅግር ፣ ሰው ፣ ተቀበ ላቸው ።

— ሚስተር ፣ ጃርቪስና ፣ ባለቤታቸው?

— ነን ።

— ዮሐንስ ፣ ሐሪሰን ፣ እባላለሁ ። የሜሪ ፣ ወንድም ፣ ነኝ ። የምታስታውሱኝ ፣ አይመስለኝም ። ያኔ ፣ ስንገናኝ ፣

ገና ፣ ልጅ ፣ ነበርሁ ። ዕቃችሁን ፣ እኔ ፣ ልያዝ ። መኪና ፣ ውጭ፣ይጠብቀናል ።

ከአይሮፕላኑ ፣ ማረፊያ ፣ አዳራሽ ፣ ከመውጣታቸው ፣ በፊት ፣ ሐሪሰን ፣ ወደ ፣ ሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ መለስ ፣ ብሎ፣ የደረሰብን ፣ ጎዘን ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ከባድ ፣ እንደሆነ ፣ መግለጽ ፣ የሚያስፈልግ ፣ አይመስለኝም ። አርሰርን ፣ የመሰለ ፣ ሰው ፣ በሕይወቱ ፣ ገጥሞኝ ፣ አያውቅም ፣ — አለ ።

መኪናው ፣ ውስጥ ፣ ከገቡ ፣ በኋላ ፣ ሐሪሰን ፣ ንግግሩን ፣ በመቀጠል ፣ — ሜሪና ፣ ልጆቹ ፣ ከእናቴ ፣ ጋር ፣ ናቸው ። ለእናንተም ፣ እዚያው ፣ ማረፊያ ፣ አዘጋጅትን ላችኋል ።

— ለመሆኑ ፣ ሜሪ ፣ እንዴ ፣ ምንድር ፣ ናት?

— ድንጋጤው ፣ ገና ፣ አልለቀቃትም ፣ ሚስተር ፣ ጃርቪስ ። የሆነ ፣ ሆኖ ፣ እንደ ፣ ምንም ፣ በመበረታታት ፣ ላይ ፣ ነች ።

— ልጆቹስ ?

— የልጆቹ ፣ ነገር ፣ አይወራ ፣ ክፉኛ ፣ ተሳቅቀዋል። ሜሪም ፣ እነርሱኑ ፣ ስታጽናና ፣ ነው ፣ የምትውለው ።

የዚያን ፣ ዕለት ፣ ማታ ፣ የሜሪ ፣ አባት ፣ ሚቹ ፣ ጃርቪስ ፣ ከመሞቱ ፣ በፊት ፣ ጀምሮት ፣ ስለ ፣ ነበረው ፣ «የጥቁሮች ፣ ወንጀል ፣ እውነተኛ ፣ ምክንያት ፣ » ስለሚለው ፣ ጽሑፍ ፣ ለጃርቪስ ፣ አባት ፣ ነገረው ።

— እኔና ፣ ልጄ ፣ በጥቁሮች ፣ ጉዳይ ፣ የነበረን ፣ አስተያየት ፣ የተለያየ ፣ ነበር ። ቢሆንም ፣ ጽሑፉን ፣ ማየት ፣ አልጠላም ፣— አለ ፣ ጃርቪስ ።

— እኔና ፣ አባቴ ፣ የጥቁሮች ፣ ጉዳይ ፣ ሲነሣ ፣ ፈጽሞ፣ እንስማማም ፣ ነበር ፣—አለ ፣ ወጣቱ ፣ ሐሪሰን ።—ይሁን ፣ እንጂ ፣ ስለ ፣ ጥቁሮች ፣ ጉዳይ ፣ በሚገባ ፣ በማሰብና ፣ በመጠበብ ፣ በደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ ውስጥ ፣ እንደ ፣ አርሰር ፣ የደከመ ፣ የለም ። ብዙ ፣ ጊዜ ፣ በደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ ውስጥ ፣ ሊያስቡበትና ፣ ሊጨነቁበት ፣ የሚገባ ፣ ከጥቁሮች ፣ ጉዳይ ፣ የበለጠ ፣ ሌላ ፣ አሳሳቢ ፣ ነገር ፣ ምን ፣ አለ? እያለ ፣ ሲናገር ፣ እሰማ ፣ ነበር ።

ቀጥሎም ፣ ሐሪሰን ፣ ከየስፍራው ፣ ስለ ፣ መጣው ፣ የጎዘን ፣ መግለጫ ፣ ለጃርቪስ ፣ ያወራለት ፣ ጀመር ።

— መቹም ፣ የመጣው ፣ የጎዘን ፣ መግለጫ ፣ መልእክት ፣ ቀጥር ፣ ስፍር ፣ የለውም ፣— አለ ፣ ሐሪሰን ።

— ከጳጳሱ ፣ ከተጠባባቂው ፣ ጠቅላይ ፣ ሚኒስትር ፣ ከከንቲባውና ፣ ከታወቁ ፣ የአገሪቱ ፣ የፖለቲካ ፣ ሰዎች ፣ ከጥቁሮች ፣ ከክልሶች ፣ ከሕንዶችና ፣ ከአይሁዶች ፣ መልእክት ፣ ደርሶናል ። እንደሚባለውማ ፣ ለሚቀጥለው ፣ የፓርላማ ፣ ምርጫ ፣ የጥቁሮች ፣ እንደራሴ ፣ ሆኖ ፣ እንዲቀርብ ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ አጭተውት ፣ ነበር ።

— እርሱን ፣ አልሰማሁም ።

— ወደ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ስፍራዎች ፣ እየተዘዋወረ ፣ በጥቁሮቹ ፣ ይፈጸማል ፣ ስለሚባለው ፣ ወንጀል ፣ ለጥቁሮች ፣ በቂ ፣ ትምህርት ፣ ቤቶች ፣ መሥራት ፣ አስፈላጊ ፣ ስለ ፣ መሆኑ ፣ ንግግር ፣ ያደርግ ፣ ነበር ፣—አለ ፣ ሐሪሰን ።

ጃርቪስ ፣ ፒፓውን ፣ በዝግታ ፣ በትምባሆ ፣ እየሞላ ፣ ስለ ፣ ሚቹ ፣ ልጁ ፣ የሚወራውን ፣ ሲያዳምጥ ፣ ልክ ፣ ስለ ፣ አንድ ፣ የማያውቀው ፣ ሰው ፣ የሕይወት ፣ ታሪክ ፣ የሚሰማ ፣ መሰለው ።

— እኔ ፣ በበኩሌ ፣— አለ ፣ ሐሪሰን ፣ — ስለ ፣ ጥቂ ሮቹ ፣ ጉዳይ ፣ ያለውን ፣ ጽኑ ፣ አስተያየት ፣ ባውቅም ፣ እንኳ ፣ ስለ ፣ ልጆቹ ፣ በማሰብ ፣ በሚሠራው ፣ እንዲጠነ ቀቅ ፣ ከመምከር ፣ አልቦዘንሁም ።

ጃርቪስ ፣ ምንም ፣ ቃል ፣ አልመለሰም ። የልጁ ፣ ተማ ባርና ፣ ዝንባሌ ፣ ከራሱና ፣ ከባለቤቱ ፣ ማስተዋል ፣ ርቆ ፣ እንደ ፣ ነበር ፣ ገባው ። ጉዳዩን ፣ ባለቤቱ ፣ አውቃው ፣ ይሆን ፣ ምናልባት ፣ ታውቀው ፣ ይሆናል ። ለእርሱ ፣ ግን ፣ ነገሩ ፣ ፍጹም ፣ እንግዳ ፣ ስለ ፣ ሆነበት ፣ የሚሰጠው ፣ አስተያየት ፣ አልነበረውም ።

ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ ጃርቪስና ፣ ሐሪሰን ፣ ወደ የማረፊያቸው ፣ ተለያዩ ። ጃርቪስ ፣ ደረጃዎቹን ፣ ወጥቶ ፣ ወደ ፣ መኝታ ፣ ክፍሉ ፣ ደረሰ ። በሩን ፣ በቀስታ ፣ ከፍቶ ፣ መብራቱን ፣ ሳያበራ ፣ በጥንቃቄ ፣ ገባ ። የጨረቃዋ ፣ ብር ሃን ፣ በመስኮቱ ፣ በኩል ፣ ገብቶ ፣ ክፍሉን ፣ ወገግ ፣ አድ ርጎታል ። ጃርቪስም ፣ ወደ ፣ መስኮቱ ፣ ጠጋ ፣ ብሎ ፣ ውጭውን ፣ ይቃኝ ፣ ጀመር ። የሰማውን ፣ ሁሉ ፣ በአእ ምሮው ፣ ሲያወጣ ፣ ሲያወርድ ፣ ባለቤቱ ፣ ከተኛችበት ፣ ገልበጥ ፣ ብላ ፣ ጃርቪስ ፣ ብላ ፣ ተጣራች ።

— አትተኛም ፣ እንዴ ? እዚያ ፣ ቆመህ ፣ ምን ፣ ታስባለህ ።

ለጥያቄዋ ፣ መልስ ፣ እስኪያገኝ ፣ ድረስ ፣ ዝም ፣ አለ ። በመጨረሻውም ፣ — እባክሽ ፣ የሰማሁትን ፣ ሁሉ ፣ አሰ ላስላለሁ ፣— አላት ።

— ትመጣለህ ፣ ብዬ ፣ አላሰብኩም ፣ ነበር ፣— አለችው ። እርሱም ፣ ወደ ፣ ተኛችበት ፣ ፈጠን ፣ ብሎ ፣ እንደ ፣ ሄደ ፣ እጁን ፣ ጭብጥ ፣ አድርጋ ፣ ያዘችው ።

— እባክህ ፣ የሰማኽውን ፣ ሁሉ ፣ ንገረኝ ፣ አለችው ።

ጃርቪስም ፣ ስለ ፣ ልጁ ፣ የሰማውን ፣ ሁሉ ፣ አንድ ፣ ባንድ ፣ አጫወታት ።

— ልቤ ፣ ኩራት ፣ ይሰማዋል ፣— አለችው ።

— እንቺማ ፣ የልጅሽን ፣ ሁኔታ ፣ ቀድሞም ፣ ታውቂ ፣ ነበር ።

— አዎን ፣ አውቅ ፣ ነበር ። ለእናት ፣ የልጅዋን ፣ ሁኔታ ፣ ማወቅ ፣ አስቸጋሪ ፣ አይደለም ።

— እርሱስ ፣ እውነት ፣ ነው ። እንደ ፣ ሰማሁት ፣ ከሆነ ፣ የሚያስቀና ፣ ኑሮ ፣ ኑሮአል ።

ጃርቪስ ፣ አልጋው ፣ ጫፍ ፣ ላይ ፣ አረፍ ፣ አለ ። ሁለ ቱም ፣ ከሐሳባቸውና ፣ ከጉዘናቸው ፣ ጋር ፣ ይሟገቱ ፣ ጀመር ።

— ኑሮው ፣ የተለየም ፣ ቢሆን ፣ ስሜቱንና ፣ ዝንባ ሌውን ፣ ታውቂ ፣ ነበር ፣ ማለት ፣ ነዋ ፣ አላት ።

— አዎን ፣ አውቅ ፣ ነበር ።

— እኔ ፣ ሳላስተውለው ፣ በመቅረቴ ፣ በጣም ፣ አዝ ናለሁ ።

ቀጥሎም ፣ ወደ ፣ ጆሮዋ ፣ ጠጋ ፣ ብሎ ፣— እንዲህ ፣ ያለ ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ያለው ፣ ሰው ፣ ይወጣዋል ፣ ብዬ ፣ አላ ሰብኩም ፣ ነበር ፣— አላት ።

እርሰዋም ፣ ወገቡን ፣ ጥምጥም ፣ አድርጋ ፣ ይዛ ፣ ትንሰቀሰቅ ፣ ጀመር ።

ንግግሩን ፣ በሹክሹክታ ፣ በመቀጠል ፣ — አሁንም ፣ የማይገባኝ ፣ እንድ ፣ ነገር ፣ አለ ። ይህ ፣ አደጋ ፣ ከሰዎች ፣ መካከል ፣ እርሱን ፣ መርጦ ፣ ለምን ፣ ቀሠፈው ? አላት ።

እርስዋም ፣ እንደ ፣ ተኛች ፣ ሁኔታውን ፣ በልብዋ ፣ ታሳ
ላስል ፣ ጀመር ። ጎዘኑም ፣ አንጀትዋን ፣ እርር ፣ አደረገው ።
ወደ ፣ ጃርቪስ ፣ መለስ ፣ ብላ ፣— እባክህ ፣ ትንሽ ፣ ለመ
ተኛት ፣ እንሞክር ፣— አለችው ።

—20—

ጃርቪስ ፣ ልጹ ፣ ቢሮ ፣ ውስጥ ፣ በሚገኘው ፣ ወን
በር ፣ ላይ ፣ ተቀምጦ ፣ ግራ ፣ ቀኙን ፣ ይቃኝ ፣ ጀመር ።

በልጹ ፣ እጅ ፣ የተጻፉ ፣ ብዙ ፣ ወረቀቶች ፣ በጠረ
ጴዛው ፣ ላይ ፣ ተከምረዋል ። ከወረቀቶቹ ፣ በአንደኛው ፣
ላይ ፣ የአንድ ፣ ዐረፍተ ፣ ነገር ፣ መጨረሻ ፣ ቃላት ፣ በሌ
ላው ፣ ወረቀት ፣ ላይ ፣ ደግሞ ፣ ገና ፣ ያልተፈጸመ ፣ ዐረ
ፍተ ፣ ነገር ፣ በማግኘቱ ፣ ተከታታዮቹን ፣ ወረቀቶች ፣ለመ
ፈለግ ፣ ጽሑፎቹን ፣ ያገላብጥ ፣ ጀመር ። ያሰበውን ፣ ለማ
ግኘት ፣ ባለመቻሉም ፣ በእጹ ፣ ያሉትን ፣ ያነብ ፣ ገባ ።

« . . . የሚገባ ፣ ነበር ። ወደ ፣ ደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ በመ
ጣን ፣ ጊዜ ፣ የፈጸምነው ፣ ተግባር ፣ የሚገባ ፣ ነበር ። የአ
ገሪቱን ፣ የተፈጥሮ ፣ ሀብት ፣ ለማደርጀት ፣ ለጊዜው ፣ ባገ
ኘነው ፣ ጉልበት ፣ መጠቀማችን ፣ የሚገባ ፣ ነበር ። ልዩ ፣
ሙያ ፣ የሚያስፈልገውን ፣ ሥራ ፣ ሙያ ፣ የሌላቸው ፣ ሠራ
ተኞች ፣ እንዲሠሩት ፣ ማድረጋችን ፣ የሚገባ ፣ ነበር ።
ዳሩ ፣ ግን ፣ ልዩ ፣ ሙያ ፣ ለማያስፈልገው ፣ ሥራ ፣ ሲባል ፣
ሰዎችን ፣ ሙያ ፣ እንዳይማሩ ፣ ማድረግ ፣ የሚገባ ፣ አይ
ደለም ።

«ወርቅ ፣ በተገኘ ፣ ጊዜ ፣ ወርቁን ፣ ቆፍረው ፣ የሚ
ያወጡ ፣ ሠራተኞች ፣ ከየባላገሩ ፣ መልምለን ፣ ወደ ፣ማዕ
ድኑ ፣ ስፍራ ፣ ማምጣታችን ፣ የሚገባ ፣ ነበር ። ለማዕድኑ ፣
ሠራተኞች ፣ መኖሪያ ፣ የሚሆኑ ፣ እፍግፍግ ፣ መንደሮች ፣
መሥራታችንም ፣ የሚገባ ፣ ነበር ። ወደ ፣ ወርቅ ፣ ቆፋ
ሪዎቹ ፣ መንደር ፣ ሴቶችና ፣ ሕፃናት ፣ እንዳይደርሱ ፣ማድ
ረጋችን ፣ የሚገባ ፣ ነበር ። በዚያን ፣ ጊዜ ፣ የተፈጸመው ፣
ማንኛውም ፣ ነገር ፣ ለሙከራ ፣ በመሆኑ ፣ የሚገባ ፣ ነበር ።
አሁን ፣ እንደ ፣ ተረዳነው ፣ ከሆነ ፣ ግን ፣ ሲፈጸም ፣ የሚ
ታየው ፣ አብዛኛው ፣ ነገር ፣ የሚገባ ፣ አይደለም ። የባልና ፣
የሚስት ፣ ተለያይቶ ፣ መኖር ፣ ለቤተ ፣ ሰብ ፣ ጠንቅ ፣ መሆ
ኑን ፣ እያወቅን ፣ ባል ፣ ከሚስቱ ፣ ሕፃናት ፣ ከወላጆቻ
ቸው ፣ ተነጥለው ፣ እንዲኖሩ ፣ ማድረጋችን ፣ የሚገባ ፣
አይደለም ።

«የሠራተኞችን ፣ የኑሮ ፣ ደረጃ ፣ እያሻሻለ ፣ የሚ
ሄድ ፣ ከሆነ ፣ ማንኛውንም ፣ ዓይነት ፣ የተፈጥሮ ፣ ሀብት ፣
ማደርጀት ፣ የሚገባ ፣ ነው ። ነገር ፣ ግን ፣ ለሠራተኞች ፣
ኑሮ ፣ መሻሻል ፣ የማይረዳ ፣ ማንኛውንም ፣ የተፈጥሮ ፣
ሀብት ፣ እንዲደረጅ ፣ ማድረግ ፣ ተገቢ ፣ አይደለም ። የሠ
ራተኞችን ፣ የኑሮ ፣ ደረጃ ፣ መሻሻል ፣ አንቆ ፣ የሚይዝ ፣
ከሆነ ፣ የወርቅ ፣ ማዕድንን ፣ ማደርጀት ፣ ፋብሪካዎችን ፣
ማቋቋም ፣ የእርሻን ፣ ሥራ ፣ ማስፋፋትም ፣ ቢሆን ፣ተገቢ ፣
አይደለም ። በሌሎች ፣ ሰዎች ፣ ኪሣራ ፣ የግል ፣ ሀብትን ፣
ማደርጀትም ፣ ተገቢ ፣ አይደለም ። ይህን ፣ የመሰለው ፣
አድራጎት ፣ አቅም ፣ ያነሳቸውን ፣ በግላጭ ፣ መዝረፍ ፣
ይባላል ። ከዚህ ፣ ቀደም ፣ እንፈጽመው ፣ የነበረው ፣ ማን
ኛውም ፣ ተግባር ፣ በጥቁሮች ፣ ሕይወትና ፣ ኑሮ ፣ ላይ ፣

ሊያስከትለው፡ የሚችለውን ፡ ነገር ፡ ባለማወቃችን ፡ ምና
ልባት ፡ የሚገባ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አሁን ፡ ግን ፡ ተግ
ባራችን ፡ ለጥቁሮች ፡ ጎብረተ ፡ ሰብ ፡ መፋለስ ፡ ለትዳሬ
ቸው ፡ መፍረስ ፡ ለደኅንነታቸው ፡ መቃወስ ፡ እፍግፍግ ፡
ለሆነው ፡ ኑሮአቸውና ፡ ለሚፈጽሙት ፡ ወንጀል ፡ መነሾ ፡
መሆኑን ፡ ስለምናውቅ ፡ ተገቢ ፡ ሊሆን ፡ የሚችልበት ፡
ምክንያት ፡ የለውም ።

«የጥቁሮችን ፡ የትምህርት ፡ ጉዳይ ፡ እስቲ ፡ እናስ
ብበት ፡ ብለው ፡ ለተነሡ ፡ እንዳንድ ፡ ክፍሎች ፡ መተዋ
ችን ፡ የሚገባ ፡ ነበር ። ጥቁሮችን ፡ ማስተማር ፡ ጥቅም ፡
የለውም ፡ ብለን ፡ መጠራጠራችንም ፡ የሚገባ ፡ ነበር ።
እንዳየነውና ፡ እንደ ፡ ተረዳነው ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ ጥርጣሬአ
ችን ፡ መሠረት ፡ አልነበረውም ። ለጥቁሮቹ ፡ ትምህርት ፡
ማግኘት ፡ ምክንያት ፡ ባንሆንም ፡ እንኳ ፡ እንዱስትሪያ
ችን ፡ የተስፋፋው ፡ ከተማውን ፡ አጣበውት ፡ በሚገኙት ፡
ጥቁሮች ፡ ድካም ፡ መሆኑ ፡ አይካድም ። ለማንኛውም ፡ ጎብ
ረተ ፡ ሰብ ፡ ጸጥታና ፡ ደኅንነት ፡ ወጣቶች ፡ ሕግ ፡ አክባሪ ፡
ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አሳቢና ፡ ተቈርቋሪ ፡ ሆነው ፡ እንዲያ
ድጉ ፡ አስፈላጊውን ፡ ትምህርት ፡ እንዲያገኙ ፡ ማድረግ ፡
የተገባ ፡ ነው ። እኛ ፡ ግን ፡ በከተሞቻችን ፡ የሚኖሩትን ፡
ጥቁሮች ፡ ትምህርት ፡ ጉዳይ ፡ ሁኔታው ፡ አሳስቦአቸው ፡
ለተነሡ ፡ ጥቂት ፡ ነጮች ፡ እርግፍ ፡ አድርገን ፡ ትተነ
ዋል ። ሥራው ፡ እንዲስፋፋ ፡ ፍላጎት ፡ የሌለን ፡ በመ
ሆኑ ፡ የምንሰጠው ፡ የገንዘብ ፡ ድጋፍ ፡ የለም ። ስለዚህ ፡
እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ እን
ዴት ፡ ይቻላል? ለግል ፡ ጥቅማቸው ፡ ብቻ ፡ የሚያስቡ ፡
እንኳ ፡ የጉዳዩን ፡ አደገኝነት ፡ መረዳት ፡ አያቅታቸውም ።

«ለሀገራቱ ፡ መሻሻል ፡ እንቅፋት ፡ የሆነውን ፡
በጎሳ ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተውን ፡ ጎብረተ ፡ሰብ ፡
ይፍረስ ፡ ማለታችን ፡ የሚገባ ፡ ነበር ። ውሎ ፡ አድሮ ፡
መፍረሱ ፡ አይቀርም ፡ ብለን ፡ ማሰባችንም ፡ የሚገባ ፡
ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ መፍረሱን ፡ ብቻ ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ በመ
መልከት ፡ በስፍራው ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ አለመተካታ
ችንና ፡ ለአንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ሕዝብ ፡ አካላዊና ፡ የሞራል ፡
ውድቀት ፡ ምክንያት ፡ መሆናችን ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ።

«በጎሳ ፡ መንፈስ ፡ ይመራ ፡ የነበረው ፡ ጎብረተ ፡
ሰብ ፡ የጭከናና ፡ የአረመኔነት ፡ የጭፈና ፡ እምነትና ፡
የአባይ ፡ ጠንቋይ ፡ ስሜት ፡ የተጫነው ፡ መሆኑ ፡ ባይካ
ድም ፡ እንኳ ፡ የሚከተለው ፡ የሞራል ፡ ግዴታ ፡ እንደ ፡
ነበረው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የዛሬዎቹ ፡ ጥቁሮች ፡ የሚያዘ
ነብሉት ፡ ወደ ፡ ወንጀል ፡ ወደ ፡ ሽርሙጥናና ፡ ወደ ፡
ስካር ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ጥቁሮቹ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ የሚ
ፈጽሙት ፡ ወደው ፡ ሳይሆን ፡ ይተዳደሩበት ፡ የነበረው ፡
ባህላቸው ፡ ስለ ፡ ተናጋባቸው ፡ ነው ። ለዚህ ፡ የባህል ፡
መፍረስ ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ ያመ
ጣነው ፡ ሥልጣኔ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሥልጣኔአችን ፡ በፈ
ረሰው ፡ ምትክ ፡ ጥቁሮቹ ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ ባህልና ፡
ሥርዓት ፡ የመመሥረት ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

«የቀለም ፡ ልዩነትን ፡ አመራር ፡ በመከተል ፡ ጥቁ
ሮቹ ፡ ባሉበት ፡ ይጸናሉ ፡ የማለት ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ነበረን ፡
የታወቀ ፡ ነው ። እደራረጋችንም ፡ የሚገባ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡
ግን ፡ የቀለም ፡ ልዩነት ፡ አመራራችንንም ፡ ቢሆን ፡
ከሙሉ ፡ ልባችን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አላዋልነውም ። ብዛታ
ቸው ፡ ከአምስት ፡ አራት ፡ እጅ ፡ ለሆኑት ፡ ጥቁሮች ፡

ከጠቅላላው ፡ የአገሪቱ ፡ መሬት ፡ በአንድ ፡ አሥረኛው ፡ ላይ ፡ እንዲተዳደሩ ፡ አደረግን ። የሰፈሩበት ፡ መሬት ፡ አላስተዳድር ፡ ስላላቸው ፡ ጥቁሮች ፡ በብዛት ፡ ወደ ፡ ከተ ሞቻችን ፡ ይጎርፉ ፡ ጀመር ። ለጥቅማችን ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ የፈጠርነው ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ድር ፡ ሁለመናችንን ፡ ተብትቦ ፡ ይዞት ፡ ይገኛል ።

«የገጠመን ፡ ችግር ፡ ቀላል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚያስብ ፡ ማንም ፡ የለም ። ችግሩም ፡ በቀላሉ ፡ መፍትሔ ፡ ይገኝለታል ፡ ብሎ ፡ የሚያምን ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ። ሁኔታው ፡ የሚያስፈራ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ ከርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ መሆናችን ፡ መጠን ፡ ድርጊታችን ፡ ከሚያስከትለው ፡ የሞራል ፡ ጎላፊነት ፡ ልናመልጥ ፡ አንችልም ። አሁን ፡ ጊዜው ፡ . . . »

ጽሑፉም ፡ በእነዚህ ፡ ቃላት ፡ አበቃ ። ባነበበው ፡ ሐሳብ ፡ ተመስጦ ፡ የነበረው ፡ ጃርቪስ ፡ ጽሑፉ ፡ ይቀጥል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በማለት ፡ በጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ የተከመሩትን ፡ ወረቀቶች ፡ አገላብጦ ፡ ተመለከተ ። በመጨረሻውም ፡ ካነበበው ፡ ጽሑፍ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ተጨማሪ ፡ ሐሳብ ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ያልሰፈረ ፡ መሆኑን ፡ ለመገንዘብ ፡ ቻለ ። ፒፓውን ፡ አቀጣጥሎ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ጢሱን ፡ ቡልቅ ፡ አደረገ ። ሳያስበውና ፡ ሳይፈልገው ፡ ያ ፡ በሐይ ፡ ፕሌስ ፡ ከእንጨት ፡ የተሠራ ፡ ጠብመንጃ ፡ እያነጣተ ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ቱር ፡ ቱር ፡ እያለ ፡ ያደገው ፡ የልጁ ፡ ሥዕል ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ በጉልህ ፡ ተሣለ ።

የአርሰር ፡ ጃርቪስ ፡ ቀብር ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከባዱን ፡ የኀዘን ፡ ሌሊት ፡ ለማሳለፍ ፡ ጃርቪስና ፡ ባለቤቱ ፡ ወደ ፡ ሐሪሰን ፡ ቤት ፡ ተመለሱ ። ጃርቪስ ፡ የባለቤቱ ፡ ኀዘን ፡ የመረረ ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ከአጠገብዋ ፡ ሳይለይ ፡ ሊያጽናናት ፡ ወሰነ ።

— ለመሆኑ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ለመቆየት ፡ አስባችኋል ፡ ጃርቪስ ? በእኛ ፡ በኩል ፡ እስከ ፡ ፈለጋችሁት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ብትቆዩ ፡ ደስ ፡ ይለናል ። ለመሆኑ ፡ በፖሊሶች ፡ በኩል ፡ የተወሰነ ፡ ነገር ፡ አለ? ፡— አለ ፡ ሐሪሰን ።

— ፖሊሶቹ ፡ አሽከርዬው ፡ እስኪሻለው ፡ ድረስ ፡ በመጠባበቅ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። አእምሮው ፡ የተመለሰለት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከተያዙት ፡ መካከል ፡ አንዱን ፡ ሳያውቅ ፡ አይቀርም ፡ የማለት ፡ ተስፋ ፡ አላቸው ።

— እውነት ፡ አምላክ ፡ እንዳለ ፡ ቶሎ ፡ ተይዘው ፡ በገመድ ፡ ለመንጠልጠል ፡ ያብቃቸው ። ይቅርታ ፡ አድርግልኝ ፡ ጃርቪስ ።

— ስሚትህ ፡ ይገባኛል ።

— እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ያሉት ፡ ጥቁሮች ፡ በሙሉ ፡ ተይዘው ፡ በገመድ ፡ ቢንጠለጠሉ ፡ ጸጥታ ፡ የምናገኝ ፡ አይመስለኝም ። አንዳንዴ ፡ ቆም ፡ ብዬ ፡ ነገሩን ፡ ሳስበው ፡ ሁኔታው ፡ አቅማችን ፡ ከሚገታው ፡ ደረጃ ፡ በላይ ፡ መድረሱ ፡ ይሰማኛል ።

— አዎን ፡ እውነትህን ፡ ነው ፡ በእኔ ፡ በኩሌ ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ በጉዳዩ ፡ ላስብበት ፡ አልሻም ።

— እርግጥ ፡ ሐሳብህ ፡ ይገባኛል ። ወንጀለኞቹ ፡ ስለሚቀጡት ፡ ቅጣት ፡ እምብዛም ፡ የምትጨነቅበት ፡ አይመስለኝም ።

— ስለ ፡ ወንጀለኞቹ ፡ ቅጣት ፡ አትጨነቅበትም ፡ ያልኸው ፡ እውነት ፡ ነው ። ጉዳዩ ፡ ለጊዜው ፡ የሚያሳስበኝ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘሁትም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የቅጣቱም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ከጉዳዩ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ መሆኑን ፡ አልዘነጋሁትም ።

— ስማኝ ፡ ጃርቪስ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለጸጥታችን ፡ ማስከበሪያ ፡ የፖሊስ ፡ ኃይል ፡ እንዲጨመርልን ፡ አቤቱታ ፡ አቅርበን ፡ ነበር ። እኔ ፡ በበኩሌ ፡ በጥቁሮች ፡ ላይ ፡ ጥላቻ ፡ የለኝም ። በተቻለኝ ፡ መጠን ፡ ደህና ፡ ደሞዝ ፡ ንዱሕ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ በቂ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ እየሰጠሁ ፡ አስተዳድራቸዋለሁ ። የቤት ፡ አገልጋዮቻችንም ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ አብረውን ፡ ይኖራሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁኔታውን ፡ በጠቅላላው ፡ ስመለከተው ፡ ጥቁሮቹ ፡ አልቻል ፡ እያሉ ፡ ሄደዋል ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ይግረማችሁ ፡ ብለው ፡ የሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ አቋቁመዋል ። ማኅበሩ ፡ ለማዕድን ፡ ሠራተኞች ፡ በቀን ፡ ሦስት ፡ ብር ፡ ከሃምሳ ፡ ሳንቲም ፡ ካልተከፈላቸው ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማ ፡ ይደረጋል ፡ እያለ ፡ ያስፈራራል ። ለጊዜው ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ ሠርተው ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ይከፈላቸዋል። እሱም ፡ ሆኖ ፡ አንዳንዶቹ ፡ የማዕድን ፡ ኩባንያዎች ፡ ከሰርን ፡ እያሉ ፡ ሥራቸውን ፡ ወደ ፡ መዝጋቱ ፡ ተቃርበዋል ። መቼም ፡ የጥቁሮች ፡ ሙያተኞች ፡ መኖሪያ ፡ ሠፈሮች ፡ የሚያስገመጁ ፡ ሆነዋል ። ባላገር ፡ በሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ በዓይናቸው ፡ አይተውት ፡ የማያውቁትን ፡ ለጤና ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ምግብ ፡ ያገኛሉ ። ሕክምና ፡ በነፃ ፡ ነው ። መቼም ፡ ምን ፡ ልበልህ ፡

የሚቀርባቸው ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ የለም ። እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ የማዕድኖቹ ፡ ባለቤቶች ፡ ከአውን ፡ የበለጠ ፡ ወጪ ፡ ከማውጣት ፡ ይልቅ ፡ ሥራቸውን ፡ ዘግተው ፡ ማረፍን ፡ እንደሚመርጡ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ምን ፡ ይውጣታል ? ጥቁሮቹስ ፡ ምን ፡ መባቢያ ፡ አላቸው ? አንዳቸውም ፡ ሳይቀሩ ፡ በረሃብ ፡ እንደሚያልቁ ፡ ይታየኛል ።

— እሺ ፡ ለመሆኑ ፡ ገበሬዎችስ ፡ ምን ፡ ይበጃቸዋል? አለ ፡ ሐሪሰን ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ። አንተስ ፡ ብትሆን ፡ ወጥተህ ፡ ወርደህ ፡ የዘራኸውንና ፡ ያመረትኸውን ፡ ሰብል ፡ የት ፡ ትሸጠዋለህ ? ሸማቹስ ፡ ገንዘብ ፡ ከየት ፡ አምጥቶ ፡ ይገዛል? ለገበሬዎች ፡ ከመንግሥት ፡ የሚሰጠው ፡ የገንዘብ ፡ ድጋፍም ፡ መቋረጡ ፡ አይቀርም ። እንዱስትሪዎችም ፡ ይዘጋሉ ። ምክንያቱም ፡ ሰዎች ፡ በእንዱስትሪ ፡ የሚሠሩትን ፡ ሸቀጣሸቀጦች ፡ መግዛት ፡ የሚችሉት ፡ በማዕድኖቹ ፡ እየሠሩ ፡ ገንዘብ ፡ ሲያገኙ ፡ ነው ። በየዓመቱ ፡ ከማዕድኖቹ ፡ የሚገኘው ፡ ትርፍ ፡ ከመቶ ፡ ሰባውን ፡ ጥጥት ፡ የሚያደርገው ፡ መንግሥታችንስ? ማዕድኖቹ ፡ ባይኖሩ ፡ እንዴት ፡ ሊንቀሳቀስ ፡ ይችል ፡ ነበር? ማዕድኖች ፡ ሥራቸውን ፡ ቢያቋርጡ ፡ በአገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ነጮች ፡ ግማሾቹ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ አይሆኑም? ማዕድኖች ፡ ባይኖሩ ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎቶች ፡ እይኖርም ። ከመንግሥት ፡ ሠራተኞችም ፡ መካከል ፡ ግማሾቹ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ይቀራሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። እውነቱን ፡ ልንገርህ ፡ ጃርቪስ ፤ ማዕድን ፡ ባይኖር ፡ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ የምትባል ፡ አገር ፡ ባልኖረች ፡ ነበር ። ማዕድን ፡ ባይኖር ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ዝግትግት ፡ አድርጎ ፡ ለጥቁሮቹ ፡ ማስረከብ ፡ በተቻለ ፡ ነበር ።

—ጃርቪስ፡ጨዋታው፡ይብቃኝና፡ሂጂ፡ልተኛ፡—አለ።
— ይቅርታ ፡ አድርግልኝ ። ዝም ፡ ብዬ ፡ ስለፈልፍ ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ እርስት ፡ አድርጌዋለሁ ።
— ምንም ፡ አይደለም ። በበኩሴ ፡ ጫዋታህ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አስረስቶኛል ። ዝም ፡ ብዬ ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ ስሰማ ፡ የቆየሁት ፡ ንግግር ፡ ጠልቼ ፡ አይደለም ።
— ይቅርታ ፡ አድርግልኝ ። በጣም ፡ አጥፍቻለሁ ። ሁሉንም ፡ ነገር ፡ እርስት ፡ ነው ፡ ያደረግሁት ።
ጃርቪስ ፡ ከመቀመጫው ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡—
— እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ በመካከላችን ፡ በሕይወት ፡ ተገኝቶ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ሲከራከር ፡ ብሰማው ፡ እወድ ፡ ነበር ፡— አለ ።

ጀን ፡ ሐሪሰንም ፡ ቀበል ፡ አድርጎ ፡—በበኩሌ ፡ ስለ፡ ጥቁሮች ፡ ጉዳይ ፡ በሚያቀርበው ፡ አስተያየት ፡ ባልስማማም ፡ እንኳ ፡ ከአእምሮው ፡ ለሚያመነጨው ፡ ሐሳብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ነበረኝ ።

በማግስቱ ፡ ሐሪሰን ፡ ጃርቪስን ፡ ወደ ፡ መኝታ ፡ ቤቱ ፡ መውጪያ ፡ ደረጃ ፡ ሥር ፡ ሁኖ ፡ ጠበቀው ።

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ ቢሮ ፡ ገቡ ። ሐሪሰን ፡ የቢሮውን ፡ በር ፡ ከዘጋ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡—
— አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ፖሊሶች ፡ ደውለው ፡ ነበር ። በጠና ፡ ታሞ ፡ የነበረው ፡ የአርሰር ፡ አሽከር ፡ ዛሬ ፡ ጠዋት ፡ ሕሊናው ፡ ተመልሶለታል ። እርሱም ፡ አደጋው ፡ በደረሰበት ፡ ዕለት ፡ አብረው ፡ የነበሩት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸውን ፡ አረጋግጦአል ። ወደ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የገ

ቡት ፡ እንዳይታወቅ ፡ አፍና ፡ አፍንጫቸውን ፡ ሸፍነው ፡ ቢሆንም ፡ እርሱን ፡ መትቶ ፡ የጣለው ፡ የሚሪ ፡ አትክልተኛ ፡ የነበረው ፡ ልጅ ፡ መሆኑን ፡ አስታውቆአል ። ሚሪ ፡ ይህንኑ ፡ አሽከርዋን ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ጭቅጭቅ ፡ ስላነሣ ፡ ከሥራ ፡ አሰናብታው ፡ ነበር ። አሽከርየው ፡ ለይቶ ፡ ሊያውቀው ፡ የቻለውም ፡ ዓይኑ ፡ አጠገብ ፡ ባለ ፡ አንድ ፡ ምልክት ፡ ነው ። ልጁ ፡ ከሚሪ ፡ እንደ ፡ ተሰናበተ ፡ በአንድ ፡ ፋብሪካ ፡ ውስጥ ፡ ተቀጥሮ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ። በፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ ጀምሮት ፡ የነበረውን ፡ ሥራ ፡ ከለቀቀ ፡ ወዲህ ፡ የት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። አሁን ፡ ግን ፡ አንድ ፡ የቅርብ ፡ ጓደኛ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ጠቆማቸው ፡ በእርሱ ፡ በኩል ፡ የገባበትን ፡ ቦታ ፡ ለማግኘት ፡ በመጣር ፡ ላይ ፡ ናቸው ። እንደ ፡ ሰማሁት ፡ ከሆነ ፡ በቅርቡ ፡ አድነው ፡ ሳይዙት ፡ አይቀርም ።

—22—

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ዳኞች ፡ የሚሠየሙበት ፡ ኮራ ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ አለ ። መቼም ፡ ዳኞች ፡ የአንድ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ የሚተዳደርበትን ፡ ሕግ ፡ አያወጡም ። ሕጉን ፡ የሚያወጣው ፡ ሕዝቡ ፡ ራሱ ፡ ነው ። የዳኞች ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባር ፡ የሕጉን ፡ ሚዛናዊነት ፡ መጠበቅና ፡ ማስከበር ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሕዝቡ ፡ ትክክለኛ ፡ ካልሆነ ፡ የሚያወጣው ፡ ሕግ ፡ ሚዛናዊ ፡ ሊሆን ፡ እንዴት ፡ ይችላል ?

የደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ሕዝብ ፡ ትክክለኛ ፡ በሆኑ ፡ ዳኞቹ ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ አለው ። የደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ጥቁ

ሮች ፣ እንኳ ፣ የአገራቱን ፣ ሕግ ፣ ትክክለኛ ፣ ነው ፣ ብለው ፣ ለመቀበል ፣ የሚያዳግታቸው ፣ ቢሆንም ፣ በዳኞቹ ፣ላይ ፣ እምነት ፣ አላቸው ። ደቡብ ፣ አፍሪቃን ፣ በመሰለች ፣ ፍጥ ሃት ፣ በሰፈነባት ፣ አገር ፣ የዳኞች ፣ ለእውነተኛ ፣ ፍርድ ፣ ብቻ ፣ መገዛት ፣ በጨለማ ፣ ውስጥ ፣ በተተከለ ፣ የብርሃን ፣ ፋና ፣ ይመሰላል ።

በፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ውስጥ ፣ ጸጥታ ፣ እንዲሆን ፣ የሚ ያገ ፣ አንድ ፣ ጐላ ፣ ያለ ፣ ድምፅ ፣ ተሰማ ። ሰዎች ፣ ተነ ሥተው ፣ ቆሙ ። ዳኞቹ ፣ ገብተው ፣ በፍርድ ፣ ወንበራ ቸው ፣ላይ ፣ ተሠየሙ ። ፍርድ ፣ ቤቱም ፣ ሥራውን ፣ ጀመረ ።

ተከሰው ፣ የቀረቡት ፣ ሦስቱ ፣ ወጣቶችም ፣ ስፍራ ቸውን ፣ ያዙ ። ስማቸው ፣ አቤሴሎም ፣ ኩማሎ ፣ ማቴ ዎስ ፣ ኩማሎና ፣ ዮሐንስ ፣ ፓፋሪ ፣ ተብሎ ፣ ተጠራ ። ሕግ ፣ አስከባሪው ፣ ረዘም ፣ ባለ ፣ ንግግር ፣ የወንጀሉን ፣ አፈጻ ጸም ፣ ሁኔታ ፣ ለፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ዘርዝሮ ፣ አስረዳ ። አቤሴ ሎም ፣ ኩማሎ ፣ የሚነገረውን ፣ ሁሉ ፣ በዝምታና ፣ በጸ ጥታ ፣ ያደምጣል ። ሁለቱ ፣ ጓደኞቹ ፣ ግን ፣ በሰሙት ፣ ነገር ፣ ያዘኑም ፣ የደነገጡም ፣ ይመስላሉ ።

— ይህን ፣ ሽጉጥ ፣ የያዝከው ፣ ለምን ፣ ነበር ? ሲል ፣ ሕግ ፣ አስከባሪው ፣ የመጀመሪያ ፣ ጥያቄውን ፣ አቀረበ ።

— የቤቱን ፣ አሽከር ፣ ለማስፈራራት ፣ ነበር ፣—አለ ፣ አቤሴሎም ።

— ሐሳብህ ፣ አሽከሩን ፣ ለማስፋራራት ፣ ከሆነ ፣ ሽጉጡ ፣ ለምን ፣ ጐረሰ ?

አቤሴሎም ፣ ግን ፣ ይህን ፣ ለመሰለው ፣ ጥያቄ ፣ መልስ ፣ አልነበረውም ። ሕግ ፣ አስከባሪው ፣ ጥያቄ ፣ በጥ

ያቄ ፣ ላይ ፣ እያከታተለ ፣ ያወርደው ፣ ጀመር ። የሚያገ ኘው ፣ መልስ ፣ ግን ፣ አልነበረም ። አቤሴሎም ፣ በመጨረ ሻው ፣ ቢጨንቀው ፣ ፊርቼ ፣ ነው ፣ ፊርቼ ፣ ነው ፣ ልገድ ለው ፣ አልነበረም ፣ የተኮሰሁት ፣—አለ ። ሕግ ፣ አስከባ ሪው ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ጥያቄውን ፣ በጥያቄ ፣ ላይ ፣ ያከታት ለው ፣ ጀመር ።

—23—

ሰሞኑን ፣ የአርሰር ፣ ጃርቪስን ፣ ገዳዮች ፣ ክስ ፣ ከቁም ፣ ነገር ፣ የቈጠረው ፣ ሰው ፣ ያለ ፣ አይመስልም ። ሰሞ ኑን ፣ ተጋኖ ፣ የሚወራው ፣ አዲንዳልስረስት ፣ በተባለች ፣ ትንሽ ፣ መንደር ፣ የተገኘው ፣ ወርቅ ፣ ዜና ፣ ነው ። አዎን ፣ በአዲንዳልስረስት ፣ ጥሩ ፣ ወርቅ ፣ ብዙ ፣ ወርቅ ፣ ተገኝቶ አል ። ትናንት ፣ አዲንዳልስረስት ፣ የተባለችዋን ፣ መን ደር ፣ መኖርዋን ፣ እንኳን ፣ የሚያውቁ ፣ ጥቂቶች ፣ ሰዎች ፣ ነበሩ ። ዛሬ ፣ ግን ፣ ዝናዋ ፣ በመላው ፣ ዓለም ፣ የገነነ ፣ ሆኖአል ።

የተገኘው ፣ ወርቅ ፣ በብዛትም ፣ ሆነ ፣ በጥራት ፣ ከጆ ሐንስበርግ ፣ ወርቅ ፣ የሚያንስ ፣ አይደለም ። ብዙዎች ፣ እንደሚያወሩት ፣ ከሆነ ፣ በሰማይ ፣ ጠቀስ ፣ ፎቆች ፣ የተ ሸቈጠቈጠ ፣ በጥርጊያ ፣ ጐዳናዎች ፣ ያጌጠ ፣ አዲስ ፣ ጆሐ ንስበርግ ፣ በአዲንዳልስረስት ፣ መሠራቱ ፣ አይቀርም ። የጆ ሐንስበርግ ፣ ወርቅ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ማለቁ ፣ አይቀርም ፣ እያሉ ፣ ይሠጉና ፣ ይጨነቁ ፣ የነበሩት ፣ ሁሉ ፣ በደስታ ፣ መፈንደቅ ፣ ይዘዋል ። በጆሐንስበርግ ፣ አዲሱ ፣ የወርቅ ፣ ማዕድን ፣ ያላስደተሰው ፣ የለም ። የወርቅ ፣ ማዕድን ፣ እከ ሲዮን ፣ ዋጋው ፣ በአንድ ፣ ቀን ፣ አዳር ፣ ሰማይ ፣ ወጥቶአል ።

ወርቅ ፡ ወርቅ ፡ ወርቅ ! አገራቱ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሀብት ፡ ሊተርፋት ፡ ነው ። አንድ ፡ የወርቅ ፡ ማዕድን ፡ አክሲዮን ፡ ዋጋ ፡ ከሰባት ፡ ብር ፡ ወደ ፡ ሠላሳ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ከፍ ፡ ብሎአል ። ግሩም ፡ የሆነ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አምላኬ ፡ ተመስገን ፡ የሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ጊዜው ፡ ባስከተለው ፡ ያልታሰበ ፡ ለውጥ ፡ ደስ ፡ ያልተሰኙ ፡ ሰዎች ፡ መኖራቸው ፡ አይካድም ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የወርቅ ፡ ማዕድን ፡ አክሲዮን ፡ ውስጥ ፡ ጥቅም ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ። ከእነዚህም ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የማዕድኑ ፡ አክሲዮን ፡ ዋጋ ፡ ከሰባት ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ እንዳይል ፡ ተደርጎ ፡ ከእያንዳንዱ ፡ አክሲዮን ፡ በተገኘው ፡ የሃያ ፡ ስምንት ፡ ብር ፡ ትርፍ ፡ ጠፍ ፡ የሆነው ፡ መሬት ፡ ቢለማበት ፡ የወንዶችና ፡ የሴቶች ፡ ወጣቶች ፡ ክበቦች ፡ ቢሠሩበት ፡ ሆስፒታሎች ፡ ቢቋቋሙበት ፡ የማዕድን ፡ ሠራተኞች ፡ ደሞዝ ፡ እንዲያድግ ፡ ቢደረግበት ፡ መልካም ፡ ነበር ፡ እያሉ ፡ ሲናገሩ ፡ ይሰማል ። የወርቅ ፡ ማዕድኑ ፡ ጥቅም ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑት ፡ ደግሞ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ አርቆ ፡ አለማሰብ ፡ ነው ፤ የወርቅ ፡ ማዕድን ፡ አክሲዮን ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ ከሠራተኞች ፡ ደመወዝ ፡ ጋር ፡ ምን ፡ ግንኙነት ፡ አለው? ይላሉ ። እንደሚወራው ፡ ከሆነ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ — ሁለተኛ ፡ ጆሐንስበርግ — በአዴንዳልስረስት ፡ መቄርቄሩ ፡ አይቀርም ።

* * *

ለመሆኑ ፡ ገንዘብ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ የሚታበድለት ፡ ነገር ፡ ነውን ? በዚህ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ሁለተኛ ፡ ጆሐንስበርግ ፡ ያስፈልጋልን? አንዱ ፡ መች ፡ አነሰና ።

ጃርቪስ ፡ ያነበው ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ የልጁ ፡ ድርሰት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ይገኝበታል ።

«. . . ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ራሴን ፡ ጊዜዬን ፡ ጉልበቴንና ፡ ችሎታዬን ፡ ለደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ አገልግሎት ፡ እሠዋለሁ ። ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚያሳስበኝ ፡ ልፈጽመው ፡ የምፈልገው ፡ ተግባር ፡ ጠቃሚነት ፡ ሳይሆን ፡ ትክክለኝነቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ላደርግ ፡ የወሰንሁት ፡ ከሌሎች ፡ የተሻልሁና ፡ ራሴን ፡ የማልወድ ፡ ነኝ ፡ በሚለው ፡ መንፈስ ፡ በመመራት ፡ ሳይሆን ፡ ሕይወት ፡ ራሱ ፡ አጭር ፡ በመሆኑና ፡ ለተረፈኝ ፡ ዕድሜዬ ፡ መምሪያ ፡ የሚሆን ፡ የኑሮ ፡ ዓላማ ፡ ስለሚያስፈልገኝ ፡ ነው ፡ . . . »

ጃርቪስ ፡ ሚቹ ፡ ልጁ ፡ በጽሑፍ ፡ ያሰፈራቸውን ፡ እነዚህን ፡ ቃላት ፡ እያነበበ ፡ ሲያሰላስል ፡ በር ፡ ተንኳኳ ። ተነሥቶ ፡ ቢከፍት ፡ አንድ ፡ ጥቁር ፡ ቄስ ፡ ደጅ ፡ ቆሞ ፡ አገኘ ። ቄሱ ፡ በዕድሜ ፡ የገፋ ፡ የለበሰው ፡ ልብስ ፡ የነተበ ፡ ያደረገው ፡ የክህነት ፡ ክሳድ ፡ በላብ ፡ ያደፈ ፡ ነበር ። ጥቁሩ ፡ ቄስ ፡ ጃርቪስን ፡ ሲያይ ፡ ባርኔጣውን ፡ ከራሱ ፡ ብድግ ፡ አደረገ ። በገጹ ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ ይታይበታል ፤ ሰውነቱም ፡ ይንቀጠቀጣል ።

—እንደምን ፡ አደርክ ፡ ኡምፉንዲሲ ፡—አለ ፡ ጃርቪስ ።

— ጤና ፡ ይስጥልኝ ፡ ጌታዬ ፡— አለ ፡ ጥቁሩ ፡ ቄስ ፡ ፍርሃት ፡ ባሸነፈው ፡ ድምፅ ። ወዲያውም ፡ እግሮቹ ፡ ሰው

ነቱን ፡ ሊሸከሙ ፡ ያቃታቸው ፡ ይመስል ፡ ከቤቱ ፡ ደረጃዎች ፡ እመጨረሻው ፡ ላይ ፡ ዘፍ ፡ አለ ።

— ምነው ፡ ደሀና ፡ አይደለህም ፡ ኡምፉንዲሲ ? ውኃ ፡ ልስጥህ? ጥቂት ፡ ምግብ ፡ ላምጣልህ?

— ግድ ፡ የለም ፡ ጌታዬ ፡ አሁን ፡ ይሻለኛል ። ጥቁሩ ፡ ቄስ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ብሎ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ተነሥቶ ፡—

— ጌታ ፡ መኖሪያዎ ፡ እንዶትሼኒ ፡ አይደለም? አለ ።

— አዎን ፡ ከእንዶትሼኒ ፡ ነው ፡ የመጣሁት ። ለመሆኑ ፡ እንዲህ ፡ በፍርሃት ፡ የምትንቀጠቀጠው ፡ ለምንድር ፡ ነው? እኔን ፡ የምትፈራበት ፡ ምን ፡ ምክንያት ፡ አለህ ?

— መፍራቴ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ። አንድ ፡ የሚያስፈራ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ደርሶብኛል ። በሕይወቴ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ አጋጥሞኝ ፡ አያውቅም ።

— ንገረኝና ፡ ይውጣልህ ፤ ይሻልሃል ።

— በሕይወቴ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ አጋጥሞኝ ፡ አያውቅም ፡ ያልሁዎት ፡ በእርስዎም ፡ ሕይወት ፡ ደርሶ ፡ የማያውቅ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡—አለ ፡ ጥቁሩ ፡ ቄስ ።

ጃርቪስ ፡ ቄሱን ፡ ትከ ፡ ብሎ ፡ ከተመለከተው ፡ በኋላ ፡—በሕይወቴ ፡ የደረሰብኝ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ነው. . . አንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ —አለ ።

— አዎን ፡ ልጅዎን ፡ የገደለው ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡— አለ ፡ ጥቁሩ ፡ ቄስ ።

ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ ሰዎች ፡ ዝም ፡ አሉ ።

—ሰምቼአለሁ ። ቅድም ፡ ያላስተዋልኩትን ፡ አሁን ፡

ተረድቼአለሁ ። ልቤ ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ የለበትም ፡ — አለ ፡ ጃርቪስ ።

— እኔ ፡ በማገለግልበት ፡ በእንዶትሼኒ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሲያልፉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይቼዎታለሁ ።

— እኔን ፡ ካየኸኝ ፡ ልጄንም ፡ ላታየው ፡ አትቀርም ፡— አለ ፡ ጃርቪስ ። ልጄም ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ በእዶትሼኒ ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያልፍ ፡ ነበር ። ቀይ ፡ ቦቃ ፡ ፈረስ ፡ ነበር ፡ የሚቀመጠው ። ከእንጨት ፡ የተሠራ ፡ ጠብመንጃ ፡ ያነግት ፡ ነበር ።

— አስታውሳለሁ ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለው ፡ ልጅ ፡ ነበር ።

— አዎን ፡ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለው ፡ ልጅ ፡ ነበር ፡— አለ ፡ ጃርቪስ ።

እንደ ፡ ገና ፡ ሁለቱም ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆሙ ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ጥቁሩ ፡ ቄስ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ግቢው ፡ በር ፡ አዞረ ። መዝጊያውን ፡ ሊዘጋው ፡ ዞር ፡ ቢል ፡ ጃርቪስ ፡ ተከትሎት ፡ በሩ ፡ ድረስ ፡ መምጣቱን ፡ አየ ። እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ከግቢው ፡ ወጣ ።

— ደህና ፡ ሁን ፡ ኡምፉንዲሲ ፡ — አለ ፡ ጃርቪስ ።

— ደህና ፡ ይሁኑ ፡ ጌታዬ ።

ጃርቪስ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሲመለስ ፡ ባለቤቱ ፡ ወጣ ፡ ብላ ፡ ተቀበለችው ።

— ምነው ፡ ፊትህ ፡ ተለዋወጠ ፡ ጃርቪስ ?

— አንድ ፡ የቆየ ፡ ትዝታ ፡ የሚቀሰቅስ ፡ ነገር ፡ አጋ

ጥሞኝ ፥ ነው ። እንዳንዴ ፥ እንድ ፥ ነገር ፥ ሳያስቡት ፥ ላይ ፈልጉት ፥ ትዝ ፥ እንደሚል ፥ ታውቂ ፥ የለም ?

ባለቤቱም ፥ እጁን ፥ ሙጭጭ ፥ አድርጋ ፥ ይዛ ፥— አዎን ፥ አውቃለሁ ፥— አለችው ።

—25—

ዮሐንስ ፥ ኩማሎ ፥ አደባባዩ ፥ ላይ ፥ ለተሰበሰበው ፥ ሕዝብ ፥ ንግግር ፥ ያደርጋል ። ነጮችና ፥ ጥቁሮች ፥ ፖሊሶች ፥ በአደባባዩ ፥ ዙሪያ ፥ አለፍ ፥ አለፍ ፥ ብለው ፥ በመሰለፍ ፥ ጸጥታ ፥ ያስከብራሉ ። በሚሰሙት ፥ ድምፅ ፥ ብቻ ፥ ተማርከው ፥ በነጮች ፥ ላይ ፥ ለመነሣት ፥ የሚቃጡ ፥ ጥቁሮች ፥ እንዳሉ ፥ ምን ፥ ይታወቃል? መቼም ፥ የዮሐንስ ፥ ድምፅ ፥ አድማጮቹን ፥ የሚማርክ ፥ አስማት ፥ ያለበት ፥ መሆኑ ፥ ተወርቶ ፥ ያለቀለት ፥ ነገር ፥ ነው ። በሰዎች ፥ፊት ፥ ቆሞ ፥ ሲናገር ፥ እንዳንዴ ፥ ያጓራል ፥ አንዳንዴም ፥ እንዳንበሳ ፥ ያገሣል ፥ እንደ ፥ ነጐድጓድ ፥ ያስገመግማል ። አንዳንዴ ፥ የመላዋን ፥ አፍሪቃ ፥ ድምፅ ፥ የሚያስተጋባ ፥ይመስላል ።

— እኛ ፥ የማይቻል ፥ ነገር ፥ ስጡን ፥ ብለን ፥ አልጠየቅንም ፥— አለ ፥ ዮሐንስ ።

— እኛ ፥ የምንጠይቀው ፥ የላባችን ፥ ዋጋ ፥ የሆነውን ፥ ተገቢ ፥ ድርሻችንን ፥ ብቻ ፥ ነው ። እንደ ፥ ሰማችሁት ፥ በደቡብ ፥ አፍሪቃ ፥ አዲስ ፥ የወርቅ ፥ ማዕድን ፥ ተገኝቶአል ። አገሪቱም ፥ እንደ ፥ ገና ፥ ሀብት ፥ በሀብት ፥ ልትሆን ፥ ነው ። እንደምታውቁት ፥ ይህን ፥ የተገኘውን ፥ ወርቅ ፥ እኛ ፥ ጥቁሮች ፥ ቆፍረን ፥ ካላወጣነው ፥ ምድር ፥ ማኅፀን ፥

ውስጥ ፥ ተቀብሮ ፥ ይቀራል ። ወርቁ ፥ ለእኛ ፥ ብቻ ፥ይጣ
ባል ፥ አንልም ፤ እኛ ፥ የምንጠይቀው ፥ ተገቢው ፥ ድርሻ
ችን ፥ እንዳይነፈገን ፥ ነው ። መቼም ፥ የአገሪቱ ፥ ሀብት ፥
የሁላችንም ፥ ነው ። የተገኘውም ፥ ወርቅ ፥ ለነጮች ፥ ለጥ
ቂሮችና ፥ ለክልሶች ፥ ሁሉ ፥ የሚበቃ ፥ ነው ። ነገር ፥ግን ፥
ከወርቁ ፥ የሚገኘው ፥ አብዛኛው ፥ ሀብት ፥ የት ፥ የሚ
ገባ ፥ ይመስላችኋል? እዚህ ፥ ላይ ፥ የዮሐንስ ፥ ድምፅ ፥
አስገመገመ ። የሚሰሙት ፥ ሰዎችም ፥ እቆሙበት ፥ ይተ
ራመሱ ፥ ጀመር ። ከዚህ ፥ ቀደም ፥ ዮሐንስ ፥ ሲናገር ፥ያል
ሰሙት ፥ ፖሊሶች ፥ ኩስተር ፥ ኩስተር ፥ አሉ ። ሌሎቹ ፥
ግን ፥ ዮሐንስ ፥ ከተፈቀደው ፥ የንግግር ፥ ወሰን ፥ እንደማ
ያልፍ ፥ ስለሚያውቁ ፥ እምብዛም ፥ አልተጨነቁም ።

እዚህ ፥ ላይ ፥ የዮሐንስ ፥ ድምፅ ፥ በምሥጢር ፥ የሚ
ያወራውን ፥ በይፋ ፥ ቢያወጣውስ ? ይህ ፥ ማራኪና ፥ አስ
ማተኛ ፥ ድምፅ ፥ የሚሰሙትን ፥ ሁሉ ፥ ልባቸውን ፥ ስቅል ፥
አድርጎ ፥ ወደ ፥ ዓመፅ ፥ ቢመራስ ? የዮሐንስ ፥ ድምፅ ፥
ይህን ፥ ሁሉ ፥ ለማድረግ ፥ የሚሳነው ፥ አልነበረም ። ነገር ፥
ግን ፥ የዮሐንስ ፥ ልብ ፥ እንደ ፥ ድምፁ ፥ አይደለም ።
ትንሽ ፥ ፍርሃት ፥ አለችበት ። ድምፁ ፥ የምሩ ፥ ዘንድ ፥
ሲደርስ ፥ ከሩቅ ፥ እንደሚሰማ ፥ የነጐድጓድ ፥ ድምፅ ፥
አስገምግሞ ፥ ጸጥ ፥ ይላል ። አድማጮቹም ፥ ደንገጥ ፥
ብለው ፥ ወደ ፥ ውኑ ፥ ዓለም ፥ ይመለሳሉ ።

የዮሐንስ ፥ ድምፅ ፥ እንደ ፥ ገና ፥ ሲያስተጋባ ፥ በዙ
ሪያው ፥ የቆሙት ፥ ሰዎች ፥ መሸበርና ፥ መቅበጥበጥ ፥ይጀ
ምራሉ ። ዮሐንስ ፥ ኃያል ፥ ድምፅ ፥ አለው ። አዎን ፥ እስከ ፥
ሰማየ ፥ ሰማያት ፥ ሊያስተጋባ ፥ የሚችል ፥ ድምፅ ፥ አለው ።
ነገር ፥ ግን ፥ ድምፁ ፥ በሚሰማው ፥ ሕዝብ ፥ ላይ ፥ ሊቀሰ

ቅስ ፣ የሚችለውን ፣ ኃይል ፣ ቆም ፣ ብሎ ፣ ሲያስብ ፣ ፍርሃት ፣ ፍርሃት ፣ ይለዋል ። ስለዚህ ፣ በሩቅ ፣ እንደሚ ሰማ ፣ የነጐድጓድ ፣ ድምፅ ፣ አስገምግሞ ፣ ጸጥ ፣ እርጭ፣ ይላል ።

በደቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ የልብን ፣ ተናግሮ ፣ እስር ፣ቤት ፣ መግባት ፣ ስም ፣ ያተርፋል ፣ ብለው ፣ የሚያምኑ ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ አሉ ። ስምም ፣ ባያተርፍ ፣ ታፍኖ ፣ ከመሞት ፣ የልብን ፣ ተናግሮ ፣ ወጎኒ ፣ ቤት ፣ መግባት ፣ ይሻላል ፣የሚ ሉም ፣ አሉ ። ዮሐንስ ፣ ግን ፣ ከሁለቱም ፣ ወገን ፣ አይደ ለም ። ወጎኒ ፣ ቤት ፣ ከገባሁ ፣ የአደባባይ ፣ ጭብጨባ ፣ ይቀርብኛል ፣ ብሎ ፣ ይፈራል ።

* * *

ሁሉም ፣ የጊዜውን ፣ አስጊነት ፣ እያነሣ ፣ ያወራል ። ሠራተኞችም ፣ የሥራ ፣ ማቆም ፣ አድማቸውን ፣ አቋር ጠዋል ። ለዚያውም ፣ በአድማው ፣ ተካፋይ ፣ የነበሩት ፣ የማዕድን ፣ ሠራተኞች ፣ ብቻ ፣ ነበሩ ። በአድማው ፣ ሰሞን ፣ ጸጥታው ፣ ደፍርሶ ፣ የነበረው ፣ ፖሊሶች ፣ ሠራተ ኞቹ ፣ ሥራቸውን ፣ እንዲጀምሩ ፣ ባስገደዱበት ፣ ስፍራ ፣ ነው ። በዚያ ፣ ስፍራ ፣ በፖሊሶችና ፣ በሠራተኞች ፣ መካ ከል ፣ በተነሣው ፣ ጸብ ፣ ምክንያት ፣ ሦስት ፣ ሰዎች ፣ መሞ ታቸው ፣ ይነገራል ። በተረፈ ፣ ሁኔታው ፣ ተረጋግቶአል ፣ ይባላል ።

* * *

ባሕሩ ፣ ጸጥታ ፣ የነገሠበትን ፣ ወደብ ፣ ጥግ ፣ እየተ ንደረደረ ፣ ያላጋዋል ። ጥቅጥቅ ፣ ባለው ፣ ደን ፣ ውስጥ ፣ ቅጠሎች ፣ እየረገፉ ፣ መሬት ፣ ይነካሉ ። ተቀብቶና ፣

እምሮ ፣ የቆመውን ፣ ቤት ፣ ግድግዳ ፣ ምስጦች ፣ ውስጥ ፣ ውስጡን ፣ ይሰረስሩታል ። ሁኔታው ፣ ተረጋግቶአል ፣ ይባላል ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ የሞኞች ፣ ወሬ ፣ ነው ። እንደ ፣ እው ነቱ ፣ ከሆነ ፣ የረጋ ፣ ነገር ፣ ፈጽሞ ፣ የለም ።

—26—

ወይዘሮ ፣ ሊቴቤ ፣ ጌርትሩድን ፣ ወደ ፣ ቤት ፣ ጠርታ ፣—ስሚ ፣ ልጄ ፣ ጠባይሽን ፣ ለማወቅ ፣ ብዙ ፣ ጥረት ፣ አድርጌአለሁ ። ነገር ፣ ግን ፣ እስከ ፣ ዛሬ ፣ ምንም ፣ አል ተሳካልኝም ፣—አለቻት ።

— ምን ፣ አጠፋሽ ፣ ነው ፣ የሚሉኝ ?

— ያጠፋሽው ፣ ነገር ፣ አለ ፣ ማለቴ ፣ አይደለም ። የዚህን ፣ ቤት ፣ የኑሮ ፣ ሥርዓትና ፣ የቤተ ፣ ሰቡንም ፣ ጠባይ ፣ የተረዳሽው ፣ አልመሰለኝም ።

ጌርትሩድም ፣ አቀርቅራ ፣ መሬት ፣ መሬቱን ፣ እየ ተመለከተች ፣— የቤቱና ፣ የቤተ ፣ ሰቡ ፣ ጠባይስ ፣ ገብ ቶኛል ፣—አለች ።

— ታዲያ ፣ ከቅድሞቹ ፣ ሰዎች ፣ ጋር ፣ ቆመሽ ፣ ትነ ጋገሪ ፣ የነበረው ፣ ለምንድር ፣ ነው?

— ጨዋ ፣ ሰዎች ፣ መስለውኝ ፣ ነው ።

— ጨዋ ፣ አለመሆናቸውን ፣ በንግግራቸው ፣ ለከት ፣ ማጣትና ፣ በሳቃቸው ፣ አትረጂም ?

— መሳቅና ፣መጫወት ፣ነውር ፣ያለበት ፣አልመሰለኝም ።

— እኔም ፣ ነውር ፣ አለበት ፣ ማለቴ ፣ አይደለም ። እንደ ፣ ሰማሁት ፣ ከሆነ ፣ ግን ፣ ንግግራቸውም ፣ ሆነ ፣ ሳቃ ቸው ፣ ለዛ ፣ የለውም ። እንቺ ፣ ደግሞ ፣ ጠባይሽን ፣ ለማ

ረም ፣ በመጣጣር ፣ ላይ ፣ ስለሆንሽ ፣ እነርሱን ፣ ከመሰሉ ፣ ሰዎች ፣ ጋር ፣ መግጠም ፣ አይጠቅምሽም ። ኡምፉንዲ ሲው ፣ ወንድምሽ ፣ እስከ ፣ አሁን ፣ የተሠቃዩት ፣ ይበቃል ።

— እርግጥ ፣ ነው ፣ ተሠቃይቶአል ።

— በሥቃያቸው ፣ ላይ ፣ ሥቃይ ፣ አትጨምሪባቸዋ ።

— ይህን ፣ ስፍራ ፣ ለቅቄ ፣ ካልሄድሁ ፣ አልሆነልኝም ፣ — አለች ፣ ጌርትሩድ ፣ ምርር ፣ ብላ ።— የዚህን ፣ ስፍራ ፣ መላ ፣ ቅጡን ፣ አላውቀው ፣ ብያለሁ ።

— ተምኘሽ ፣ የእኔ ፣ ልጅ ። ከስፍራው ፣ እንዳይመስልሽ ፣ — አለች ፣ ወይዘሮ ፣ ሊቴቤ ።— በእንዶትሺኒም ፣ ቢሆን ፣ ንግግራቸውና ፣ ሳቃቸው ፣ ለዛ ፣ ቢስ ፣ የሆነ ፣ ሰዎች ፣ ያጋጥሙሻል ።

— እምቢየው ፣ ከቦታው ፣ ነው ፣—አለች ፣ ጌርትሩድ ፣ አሁንም ፣ ምርር ፣ ብላ ።— ጆሐንስበርግ ፣ ከመጣሁ ፣ አንድም ፣ ደህና ፣ ነገር ፣ አጋጥሞኝ ፣ አያውቅም ። ከዚህ ፣ ካልሄድሁ ፣ ምንም ፣ አላርፍም ።

— መሄዳችሁስ ፣ ተቃርቦአል ። የፍርድ ፣ ቤቱም ፣ ጉዳይ ፣ ነገ ፣ ሳያልቅ ፣ አይቀርም ፣ ይባላል ።

የወይዘሮ ፣ ሊቴቤንና ፣ የጌርትሩድን ፣ ንትርክ ፣ የበሩ ፣ መንኳኳት ፣ አቋረጠው ። የወይዘሮ ፣ ሊቴቤ ፣ ጐረቤት ፣ ከሆኑት ፣ ሴቶች ፣ አንዲ ፣ የዕለቱን ፣ ጋዜጣ ፣ ይዛ ፣ ዘው ፣ አለች ።

— የዛሬ ፣ ጋዜጣም ፣ አጉል ፣ ወሬ ፣ ይዞአል ፣ — ብላ ፣ በጉልህ ፣ የተጻፈውን ፣ አርእስት ፣ ለወይዘሮ ፣ ሊቴቤና ፣ ለጌርትሩድ ፣ አሳየቻቸው ።

« በከተማይቱ ፣ ውስጥ ፣ የተፈጸመ ፣ ሌላ ፣ አሰቃቂ ፣ ወንጀል ፣ አንድ ፣ ነጭ ፣ በጥቁር ፣ ወንበዴ ፣ ተገደለ ።»

ከድንጋጤ ፣ የተነሣ ፣ ሦስቱም ፣ ሴቶች ፣ አንዳችም ፣ ቃል ፣ ሳይተነፍሱ ፣ ረጅም ፣ ጊዜ ፣ አለፈ ። በመጨረሻው ፣ ጋዜጣውን ፣ ይዛ ፣ የመጣችው ፣ ሴት ፣—የእናንተ ፣ ጉዳይ ፣ ውሳኔ ፣ ወደማግኘው ፣ ሲቃረብ ፣ ይህ ፣ ወንጀል ፣ መፈጸሙ ፣ በጣም ፣ ያሳዝናል ፣—አለች ። ወዲያው ፣ የማቢው ፣ በር ፣ ሲከፈት ፣ ተሰማ ። ወይዘሮ ፣ ሊቴቤም ፣ በድንጋጤ ፣ ግራ ፣ ቀኙን ፣ በዓይንዋ ፣ ካማተበች ፣ በኋላ ፣ ይዛው ፣ የነበረውን ፣ ጋዜጣ ፣ ከተቀመጠችበት ፣ ወንበር ፣ ሥር ፣ ውሽቅ ፣ አደረገችው ። ቀና ፣ ብላ ፣ ወደ ፣ በሩ ፣ብት መለከት ፣ ኩማሎን ፣ ልጅቱ ፣ ደግፋ ፣ ወደ ፣ ማረፊያው ፣ ስትመራው ፣ አየች ። ወዲያው ፣ ከተል ፣ ብሎ ፣ ምሲማንጉ ፣ ወይዘሮ ፣ ሊቴቤ ፣ ካለችበት ፣ ክፍል ፣ ገባ ። እንደ ፣ ገባም ፣ ዓይኑ ፣ ወንበሩ ፣ ሥር ፣ በተደበቀው ፣ ጋዜጣ ፣ ላይ ፣ ትክል ፣ አለ ።

— ይህን ፣ ጋዜጣ ፣ አይቶታል? አለ ፣ ምሲማንጉ ።

— የለም ፣ ኡምፉንዲሲ ፣ አላዩትም ፣—አለች ፣ ጋዜጣውን ፣ ያመጣችው ፣ ሴትዮ ።

— ለመሆኑ ፣ የፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ጉዳይ ፣ ወደ ፣ ፍጻሜ ፣ ሊደርስ ፣ ሲል ፣ ይህ ፣ ወንጀል ፣ መፈጸሙ ፣ እያሳዝንም?

— እርግጥ ፣ ነው ፣ ሁኔታው ፣ ያሳዝናል ። ቢሆንም ፣ ዳኛው ፣ ትልቅ ፣ ሰው ፣ ነው ። መቼም ፣ ኩማሎ ፣ ጋዜጣ ፣ ሳያነብ ፣ አይውልም ። ነገሩን ፣ ይሰማዋል ፣ ማለት ፣ ነው ። ምን ፣ ማድረግ ፣ ይሻል ፣ ይሆን ?

— መቼም ፣ ሚስዮኑ ፣ ግቢ ፣ ሲሄድ ፣ ያነብ ፣ እንደሆን ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ እዚህ ፣ ቤት ፣ ከዚህ ፣ በስተቀር ፣ ሌላ ፣ ጋዜጣ ፣ የለም ።

— እኔም ፣ ስሮጥ ፣ የመጣሁት ፣ ለዚሁ ፣ ነው ። ይስ

ሙኝ ፡ ወይዘሮ ፡ ሊቴቤ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ እራታችንን ፡ እር
ስዎ ፡ ዘንድ ፡ መብላት ፡ እንችላለን ?

— እናንተ ፡ የተገኘውን ፡ ጥሞአችሁ ፡ ከበላችሁ
ልኝ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

— መቼም ፡ ውለታዎ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ወይዘሮ ፡
ሊቴቤ ።

— ለዚህ ፡ ጊዜ ፡ ካልሆን ፡ የመኖራችን ፡ ትርጉሙ ፡
ምንድር ፡ ነው? አለች ፡ ወይዘሮ ፡ ሊቴቤ ፡ ወደ ፡ ጓዳዋ ፡
ተፍ ፡ ተፍ ፡ እያለች ።

ጋዜጣውን ፡ ራቅ ፡ ካለ ፡ ስፍራ ፡ ደብቀው ፡ ሁሉም ፡
ወይዘሮ ፡ ሊቴቤ ፡ ያሰናዳችውን ፡ እራት ፡ ተመግበው ፡
አደሩ ።

—27—

ዳኞቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲገቡ ፡ አዳራሹን ፡
ግጥም ፡ አድርጎ ፡ ሞልቶት ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ከተቀ
መጠበት ፡ ብድግ ፡ አለ ። ዳኞቹ ፡ መንበራቸው ፡ ላይ ፡ እን
ደተሠየሙ ፡ የቆመው ፡ ሁሉ ፡ በየስፍራው ፡ ተቀመጠ ።
ዕለቱ ፡ በቀረበው ፡ የነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡
የሚሰጥበት ፡ በመሆኑ ፡ ሁሉም ፡ አቆብቁቦ ፡ የሚመለ
ከተው ፡ የዳኞቹን—በተለይም ፡ የዋናውን ፡ ዳኛ—አፍ ፡ ነበር ።

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ሥስቱ ፡ ተከሳሾች ፡ ቀረቡ ።
የተሰበሰበውም ፡ ሕዝብ ፡ ዓይን ፡ እነርሱ ፡ ላይ ፡ ትክል ፡
አለ ። ድምፁም ፡ ያስገመግም ፡ ጀመር ።

— በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ብዙ ፡ አስቤበታለሁ ። ብዙ ፡
ጊዜም ፡ በአእምሮዬ ፡ አውጥቼ ፡ አውርጄዋለሁ ፡ —አለ ፡

ዋናው ፡ ዳኛ ። — የጉዳዩን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታና ፡ የቀረቡ
ትንም ፡ ማስረጃዎች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ መርምሬአቸዋለሁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዋናው ፡ ዳኛ ፡ አቤሴሎም ፡ ኩማሎ ፡
አርሰር ፡ ጃርቪስን ፡ ሽጉጥ ፡ ተኩሶ ፡ ሲገድል ፡ ማቴዎስ ፡
ኩማሎና ፡ ዮሐንስ ፡ ፓፋሪ ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ፡ መሆናቸ
ውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ለቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ ሰፊ ፡ ሐተታ ፡
ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ —ሁለተኛና ፡ ሦስተኛ ፡ ተከሳሾች ፡ በተ
ፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ግብረ ፡ አበሮች ፡ ለመሆናቸው ፡
በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ስላልተገኘ ፡ በነፃ ፡ እንዲለቀቁ ፡ ፍርድ ፡
ቤቱ ፡ በይኖአል ፡ —አለ ።

ዳኛው ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሲናገር ፡ አቤሴሎም ፡ ኩማሎ ፡
ከቆመበት ፡ ነቅነቅ ፡ እንኳን ፡ አላለም ። ነፃ ፡ የተለቀቁ
ትን ፡ ጓደኞቹን ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ እንኳን ፡ አልተመለከተም ።
ፓፋሪ ፡ ግን ፡ የፍርዱን ፡ ትክክለኝነት ፡ የሚያረጋግጥ ፡
ይመስል ፤ ገልመጥ ፡ ገልመጥ ፡ ብሎ ፡ የተቀመጠውን ፡
ሕዝብ ፡ በዓይኑ ፡ ቃኘ ።

— አሁን ፡ የሚቀረው ፡ የመጀመሪያው ፡ ተከሳሽ ፡
ፍርድ ፡ ነው ፡ — አለ ፡ ዋናው ፡ ዳኛ ። —የመጀመሪያው ፡
ተከሳሽ ፡ አቤሴሎም ፡ ኩማሎ ፡ አርሰር ፡ ጃርቪስን ፡
ሽጉጥ ፡ ተኩሶ ፡ መግደሉን ፡ በገዛ ፡ ቃሉ ፡ አምኖአል ። ጠበ
ቃውም ፡ የተከሳሹን ፡ ወጣትነት ፡ ይህ ፡ የምንኖርበት ፡
ክፉ ፡ ከተማ ፡ በጠባዩ ፡ ላይ ፡ ያስከተለውን ፡ አጉል ፡
ለውጥ ፡ አስረድቶናል ። ሥራ ፡ ለመፈለግ ፡ ወደየከተ
ማው ፡ በሚጓጓፈው ፡ የዋሕ ፡ ባላገር ፡ ብልጭልጭ ፡ የነ
ጮች ፡ ሥልጣኔ ፡ ያስከተለውን ፡ የተናቃላነት ፡ መንፈስ ፡
ለዚህም ፡ የጥቁሮች ፡ የንሳ ፡ ኑሮ ፡ ሥርዓት ፡ መናጋት ፡
በጎላፊነት ፡ መጠየቅ ፡ የሚገባው ፡ የነጮች ፡ ጎብረተ ፡

ሚያው ፣ አስተዳዳሪ ፣ ፈረንጅ ፣ የአገሩን ፣ ሕግ ፣ በመ
ጣስ ፣ ለጥቁሮች ፣ ብቻ ፣ ወደ ፣ ተመደበው ፣ መቀመጫ ፣
እመሩ ። ከምሲማንጉ ፣ ጋር ፣ ሆነው ፣ በጎዘን ፣ የተደቆ
ሰውን ፣ ሽማግሌ ፣ ኩማሎን ፣ ደግፈው ፣ አነሡት ። በደ
ቡብ ፣ አፍሪቃ ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ ውስጥ ፣ ነጮች ፣ ለጥ
ቁሮች ፣ ብቻ ፣ ወደ ፣ ተከለለው ፣ መቀመጫ ፣ አልፈው ፣
ከጥቁሮች ፣ ጋር ፣ ሲቀላቀሉ ፣ እምብዛም ፣ ታይቶ ፣ አይ
ታወቅም ። ዳሩ ፣ ግን ፣ በርኅራኄ ፣ የገነፈለን ፣ ልብ ፣ ምን ፣
ዓይነት ፣ ሕግ ፣ ሊያግደው ፣ ይችላል ?

—28—

አባ ፣ ቪንሴንት ፣ ኩማሎ ፣ ጌርትሩድ ፣ ልጅቱና ፣
ምሲማንጉ ፣ አስፈሪ ፣ የሆነ ፣ ግርማ ፣ ያለውን ፣ የወጎኒ ፣
ቤት ፣ መግቢያ ፣ በር ፣ አልፈው ፣ አቤሴሎም ፣ ወደታሰ
ረበት ፣ ክፍል ፣ አመሩ ።

አቤሴሎም ፣ ዝልፍልፍ ፣ ያለ ፣ እጁን ፣ ዘርግቶ ፣ ለል
ጅቱ ፣ ሰላምታ ፣ ሰጣት ። ላያቸው ፣ ከዚህ ፣ ቀደም ፣ የሚ
ተዋወቁ ፣ አይመስሉም ።

ኩማሎም ፣ ተስፋ ፣ በቈረጠ ፣ ድምፅ ፣—

— ልጄ ፣ ለጤናህ ፣ ደህና ፣ ነህ? አለ ።

— በጣሙን ፣ ደህና ፣ ነኝ ። አንተስ ፣ አባቴ ፣ ለጤ
ናህ ፣ ደህና ፣ ነህ ?

— አዎን ፣ ደህና ፣ ነኝ ።

ኩማሎ ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ ከልጁ ፣ ጋር ፣ ለመነጋገር ፣
እስቦ ፣ አንደበቱ ፣ አልፈታ ፣ አለው ።

የዚያኑ ፣ ዕለት ፣ አባ ፣ ቪንሰንት ፣ ልጅቱንና ፣ አቤ
ሴሎምን ፣ በሕግ ፣ አጋቡአቸው ። ከጋብቻውም ፣ ሥነ ፣
ሥርዓት ፣ በኋላ ፣ አባትና ፣ ልጁን ፣ ብቻ ፣ ትተው ፣ የቀ
ሩት ፣ ከክፍሉ ፣ ወጡ ።

— ልጄ ፣ የጋብቻህ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ በመፈጸሙ ፣
ደስ ፣ ብሎኛል ።

— እኔም ፣ ደስ ፣ ብሎኛል ፣ አባቴ ።

— ልጅህን ፣ ደህና ፣ አድርጌ ፣ አሳድግልሃለሁ ።

— ለእናቴ ፣ ምን ፣ ጊዜም ፣ አልረሳሽም ፣ ብለህ ፣
ንገርልኝ ።

— እሺ ፣ እነግራታለሁ ።

— አባቴ ፣ ወደ ፣ እንዶትሼኒ ፣ መቼ ፣ ትመለሳለህ ?

— ነገ ፣ ለመነሣት ፣ አስቤአለሁ ፣ ልጄ ።

— ነገ ፣ ለመነሣት ?

— አዎን ፣ ነገ ።

በዚህ ፣ ጊዜ ፣ አቤሴሎም ፣ ወለሉ ፣ ላይ ፣ ድፍት ፣
ብሎ ፣ ይንሰቀሰቅ ፣ ጀመር ። ሞት ፣ ዓይኑን ፣ አፍጥጦ ፣
ሲመጣ ፣ የማይፈራ ፣ ማን ፣ አለ? ኩማሎም ፣ ወለል ፣ ላይ ፣
በርከክ ፣ ብሎ ፣ ልጁን ፣ ከተደፋበት ፣ ቀና ፣ እያደረገ ፣—
አይዞህ ፣ ልጄ ፣ በርታ ፣— አለው ።

— አባብዬ ፣ ፈርቼአለሁ ፤ በጣም ፣ ፈርቼአለሁ ፣—
አለ ፣ አቤሴሎም ።

የወጎኒ ፣ ቤቱ ፣ ዘበኛ ፣ ወደ ፣ ክፍሉ ፣ ገባ ፣ ብሎ ፣—
ይሰሙኝ ፣ አባቴ ፤ ሰዓቱ ፣ አልፎአል ፣ ይውጡ ፣—አለ ።

— ልጄ ፣ እንግዲህ ፣ መሄዴ ፣ ነው ፣—አለ ፣ ኩማሎ ።
በርከክ ፣ ካለበትም ፣ እነሣለሁ ፣ ሲል ፣ አቤሴሌም ፣ ጕል

[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
[illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
አልፎአል ፡ ይውጡ ፡ — አለ ። ከማሎ [illegible] ፡ [illegible] በ[illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
ሰውና ፡ ከመኸቱ ፡ የተነሣ ፡ የአባቱን ፡ [illegible]

በኀዘንና ፡ [illegible] ከማሎ ፡
የወንጂ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡
የሚታይበት ፡ ፈገግታ ፡ እያሳየች ፡ ወደ ፡ ከማሎ [illegible]
። ህፃኗ [illegible] ፡ [illegible] —
፤ ህለኮስ [illegible] ፡ [illegible] ፡ ቷወ ፡ ቷበለ —
— [illegible] ፡ [illegible] ፡ የኔ —
— ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ [illegible] ! የኔ —
— አዎን ፡ ልጄ ፡ ነሽ ፡ — አሏትና ፡ [illegible] —

፡ [illegible] ፡ ዳሶ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ ዘገ ፡ ህዘበ
፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ የም ፡ [illegible] ፡ [illegible]
— ፡ [illegible] ፡ ጋቀ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
— ልሰናበትህ ፡ [illegible] ፡ [illegible]
ከወንጂ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] —

— ወደ ፡ እንዶትሼኒ ፡ መመለሻህ [illegible]
ነው ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።
[illegible] ፡ [illegible]
ለመኑሣት ፡ እሰበሃል ?
። [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] እስ
[illegible] ፡ [illegible] ፡ ሌስ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]

፡ [illegible] ፡ [illegible]
ነው ? ጥሩ ፡ አድርገሃል ፡ ወንድሜ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።
፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ ቶብ ፡ ዷወ
፡ [illegible]
[illegible]
ትልቅ ፡ ነገር ፡ ነው ። ። ወለለ ! ህለሰመ ፡ ህሉወተሚገ
[illegible] ፡
[illegible] —
— ምን ፡ ነበር ? ። ወኗ ፡ ቻመለ
፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡
ልገልጽልህ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ ቶገ ፡ [illegible]
[illegible] ፡
እንጀ[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
መወቃቀስ ፡ ያስፈልገናል ። ። ህለቂወለ ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ።
[illegible] ፡ [illegible] እልቀለ
[illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible]
[illegible]
፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible]
ብቻ ፡ እንድንለ[illegible] ፡ [illegible]
[illegible] ፡
ከወላጆቹና ፡ ከዘመድ ፡ አዝማድ ፡ መራቁ ፡ [illegible] እንደ ፡
[illegible] ፡ [illegible] ፡

ጊዜው ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ምን ፡ እስኪሆን ፡ ነው ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ የምታየው ?

— አዎን ፡ በጉዳዩ ፡ እኔም ፡ አስቤበታለሁ ፡ አለ ፡ ዮሐንስ ። —ሁኔታው ፡ እስኪረጋጋ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መመለሱ ፡ አይቀርም ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ እየሳቀ ፡ —ስማኝ ፡ ወንድሜ ፡ መልካሙን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ እንድትሠራው ፡ የምተውልህ ፡ መሰለህ ? አለው ።

— አንድ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ አለኝ ፡—አለ ፡ ኩማሎ ።

— ያሻህን ፡ ተናገር ። ታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ መሆንህ ፡ ለመቼ ፡ ነው ።

— ይህ ፡ በየጊዜው ፡ የምታወራው ፡ የፖለቲካ ፡ ጉዳይ ፡ የት ፡ የሚያደርስህ ፡ ይመስልሃል ?

— በፖለቲካ ፡ ስሜቴ ፡ ላይ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዲተች ፡ አልፈልግም ። እኔ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖትህ ፡ መች ፡ አንሥቼብህ ፡ አውቃለሁ ።

— ያሻህን ፡ ተናገር ፡ ብለኸኝ ፡ አልነበረም ?

— አዎን ፡ ብዬሃለሁ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሕይወቴን ፡ የምሠዋለት ፡ ጉዳይ ፡ የት ፡ እንደሚያደርሰኝ ፡ የማውቀው ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ነኝ ። ላባቸውን ፡ እያንጠፈጠፉ ፡ የአገሪቱን ፡ ሀብት ፡ የሚያዳብሩ ፡ ተራ ፡ ሠራተኞች ፡ መብታቸውን ፡ ለዘላለም ፡ ተነጥቀው ፡ እንደማይቀሩ ፡ ታሪክ ፡ የሚመሰክር ፡ መሆኑን ፡ አንተም ፡ አትዘነጋውም ። ለመሆኑ ፡ ስታስበው ፡ ሠራተኞች ፡ ተባብረው ፡ ከተነሡ ፡ ማን ፡ ሊቋቋማቸው ፡ ይችላል?

— ሥራቸውን ፡ ለማቆም ፡ ካደሙ ፡ ማለትህ ፡ነው?

— አዎን ።

— ያለፈው ፡ የሥራ ፡ ማቆም ፡ አድማቸው ፡ ተሳካ?

ዮሐንስ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ። ድምፁ ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ያስገመግም ፡ ጀመር ።

— ያደረጉንን ፡ አይተህ ፡ የለም ፡—አለ ፡ ሁለቱን ፡ እጆቹን ፡ እያርገፈገፈ ።

— እንደ ፡ ከብት ፡ እየነዱ ፡ ነው ፡ እኮ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ የመለሱን ። እሻፈረን ፡ እንሠራም ፡ ለማለት ፡ የማንችል ፡ ባሮቻቸው ፡ እንመስላቸው ፡ ይሆን ?

— ነጮችን ፡ ትጠላለህ ?

ዮሐንስ ፡ ወንድሙን ፡ በጥርጣሬ ፡ ዓይን ፡ እየተመለከተ ፡—እኔ ፡ ማንንም ፡ አልጠላ ። እኔ ፡ የምጠላው ፡ ግፍን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡— አለ ።

— እዚህ ፡ ሱቅህ ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ የሚያስጠይቅህ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ የምትናገር ፡ መሆንህን ፡ ለመገንዘብ ፡ ችያለሁ ። ባለሥልጣኖቹም ፡ የሚከታተሉህ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቻለሁ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ የምነግርህ ፡ ወንድሜ ፡ ስለሆንህ ፡ ነው ።

ዮሐንስ ፡ ይህንን ፡ ሲሰማ ፡ ፍርሃት ፡ ኩምሽሽ ፡አደረገው ።

— እዚህ ፡ እኔ ፡ ሱቅ ፡ ውስጥ ? አይደረግም ። ለመሆኑ ፡ እኔ ፡ ሱቅ ፡ ውስጥ ፡ የሚነገረውን ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ሊሰማ ፡ ይችላል? አለ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደምንም ፡ ተበራታቶ ። ኩማሎ ፡ ሳይወድ ፡ በግድ ፡ ወንድሙን ፡ ሊያስቀይም ፡ ፈለገ ። ሳይወድ ፡ በግድ ፡ ውሸት ፡ ለመናገር ፡ ፈለገ ። —ጓደኛ ፡ መስሎ ፡ የምትናገረውን ፡ ሁሉ ፡ ለመስማት ፡ ሱቅህ ፡ የሚመጣ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መኖሩን ፡ሰምቼአለሁ ፡— አለ ።

ምሲማንጉም ፣ የኩማሎን ፣ የምስጋና ፣ ንግግር ፣ አቋርጦ ፡—እንደምታውቀው ፣ ደካማ ፣ ሰው ፣ ነኝ ። ይህ ፣ ያለ ብዙት ፣ ጉዳይ ፣ እንዲሳካልኝ ፣ በጸሎትህ ፣ አትርሳኝ ፡— አለው ።

— እጸልይልሃለሁ ፤ ሌት ፣ ተቀን ፣ ሳልል ፣ እጸልይ ልሃለሁ ።

— ደህና ፣ እደር ፣ ወንድሜ ።

— ደህና ፣ እደር ፣ ምሲማንጉ ፣ ቀኝ ፣ እጁ ። የእግዚአብሔር ፣ በረከት ፣ በሕይወትህ ፣ ዘመን ፣ ሁሉ ፣ አይለይህ ።

— ከአንተም ፣ አይለይ ፣ ወንድሜ ።

ምሲማንጉ ፣ ወደ ፣ ቤቱ ፣ የሚያደርሰውን ፣ መንገድ ፣ ይዞ ፣ ሲሄድ ፣ ኩማሎ ፣ ከዓይኑ ፣ እስኪሠወር ፣ ድረስ ፣ ቁሞ ፣ ተመለከተው ።

በማግስቱ ፣ ኩማሎ ፣ ማለዳ ፣ ተነሣ ። ልጅቱ ፣ የተኛችበትን ፣ ክፍል ፣ ከፍቶ ፣ ቀስቀስ ፣ ቀስቀስ ፣ እያደረጋት ፡—ልጂ ፣ ተነሽ ፣ የመሄጃችን ፣ ጊዜ ፣ ደርሶአል ፡—አላት ።

— እሺ ፣ ተነሣሁ ፡—አለች ፣ ልጅቱም ። የሽማግሌ ፣ ፈገግታውን ፣ እያሳያት ፡—ነገ ፣ ይህን ፣ ጊዜ ፣ እንዶትሼኒ ፣ ነን ፡— አላትና ፣ ከክፍልዋ ፣ ወጣ ። ከዚያም ፣ ጌርትሩድ ፣ የምትተኛበትን ፣ ክፍል ፣ ከፍቶ ፣ ገባ ። ጌርትሩድን ፣ ግን ፣ አላገኛትም ። ሕፃኑ ፣ ልጅ ፣ ብቻውን ፣ ተኝቶአል ። የገዛላት ፣ ቀይ ፣ ቀሚስ ፣ አልጋው ፣ ላይ ፣ ተዘርሮአል ። ጌርትሩድ ፣ ግን ፣ ሄዳለች ።

ክፍል ፣ ሦስት ።

—29—

ባቡሩ ፣ እያፏጨና ፣ ጢሱን ፣ ቡልቅ ፣ ቡልቅ ፣ እያደረገ ፣ ጉዞውን ፣ ጀመረ ። ከወርቁ ፣ ማዕድን ፣ እየወጣ ፣ በየስፍራው ፣ የተከመረው ፣ ነጭ ፣ አፈርና ፣ የኮረት ፣ ቋልል ፣ ወደ ፣ ኋላ ፣ ቀርቶ ፣ ዓይን ፣ እስኪታክት ፣ ቢታይ ፣ የማይደርስበት ፣ አገር ፣ ትርአይት ፣ ብቅ ፣ አለ ። ኩማሎ ፣ ልጅቱና ፣ ሕፃኑ ፣ በባቡሩ ፣ ውስጥ ፣ አብረው ፣ ተቀምጠዋል ። ሕፃኑ ፣ እናቴ ፣ የት ፣ አለች? ብሎ ፣ ጠይቆ ፣ ነበር ። ኩማሎ ፣ የለችም ፡ ጠፍታለች ፡ ብሎ ፣ እቅጩን ፣ ስለ ፣ ነገረው ፣ ዳግመኛ ፣ ስምዋን ፣ አላነሣም ።

ቀኑን ፣ ሲጓዙ ፡ ውለው ፣ ሌሊቱንም ፡ ሲጓዙ ፡ አደሩ ። ሊነጋጋ ፣ ሲል ፣ የታላቁን ፣ ተራራ ፣ ቀልቀለት ፣ ወርደው ፣ ውብ ፣ ከሆነችው ፣ ፒተርማሪትዝቡርግ ፣ ከተማ ፣ ደረሱ ። ከዚያም ፣ ወደ ፣ ሌላ ፣ ባቡር ፣ ተጋብተው ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ጎሳዎች ፣ በሚኖሩበት ፣ ሸለቆ ፣ በኩል ፣ አድርገው ፡ ጉዞአቸውን ፣ ቀጠሉ ። የመሬቱ ፣ ጠፍነት ፣ የወራቱን ፡ ድርቀት ፣ የተመለከቱ ፡ ሁሉ ፣ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፣ በሚኖሩት ፣ ሰዎች ፣ ላይ ፣ የተነሣው ፣ ረሃብ ፣ እየበረታ ፡ የሚሄድ ፣ መሆኑን ፣ እየተወያዩ ፣ አለፉ ።

በመጨረሻው ፣ ኩማሎ ፣ ልጅቱና ፡ ሕፃኑ ፣ እንዶትሼኒ ፣ ወደሚያደርሳቸው ፡ ባቡር ፣ ተጋብተው ፡ ውብ ፡ በሆነው ፣ መንገድ ፣ በኩል ፣ አድርገው ፡ ወደ ፡ ከረብቶቹ ፡ ደረሱ ። በአካባቢው ፣ የሚኖሩት ፣ ሰዎች ፡ ኩማሎን ፡ ስለሚያውቁት ፡ ልቡን ፡ ፍርሃት ፡ ፍርሃት ፡ አለው ። የሰ

ዎቹ ፡ ባሕርይ [illegible] ሆኑን ፡ ያውቃል ።
ይሉኝታን ፡ የማያውቁ ፡ የሆን ፡ ያልሆነውን ፡ በማን
ሣትና ፡ በመጣል ፡ የሰውዮቿብ ፡ የሚያወልቁ ፡ ነበሩ ።
መቼም ፡ ያ ፡ ሰውዬ ፡ ማን ፡ ነው? ያች ፡ ልጅ ፡ ማን ፡ ናት?
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible] ፡ ተበሰጋጺጺ[illegible]
[illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible]
[illegible]
[illegible]
ወርዳለች [illegible]
አንድ ፡ ወዳጄ ፡ ቆመው ፡ ይጠብቃል ። [illegible]
[illegible] አለ ።
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
፡ የተ[illegible] ፡ ተ[illegible] ፡ ተ[illegible] ። ሰጠቀ ፡ [illegible]
ምበ [illegible]
[illegible]
ስንደርስ ፡ በሰፊው [illegible]

[illegible] ፡ ወሸኔጠመበ
፡ በውጭ [illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible] ፡ ተቀውጊምለሰ

የከ[illegible] እድርጋ ፡
አንዱ [illegible]
ችው ። ሕፃኑን ፡ መሬት ፡ [illegible] — አለ
[illegible] ፡ መለስ ፡
[illegible] ፡ ሞሰስ ፡ ሚሰ ፡ የሰጋጋጸየ
። ሰለ [illegible]
[illegible] ፡ [illegible] በጄዳ ፡ [illegible]
[illegible]
[illegible]
አንድ ፡ ሰውዬ ፡ [illegible]
[illegible] ፡ —
[illegible]
[illegible]
[illegible] ። ለለጋሚኛ ፡ የኃጺም
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible] ፡ መቼስ ፡
ምን ፡ ይደረጋል ፤ ባይመችም ፡ የተወለዱበት [illegible]

— [illegible] ።
— [illegible] ።

[illegible] ፡ እን
[illegible]
ከደረቀ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ [illegible]

— ታዲያ ፡ ምን ፡ ስትጠጡ ፡ ሰነበታችሁ?
— ሴቶቻችን ፡ ወንዝ ፡ እየወረዱ ፡ የቀዱትን ።
— ከየትኛው ፡ ወንዝ ?
— በጃርቪስ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ከሚያልፈው ፡ ወንዝ ።

የጃርቪስን ፡ ስም ፡ ሲሰማ ፡ ኩማሎ ፡ ድንግጥ ፡አለ ። እንደምንም፡ብሎ፡—ለመሆኑ፡ጃርቪስ፡ደህና፡ናቸው?አለ ።
— እርሳቸው ፡ ገና ፡ ትናንት ፡ ነው ፡ የተመለሱት ፡ ኡምፉንዲሲ ። ባለቤታቸው ፡ ከመጡ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ሳምንት ፡ ሆናአቸዋል ። ታምመው ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ ሰው ነታቸው ፡ ሁሉ ፡ ክስት ፡ ብሎአል ።

ሁሉም ፡ አንዳች ፡ ቃል ፡ ሳይተነፍሱ ፡ ጕዞአቸውን ፡ ቀጠሉ ። ቀጭንዋም ፡ የእግር ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ መንደር ፡ አደረሰቻቸው ። ጊዜው ፡ ለዓይን ፡ ያዝ ፡ ማድረግ ፡ ጀምሮአል ። ራቅ ፡ ብሎ ፡ የጥሪ ፡ ድምፅ ፡ ይሰ ማል ። አንድ ፡ ሰው ፡ የዙሉ ፡ ተወላጅ ፡ ካልሆነ ፡ ቋንቋ ውን ፡ እንኳን ፡ ቢያውቅ ፡ የጥሪውን ፡ ምሥጢር ፡ ሊያውቅ ፡ አይችልም ። አንዳንድ ፡ ነጮች ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ የጥሪ ፡ ድምፅ ፡ አስማት ፡ ነው ፡ ይሉታል ። ነገር ፡ ግን ፡ ባያውቁ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ድምፁ ፡ አስማት ፡ የለበትም ። ድምፁ ፡ መጥ ሪያ ፡ መቀስቀሻ ፡ ነው ። የውዲቱ ፡ አፍሪቃ ፡ ድምፅ ፡ ነው ።
— የአንተን ፡ መመለስ ፡ ነው ፡ የሚያበሥሩት ፡ ኡምፉንዲሲ ።
— አዎን ፡ ይሰማኛል ።
— ደስ ፡ ብሎአቸዋል ፡ ኡምፉንዲሲ ።

ድምፁ ፡ ከጎጆ ፡ ወደ ፡ ጎጆ ፡ ከኮረብታ ፡ ወደ ፡ ኮረ ብታ ፡ ያስተጋባል ። የምሥራች ፡ ኡምፉንዲሲ ፡ በደህና ፡ ተመልሶአል ፡ ይላል ።

ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደጅ ፡ የተንጠለጠለው ፡ ፋኖስ ፡ ያበራል ። ኩማሎና ፡ ባለቤቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በር ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ የምስጋና ፡ መዝ ሙር ፡ አስተጋባ ።

ኩማሎም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ጸሎት ፡ ማድ ረስ ፡ ጀመረ ። አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እናመሰግንሃለን ። ፈጣ ሪያችን ፡ ሆይ ፡ ዝናብህን ፡ አውርድልን ። በመጨረ ሻውም ፡— አምላኬ ፡ ሆይ ፡ ልጄን ፡ እደራህን ። ኃጢአ ቱን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ በለው ፡— ብሎ ፡ ጸለየ ።

ሳያስበው ፡ የፈራውን ፡ የደበቀውን ፡ የልጁን ፡ ጉድ ፡ ይፋ ፡ አወጣው ።

—እግዚአብሔር ፡ ይባርካችሁ ፡ ይጠብቃችሁ ። እግዚአብሔር ፡ ፊቱን ፡ ያብራላችሁ ፡ ሰላሙንም ፡ ይስ ጣችሁ ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ።

ሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ ቆሞ ፡ «አምላክ ፡ አፍሪቃን ፡ አድ ናት ፡» የሚለውን ፡ አዲስ ፡ መዝሙር ፡ በኅብረት ፡ ዘመረ ። አዎን ፡ አምላኬ ፡ ውዲቱን ፡ አፍሪቃን ፡ ታደጋት ። አም ላክ ፡ ሁላችንንም ፡ ከፍርሃት ፡ አድነን ።

* * *

ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ወጥተው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ኩማሎ ፡ አብሮት ፡ ወደ ፡ ቆመው ፡ ወዳጁ ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለው ። የማጫውትህ ፡ ጉዳይ ፡ አለኝ ። እኅቴ ፡ ጌርትሩድ ፡ አብራኝ ፡ ወደዚሁ ፡ ልት መጣ ፡ ነበር ። በተነሣንበት ፡ ቀን ፡ ጠዋት ፡ ልቀሰቅሳት ፡

ወደ ፡ ክፍልዋ ፡ ብንባ ፡ ሕያኑን ፡ ልጅዋን ፡ ትታልኝ ፡ ጠፋች ። ልጂ ፡ አቢይሉም ፡ ሰው ፡ ገድሎ ፡ የስቅላት ፡ ፍርድ ፡ ተፈርዶቢታል ። ሁኔታውን ፡ ለምታውቃቸው ፡ ሁሉ ፡ እሜታቸው ። ሊደበቅ ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ አይደለም ። እኔም ፡ በዚህ ፡ ሥራዬ ፡ ልቀጥል ፡ የምችል ፡ አይመስለኝም ።

— ለምን ፡ ብለህ ፡ ኡምፉንዲሲ ?

— የወለደችውን ፡ ልጅ ፡ ጥላ ፡ የኮበለለች ፡ እኅት ፤ ሰው ፡ የገደለ ፡ ልጅ ፡ ይዤ ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ በቅስና ፡ ሥራዬ ፡ እቆያለሁ ?

— አንተ ፡ እንዳሻህ ፡ ኡምፉንዲሲ ። በበኩሌ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሥራህን ፡ ለቀህ ፡ እንድትሄድ ፡ የሚፈልግ ፡ በመካከላችን ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ የለም ። በደረሰብህ ፡ ችግር ፡ ያላዘነ ፡ የለም ። በደህና ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ በመመለስህ ፡ ያልተደሰተ ፡ የለም ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ አይታይህም ?

— ይታየኛል ። በተደረገልኝ ፡ አቀባበል ፡ ልቤ ፡ ተነክቶአል ። ሜንቄንና ፡ መከራዬንም ፡ ጠግኖታል ። ፅድሜዬን ፡ በሙሉ ፡ እዚሁ ፡ ስላሳለፍሁ ፡ ከዚህ ፡ መሄድን ፡ የግድ ፡ ካልሆነብኝ ፡ በቀር ፡ በራሴ ፡ ፍላጎት ፡ አልመኝም ። ይግሞ ፡ አንድ ፡ ያስተዋልሁት ፡ ነገር ፡ አለ ። ሜንቄትና ፡ መከራ ፡ ራሱ ፡ ምሥጢር ፡ ነው ። ደግነትና ፡ ፍቅርም ፡ ምሥጢር ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ደግነትና ፡ ፍቅር ፡ ሜንቄትንና ፡ መከራን ፡ እንደሚጠግኑ ፡ ተረድቼአለሁ ።

ኩማሎ ፡ ከወዳጁ ፡ ተሰናብቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ። ልጁቱ ፡ ከተኛች ፡ በኋላ ፡ ከምሲማንጉ ፡ የተሰጠውን ፡ የፕንዘላ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ይብተር ፡ ለባለቤቱ ፡ አሰረከባት ።

ባለቤቱም ፡ ያብኮሩን ፡ ከፍታ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አሥር ፡ ብር ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ከተመለከተች ፡ በኋላ — ይህን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ከየት ፡ አመጣኸው ? ብላ ፡ ጮኸች ።

— የራሳችን ፡ ነው ። ከልብ ፡ ወዳጄ ፡ ከምሲማንጉ ፡ የተሰጠን ፡ ስጦታ ፡ ነው ። አረፍ ፡ በይና ፡ ስለ ፡ ምሲማንጉ ፡ ስለ ፡ ሌላውም ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ላጫውትሽ ፡ — አላት ።

ሰውነትዋ ፡ ቀጥቀጥ ፡ አያለ ፡ ተቀመጠች ።

— እሺ ፡ አጫውተኝ ፡ — አለችው ።

—30—

ኩማሎ ፡ እንዶትሺኒ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የምትለማበትን ፡ መንገድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያሳየው ፡ በማለት ፡ ዘወትር ፡ በጸሎት ፡ ይተጋ ፡ ጀመር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለአገር ፡ ልማትና ፡ ብልጽግና ፡ የሰዎች ፡ ተባብሮና ፡ ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑ ፡ እያደር ፡ እያደር ፡ እየታየው ፡ ሄደ ። ወደ ፡ አገሩ ፡ ባላባት ፡ ሂዶ ፡ ለቀበሌው ፡ ችግር ፡ አንድ ፡ መፍትሔ ፡ እንዲፈልግ ፡ ቢጠይቀው ፡ እኔ ፡ አርጅቻለሁ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ምንም ፡ ግድ ፡ ሪግ ፡ አልችልም ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ አገኘ ። የቀበሌውን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ዕርዳታ ፡ ቢጠይቅ ፡ እኔ ፡ ማስተማር ፡ እንጂ ፡ በአገራቱ ፡ ልማት ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አቅሜ ፡ አይፈቅድልኝም ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ አገኘ ። ኩማሎ ፡ እያዘነና ፡ እየተከዘ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲመለስ ፡ አንድ ፡ የፈረንጅ ፡ ልጅ ፡ በቀይ ፡ ቦቃ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲመጣ ፡ አየ ። ሁኔታው ፡ የሚያስገርም ፡ አጋጣሚ ፡

ሆነበት ። ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ይህንኑ ፡ በመሰለ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጠ ፡ በእንዶትሼኒ ፡ በኩል ፡ ያልፍ ፡ የነበረው ፡ ሚቹ ፡ የጃርቪስ ፡ ልጅ ፡ ትዝ ፡ አለው ።

ልጁም ፡ በፈገግታ ፡ ለኩማሎ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠው ።

— እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ። የዛሬው ፡ ሙቀት ፡ ፈረስ ፡ ያስጋልባል ? አለ ፡ ኩማሎ ።

ልጁ ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ ሕፃን ፡ ከሽማግሌ ፡ ጋር ፡ እንደሚነጋገር ፡ ሁሉ ፡ እርሱም ፡ ከኩማሎ ፡ ጋር ፡ ጭውውት ፡ ያዘ ። በንግግሩም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አንዳንድ ፡ የዙሉ ፡ ቃላት ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ያደርግ ፡ ነበር ። ኩማሎም ፡ ፈገግ ፡ እያለ ፡ ልክ ፡ ነው ፡ ልክ ፡ ነው ፡ ይለው ፡ ነበር ።

— በጣም ፡ ሞቆሃል ፡ ውኃ ፡ መጠጣት ፡ ትፈልጋለህ? አለ ፡ ኩማሎ ።

— ባገኝስ ፡ ወተት ፡ መጠጣት ፡ እፈልግ ፡ ነበር ፡— አለ ፡ ልጁ ።

— በእንዶትሼኒ ፡ ወተት ፡ የለም ።

— ወተት ፡ ከሌለ ፡ ውኃ ፡ ይሰጠኝ ፡—አለ ፡ ልጁ ። ኩማሎ ፡ ውኃውን ፡ አምጥቶ ፡ ለልጁ ፡ ሲሰጠው ፡—

— እዚህ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ትቆያለህ? ብሎ ፡ ጠየቀው ።

— ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልቆይም ፡ ኡምፉንዲሲ ። ይህ ፡ ደንበኛው ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜአችን ፡ አይደለም ። እዚህ ፡ የመጣነው ፡ ለአንድ ፡ ለተለየ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡— አለ ፡ ልጁ ።

— ምክንያቱን ፡ አውቀዋለሁ ። አፈር ፡ ይብላኝ ። እባትህን ፡ በድንገት ፡ ተነጠቅህ ፡ —አለ ፡ ኩማሎ ፡ በሆዱ ።

— በእንዶትሼኒ ፡ ወተት ፡ የሌለው ፡ ለምንድር ፡ ነው? ሕፃናት ፡ ምን ፡ ይጠጣሉ? አለ ፡ ልጁ ።

ኩማሎም ፡ ልጁን ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ እየተመለከተ ፡—

—ልጄ ፡ በረሃብ ፡ ይሞታሉ ፡— አለ ።

— ሐኪሙ ፡ አይረዳቸውም?

— ሐኪሙማ ፡ ሕፃናት ፡ ወተት ፡ ማግኘት ፡ አለባቸው ፡ ይላል ።

ልጁም ፡ አነሰ ፡ ባለች ፡ ድምፅ ፡ ገባኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ፈረሱ ፡ አመራ ። እርካቡን ፡ ቆንጠጥ ፡ አድርጎ ፡ —ደህና ፡ ሁን ፡ ኡምፉንዲሲ ፡—አለ ።

* * *

ምሽቱ ፡ ቀዝቀዝ ፡ ያለ ፡ ነበር ። ቤተ ፡ ሰቡ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ራት ፡ ሲመገብ ፡ ኩማሎን ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ድረስ ፡ ሂዶ ፡ የተቀበለው ፡ ወዳጁ ፡ በር ፡ አንኳኩቶ ፡ ገባ ።

— ሚስተር ፡ ጃርቪስ ፡ ልኮኝ ፡ ነው ፡ የመጣሁት ፡— አለ ፡ ሰውዬው ። ኩማሎም ፡ ድንግጥ ፡ ብሎ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ተነሣ ።

— ይገርው ፡ የመጣሁትን ፡ ሲሳይ ፡ ናና ፡ ተመልከት ፡— አለ ፡ ሰውዬው ፡ ደስ ፡ በተሰኘ ፡ ድምፅ ። ኩማሎ ፡ ወዳጁን ፡ ተከትሎ ፡ ወጣ ፡ ቢል ፡ ወተት ፡ የተጫነ ፡ ጋሪ ፡ በራፉ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ አየ ።

— ይህ ፡ ወተት ፡ የተላከው ፡ በእንተ ፡ አማካይነት ፡ ለመንደሩ ፡ ሕፃናት ፡ እንዲታደል ፡ ነው ። ጠዋት ፡ የተጋቡትን ፡ የወተት ፡ መያዣዎች ፡ ይገር ፡ እሄድና ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ ወተቱን ፡ አመጣለሁ ። ዝናብ ፡ ዘንቦ ፡ ሳሩ ፡ በቅሎ ፡ ወተት ፡ እስክናገኝ ፡ ድረስ ፡ እንችላችኋለን ፡ አት ሥጉ ፡ ብሎአል ፡ ሚስተር ፡ ጃርቪስ ። አንድ ፡ ቦታ ፡ አላየኝና ፡ ወተቱ ፡ ይውረድ ፡ ኡምፉንዲሲ ።

ኩማሎ ፣ ግን ፣ እንደበቱ ፣ ምንም ፣ ሊፈታ ፣ አል ቻለም ። ሰውዬውም ፣ አታስብ ፣ ኡምፉንዲሲ ፣ እግዚአ ብሔር ፣ ዋጋውን ፣ ይከፍለዋል ፦— አለ ። ኩማሎም ፣ በነገሩ ፣ መስማማቱን ፣ ለመግለጽ ፣ ጭንቅላቱን ፣ ወደ ፣ ላይና ፣ ወደ ፣ ታች ፣ አነቃነቀ ።

—31—

ለኩማሎ ፣ ብዙ ፣ ደብዳቤዎች ፣ ከጆሐንስበርግ ፣ ደረሱት ። ዳሩ ፣ ግን ፣ አንዳቸውም ፣ ስለ ፣ አቤሴሎም ፣ ምሕረት ፣ አያበሥሩም ፣ ነበር ። በመጨረሻው ፣ ከምሲማንጉ ፣ በተላከለት ፣ ደብዳቤ ፣ አቤሴሎም ፣ በያዙት ፣ ወር ፣ በአሥራ ፣ አምስተኛው ፣ ቀን ፣ በስቅላት ፣ እንዲሞት ፣ መወሰኑን ፣ ተረዳ ።

ኩማሎና ፣ ባለቤቱ ፣ ደብዳቤውን ፣ አንብበው ፣ አንዲት ፣ ቃል ፣ እንኳን ፣ ሳይለዋወጡ ፣ በጎዘን ፣ ተቆራምደው ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ አሳለፉ ። በመጨረሻው ፣ ኩማሎ ፣ ከተቀመጠበት ፣ ብድግ ፣ ብሎ ፣ በመስኮት ፣ አሸልኮ ፣ ይመለከት ፣ ጀመር ። ወዲያውም ፣ ባለቤቱን ፦— ነይ ፣ ጉድ ፣ እይ ፤ የጣለውን ፣ ደመና ፣ ነይና ፣ እይ ፣— አላት ። ባለቤቱም ፣ ከተቀመጠችበት ፣ ተነሥታ ፣ አጠገቡ ፣ ቆማ ፣ ከአምዚምኩሉ ፣ ሽለቆ ፣ ባሻገር ፣ ከብዶ ፣ የመጣውን ፣ ደመና ፣ ተመለከተች ።

— እግዜር ፣ ፊቱን ፣ ሊመልስልን ፣ ነው ፣ መሰለኝ ፣— አላት ።

— አዎን ፣ ሊዘንብ ፣ ነው ፣ — አለችው ።

ኩማሎም ፣ ዝናብ ፣ አዝሎ ፣ የመጣውን ፣ ደመና ፣ ይህና ፣ አድርጎ ፣ ለመመልከት ፣ ከቤት ፣ ወጣ ፣ አለ ። ከቤቱ ፣ እልፍ ፣ እንዳለም ፣ የምሲማንጉን ፣ ደብዳቤ ፣ ከኪሱ ፣ አውጥቶ ፣ ዳግመኛ ፣ ያነብ ፣ ጀመር ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ደብዳቤውን ፣ ጨርሶ ፣ አነበበው ። በደብዳቤው ፣ መደምደሚያ ፣ ላይ ፣ የተገለጠው ፣ ቃል ፣ የማይታመን ፣ ሆነበት ። ቃሉ ፣ ሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ በሚቹ ፣ ልጁ ፣ ጥሬ ዚደንትነት ፣ ይተዳደር ፣ ለነበረው ፣ የጥቁሮች ፣ ወጣቶች ፣ ክበብ ፣ የሰባት ፣ ሺህ ፣ ብር ፣ ዕርዳታ ፣ የሰጠ ፣ መሆኑን ፣ ከአባ ፣ ቪንሴንት ፣ ለመረዳት ፣ ችያለሁ ፣ የሚል ፣ ነበር ።

ኩማሎ ፣ ደብዳቤውን ፣ ኪሱ ፣ ከቶ ፣ አሻግሮ ፣ ቢመለከት ፣ አንድ ፣ መኪና ፣ ወደ ፣ እንዶትሺኒ ፣ ሲመጣ ፣ አየ ። ወደ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያኑ ፣ አቅጣጫ ፣ ዞር ፣ ቢል ፣ በአቅራቢያው ፣ ጃርቪስ ፣ በፈረስ ፣ ሆኖ ፣ መኪናው ፣ ወደ ሚመጣበት ፣ አቅጣጫ ፣ ሲመለከት ፣ አየ ። ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ መኪናው ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያኑ ፣ አጠገብ ፣ ደርሶ ፣ ቆመ ። በውስጡ ፣ የነበሩት ፣ ነጮች ፣ ወርደው ፣ ለአንድ ፣ ሰዓት ፣ ያህል ፣ ከጃርቪስ ፣ ጋር ፣ መሬቱን ፣ እየለኩ ፣ ችካል ፣ ይተክሉ ፣ ገቡ ። ለተመለከታቸው ፣ አንድ ፣ ሕንፃ ፣ ለመሥራት ፣ የሚቀይሱ ፣ ይመስሉ ፣ ነበር ። የጀመሩትን ፣ ሊጨርሱ ፣ ትንሽ ፣ ሲቀራቸው ፣ ከማዕበል ፣ ጋር ፣ የተቀላቀለ ፣ ኃይለኛ ፣ ዶፍ ፣ ጣለ ። ነጮቹ ፣ በመኪናቸው ፣ ተጋብተው ፣ ወደ ፣ ቤታቸው ፣ ፈጠኑ ። ጃርቪስ ፣ ግን ፣ ኩማሎ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያኑ ፣ ውስጥ ፣ ሲገባ ፣ እይቶት ፣ ኖሮ ፣ ተከትሎት ፣ ጎራ ፣ አለ ።

ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ አብ
ረው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆዩ ። የኩማሎ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ያፈስ ፡ ነበረ ። ጃርቪስም ፡ ከፍላሹ ፡
ለመዳን ፡ ከስፍራው ፡ ስፍራ ፡ እየተንቀራጠጠ ፡ ዶፉ ፡
ጋብ ፡ እስኪል ፡ ቆየ ። በመጨረሻው ፡ ዓይናቹን ፡ ወደ ፡
መስኮቱ ፡ አቅጣጫ ፡ ጣል ፡ አድርጎ ፡ — ለመሆኑ ፡ የም
ሕረት ፡ ወሬ ፡ አለ? ብሎ ፡ ኩማሎን ፡ ጠየቀው ። ኩማ
ሎም ፡ ደብዳቤውን ፡ ከኪሱ ፡ አውጥቶ ፡ ሰጠው ። ጃር
ቪስ ፡ ደብዳቤውን ፡ ካነበበ ፡ በኋላ ፡— መቼስ ፡ ምን ፡
ይደረግ ፡— አለ ። —የያዝነው ፡ ወር ፡ አሥራ ፡ አምስ
ተኛ ፡ ቀን ፡ ሲደርስ ፡ አስታውስሃለሁ ። ይህና ፡ ሁን ፡
ኡምፉንዲሲ ፡— አለ ። ከዚያም ፡ ፈረሱን ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡
ቤቱ ፡ አመራ ።

—32—

ችካሎቹ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አቅራቢያ ፡ ከተተከሉ ፡
ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አለፈ ። የአካባቢው ፡ ሠፈርተኞች ፡ የውኃ ፡
ግድብ ፡ ሊሠራልን ፡ ነው ፡ በጃርቪስ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡
ከሚያልፈው ፡ ወንዝ ፡ ውኃ ፡ በቧንቧ ፡ ሊመጣልን ፡
ነው ፡ እያሉ ፡ ያወሩ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡ የኩማሎ ፡
ወዳጅ ፡ ሊጐበኘው ፡ መጥቶ ፡ ጃርቪስ ፡ የግድቡን ፡
አቅድ ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ ወደ ፡ ፕሪቶሪያ ፡ መሄዱን ፡
ነገረው ።

ከጥቂት ፡ ቀናት ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ልጅግር ፡ ሰው ፡
ኩማሎ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ መጣ ።

— እርስዎ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ የመጣሁት ፡— አለ ፡ ልጅ
ግሩ ፡ ሰውዬ ። —እኔ ፡ አዲሱ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ወኪል ፡
ነኝ ።

— ወደ ፡ ቤት ፡ ሳራ ፡ እንበል ። ለመሆኑ ፡ ወደ ፡እኔ ፡
የላከህ ፡ ማነው? አለ ፡ ኩማሎ ፡ በደስታ ።

—አልሰሙም ፡ እንዴ? ጃርቪስ ፡ ነው ፡ እኮ ፡ ቀጥሮ ፡
ያመጣኝ ። ለእንዶትሼኒ ፡ ገበሬዎች ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ ላስ
ተምራቸው ፡ ነው ፡ የመጣሁት ፡— ኡምፉንዲሲ ።

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ወኪሉ ፡
በእንዶትሼኒ ፡ አካባቢ ፡ የማስተማር ፡ ተግባሩን ፡ ጀመረ ።
ገበሬዎቹንም ፡ ሰብስቦ ፡ ኮረብቶቹን ፡ አግድም ፡ እንጂ ፡
ቁልቁል ፡ እንዳያርሱ ፡ አስረዳቸው ። የአፈሩን ፡ ተቦር
ቡሮ ፡ ማለቅ ፡ ለመከላከል ፡ ዛፍ ፡ መትከል ፡ እንዳለባ
ቸውና ፡ ለደን ፡ ማልሚያና ፡ ለከብቶች ፡ መሰማሪያ ፡ከመ
ሬታቸው ፡ ቁርሰው ፡ መስጠት ፡ ያለባቸው ፡ መሆኑን ፡
አስገነዘባቸው ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡
ካለው ፡ ኩርማን ፡ መሬት ፡ ጋር ፡ ከመታገል ፡ ይልቅ ፡
በጎብረት ፡ ሆነው ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ቢጀምሩ ፡ እያንዳን
ዳቸው ፡ ተጠቅመው ፡ አገራቸውን ፡ ለማልማት ፡ እንደ
ሚችሉ ፡ ዘርዝሮ ፡ ገለጸላቸው ።

— ኡምፉንዲሲ ፡—አለ ፡ ልጅግሩ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡
ወኪል — ይህ ፡ ሽለቆ ፡ ለምቶ ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ እንደሚ
ሰጥ ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ሥራው ፡
ብዙ ፡ ድካም ፡ ይጠይቃል ። ቢሆንም ፡ መልማቱ ፡ አይ
ቀርም ።

— የእግዜር ፡ ፈቃድ ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ሽለቆ ፡ ለምቶ ፡
ለማየት ፡ ያበቃኝ ፡ ይሆናል ፡— አለ ፡ ኩማሎ ፡ ትሕ

ትና ፣ በተመላ ፣ ድምፅ ። — መቼም ፣ በዚህ ፣ ዕድሜዬ ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ ሲወድም ፣ ብዙ ፣ ነገር ፣ ሲጠፋ ፣ አይቻለሁ ። ይህ ፣ ሽለቆ ፣ ለምቶ ፣ ለማየት ፣ ያበቃኝ ፣ ይሆን ?

—33—

ከታላቁ ፣ ሸለቆ ፣ ባሻገር ፣ ያለው ፣ ሰማይ ፣ በደመና ፣ ከብዶአል ። ኩማሎም ፣ ድጅ ፣ ቆሞ ፣ ዙሪያውን ፣ አን ጋጦ ፣ ይመለከታል ። ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ ወዳጁ ፣ በጋሪ ፣ ወተት ፣ ጭኖ ፣ ሲመጣ ፣ አየ ።

— ምነው ፣ ዛሬስ ፣ በጊዜ ፣ መጣህ? አለ ፣ ኩማሎ ፣ ትንሽ ፣ ደንገጥ ፣ ብሎ ።

— አዎን ፣ በጊዜ ፣ ነው ፣ የመጣሁት ፣ ኡምፉንዲሲ ፣ የሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ ባለቤት ፣ አርፈው ፣ ሥራ ፣ አቁመ ናል ።

— አረፉ ፣ እንዴት ፣ ያሳዝናል? ሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ ምን ፣ ተሻላቸው ፣ ታዲያ?

— በጣም ፣ አዝነዋል ፤ ፈጽሞ ፣ አይናገሩም ።

ኩማሎም ፣ እንደ ፣ ምንም ፣ ተጨንቆ ፣ የሚከተለ ውን ፣ የኅዘን ፣ መግለጫ ፣ ደብዳቤ ፣ ለሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣ ጽፎ ፣ ላከ ።

«ለተከበሩ ፣ ሚስተር ፣ ጃርቪስ ፣—

«የእንዶትሼኒ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ አባሎች ፣ ሁላ ችን ፣ የእመቤታችንን ፣ የባለቤትዎን ፣ ዕረፍት ፣ ሰምተን ፣

በጣም ፣ አዝነናል ። እርስዎና ፣ ሚችዋ ፣ ባለቤትዎ ፣ ያደ ረጋችሁልን ፣ ታላቅ ፣ ውለታ ፣ መቼም ፣ አይረሳንም ። ጥና ፣ እርስዎንም ፣ በኀዘንዎ ፣ እንዲያጽናናዎ ፣ የዘወትር ፣ ጸሎታችን ፣ ነው ። »

ታማኝ ፣ አገልጋይዎ ፣
(ቄስ) እስጢፋኖስ ፣ ኩማሎ ።

በኋላም ፣ የሚከተለው ፣ መልስ ፣ ለኩማሎ ፣ ደረሰው ።

«ኡምፉንዲሲ ፣—

«ስለላካችሁልኝ ፣ የኀዘን ፣ መግለጫ ፣ መልእክትና ፣ ስለ ፣ ጸሎታችሁም ፣ አመሰግናችኋለሁ ። እርግጥ ፣ ነው ፣ ለእንዶትሼኒ ፣ ነዋሪዎች ፣ ላደረግነውና ፣ ወደፊትም ፣ እናደርጋለን ፣ ብለን ፣ ለምናስበው ፣ በጎ ፣ ነገር ፣ ሁሉ ፣ አሳቢዋና ፣ አነሳሽዋ ፣ ባለቤቴ ፣ ነበረች ። ይህን ፣ ሁሉ ፣ ለማድረግ ፣ ያሰብነው ፣ ለልጃችን ፣ መታሰቢያ ፣ ይሆናል ፣ ብለን ፣ ነው ። ባለቤቴ ፣ በእንዶትሼኒ ፣ አንድ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ለማሠራት ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ምኞት ፣ ነበራት ። ስለዚህ ፣ ጉዳይ ፣ በቅርቡ ፣ ከአንተ ፣ ጋር ፣ ለመመካከር ፣ አስቤአለሁ ።

«በተረፈ ፣ ባለቤቴ ፣ ወደ ፣ ጆሐንስበርግ ፣ ከመሄድ ዋም ፣ በፊት ፣ ያማት ፣ እንደ ፣ ነበር ፣ ልገልጽልህ ፣ እወ ዳለሁ ። »

ከሰላምታ ፣ ጋር ።
ጄምስ ፣ ጃርቪስ ።

የእንዶትሼኒ ፣ ገበሬዎች ፣ በሙሉ ፣ እርሻ ፣ ጀምረ
ዋል ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ የእርሻው ፣ ሥራ ፣ እንደ ፣ ቀድ
ሞው ፣ አልተቀላጠፈላቸውም ። ምክንያቱም ፣ ልጅግሩ ፣
የእርሻ ፣ ሥራ ፣ ወኪል ፣ ገበሬዎች ፣ ኮረብቶቹን ፣ ቊል
ቊል ፣ ሳይሆን ፣ አግድሞሽ ፣ እንዲያርሱ ፣ አጥብቆ ፣ ስለ ፣
ሚቈጣጠራቸውና ፣ ማሳዎቹ ፣ ከቀድሞው ፣ የተለየ ፣
መልክ ፣ እንዲኖራቸው ፣ ስለፈለገ ፣ ነው ።

ከገበሬዎቹ ፣ መካከል ፣ ያዘኑም ፣ ያኰረፉም ፣ ሞል
ተዋል ። በተለይም ፣ ደግሞ ፣ ከመሬታቸው ፣ ላይ ፣ ለደን ፣
ማልሚያና ፣ ለከብት ፣ ማሰማሪያ ፣ መሬት ፣ ተቆርሶ ፣
የተወሰደባቸው ፣ እንጀታቸው ፣ አሮአል ። ይሁን ፣ እንጂ ፣
አዲስ ፣ መንፈስ ፣ አዲስ ፣ ሕይወት ፣ ሸለቆውን ፣
የጐበኘው ፣ መሆኑ ፣ በግልጽ ፣ መታየት ፣ ጀምሮአል ።
የአገሩም ፣ ሰዎች ፣ የሚወያዩበትና ፣ የሚከራከሩበት ፣
ቁም ፣ ነገር ፣ አግኝተዋል ። የተጀመረው ፣ ሥራ ፣ ውጤት ፣
በግዙፍ ፣ ባይታይም ፣ እንኳ ፣ በአካባቢው ፣ አንድ ፣ የለ
ውጥ ፣ ነፋስ ፣ ሽው ፣ ያለ ፣ መሆኑ ፣ ለሁሉም ፣ ይሰማው ፣
ጀምሮአል ።

* * *

— በሥራህ ፣ ፍሬ ፣ መደሰት ፣ አለብህ ፣— አለው ፣
ኩማሎ ፣ የእርሻ ፣ ሥራ ፣ ወኪሉን ።—እንደምታየው ፣ ሽለ
ቆአችን ፣ ነፍስ ፣ በመዝራት ፣ ላይ ፣ ይገኛል ። እዚህ ፣ አገር ፣
ብዙ ፣ ዘመን ፣ ኖሬአለሁ ። ነገር ፣ ግን ፣ እንደ ፣ ዘንድሮ ፣

የእንዶትሼኒ ፣ ገበሬ ፣ ለእርሻ ፣ ታጥቆ ፣ ሲነሣ ፣ አይቼ ፣
አላውቅም ። ገበሬው ፣ ለሥራ ፣ የተጋው ፣ በዝናቡ ፣ ምክን
ያት ፣ ብቻ ፣ እንዳይመስልህ ። ከዚህ ፣ ቀደም ፣ ታይቶ ፣ የማ
ይታወቅ ፣ የተስፋ ፣ ስሜት ፣ አድሮበታል ።

—እባክዎን ፣ ቶሎ ፣ ብሎ ፣ ብዙ ፣ ተስፋ ፣ ማድረግ ፣
አይገባም ፣—አለ ፣ ወጣቱ ፣ የእርሻ ፣ ሥራ ፣ ወኪል ።—በበ
ኩሌ ፣ በዚህ ፣ ዓመት ፣ ብዙ ፣ ውጤት ፣ ይገኛል ፣ ብዬ ፣
ተስፋ ፣ አላደርግም ። ምናልባት ፣ የቦቆሎው ፣ ቁመት ፣
ትንሽ ፣ ከፍ ፣ አዝመራውም ፣ በመጠኑ ፣ በርከት ፣ ይል ፣
ይሆናል ። የመሬቱ ፣ ጠፍነት ፣ ግን ፣ እንዲህ ፣ በቶሎ ፣
ሊሽር ፣ የሚችል ፣ አይደለም ።

— ዛፎቹ ፣ እስኪደርሱ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ጊዜ ፣ ይወ
ስድ ፣ ይመስልሃል?

— ዛፎቹ ፣ እስኪደርሱ ፣ ብዙ ፣ ዓመት ፣ ይወስዳል ።
ለመሆኑ ፣ የአገሬው ፣ ሕዝብ ፣ ድርቁን ፣ ሰባት ፣ ዓመት ፣
ሙሉ ፣ የሚችለው ፣ ይመስልዎታል?

— አትቸኩል ፣ ወዳጄ ። እኔም ፣ ባላባቱም ፣ በጉዳዩ ፣
እየደከምንበት ፣ ነው ።

— የውኃው ፣ ግድብ ፣ ተሠርቶ ፣ ለማየት ፣ በጣም ፣
ተጣድፌአለሁ ፣— አለ ፣ የእርሻ ፣ ሥራ ፣ ወኪሉ ። —
ግድቡ ፣ ከተሠራ ፣ ለሣር ፣ ሜዳው ፣ የሚሆን ፣ በቂ ፣ ውኃ ፣
እናገኛለን ። በዚያን ፣ ጊዜ ፣ ወተት ፣ እንደ ፣ ልብ ፣ ይገ
ኛል ፣ ማለት ፣ ነው ። ከዚያ ፣ በኋላ ፣ የነጮችን ፣ እጅ ፣
ማየት ፣ አያስፈልግም ።

ኩማሎ ፣ ወጣቱን ፣ የእርሻ ፣ ሥራ ፣ ወኪል ፣ ትኩር ፣
ብሎ ፣ እየተመለከተ ፣ — ለመሆኑ ፣ የነጮችን ፣ ወተት ፣
ባናገኝ ፣ እስከዛሬ ፣ ምን ፣ ይውጠን ፣ ነበር? ብሎ ፣ ጠየ

ቀው ። —ነጮች ፡ ባያዝኑልን ፡ ነጮች ፡ ባይረዱን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ምን ፡ እንሆን ፡ ነበር? ለመሆኑ ፡ ነጮች ፡ ባያስቡልን ፡ አንተስ ፡ ብትሆን ፡ በገዛ ፡ እጅህ ፡ መጥተህ ፡ ትረዳን ፡ ኖሮአል ?

— ይስሙኝ ፡ ኡምፉንዲሲ ፡ እዚህ ፡ እንድሠራ ፡ የቀጠረኝ ፡ ነጭ ፡ ነው ። እኔም ፡ ምስጋና ፡ ቢስ ፡ አይደለሁም ።

— ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የድፍረት ፡ ቃል ፡ ምን ፡ ያናግርሃል ? አለ ፡ ኩማሎ ፡ ቁጣ ፡ ብሎ ።

— ሐሳብዎ ፡ ይገባኛል ፡— አለ ፡ ወጣቱ ። — እርግጥ ፡ ነው ፡ ጀርቪስ ፡ ቀና ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ ለእኔም ፡ ተሰምቶኛል ። በእውነቱ ፡ አክብሮት ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ነው ። ይስሙኝ ፡ ኡምፉንዲሲ ፡ ይህንን ፡ ሥራዬን ፡ ከልቤ ፡ ነው ፡ የምሠራው ። ምክንያቱም ፡ ጥቅሙ ፡ ለአገሬና ፡ ለገዛ ፡ ወገኖቼ ፡ መሆኑን ፡ ስለማውቅ ፡ ነው ። ለማንም ፡ ጌታ ፡ ቢሆን ፡ እንዲህ ፡ ከልቤ ፡ የምለፋ ፡ እንዳይመስልዎት ። እውነቱን ፡ ለማወቅ ፡ ከፈለጉ ፡ ግን ፡ ለሙን ፡ መሬታችንን ፡ የነጠቁን ፡ ነጮች ፡ ናቸው ። ካለችንም ፡ ኩርማን ፡ መሬት ፡ ለይተው ፡ እንደ ፡ ባርያ ፡ እንድናገለግላቸው ፡ የሚያስገድዱን ፡ ነጮች ፡ ናቸው ። ለመሆኑ ፡ ይህ ፡ ሽለቆ ፡ ቢለማና ፡ ቢቀና ፡ ከዚህ ፡ ተሰደው ፡ የሄዱትን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚችል ፡ ይመስልዎታል?

— ኧረ ፡ እኔ ፡ አላውቅም ።

— እኔ ፡ አውቃለሁ ፡ ኡምፉንዲሲ ። ይህን ፡ ሽለቆ ፡ አልምተን ፡ አሁን ፡ የሰፈሩበትን ፡ ሰዎች ፡ እንዲያስተዳድር ፡ ለማድረግ ፡ እንችላለን ። ልጆች ፡ ሲወለዱስ? የተወለዱት ፡ ሲያድጉስ? የት ፡ ይደርሳሉ? ጥቂቶቹ ፡ እንጂራ ፡ ለመፈለግ ፡ ተነሥተው ፡ መሄዳቸው ፡ አይቀርም ።

ኩማሎ ፡ የሚመልሰው ፡ ቢያጣ ፡ እንዲያው ፡ ዝም ፡ አለ ።

— እኛ ፡ የምንለፋው ፡ የምንሠራው ፡ ለአፍሪቃ ፡ ነው ፡— አለ ፡ ወጣቱ ። —የምንሠራው ፡ ለነጮች ፡ ወይም ፡ ለጥቂቶች ፡ ብለን ፡ አይደለም ፡ ለአፍሪቃ ፡ ብለን ፡ ነው ።

ወጣቱ ፡ የእርሻ ፡ ሥራ ፡ ወኪል ፡ ኩማሉን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገባ ። ኩማሎም ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ቆሞ ፡ ቀረ ። በመልማት ፡ ላይ ፡ ወዳለው ፡ ሽለቆ ፡ አሻግሮ ፡ ቢመለከት ፡ ሰማዩ ፡ በከዋክብት ፡ አጊጦአል ። ውበቱ ፡ ልቡን ፡ ደስ ፡ አሰኘው ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የሰማውን ፡ አዲስና ፡ አሸባሪ ፡ ሐሳብ ፡ ለማስተዋል ፡ ግን ፡ ዕድሜው ፡ ያለፈበት ፡ መሆኑ ፡ ተሰማው ።

ዞር ፡ ብሎ ፡ ወጣቱ ፡ ወደ ፡ ገባበት ፡ ቤት ፡ ዘው ፡ አለ ።

—35—

ዕለቱ ፡ የወሩ ፡ አሥራ ፡ አራተኛ ፡ ቀን ፡ ነበር ። ኩማሎ ፡ ወደ ፡ ባለቤቱ ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡—ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ እወጣለሁ ፡ —አላት ። እርስዋም ፡ ጉዳዩን ፡ በመረዳት ፡— መልካም ፡ ነው ፡— አለችው ።

ኩማሎ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብቻውን ፡ ጸሎት ፡ ለማድረስ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ወጥቶአል ።

የመጀመሪያው ፡ አቤሴሎም ፡ በጠና ፡ ታሞ ፡ ሁለተኛው ፡ የከህነት ፡ ሥራውን ፡ ትቶ ፡ ጠቀም ፡ ያለ ፡ ደመወዝ ፡ በሚያገኝበት ፡ አንድ ፡ ሱቅ ፡ ውስጥ ፡ ተቀጥሮ ፡ ለመሥራት ፡ ባሰበበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።

— ወደ ፡ ተራራው ፡ አብረን ፡ ብንወጣ ፡ አይሻልም ? ብቻሽን ፡ ልተውሽ ፡ አልፈልግም ፡— አላት ፡ ኩማሎ ፡ ባለቤቱን ።

— እኔስ ፡ እዚሁ ፡ ብሆን ፡ ሳይሻል ፡ አይቀርም ። ልጅቱ ፡ እኮ ፡ ቀንዋ ፡ ገብቶአል ፤ አንተ ፡ ብቻህን ፡ ብትሄድ ፡ ይሻላል ።

ከዚያም ፡ ይዞት ፡ የሚሄደው ፡ ሻይና ፡ የበቆሎ ፡ ቂጣ ፡ አሰናዳችለት ። ኩማሎም ፡ ካፖርቱን ፡ አጥልቆ ፡ ከዘራውን ፡ ይዞ ፡ ስንቁን ፡ አንጠልጥሎ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ አመራ ።

ጊዜው ፡ ጨለምለም ፡ ብሎ ፡ ነበር ። ኩማሎ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ወደምትወስደው ፡ ቀጭን ፡ የግር ፡ መንገድ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አንድ ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ። ዞር ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ የተቀመጠ ፡ ሰው ፡ አየ ።

— አንተ ፡ ነህ ፡ ኡምፉንዲሲ ?

— አዎን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ሚስተር ፡ ጃርቪስ ።

— ፈልጌህ ፡ ነበር ፡ ኡምፉንዲሲ ። ለእንዶትሼኒ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አባሎች ፡ የሚደርስ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ ይገፍአለሁ ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑስ ፡ ነገር ? ኡምፉንዲሲ ።

— የሕንፃው ፡ ሥራ ፡ ፕላን ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ተጠናቅቆ ፡ ይደርስሃል ። ፕላኑ ፡ እንደ ፡ ደረሰህ ፡ የሕንፃው ፡ አሠራር ፡ ይዞታ ፡ ለአንተ ፡ የሚስማማ ፡ መሆን ፡

አለመሆኑን ፡ እንድታስታውቀኝ ፡ እፈልጋለሁ ። በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ ሥራው ፡ ከተያያዘ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ስፍራ ፡ ለቅቄ ፡ መሄድ ፡ አስቤአለሁ ።

ይህን ፡ ሲሰማ ፡ ኩማሎ ፡ ክው ፡ ብሎ ፡ ቀረ ። ጃርቪስም ፡ የኩማሎን ፡ ሰውነት ፡ መለወጥ ፡ ስላየ ፡— በየ ጊዜው ፡ ወደ ፡ እንዶትሼኒ ፡ መመላለሴ ፡ አይቀርም ። መቼም ፡ እዚህ ፡ ያለውን ፡ ሥራዬንና ፡ ንብረቴን ፡ እርግፍ ፡ አድርጌ ፡ አልተወውም ። ቢሆንም ፡ እዚህ ፡ ብቻዬን ፡ ከምሆን ፡ ወደ ፡ ጆሐንስበርግ ፡ ሄጄ ፡ ከሚቹ ፡ ልጄ ፡ ባለቤት ፡ ጋር ፡ መኖር ፡ የሚሻል ፡ መስሎ ፡ ስለ ፡ ታየኝ ፡ ነው ። የሚቹን ፡ ልጄን ፡ ልጅ ፡ አይተኸው ፡ የለም ?

— አዎን ፡ አይቼዋለሁ ።

— አይ—መሳ— ሰሉም ?

— በጣም ፡ እንጂ ። ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ያለው ፡ ልጅ ፡ ነው ።

— አዎን ፡ አባቱም ፡ እንደዚሁ ፡ ነበር ።

ሁለቱም ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆሙ ። በመጨረሻው ፡— ከመሸ ፡ በኋላ ፡ ወዴት ፡ ለመሄድ ፡ አስበሃል ፡ ኡምፉንዲሲ ? አለ ፡ ጃርቪስ ።

— ወደ ፡ ተራራው ፡ ልወጣ ፡ አስቤአለሁ ፡— አለ ፡ ኩማሎ ።

— ገባኝ ፡ ገባኝ ፡ አለ ፡ ጃርቪስ ።

ከዚያም ፡ ጃርቪስ ፡ ጨለማ ፡ ወደ ፡ ሸፈነው ፡ ሸለቆ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡— በመካከላችን ፡ አንድ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ የደረሰ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ገና ፡ የተጀመረ ፡ ነገር ፡ አለ ። በሕይወቴ ፡ እስካለሁ ፡ ድረስ ፡ የተጀመረው ፡ ይቀጥላል ። ደህና ፡ ሁን ፡ ኡምፉንዲሲ ።

— ሳላመሰግንዎት ፣ አይሂዱ ፣ ጌታዬ ፣ — አለ ፣ ኩማሎ ።
— መጀመሪያ ፣ የእርሻ ፣ ሥራችንን ፣ እንዲያሻ
ልልን ፣ ለቀጠሩልን ፣ ሠራተኛ ፤ ሁለተኛ ፣ የልጆቻችንን ፣
ሕይወት ፣ ለጠበቀው ፣ ወተት ፣ አመሰግንዎታለሁ ።
— ምንም ፣ አይደለም ፣ ኡምፉንዲሲ ። ደህና ፣ ሁን ፤
ሴሊቱኑ ፣ በሙሉ ፣ በደህና ፣ ያሳድርህ ፣ ኡምፉንዲሲ ።
— ያሰንብትዎት ፣ ጌታዬ ፣ — አለ ፣ ኩማሎ ።

ኩማሎ ፣ ተራራው ፣ ጫፍ ፣ ላይ ፣ ወጥቶ ፣ ከነፋሱ ፣
መጠለያ ፣ የሚሆን ፣ ስፍራ ፣ ካገኘ ፣ በኋላ ፣ ጸሎቱን ፣
ጀመረ ። ከሁሉ ፣ አስቀድሞ ፣ ለጌርትሩድና ፣ በሻንቲ ፣
ታውን ፣ ለሚኖሩ ፣ ወገኖቹ ፣ ጸለየ ። ከዚያም ፣ በምሲማንጉ ፣
በአባ ፣ ቪንሴንት ፣ በወይዘሮ ፣ ሊቴቤና ፣ በሚስተር ፣ ጀር
ቪስ ፣ በኩል ፣ ስለ ፣ ተቀበለው ፣ ቸርነትና ፣ በጎነት ፣ የእ
ንዶትሼኒ ፣ ሕዝብ ፣ ስላደረገለት ፣ መልካም ፣ አቀባበል ፣
ስለ ፣ ተጀመረው ፣ የመሻሻልና ፣ የልማት ፣ ሥራ ፣ አምላ
ክን ፣ አመሰገነ ።

ከዚያም ፣ የደረሰበት ፣ መከራና ፣ ሥቃይ ፣ ወደ ፣
ደስታ ፣ የተለወጠበትን ፣ ምክንያት ፣ በልቡ ፣ ውስጥ ፣ ያስ
ላሰል ፣ ጀመር ።

ወዲያው ፣ ከእንቅልፉ ፣ እንደ ፣ ነቃ ፣ ሰው ፣ ብንን ፣
አለ ። ተራራው ፣ ላይ ፣ ቆራ ፣ መጣል ፣ ጀምሮአል ። ልጁ ፣
አቤሴሎም ፣ ትዝ ፣ አለው ።
— ተኝቶ ፣ ይሆን? ወይስ ፣ ዓይኑ ፣ ፍጥጥ ፣ ብሎ ፣ የሌ
ሊቱን ፣ መንጋት ፣ ይጠባበቃል? እያለ ፣ ያስብ ፣ ጀመር ፣
ወዲያው ፣ — ወየው ፣ ልጄ ! ወየው ፣ ልጄ ! ብሎ ፣ ጮኸ ።

* * *

ኩማሎ ፣ ከሽልብታው ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ቢነቃ ፣ የም ሥ
ራቁ ፣ አድማስ ፣ መልኩን ፣ ለውጦ ፣ አገኘው ። ልክ ፣
በዚህ ፣ ሰዓት ፣ ልጁን ፣ ከተኛበት ፣ ቀስቅሰው ፣ በል ፣ እን
ግዲህ ፣ ተዘጋጅ ፣ እንደሚሉት ፣ ተሰማው ። ሌሊቱን ፣
ካሳለፈበት ፣ ስፍራ ፣ ወደ ፣ ሌላ ፣ ተዛውሮ ፣ የምሥራቁን ፣
እድማስ ፣ ትክ ፣ ብሎ ፣ ይመለከት ፣ ጀመር ። ሰዎች ፣ የሚ
ሉት ፣ እውነት ፣ ከሆነ ፣ ፀሐይዋ ፣ ብቅ ፣ ስትል ፣ የልጄ ፣
የሕይወቱ ፣ ፍጻሜ ፣ ይሆናል ፣ ብሎ ፣ አሰበ ።

የምሥራቁ ፣ አድማስ ፣ ወገግ ፣ እያለ ፣ ሄደ ። የጊ
ዜው ፣ መቃረብ ፣ ለኩማሎ ፣ ተሰማው ። ከተቀመጠበ
ትም ፣ ብድግ ፣ አለ ። ባርኔጣውን ፣ ከራሱ ፣ ላይ ፣ አውልቆ ፣
መረት ፣ ላይ ፣ አስቀምጦ ፣ እጆቹን ፣ ደረቱ ፣ ላይ ፣ እጥ
ፍጥፍ ፣ እድርጎ ፣ ቆመ ። ጥቂት ፣ ጊዜ ፣ እንደቆየ ፣ ፀሐ
ይዋ ፣ ብቅ ፣ አለች ።

* * *

አዎን ፣ ጎህ ፣ ቀደደ ። ቲቲሆያ ፣ የተባለችው ፣ ወፍ ፣
ከሽልብታዋ ፣ ነቅታ ፣ የብቸኝነት ፣ ድምፅዋን ፣ ማሰማት ፣
የምትጀምርበት ፣ ጊዜ ፣ ደረሰ ። የፀሐይዋ ፣ ብርሃን ፣ የተ
ራሮቹን ፣ እናት ፣ ነካ ፣ አደረገው ። የታላቁ ፣ የኡምዙም
ኩሉ ፣ ሽለቆ ፣ ገና ፣ ጨለማ ፣ እንደ ፣ ሸፈነው ፣ ነው ። ከጥ
ቂት ፣ ጊዜ ፣ በኋላ ፣ ፀሐይዋ ፣ ብርሃንዋን ፣ ሳትፈነጥቅበት ፣
አትቀርም ። በእንዶትሼኒም ፣ ገና ፣ እንደ ፣ ጨለመ ፣ ነው ።
የፀሐይዋ ፣ ብርሃን ፣ እዚያም ፣ መድረሱ ፣ አይቀርም ። አዎን ፣
በብዙ ፣ ሺህ ፣ ዘመናት ፣ ውስጥ ፣ አንዴም ፣ ላያስልስ ፣ ብር

ሃንና ፡ ንጋትን ፡ የሚያበሥረው ፡ ኅሀ ፡ ቀዱአል ። ለመሆኑ ፡
ከፍርሃት ፡ ባርነት — ከባርነት ፡ ፍርሃት ፡ የሚገላግለን ፡
ኅሀ ፡ መቼ ፡ ይቀድ ፡ ይሆን ? ማን ፡ ያውቃል ?

ተፈጸመ ።

ዘተርጎሙ ፡ ቀረበ ፡ መጻሕፍት ።

1. ማርቲን ፡ ሉተር ፡
2. ያጸጋ ፡ አርጎት ፡
3. የክርስቶስ ፡ ሰማዕት ፡
4. እንዲት ፡ ልጅ ፡ ወድኝ ፡
5. አንድ ፡ ሙሳት ፡ ወድጀ ፡
6. ቅድስት ፡ ሀገር ፡
7. ሳትና ፡ ቅም ፡ ነገር ፡
8. አራ ፡ ባይ ፡ አገሬ ፡

ማዮራት ፡ ደምፅ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪክ ፡